# ተጽናና

## 2ኛ ቆሮንቶስ

### እግዚአብሔር

### መከራችሁን ወደ ድል ሊለውጥ ይችላል።


ጸሐፊ፦ በዋረን ደብልዩ ዌርዝቢ

ትርጉም፦ በግርማዊ

እርማት፦ ዐቢይ ደምሴ



የመጀመሪያ እትም ጥቅምት 1988 ዓ.ም.

ሁለተኛ እትም ታኅሣሥ 1990 ዓ.ም.

ሦስተኛ እትም ሐምሌ 1992 ዓ.ም.



Copyright © 1995 by SIM, Addis Ababa, ETHIOPIA. Originally published in English under the title of BE ENCOURAGED, Copyright © 1984 by SP Publications, Inc., Wheaton, Illinois, USA. All rights reserved.

# ማውጫ


1. ብንወድቅም - አልተጣልንም!
(2ኛ ቆሮ. 1:1-11) ........................................ 1
2. «እወድቃለሁ» ብለህ ተስፋ አትቁረጥ!
(2ኛ ቆሮ. 1:12-2:17) ........................................ 14
3. ከክብር ወደ ክብር (2ኛ ቆሮ. 3) ........................................ 27
4. ለግጭቱ የሚያስፈልገው ብርታት
(2ኛ ቆሮ. 4:1-5:8) ........................................ 39
5. የአገልግሎት መንስዔዎች
(2ኛ ቆሮ.5:9-21) ........................................ 52
6. ልብ ለልብ (2ኛ ቆሮ. 6-7) ........................................ 64
7. የመስጠት ጸጋ፡- ክፍል 1 (2ኛ ቆሮ. 8) ........................................ 76
8. የመስጠት ጸጋ፡- ክፍል 2 (2ኛ ቆሮ. 9) ........................................ 89
9. በአገልግሎት ውስጥ የሚከሰቱ
የአሳብ አለመግባባቶች (2ኛ ቆሮ. 10) ........................................ 101
10. አባት ከሁሉም በላይ ያውቃል
(2ኛ ቆሮ. 11) ........................................ 114
11. ሰባኪው በገነት (2ኛ ቆሮ. 12:1-10) ........................................ 126
12. ለዝግጅት የሚረዱ ሦስት ነጥቦች
(2ኛ ቆሮ. 12:11-13:14) ........................................ 137

# መግቢያ

ተስፋ መቁረጥ ሰውን ከሰው በማበላለጥ ደረጃ ተመልክቶ አክብሮት የሚቸር አይደለም። ልክ በእምነት ጎዳና ላይ እንደሚድኸው አዲስ አማኝ ሁሉ፥ በጌታ ቤት ቆይታ ያደረገው ቅዱስ ሰውም ተስፋ በመቁረጥ የሚሰቃይባቸው ጊዜያት አሉ። እንዲያውም የበሰለው አገልጋይ በቅርቡ ወደ አገልግሎት ከመጣው ወጣት መጋቢ ይልቅ በበለጠ ተስፋ የሚቆርጥባቸው አጋጣምዎች ሊኖሩ ይችላሉ።

የ2ኛ ቆሮንቶስ መልእክት ለእኔ ለረዥም ዓመታት መጽናኛዬ ነበርና አሁን ደግሞ አንተም እንድትጽናናበት እነሆኝ እላለሁ። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ከተካተቱት ትምህርቶች አንዳንዶቹ «ወደ መጽሐፍ ቅዱስ እንመለስ» የሚለው የሬድዮ አገልግሎት ክፍል ቀርበው ስለ ነበር፥ ከአድማጮቼ ያገኘኋቸው ምላሾች ጳውሎስ ከምዕተ-ዓመታት በፊት የጻፈው መጽሐፍ ለዛሬውም ዘመን ተፈላጊነት አለው ብዬ እንዳምን አደረገኝ።

ይህን መጽሐፍ በማዘጋጅበት ጊዜ ላደረጉልኝ እገዛና መጽናኛ መልካሙን ወዳጄን ጂም አዴርን ላመሰግን እወዳለሁ። ከእርሳቸውና ከቪክተር ቡክስ የሥራ ባልደረቦቻቸው ጋር ያሳለፍኳቸው ዓመታት እጅግ አስደሳች ነበሩ።

ምናልባት የዚህ መጽሐፍ መልእክት ያጽናናህ ከሆነ፥ አንተም በተራህ ወጣ ብለህ ሌሎችን ለማጽናናት በቆራጥነት ተነሣ።

ዋረን ደብልዩ ዌርስቢ

የ2ኛ ቆሮንቶስ አስተዋጽኦ

I. ጳውሎስ አገልግሎቱን ይገልጻል - 1፡1-7፡16

ሀ. ድል ነሺ - 1፡1-2፡17

ለ. የከበረ - 3፡1-18

ሐ. እውነተኛ - 4፡1-18

መ. የሚያምን - 5፡1-21

ሠ. አፍቃሪ - 6፡1-7፡16

II. ጳውሎስ ልግስናቸውን ያበረታታል - 8፡1-9፡15

(ለአይሁዳውያን ቅዱሳን የሚሰጠውን ስጦታ እየተቀበለ ነበር)

ሀ. «በጸጋ የመስጠት» መመሪያዎች - 8፡ 1-24

ለ. «በጸጋ ለሚሰጡ ሰዎች» የተሰጡ የተስፋ ቃሎች - 9፡ 1-15

III. ጳውሎስ ሥልጣኑን ከሥራ ላይ ያውለዋል - 10፡ 1-13፡ 14

ሀ. ተቃዋሚዎቹን የሚያጠቃው ተዋጊ - 10፡ 1-18

ለ. ቤተ ክርስቲያኒቱን የሚጠብቀው መንፈሳዊ አባት 11፡ 1-15

ሐ. «ሞኙ ሰው» - በመከራ ሲመካ - 11፡ 16-12፡ 20

መ. ሐዋርያው የፍቅርን ሥልጣን ሲገልጽ - 12፡ 11-13፡ 14

# ብንወድቅም - አልተጣልንም!

## 2ኛ ቆሮንቶስ 1፡ 1-11

«እናንተ የምትገምቱት፥ በሕይወቴ ውስጥ አንዳችም ውጣ ውረድ እንዳልገጠመኝ፥ በምትኩ የሠመረ መንፈሣዊ ሕይወት እንደ መራሁና በትፍስሕት የተሞላ ሰላማዊ ኑሮ እንደ ኖረኝ አድርጋችሁ ነው። ጨርሶ ያላጋጠመኝ ነገር ነው! እኔ ብዙውን ጊዜዬን በጉስቁልና ያሳለፍሁና ነገር ዓለሙ የጨለመብኝ ሰው ነኝ።»

ከላይ የቀረበውን ጽሑፍ ያሰፈሩት በዘመናቸው «በእንግሊዝኛ ተናጋሪ ህብረተሰብ ውስጥ ከሁሉም የላቁ ሰባኪ» የሚል ቅጽል የተቸራቸው ዶክተር ጆን ሄንሪ ጆውት ነበሩ። እኚህ ሰው የአንጋፋ አብያተ-ክርስቲያናት መጋቢ፥ የታላላቅ መንፈሳዊ ስብሰባዎች ሰባኪና ከፍተኛ ተፈላጊነት የነበራቸውን መጻሕፍት የጻፉ ነበሩ።

«እኔ የመንፈስ ጭንቀት ቁራኛና ስጋት የተጫነኝ ሰው በመሆኔ ማናችሁም የእኔ ዓይነቱ ሥቃይ እንዳይደርስባችሁ አጥብቄ እመኛለሁ።»

እነዚህ ቃላት የፈለቁት በለንደን ከተማ ባበረከቱት አስደናቂ አገልግሎታቸው የተነሣ እንግሊዝ ካፈራቻቸው ሰባኪዎች ሁሉ የበላይ ተደርገው ከሚቆጠሩት ከቻርልስ ሂደን እስፐርጀን ስብከት ውስጥ ነበር።

ተስፋ መቁረጥ የሰዎችን የኑሮ ደረጃ ተመልክቶ አክብሮት አይለግስም። እንዲያውም ተስፋ መቁረጥ በይበልጥ የሚያጠቃው የተሳካላቸውን ሰዎች ይመስላል - ይበልጥ ወደ ተራራው ጫፍ በቀረብን መጥን፥ አወዳደቃችንም ያንኑ ያህል የከፋ ሊሆን ይችላል። ስለ ሆነም ታላቁ ሐዋርያ ጳውሎስ «ስለ ሕይወታችን እንኳ ተስፋ እስክንቈርጥ ድረስ ከአቅማችን በላይ ያለ ልክ ከብዶብን ነበር» (2ኛ ቆሮ. 1፡8) በማለት የጻፈውን ነገር ስንመለከት በአድናቆት አንዋጥም። ጳውሎስ በባሕርይና በአገልግሎት ታላቅ እንደ ነበር ቢታወቅም፥ እንደ እኛው ሰው ነበር።

ጳውሎስ ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥሪ ባይኖረውና (1፡ 1) ሌሎችን የመርዳት ፍላጎት ባይኖረው ኖሮ ከእነዚህ ሸክሞች ጋና በዳነም ነበር። በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን መሥርቶ በዚያው ለአንድ ዓመት ተኩል ጊዜ

አገልግሎ ነበር (የሐዋ. 18፡1-18)። ከእርሱ መለየት በኋላ ከባባድ ችግሮች ሲያቆጠቁጡ፥ ጢሞቴዎስ ሁኔታውን እንዲያስተካክል ከሰደደው በኋላ (1ኛ ቆሮ. 4፡17)፥ አንደኛ ቆሮንቶስ ብለን የምንጠራውን ደብዳቤ ጻፈላቸው።

የሚያሳዝነው ሁኔታዎቹ እየተባባሱ ሄዱና ጳውሎስ ችግር ፈጣሪዎችን ለመጋፈጥ ወደ ቆሮንቶስ «አሳዛኝ ጉዞ» አደረገ (2ኛ ቆሮ. 2 ከቁ. 1 ጀምሮ)። አሁንም መፍትሔ አልተገኘም። ከዚያም የሥራ ተባባሪው ቲቶ የሚያደርስላቸውን «ከባድ ደብዳቤ» ይጽፋል (2፡4-9፤ 7፡8-12)። በጉዳዩ ብዙ ከተጨነቀበት በኋላ፥ ጳውሎስ በመጨረሻው ቲቶን አገኘውና ችግሩ እልባት እንዳገኘ የሚያመለክት መልካም ዜና ሰማ። ከዚያ በኋላ ነበር ሁለተኛ ቆሮንቶስ የምንለውን ደብዳቤ የጻፈላቸው።

ደብዳቤውን የጻፈውም ለበርካታ ምክንያቶች ነው። በመጀመሪያ፥ ቤተ ክርስቲያኗ ያንን ሁሉ ችግር የፈጠረውን ምዕመን ይቅር ብላ እንድትመልሰው በመፈለጉ ነበር (2፡6-11)። እንዲሁም የዕቅዶቹን ለውጥ ለመግለጽና (1፡5-22) ሐዋርያ እንደ መሆኑ ሥልጣኑን ከሥራ ላይ ለማዋል ሲሆን (4፡1-2፤ ምዕ. 10-12)፥ በመጨረሻም በይሁዳ ለሚገኙ ድሆች በሚሰበሰበው የተለየ «የርዳታ አሰጣጥ» ላይ ቤተ ክርስቲያን ተካፋይ እንድትሆን ለማበረታታት በመፈለጉ ነበር (ምዕ. 8-9)።

በዚህ ደብዳቤ ውስጥ ከሚገኙ ቁልፍ ቃላት አንዱ መጽናናት ወይም መበረታታት ነው። ይህንን የሚገልጸው የግሪኩ ቃል «ይረዳው ዘንድ ከአንድ ሰው አጠገብ ተጠርቶ የቆመ» የሚል ትርጉም ይሰጣል። በዚህ ደብዳቤ ውስጥ አንቀጹ (ግሱ) 18 ጊዜ ያገለገለ ሲሆን፥ መጠሪያው (ስም) 11 ጊዜ አገልግሏል። ጳውሎስ ከመከራዎቹ ሁሉ ባሻገር፥ (በእግዚአብሔር ጸጋ) በመጽናናት የተሞላ ደብዳቤ ሊጽፍ በቅቷል።

ይህን በመሰለ መከራን ጫናዎች መካከል ያለውን ጳውሎስ ድልን ለመቀዳጀት ያበቃው ምሥጢር ምንድን ነበር? ምሥጢሩ እግዚአብሔር ነበር። አንተም ተስፋ በቆረጥህና የጀመርኸውን ሥራ እርግፍ አድርገህ ለመተው በተቃረብህ ጊዜ፥ አትኩሮትህን ከራስህ ላይ አንሥተህ በእግዚአብሔር ላይ አስቀምጥ። ጳውሎስ ከራሱ አስቸጋሪ ልምምድ ውስጥ፥ እንዴት በእግዚአብሔር መጽናናትን እንደምናገኝ ይነግረናል። ሦስት ቀላል ማሳሰቢያዎችንም ይሰጠናል።

## እግዚአብሔር ለአንተ ማን እንደሆነ አስታውስ
## (2ኛ ቆሮ. 1፡3)

ጳውሎስ ደብዳቤውን በምስጋና ይጀምራል። በርግጥ ስለ ነበረባቸው ሁኔታዎች የምስጋና መዝሙር ሊዘምር ባይችልም፥ ዳሩ ግን ሁኔታዎችን ሁሉ በመቆጣጠር ላይ ስለሚገኘው እግዚአብሔር ሊዘምር ይችል ነበር። ጳውሎስ ምስጋና ተስፋ በመቁረጥና በጭንቀት ላይ ድል ለማግኘት አስፈላጊ መሆኑን ተረድቶ ነበር። «ጸሎት ነገሮችን እንደሚለውጥ» ሁሉ «ምስጋናም ነገሮችን ይለውጣል»።

አምላክ ነውና አመስግኑት! «እግዚአብሔር ይባረክ» የሚለውን ይህንኑ ሐረግ በአዲስ ኪዳን ውስጥ በሌሎች ሁለት ሥፍራዎች ውስጥ ማለትም በኤፌሶን 1፡3 እና በ1 ጴጥሮስ 1፡3 ላይ እናገኛለን። በኤፌሶን 1፡3 ጳውሎስ እግዚአብሔርን የሚባርከው «በክርስቶስ በመረጠን» (ቁ. 4) እና «በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ» በባረከን ጊዜ አስቀድሞ ስላደረገው ነገር ነው። በ1ኛ ጴጥሮስ 1፡3 ላይ ደግሞ ጴጥሮስ ወደ ፊት ስለሚመጡ በረከቶችና ስለ «ሕያው ተስፋ» እግዚአብሔርን ያመሰግናል። ዳሩ ግን በ2ኛ ቆሮንቶስ ውስጥ ጳውሎስ በዚያን ጊዜ በዚያው ሥፍራው ስለ ነበሩት የወቅቱ በረከቶች እግዚአብሔርን እያመሰገነ ነበር።

በሠላሳ ዓመቱ ጦርነት ቀውጢ ወቅት፥ መጋቢ ማርቲን ሪንካርት በኢላንበርግ ሳክሰኒ ሕዝቡን በታማኝነት አገልግለው ነበር። በየቀኑ ወደ 40 የሚጠጉ የቀብር ሥነ ሥርዓቶች ከመምራታቸውም፥ በጠቅላላው በአገልግሎታቸው ደግሞ ከ4000 የሚበዙ ቀብሮች አስፈጽመዋል። ይሁንና ከዚህ አሳዛኝ ልምምዳቸው ውስጥ ዛሬ የምስጋና መዝሙር አድርገን የምንጠቀምበትን «የጸጋ ማዕድ» ቡራኬ ለልጆቻቸው ጽፈዋል።

ሁላችንም እናወድሰው - አምላካችንን ዛሬ፥

ከልባችን ተነሥተን - በጭብጨባ በዝማሬ፥

ድንቅ ነገሮችን በመሥራቱ፥

ፍጡራኑ በርሱ ይደሰቱ!

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት ነውና አመስግኑት! እኛም እግዚአብሔርን «አባት»ብለን የምንጠራውና እንደ ልጆቹ ከፊቱ ልንቀርብ የምንችለው ከኢየሱስ ክርስቶስ የተነሣ ነው። እግዚአብሔር እኛን በልጁ ውስጥ ስለሚያየን ልጁን እንደሚወደው አድርጎ ይወደናል

(ዮሐ. 17፡26)። «በውድ ልጁ» (ኤፌ. 1፡6) ተቀባይነትን ስላገኘን፥ «በእግዚአብሔር የተወደድን» (ሮሜ 1፡7) ነን።

ኢየሱስ በምድር ላይ ሲያገለግል ሳለ ያደረገለትን ሁሉ፥ እግዚአብሔር ዛሬም ለኛ ሊያደርግልን ይችላል። ልጁ ለእርሱ ውድ ስለ ሆነና እኛም የ«ፍቅሩ ልጅ መንግሥት» (ቆላ. 1፡13) ዜጎች ስለ ሆንን፥ ለአብ ውድ ነን። ለእርሱ ውድና ብርቅ በመሆናችን፥ የሕይወት ጫናዎች እንዳያጠፉን ይቆጣጠርልናል።

የምህረት አባት ስለ ሆነ አመስግኑት! ለአይሁድ ሰዎች «አባት» የሚለው ቃል «ምንጭ» ማለት ነው። ውሸቶች የመነጩት ከሰይጣን ስለ ሆነ፥ ሰይጣን የውሸቶች አባት ነው (ዮሐ. 8፡44)። በዘፍጥረት 4፡21 ላይ እንደተ ገለጸው፥ ዩባል በገናንና መለከትን ስለ ሠራ፥ የሙዚቃ መሣሪያዎች አባት ነበር። እንደዚሁም ምህረት ሁሉ የሚመነጨውና ሊገኝ የሚችለው ከእግዚአብሔር ብቻ ስለ ሆነ፥ እግዚአብሔር የምህረት አባት ነው።

እግዚአብሔር በጸጋው የማይገባንን ነገር ይሰጠናል፤ እንዲሁም በምህረቱ ለጥፋተኛነታችን ተመጣጣኝ ቅጣት እንድናገኝ አያደርግም። «ያልጠፋነው ከእግዚአብሔር ምህረት የተነሣ ነው» (ሰቆቃ. 3፡23)። የእግዚአብሔር ምህረት ብዙ (ነህ. 9፡19)፥ ፍቅር ያለበት [መዝ. (25)፡6] እና ታላቅ (ዘኍ. 14፡9) ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በተደጋጋሚ «የእግዚአብሔር ጸጋ ብዙ» እንደ ሆነና ከዚህም የተነሣ አቅርቦቱ ሊጎድል እንደማይችል ይናገራል [መዝ. 5፡8፤ (51)፡1፤ (69)፡13፥ 16፤ (106)፡7፥ 45፤ ሰቆቃ. 3፡32]።

የመጽናናት ሁሉ አምላክ ስለ ሆነ አመስግኑት! (በግሪክ ተመሳሳይ ሥርወ-ቃል ያላቸው) መጽናናት ወይም ዳረጎት የሚሉ ቃላት ከቁጥር 1-11 ውስጥ 10 ጊዜ ተደጋግመው ይገኛሉ። ስለ መጽናናት ስናስብ እንደ «ርኅራኄ» አድርገን ማሰብ የለብንም - ርኅራኄ ከማበርታቱ ይልቅ ሊያዝለን ወይም ሊያሳንፈን ይችላልና። እግዚአብሔር አእምሮአችንን ከተጨነቀበት ነገር ለማዘናጋት ጣፋጭ ከረሜላ ወይም አሻንጉሊት በመስጠት አይደልለንም። ይልቁንም መከራችንን ተጋፍጠን በድል እንወጣ ዘንድ በልባችን ውስጥ ብርታቱን ያኖራል። «መጽናናት» የሚለው ቃል «ብርታት ያለው» የሚል ትርጉም ካላቸው ሁለት የላቲን ቃላት የተገኘ ነው። የግሪኩ ቃል ትርጉም ወደ አንድ ሰው «ቀረብ ብሎ መርዳት» የሚል ነው። ይህንኑ ቃል በዮሐንስ 14-16 ስለ («አጽናኙ») መንፈስ ቅዱስ ተጠቅሶ እናገኘዋለን።

እግዚአብሔር በቃሉና በመንፈሱ አማካኝነት ሊያጽናናን ይችላል፤ ዳሩ ግን አንዳንድ ጊዜ፥ የሚያስፈልገንን መጽናናት ለመስጠት በሌሎች አማኞች ይጠቀማል (2ኛ ቆር. 2፡7-8፤ 7፡6-7)። ለሁላችንም «በርናባስ - የመጽናናት ልጅ» የሚለው ቅጽል-ስም ቢኖረን ኖሮ ምንኛ ግሩም በሆነ ነበር! (የሐዋ. 4፡36)።

ከአስቸጋሪ ሁኔታዎች የተነሣ ተስፋ በቆረጥህ ጊዜ፥ ወደ ራስህና ወደ ሰሚቶች መመልከት ወይም ዙሪያውን በከበቡህ ችግሮች ላይ ማተኩሩ ቀላል ነው። ዳሩ ግን ልንወስደው የሚገባን የመጀመሪያው እርምጃ በእምነት አቅንተን ጌታን ማየትና እግዚአብሔር ሊረዳን ከጎናችን መቆሙን መረዳት ነው። «ዓይኖቼን ወደ ተራሮች አነሣሁ፤ ረዳቴ ከወዴት ይምጣ? ረዳቴ ሰማይና ምድርን ከሠራ ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው» [መዝ. (121)፡ 1-2]።

## እግዚአብሔር ያደረገልህን ነገሮች አስታውስ (2ኛ ቆሮ. 1፡4፥ 8-11)

ቀድሞ ነገር እግዚአብሔር መከራዎቹ እንዲመጡ ይፈቅዳል። በግሪክ ቋንቋ መከራን ለመግለጽ የሚያገለግሉ አሥር መሠረታዊ ቃላት ቢኖሩ፥ ጳውሎስ በዚህ ደብዳቤው ውስጥ በአምስቱ ተጠቅሟል። ከሁሉም በላቀ ሁኔታ ተደጋግሞ የተጠቀሰው ትሊፕሲስ የሚለው ሲሆን፥ ትርጉሙም «ጠባብ፥ የታሰረ፥ የተወጠረ» ማለት ነው፤ ይህ ቃል በዚህ ደብዳቤ ውስጥ መከራ (2፡4፤ 4፡17፤ 1፡4፥ 8) ተብሎ ተተርጉሞአል። ጳውሎስ ዙሪያውን በአስቸጋሪ ሁኔታዎች እንደተከበበ ስለ ተሰማው፥ ማየት የሚችለው ወደ ላይ ወደ አምላኩ ብቻ ነበር።

ጳውሎስ በቁጥር 5 እና 6 የጌታችንን መከራ ለመግለጽ ባገለገለው «ፓቴማ» በሚለው ቃል ይጠቀማል (1 ጴጥ. 1፡ 11፤ 5፡ 1)። ሰብዓዊ ሰዎች በመሆናችንና ለችግር ስለ ተጋለጥን ብቻ የምንታገሣቸው አንዳንድ መከራዎች አሉ፤ ዳሩ ግን የእግዚአብሔር ሕዝብ ስለ ሆንንና እርሱን ለማገልገል ስለምንፈልግ የምንቀበላቸው ሌሎች መከራዎች ይኖራሉ።

መከራ በድንገት የሚመጣ ነገር እንደ ሆነ አድርገን ማሰብ የለብንም። ለአማኝ፥ ሁሉም ነገር በመለኮታዊ ቀጠሮ የሚመጣ ነው። ወደ ሕይወታችን የሚመጡትን መከራዎች በተመለከተ፥ አንድ ሰው ሊይዛቸው የሚችላቸው ሦስት አማራጭ አመለካከቶች ብቻ አሉ። መከራዎቻችን የ«ዕጣ-ፈንታ» ወይም የ«ዕድል» ውጤቶች ከሆኑ፥ ማድረግ የምንችለው ነገር ብቻ ይሆናል። ማንም ሰው ዕጣ-ፈንታን

ወይም ዕድልን ሊቆጣጠር አይችልም። በሌላ በኩል ደግሞ ሁሉንም ነገር መቆጣጠር ያለብን እኛው ከሆንን፥ ሁኔታው በተመሳሳይ ደረጃ ተስፋ የሚጣልበት አይሆንም። ዳሩ ግን እግዚአብሔር ሁኔታዎችን የሚቆጣጠር ከሆነና እኛም በእርሱ ከታመንን፥ በእርሱ እርዳታ ሁኔታዎችን ልናሸንፍ እንችላለን።

እግዚአብሔር መከራዎቹ እንዲመጡ የሚፈቅደው እርሱ እንደ ሆነ ከቃሉ ውስጥ በማስተማር፥ በመከራችን ሁሉ እንዳንሸነፍ ያደፋፍረናል። የሚገጥሙንን መከራዎች በመቆጣጠር ላይ እንዳለ በማስታወስ ያጽናናናል (1፡8)። «ስለ ሕይወታችን እንኳ ተስፋ እስከንቆርጥ ድረስ ከዓቅማችን በላይ ያለ ልክ ከብዶብን ነበር።» ጳውሎስ ከሚችለው በላይ ጭነት እንደ ተከመረበት የጋማ ከብት ሁኔታው ከብዶት ነበር። ዳሩ ግን እግዚአብሔር የጳውሎስን ዓቅም ስለሚያውቅ፥ ሁኔታውን ተቆጣጥሮታል።

የገጠመው «መከራ» በትክክል ምን እንደ ነበር ባናውቅም፥ ዳሩ ግን ጳውሎስ ለሞት እንደ ተቃረበ እስኪመስለው ድርስ ከባድ እንደ ነበር እንረዳለን። ከበርካታ ጠላቶቹ የተሰነዘረ አደጋ ይሁን (1ኛ ቆሮ. 15፡30-32፤ የሐዋ. 19፡ ከ21 ጀምሮ)፥ ወይም ብርቱ ሕመም ይሁን፥ ወይም የተለየ ሰይጣናዊ ጥቃት ይድረስበት ግልጽ የሆነልን ነገር የለም፤ ዳሩ ግን እግዚአብሔር ሁኔታዎቹን እንደ ተቆጣጠረና ባሪያውን እንደ ጠበቀው አሳምረን እናውቃለን። እግዚአብሔር ልጆቹን በመከራ እቶን ውስጥ ሲያስቀምጥ፥ እጁን በሙቀት መቆጣጠሪያው መሣሪያ ላይ፥ ዓይኑን ደግሞ በሙቀት መለኪያው ላይ ያኖራል (1ኛ ቆሮ. 10፡13፤ 1 ጴጥ. 1፡6-7)። ጳውሎስ እሞታለሁ ሲል ተስፋ ቆርጦ እንደ ሆነ እንጂ፥ እግዚአብሔር ግን ስለ ጳውሎስ አልተጨነቀም ነበር።

እግዚአብሔር መከራችንን እንድንሸከም ይረዳናል (2ኛ ቆሮ. 1፡9)። በመጀመሪያ ደረጃ እግዚአብሔር የሚያደርገው ነገር በራሳችን ምን ያህል ደካሞች እንደ ሆንን ማሳየት ነው። ጳውሎስ በተለያዩ ዓይነት መከራዎች ውስጥ ያለፈ፥ ስጦታና ልምድ የነበረው የእግዚአብሔር አገልጋይ ነበር (4፡8-12፤ 11፡ ከቁ. 23 ጀምሮ ይመልከቱ)። በመሠረቱ ይህ ሁሉ ልምምድ እነዚህን አዳዲስ ችግሮች ለመጋፈጥና ለማሸነፍ ባስቻለውም ነበር።

እግዚአብሔር ግን በስጦታችን ወይም በችሎታችን፥ በልምምዳችን ወይም «ባካበትነው መንፈሳዊ ብቃታችን» ሳይሆን፥ በእርሱ እንድንታመን ይፈልጋል። በራስ የመተማመን ስሜት ተሰምቶን

ከጠላት ጋር ስንጋጠም በሚያሳዝን ሁኔታ ለሽንፈት እንዳረጋለን። «ስደክም ያን ጊዜ ኃይለኛ ነኝና» (12፡10)።

አንተና እኔ የእኔነት ስሜታችንን ስናስወግደው (ስንገድለው)፥ በዚያን ጊዜ የእግዚአብሔር የትንሣኤው ኃይል በውስጣችን መሥራት ይጀምራል። የእግዚአብሔር የትንሣኤው ኃይል አብርሃምና ሣራን በሥጋቸው ልጅ እንዲያገኙ ያስቻላቸው እንደ ሙት በሆኑ ጊዜ ነበር (ሮሜ 4፡16-25)። ይሁንና «ለእኔነት መሞት» ማለት ምንም ነገር አለማድረግና ዝም ብሎ እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር እንዲያደርግ በመጠበቅ በግድየለሽነት መመልከት አይደለም። ጳውሎስ እንደ ጸለየ፥ ቅዱሳት መጻሕፍትን እንደ መረመረ፥ ከሥራ ተባባሪዎቹ ጋር እንደ ተማከረና እግዚአብሔር ሥራውን እንዲሠራ እንደ ታመነበት እርግጠኛ ልትሆን ትችላለህ። ሙታንን የሚያስነሣ አምላክ ለማንኛውም የሕይወት እንቆቅልሽ ብቁ ነው። እርሱ ሁሉንም የሚችል ብቁ አምላክ ነው፤ ዳሩ ግን እኛም እንዲጠቀምብን ፈቃደኞች መሆን ይገባል።

ጳውሎስ የተሰማውን ስሜት ለማስተባበል ወይም ለመካድ አልሞከረም፤ እግዚአብሔር ስሜቶቻችንን እንድንክድ ወይም እንድንደብቅ አይፈልግም። «በሁሉ ነገር መከራን ተቀበልን ... በውጭ ጠብ ነበረ፤ በውስጥ ፍርሃት ነበር» (2ኛ ቆሮ. 7፡5)። በ1፡9 ላይ የተጠቀሰው «የሞት ፍርድ» ምናልባት በጳውሎስ ላይ የተበየነውን የእስራትና ሞት ይፋዊ ውሳኔ የሚያመለክት ይሆናል። እዚህ ላይ ልብ ልትል የሚገባው የማያምኑ አይሁዶች የጳውሎስን ስደት እንዳባባሱና ሊያስወግዱትም እንደ ፈለጉ ነው (የሐዋ. 20፡19)። «በወገኔ በኩል ፍርሃት» (2ኛ ቆሮ. 11፡26) የሚለው ከአደጋዎች ዝርዝር ውስጥ አነስተኛ ሥፍራ ሊሰጠው አይገባም።

እግዚአብሔር ከመከራችን ያድነናል (2ኛ ቆሮ. 1፡10)። ጳውሎስ ወደ ኋላም ሆነ ወደፊት፥ ወይም ደግሞ ዙሪያ-ገባውን ቢያይም፥ የተመለከተው የእግዚአብሔርን የማዳን እጅ ነበር። ጳውሎስ የተጠቀመበት ቃል «በጭንቀት ውስጥ መርዳት፥ ማዳንና መጠበቅ» የሚል ትርጉም አለው። እግዚአብሔር ሁልጊዜም ከመቅጽበት አያድነንም፤ ልጆቹንም ሁሉ በተመሳሳይ መንገድ አያድናቸውም። ሐዋርያው ያዕቆብ ራሱን ተቆርጦ ሲሞት፥ ጴጥሮስ ግን ከወኅኒው እስራት አምልጧል (የሐዋ. 12)። ሁለቱም ድነዋል - ዳሩ ግን በተለያየ መንገድ። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ከመከራዎች ይሰውረናል - ሌላ ጊዜ ደግሞ በመከራዎቻችን ያድነናል።

እግዚአብሔር ማዳኑን የገለጸው ለጳውሎስ እምነት፥ እንዲሁም በቆሮንቶስ ከተማ ለሚጸልዩ ሰዎች እምነት ምላሽ በመስጠት ነበር (2ኛ ቆሮ. 1፡11)። «ይህ ችግረኛ ጮኸ፤ እግዚአብሔርም ሰማው፤ ከመከራውም ሁሉ አዳነው» [መዝ. (34)፡6]።

በመጨረሻም፥ እግዚአብሔር በመከራችን ይከብራል (2ኛ ቆሮ. 1፡11)። ጳውሎስ እግዚአብሔር ያደረገለትን በሚዘግብበት ጊዜ፥ ታላቅ የውዳሴና የምስጋና አዝማች ከቅዱሳኑ ወደ እግዚአብሔር ዙፋን አርጓል። እኔም ሆንኩኝ አንተ በምድር ላይ ልንፈጽመው የምንችለው ከሁሉም የላቀው አገልግሎት ለእግዚአብሔር ክብርን ማምጣት ሲሆን፥ አንዳንድ ጊዜ ያ አገልግሎት መከራ መቀበልንም ይጨምራል። «የተሰጠን ... ስጦታ» የሚለው ገለፃ የጳውሎስን ከሞት መዳን ያመለክታል - እውነትም ድንቅ ስጦታ ነበር!

ጳውሎስ ክርስቲያኖች እንዲጸልዩለት ለመጠየቅ አላፈረም ነበር። ቢያንስ በሰባቱ ደብዳቤዎቹ ውስጥ፥ ጸሎት በጣም እንደሚያስፈልገው ጠቅሶአል (ሮሜ 15፡30-32፤ ኤፌ.6፡18-19፤ ፊልጵ.1፡19፤ ቆላ. 4፡3፤ 1ኛ ተሰ. 5፡25፤ 2ኛ ተሰ. 3፡1፤ ፊል. 22)። ጳውሎስና የቆሮንቶስ አማኞች እርስ-በርሳቸው ይረዳዱ ነበር (2ኛ ቆሮ. 1፡11፥ 24)።

በቅርቡ አንድ ሚስዮናዊ ወዳጄ ሐኪሞች ትሞታለች ያሉዋት በሽተኛ ልጁ በድንቅ ስለ ዳነችበት ሁኔታ አጫውቶኝ ነበር። ልጅቱ በጣም በታመመችበት ወቅት፥ በርካታ ወገኖች በዩናይትድ እስቴትስ እየጸለዩላት ነበርና እግዚአብሔርም ጸሎታቸውን ሰምቶ ልጅቱን ፈወሳት። ለእግዚአብሔር አገልጋዮች ልንሰጥ የምንችለው ታላቁ እገዛ «በጸሎት መርዳት» ነው።

«እየጸለያችሁ አብራችሁ ስትረዱን» (ለ በጸሎት መረዳዳት) ተብሎ የተተረጎመው ሳኑፖርጂዎ በግሪክ አዲስ ኪዳን ውስጥ ያገለገለው በዚህ ሥፍራ ብቻ ሲሆን፥ ቃሉም፡- ከ-ጋር፥ ከ-ሥርና ሥራ ከሚሉት ሦስት ቃላት የተገነባ ነው። ይህም ከሸክም ሥር ሆነው፥ ሥራውን ለማጠናቀቅ በኅብረት የሚተጉትን ሠራተኞች ያመለክታል። እዚህ ላይ መንፈስ ቅዱስ በጸሎታችን እንደሚያግዘንና ሸክሙን ለመሸከም ትከሻችንን እንደሚያጠነክረው መረዳቱ የሚያጽናና ነገር ነው (ሮሜ 8፡26)።

ራሳችንን ለርሱ ብንሰጥ፥ ብንታመንበትና እንድናደርገው የሚሰጠንን ትዕዛዝ ሁሉ ብንፈጽም፥ እግዚአብሔር ዓላማዎቹን በመከራ በምንፈተንበት ጊዜ ይፈጽማል። ችግሮች እምነታችንን ሊጨምሩና የጸሎት ሕይወታችንን ሊያጠናክሩ ይችላሉ። የችግሮቻችንን ሸክሞች ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር በምንጋራበት ጊዜ ከእነርሱ ጋር የቀረበ ኅብረት እንዲኖረን ሊያደርጉን ይችላሉ። ችግሮች እግዚአብሔርን ለማስከበር ሊረዱ ይችላሉ። በመሆኑም፥ አንተም በመከራ ሕይወት ውስጥ ስትገኝ፥ እግዚአብሔር ለአንተ ምን እንደ ሆነና ምንስ እንደሚያደርግልህ አስታውስ።

## እግዚአብሔር በአንተ በኩል ያደረገውን ነገር አስታውስ (2ኛ ቆሮ. 1፡4-7)

በመከራ ጊዜ፥ ብዙዎቻችን ስለ ራሳችን ብቻ ወደ ማሰብና ሌሎችን ወደ መዘንጋት እናዘነብላለን። ማስተላለፊያ ቧንቧዎች በመሆን ፈንታ ማጠራቀሚያ ጋኖች እንሆናለን። ይሁንና መከራዎች የሚመጡበት አንድኛው ምክንያት እኔና አንተ ሌሎችን ለማጽናናትና ለማበረታታት የበረከት ቧምቧዎች እንሆን ዘንድ ነው። እግዚአብሔር እኛን ስላጽናናን፥ ሌሎችን ለማጽናናት እንችላለን።

ከምወዳቸው ሰባኪዎች አንዱ በዳላስ፥ ቴክሳስ የምትገኘውን የመጀመሪያ የባፕቲስት ቤተ ክርስቲያንን ለ50 ዓመታት ያህል በመጋቢነት ያገለገሉት ዶክተር ጆርጅ ደብልዩ ትሩዬት ናቸው። ከስብከቶቻቸው በአንድኛው ወቅት፥ ሕፃናቸው ስለ ሞተባቸው የማያምኑ ባልና ሚስት ታሪክ ነገሩን። ሥነ-ሥርዓት ያስፈጸሙት ዶክተር ትሩዬት ከመሆናቸውም የኋላ ኋላ ባለትዳሮቹ በኢየሱስ ክርስቶስ ሲታመኑ በማየት ደስ ተሰኝተዋል።

ከብዙ ወራት በኋላ፥ አንዲት ወጣት እናት ልጇ ሞተባትና አሁንም ዶክተር ትሩዬት እንዲያጽናኑዋት ተጠየቁ። ይሁንና እርሳቸው ያካፈሉዋት የማጽናኛ ቃላት ሁሉ ሐዘኗን የቀነሱላት አይመስልም ነበር። ዳሩ ግን የቀብሩ ሥነ-ሥርዓት በመፈጸም ላይ እንዳለ ያቺ ቀደም ሲል የተለወጠችው እናት ወደ አሁኗ ወጣት ሐዘንተኛ አጠገብ በመቅረብ፥ «እኔ በተመሳሳይ ሁኔታ ስላለፍሁ፥ አንቺም እያለፍሽ ያለሽበትን ነገር አውቃለሁ። እግዚአብሔር ጠርቶኛልና በዚያ በጨለማ አማካኝነት ወደ እርሱ መጣሁ። እርሱ አጽናንቶኛልና አንቺንም እንደ እኔ ያጽናናሻል!» አለች።

ዶክተር ትሩዬትም እንዲህ አሉ:- «የመጀመሪያዬቱ እናት ለሁለተኛዬቱ እናት እኔ ምናልባት በዕለታትና በወራት ውስጥ ላደርግ ከምችለው እጅግ የላቀ ነገር አድርጋለች፤ ይኸውም የመጀመሪያዬቱ እናት ራሷ በዚሁ ዓይነት የስቃይ መንገድ በመጓዟ ነው።»

ይህም ሆኖ ግን ሐዋርያው ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ማጽናናት ለመጋራት በትክክል ተመሳሳይ መከራዎችን ማለፍ እንደማያስፈልገን ይናገራል። የእግዚአብሔርን መጽናናት ካገኘን፥ «በመከራ ሁሉ ያሉትን ማጽናናት እንችላለን» (2ኛ ቆሮ. 1:4)። በርግጥ ተመሳሳይ መከራዎችን አሳልፈን ከሆነ፥ በመከራ ውስጥ የሚገኙትን ሰዎች ችግር በቀላሉ እንድንረዳና እንዴት እንደሚሰማቸውም በበለጠ እንድንገነዘብ ያስችለናል። ዳሩ ግን ልምምዶቻችን የእግዚአብሔርን ማጽናናት ሊለውጡት አይችሉም። የእኛ ልምምድ ምንም ይሁን ምን፥ ያ የእግዚአብሔር ማጽናናት ለምንጊዜም በቂና ብቁ ሆኖ ይኖራል።

ወደ በኋላ በ2ኛ ቆሮንቶስ 12፥ እንደምንመለከተው ጳውሎስ የዚህን መመሪያ ምሳሌ ይሰጠናል። እንደ ሹል እሾክ ሆኖ ሥጋውን - ባለማቋረጥ በመቸክቸክ የሚያውከው አንድ የሆነ ሥጋዊ ሥቃይ ተሰጥቶት ነበር። ይህ «የሥጋ መውጊያ» ምን እንደ ሆነ አናውቅም - ማወቁም የሚሰጠን ፋይዳ የለውም። የምናውቀው ነገር ቢኖር ግን፥ ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ጸጋ እንደ ተለማመደና ከዚያም ያንኑ መጽናናት ለእኛ እንዳጋራን ብቻ ነው። መከራህ ምንም ዓይነት ቢሆን፥ «ጸጋዬ ይበቃሃል» (12:9) የሚለው አለኝታ ልትመካበት የምትችለው የተስፋ ቃል ነው። ጳውሎስ መከራ ባይቀበል ኖሮ፥ እኛም ይህንን የተስፋ ቃል ባልተቀበልንም ነበር።

የሰብዓዊ መከራ ጉዳይ እንዲህ በቀላሉ የምንረዳው አይደለም። ወደ መንግሥተ-ሰማይ እስክንደርስ ድረስ ስለ እግዚአብሔር አሠራር የማንረዳቸው ምሥጢራት ስላሉ፥ እንዲህ በዋዛ የምንገነዘበው አይሆንም። አንዳንድ ጊዜ እንደ ዮናስ በራሳችን ኃጢአትና ዓመፅ ምክንያት እንሰቃያለን። አንዳንድ ጊዜ እንደ ጳውሎስ፥ ከኃጢአት ለመራቅ እንሰቃያለን (2ኛ ቆሮ. 12:7)። መከራ ባሕርያችንን በመቅረጽ (ሮሜ 5:1-5)፥ የእግዚአብሔርን ባሕርይ እንድንጋራ ይረዳናል (ዕብ. 12:1-11)።

ዳሩ ግን መከራ ሌሎችን እንድናገለግል ሊረዳንም ይችላል። በሁሉም ቤተ ክርስቲያን፥ መከራ የተቀበሉና የእግዚአብሔር ጸጋ የተለማመዱ በሳል ቅዱሳን አሉ፤ እነዚህም በማህበረ-ምዕመናኑ ውስጥ

ታላቅ «አጽናኞች» ናቸው። ጳውሎስ መከራ የተቀበለው ለፈጸመው ጥፋት በአፀፋው ቅጣት ተወስኖበት ሳይሆን፥ ዳሩ ግን ከፊቱ ለሚጠብቀው ሥራ እንዲዘጋጅ ነበር። ንጉሥ ዳዊት በመዝሙሩ ውስጥ የምናገኘውን ታላቅ መጽናናት ለእኛ ለማስተላለፍ ይቻለው ዘንድ፥ እስቲ የቱን ያህል ከባድ መከራዎች በትዕግሥት እንዳሳለፈ አስብ።

ከ2ኛ ቆሮንቶስ 1፡7 እንደምንረዳው ሁኔታው ምንጊዜም ሊቀለበስ እንደሚችል በግልጽ ሰፍሯል፡- የቆሮንቶስ አማኞች በመከራ ውስጥ ያልፉ ይሆናል፤ በዚያን ጊዜ ልክ እንደ ጳውሎስ ሌሎችን ለማጽናናት የሚያስችላቸውን የእግዚአብሔርን ጸጋ ይቀበላሉ። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር የቤተ ክርስቲያን ቤተሰብን ለተለየ መከራ የሚጠራው፥ በእነርሱ በኩል የተለየና የሚበዛ ጸጋውን ለማስተላለፍ ነው።

መታገሥን የምንማር እስከ ሆነ፥ የእግዚአብሔር የቸርነት መጽናናት በእጅጉ ይረዳናል። «በትዕግሥት መጽናት» የእምነትን መኖር የሚያመለክት መረጃ ነው። ለእግዚአብሔር መራራ ወይም ግትር ብንሆን፥ ከመገዛት ይልቅ ብናምፅ፥ መከራዎቻችን ለመልካም ሳይሆን ለክፋት በላያችን ላይ ይሰለጥናሉ። ተስፋ ባለመቁረጥ፥ በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ በትዕግሥት መጽናት የመንፈሳዊ ብስለት ምልክት ነው (ዕብ. 12፡1-7)።

እግዚአብሔር በእኛ በኩል ሥራውን ከማከናወኑ በፊት፥ በውስጣችን መሥራት አለበት። ለእኛ ግን ከጸጋ ይልቅ በእውቀት ማደጉ ይቀለናል (2 ጴጥ. 3፡18)። የእግዚአብሔርን እውነት መማርና በጭንቅላታችን ውስጥ ማከማቸት አንድ ነገር ሲሆን፥ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር እውነት መኖርና ይህንኑም ከባሕርያችን ጋር ማዋሃድ ፍጹም የተለየ ነገር ነው። እግዚአብሔር ወጣቱን ዮሴፍ ሁለተኛው የግብፅ ባለሥልጣን አድርጎ ከመሾሙ በፊት በ13 ዓመታት መከራ ውስጥ አሳለፈው፤ ዮሴፍም ግሩም ሰው ሆኖ ተለወጠ። እግዚአብሔር ሁልጊዜም ለእኛ ለሚያዘጋጀው ነገር እኛንም ያዘጋጀናል፤ የዝግጁቱም አንድኛው አካል በመከራ መፈተን ነው።

በዚህ አንፃር እስካየነው ድረስ፥ 2 ቆሮንቶስ 1፡5 በጣም አስፈላጊ ነው፡- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንኳ መከራ መቀበል ነበረበት! በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ ሆነን በምንሰቃይበት ጊዜ፥ የአዳኛችንን መከራዎች እየተካፈልን ነው ማለት ነው። ይህ በመስቀል ላይ «በሌሎች ምትክ መሰቃየቱን» አያመለክትም - የመስቀሉን ሞት ኃጢአት

ያልነካው ምትካችን ሆኖ ሊቀበል የሚችለው እርሱ ብቻ ስለ ሆነ (1 ጴጥ. 2፡21-25) ነው። እዚህ ላይ ጳውሎስ መከራዎችን የምንታገሠው፥ እኛም እንደ ክርስቶስ የአብን ሥራ በታማኝነት ስለምንሠራ ነውና «በመከራው ወደ መካፈል» (ፊልጵ. 3፡10) እያመለከተ ነበር። ይህ «ስለ ጽድቅ» (ማቴ. 5፡10-12) መከራ መቀበል ነው።

ዳሩ ግን የመከራው መጠን ሲጨምር፥ የእግዚአብሔርም የጸጋ አቅርቦት ይጨምራል። «የተትረፈረፈ» የሚለው ቃል ሞልቶ የሚፈሰውን የወንዝ ምስል ያሳስበናል። «ነገር ግን ጸጋን አብልጦ ይሰጣል» (ያዕ. 4፡6)። ይህ ልንረዳው የሚገባን አስፈላጊ መመሪያ ነው፡- እግዚአብሔር ለሚያስፈልገን ነገር ሁሉ የሚበቃ ጸጋ አለው፤ ዳሩ ግን ጸጋውን ተገቢው ጊዜ ከመድረሱ በፊት አይሰጠንም። «እንግዲህ ምህረትን እንድንቀበል፥ በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ ወደ ጸጋው ዙፋን ፊት በእምነት እንቅረብ» (ዕብ. 4፡16)። የግሪኩ ቃል «በሚያስፈልገን ጊዜ የምንቀበለው እርዳታ፥ ወቅታዊ እርዳታ» ይለዋል።

ስለ አንድ በእምነቱ ምክንያት ከታሰረ በኋላ በመጨረሻም በአደባባይ ተቃጥሎ እንዲሞት ስለ ተፈረደበት ብሪቱ አማኝ አንድ ጊዜ አንብቤ ነበር። ሰውየው እንደነገ ሊቃጠል ሲል ማምሻውን ያንን የሚጠብቀውን ነዲድ እሳት ለመቋቋም የሚያበቃ ጸጋ ይኖረው እንደ ሆነ ያስብ ነበርና ለሙከራ ያህል ጣቱን በሻማ ነበልባል ውስጥ በመጨመር ብርታቱን ለካው። ሻማውም ስለ አቃጠለው እጁን በፍጥነት ስቦ መለሰው። ከዚያም ያንን ሰማዕትነትን ሞት በቆራጥነት ሊጋፈጥ ከቶውንም እንደማይችል እርግጠኛ ሆነ። ዳሩ ግን በቀጣዩ ዕለት፥ እግዚአብሔርና የሚያስፈልገውን ጸጋ ስለ ሰጠው፥ በጠላቶቹ ሁሉ ፊት በደስታ የተሞላና በድል ያሸበረቀ የሰማዕትነት ተግባር ፈጽሟል።

አሁን 2ኛ ቆሮንቶስ 1፡9ን በተሻለ ሁኔታ ልንረዳ እንችላለን፤ የእግዚአብሔርን ጸጋ በድንገተኛ ችግራችን ወቅት ልንጠቀምበት የምናከማች ከሆነ፥ በራሳችን እንጂ «በጸጋ ሁሉ አምላክ» (1ኛ ጴጥ. 5፡10) ወደ መታመን አላዘነበልንም ማለት ነው። ገንዘብ፥ ምግብ፥ እውቀትና የመሳሰሉትን እግዚአብሔር የሚሰጠን ሀብቶች በሙሉ ምናልባትም ለወደፊት ግልጋሎታችን ልናጠራቅማቸው እንችል ይሆናል። የእግዚአብሔር ጸጋ ግን ለወደፊት አይጠራቀምም።

ይልቁንም፥ በዕለታዊ ሕይወታችን ውስጥ የእግዚአብሔርን ጸጋ ስንለማመድ፥ በሕይወታችን ውስጥ የሚከሰተው የፈሪሃ-እግዚአብሔር ባሕርይ እጅግ ትርፋማ እየሆነ ይሄዳል (ሮሜ 5፡1-5 ተመልከት)። በዚህም ባሕርያችን የመበልፀጋችን ጠቀሜታው የሚለካው፥ ለእግዚአብሔር ክብር ስንል ወደ ፊት የሚያጋጥሙንን አዳዲስ መከራዎች ለመቋቋም በሚኖረን የብቃት ደረጃ ነው።

መከራ ወደ ክርስቶስና የእርሱ ወደ ሆነው ሕዝቡ ይበልጥ ስለሚያቀርበን፥ በመከራ ውስጥ «አንድነት» አለ። ዳሩ ግን በራስ-ወዳድነት ተይዘን ስለ ራሳችን ብቻ ማሰብ ብንጀምር መከራ ከኅብረት ይልቅ መለየትን ሊፈጥር ይችላል። በዚህ ጊዜ የሚያገናኙ ድልድዮችን ሳይሆን፥ የሚያለያዩ ግድግዳዎችን እንገነባለን።

ስለዚህ አስፈላጊው ነገር አትኩሮትን በራስ ላይ ሳይሆን፥ በእግዚአብሔር ላይ ማስቀመጡ ነው። እግዚአብሔር ለአንተ ምን እንደ ሆነ አስታውስ - «የርኅራኄ አባት፥ የመጽናናትም ሁሉ አምላክ፥ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት» (2ኛ ቆሮ. 1፡3) ነው። እግዚአብሔር ምን እንደሚያደርግልህ አሁንም አስታውስ - እርሱ መከራዎችህን ሊቆጣጠርና ለአንተ በጎነትና ለራሱም ክብር ሊለውጣቸው የሚችል ነው። በመጨረሻም፥ እግዚአብሔር በአንተ በኩል የሚሠራውን ነገር በማስታወስ - ለሌሎች መጽናኛ አድርጎ እንዲጠቀምብህ ፍቀድለት።

## «እወድቃለሁ» ብለህ ተስፋ አትቁረጥ!

### 2ኛ ቆሮንቶስ 1፡12-2፡17

«ፕሮፋይልስ እን ከሬጅ» በሚለው መጽሐፋቸው ውስጥ፥ ጆን ኤፍ ኬኔዲ፥ «ታላላቅ ፈተናዎች ታላላቅ ሰዎችንና ታላላቅ የጀግንነት ሥራዎችን ያስገኛሉ» በማለት ጽፈዋል።

በአንድ ሰው ሕይወት ውስጥ የሚደርሰው ፈተና ሰውየውን እንደሚያንጸው እውነት ቢሆንም፥ በሌላም በኩል ፈተናው የሰውየውን የመንፈስ ጥንካሬ እንደሚያመለክት የታወቀ ነው። ጲላጦስ ታላቅ ፈተና ተጋርጦበት ነበር፤ ዳሩ ግን ፈተናውን ያስተናገደበት መንገድ ጀግንነት ወይም ታላቅነት አላጎናጸፈውም። የሕይወታችን አስቸጋሪ ሁኔታዎች የምናስተናግድበት መንገድ የሚወሰነው ባመዛኙ በባሕርያችን የጥንካሬ ደረጃ ሲሆን፥ ይህም የሚያሳየን ሕይወት በእኛነታችን ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ እንደ ግል ጥንካሬአችን መጠን መሆኑን ነው።

ጳውሎስ በዚህ እጅግ የግላዊነት ባሕርይ ጎልቶ በሚታይበት ደብዳቤ ውስጥ፥ ልቡን ለቆሮንቶስ ሰዎች (እና ለእኛ) በመክፈት ያለፈባቸውን መከራዎች ገልጿል። በመጀመሪያ ደረጃ፥ ዕቅዶቹን በመቀየሩ ብቻ የገባውን የተስፋ ቃል ያልጠበቀ የመሰለባቸው አንዳንድ በቆሮንቶስ ውስጥ የሚገኙ ሰዎች አጥብቀው ይተቹት ነበር። ክርስቲያኖች በአሳብ ሳይገናኙ ሲቀሩ፥ ቅሬታቸው ሥር እየሰደደ ሊሄድ ይችላል። ከዚህ በተጨማሪ፥ በቤተ ክርስቲያኗ ውስጥ ሐዋርያዊ ሥልጣኑን የሚፈታተን የተቃውሞ ችግር ገጥሞት ነበር። ከምዕመኖቹ ውስጥ አንድ ሰው - ምናልባትም መሪ ሳይሆን አይቀርም - ለዚህ ጥፋቱ መቀጣት ይገባው ስለ ነበረ ጳውሎስ በዚህ የተነሣ በጣም አዝኖ ነበር። በመጨረሻም፥ ጳውሎስ በእስያ ውስጥ በትዕግሥት ሊያሳልፋቸው የሚገባ ሌሎችም አስቸጋሪ ሁኔታዎች ተፈጥረው ነበር (2ኛ ቆሮ. 1፡8-11)፤ መከራዎቹም የገዘፉ በመሆናቸው፥ በሕይወቱ ተስፋ ቆርጦ ነበር።

ጳውሎስን ከውድቀት የታደገው ምን ይሆን? ከነዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ችግሮች የደረሱባቸው ሌሎች ሰዎች ለውድቀት ተዳርገው ይሆናል! ይሁንና ጳውሎስ ሁኔታዎቹን ድል-መንሣት ብቻ ሳይሆን፥

ዳሩ ግን ከዚያው አስቸጋሪ ልምምዱ ካገኘው ትምህርት፥ ዛሬም የእግዚአብሔር ሕዝብ ወደ ድል እንዲሻገር የሚረዳ ታላቅ ደብዳቤ አዘጋጅቷል። ጳውሎስ ጉዞውን እንዲቀጥል ያበረታቱት መንፈሳዊ ሀብቶች ምን ምን ነበሩ?

## ንጹሕ ሕሊና (2ኛ ቆሮ. 1፡ 12-24)

ሕሊና የሚለው ቃል ኮም እና እስኪሬ ከሚሉ ሁለት የላቲን ቃላት የተገኘ ሲሆን፥ ትርጉማቸውም ኮምለ«ከ...ጋር»፥ እስኪሬለ«ማወቅ» ማለት ነው። ሕሊና ከመንፈሳችን ጋር በመተባበር ነገሮችን የሚያውቅና ትክክል ስንሠራ ትክክለኛነቱን የሚያረጋግጥ፥ ስናጠፋ ደግሞ የሚወቅሰን ውስጣዊ ብቃት ነው። ሕሊና የእግዚአብሔር ሕግ አይደለም፤ ዳሩ ግን ለዚያው ሕግ ምስክርነቱን ይሰጣል። ሕሊና ብርሃንን ወደ ቤት የሚያስገባ መስኮት ነው፤ በመሆኑም ባለመታዘዛችን ምክንያት መስኮቱ ቢቆሽሽ፥ ብርሃኑ እየደበዘዘ ይሄዳል (ማቴ. 6፡22-23፤ ሮሜ 2፡ 14-16 ተመልከት)።

ጳውሎስ ሕሊና የሚለውን ቃል በመልእክቶቹ ውስጥና በሐዋርያት ሥራ ውስጥ እንደ ተገለጸውም በአገልግሎቱም ውስጥ ጭምር በአጠቃላይ 23 ጊዜ ያህል ተጠቅሞበታል። «ስለዚህ እኔ ደግሞ በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ሁልጊዜ ነውር የሌለባት ሕሊና ትኖረኝ ዘንድ እተጋለሁ» (የሐዋ. 24፡ 16)። አንድ ሰው ንጹሕ ሕሊና ካለው፥ ሌሎችን ለማጥላላት የሚጥር አታላይ ሳይሆን፥ ሐቀኛ በመሆኑ ሊታመን ይችላል።

የቆሮንቶስ ሰዎች ጳውሎስ እንዳታለላቸውና ግድ የለሽ እንደ ሆነባቸው አድርገው የወቀሱት ለምን ነበር? ዕቅዶቹን ለመቀየር ስለ ተገደደ ነው። በመጀመሪያ «ጌታ ቢፈቅድ» (1ኛ ቆሮ. 16፡2-8) በጋውን በቆሮንቶስ እንደሚያሳልፍ ተስፋ ሰጥቶ ነበር። ጳውሎስ የቆሮንቶስ ሰዎች ለአይሁዳውያን ድሆች አማኞች ያዋጡትን ገንዘብ ለመሰብሰብና ቤተ ክርስቲያኒቱ እርሱንና የሥራ ተባባሪዎቹን ወደ ኢየሩሳሌም በሚያደርጉት ጉዞ የመሸኘት ዕድል እንድታገኝ ፈልጎ ነበር።

ሆኖም ግን ጳውሎስ ከፍተኛ ጸጸትና እፍረት ቢያድርበትም ቅሉ፥ እነዚያን ዕቅዶች ለመቀየር ተገድዶ ነበር። እኔም በራሴ ውስን አገልግሎት ውስጥ እንኳን አንዳንዴ ዕቅዶችን ለመቀየርና የጉባዔዎችን ቀናት እስከ መሰረዝ ጭምር ስለምገደድ (ሐዋርያዊ ሥልጣን ሳይኖረኝ)፥ ለገጠመው ነገር አዝንላታለሁ። ዊል ሮጀርስ እንደሚሉት፥ «ዕቅዶች ወደ ነገሮች ያደርሱዎታል፤ ዳሩ ግን መንገድዎን ማስተካከል

አለብዎት።» ጳውሎስ ወደ መቄዶንያ ሲሄድና ሲመለስ፥ ሁለት ጊዜ ቆሮንቶስን ሊጎበኝ አቅዶ ነበር። ሐሳቡም ከቆሮንቶስ የተሰበሰበውን ገንዘብ ከመቄዶንያ አብያተ ክርስቲያናት በተሰበሰበው ላይ በመጨመር ወደ ኢየሩሳሌም ለመጓዝ ነበር።

የሚያሳዝነው ግን ሁለተኛውም ዕቅድ ሳይቀር አልተሳካለትም ነበር። ለምን? ምክንያቱም በፍቅር የተሞላው ልቡ ተጨማሪ «አሳዛኝ ጉብኝት» የማድረግ ጽናት ሊኖረው አይችልም ነበር (1፡23፤ 2፡1-3)። ጳውሎስ ዕቅዶቹን እንደ ቀየረ ቀደም ሲል ያሳወቃቸው ቢሆንም፥ ተቃውሚቸው ግን ሊበርድ አልቻለም ነበር። «ሥጋዊ ጥበብ» (1፡12) እንደ ተከተለ፥ ለእግዚአብሔር ፈቃድ ግድ እንዳልነበረው (1፡17)፥ እንዲሁም ዕቅዶቹን የሚወጥነው ራሱን ለማስደሰት ብቻ እንደ ሆነ በመግለጽ ወቀሱት። «ጳውሎስ አንድ ነገር ቢናገር ወይም ቢጽፍ፥ በርግጥ የሚያስበው ሌላ ነገር ነው። እርሱ አዎን የሚለው አይደለም ለማለት ሲሆን፥ አይደለም የሚለው ደግሞ አዎን ለማለት ነው» ይሉ ነበር።

አንድኛው አለመግባባት ወደ ሌላው ስለሚያመራ፥ ብዙውን ጊዜ በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል የሚፈጠሩትን አሳብ አለመግባባቶች ለማስተካከል በጣም አስቸጋሪ ነው። አንድ ጊዜ የሌሎችን ታማኝነት ወይም ቃላቸውን መጠራጠር ከጀመርን፥ ለሁሉም ዓይነት ችግሮች መከተል በሩ ወለል ብሎ ይከፈታል። ዳሩ ግን ወቃሾቹ ምንም ቢናገሩ፥ ጳውሎስ ንጹሕ ሕሊና ስለ ነበረው፥ ጸንቶ ይቆማል። የጻፈው፥ የተናገረውና የኖረው ሕይወት በሙሉ እርስ-በርሱ የሚቃረን ሳይሆን የሚደጋገፍ ነበር። በተጨማሪም፥ በመጀመሪያው ዕቅዱ ላይ «ጌታ ቢፈቅድ» የሚለውን ሐረግ ማከሉ ሊታወስ ይገባል (1ኛ ቆሮ. 16፡7 ፤ ያዕ. 4፡13-17 ተመልከት)።

ንጹሕ ሕሊና እስካለህ፥ የኢየሱስ ክርስቶስን መመለስ በመጠባበቅ ትኖራለህ (2ኛ ቆሮ. 1፡14)። «በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ቀን» የሚለው ክርስቶስ ወደሚገለጽበትና ቤተ ክርስቲያኑን ወደ ሰማይ ወደምትወሰድበት ሁኔታ ያመለክታል። ጳውሎስ በኢየሱስ ክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት በቆሮንቶስ አማኞች ደስ እንደሚሰኝና እነርሱም በእርሱ ሐሤት እንደሚያደርጉ እርግጠኛ ነበር። ዛሬ ምንም ዓይነት የአሳብ ልዩነት (ያለመግባባት) ቢኖርም፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት በምንቆምበት ጊዜ፥ ሁሉም ይቅር ተብሎና ተዘንግቶ ለኢየሱስ ክርስቶስ ምስጋና ወደ ክብር ይለወጣል።

ንጹሕ ሕሊና ሲኖርህ፥ ከፍተኛውን ሥፍራ የምትሰጠው ለእግዚአብሔር ፈቃድ ይሆናል (ቁ. 15-18)። ጳውሎስ ዕቅዶቹን በግድየለሽነት ወይም ሳያስብበት አልወጠነም፤ የጌታን ምሪት ሽቷል። ዳሩ ግን አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ከእርሱ ምን እንደሚጠብቅ እርግጠኛ አልነበረም (የሐዋ. 16፡6-10)፤ ይህም ሆኖ ግን እንዴት ጌታን መጠበቅ እንዳለበት ያውቅ ነበር። አነሳሽ ምክንያቶቹ (ዓላማዎቹ) ታማኝነትን የተንተራሱ ነበሩ፡- እግዚአብሔርን እንጂ ሰዎችን ለማስደሰት አይጥርም ነበር። እንዲያውም በዚያ የመገናኛና የመጓጓዣ አገልግሎት አስቸጋሪ በነበረበት ወቅት ጳውሎስ ከሌላው ውጥረት ጎን ለጎን ስለዚህ ጉዳይ ጭምር ማሰቡን ስናሰላስል መገረማችን አይቀርም።

ኢየሱስ የምንለውን ነገር በትክክል እንድንናገር አስተምሮናል። «ቃላችሁ አዎን አዎን ወይም አይደለም አይደለም ይሁን፤ ከነዚህም የወጣ ከክፉው ነው» (ማቴ. 5፡37)። አዎንታዊ ወይም አሉታዊ አባባሉን ለማጠናከር ተጨማሪ ቃላት የሚጠቀመው የመሠሪነት ባሕርይ ያለው ሰው ብቻ ነው። ጳውሎስ ንጹሕ ሕሊና ስለ ነበረው፥ የቆሮንቶስ ሰዎች እውነተኛ ባሕርይ እንዳለው ያውቁ ነበር። ለ18 ወራት በመካከላቸው ተገኝቶ ሲያገለግል፥ ጳውሎስ ታማኝነቱን አረጋግጦላቸዋል፤ ባሕርዩም አንድም ቀን ተለውጦ አያውቅም ነበር።

ንጹሕ ሕሊና ሲኖርህ፥ ኢየሱስ ክርስቶስን ታስከብራለህ (2ኛ ቆሮ. 1፡19-20)። በተመሳሳይ ጊዜ ክርስቶስን ማስከበርና የአታላይነትን ተግባር መወጣት አይቻልም። ይህን ለማድረግ ከሞከርህ ግን፥ ሕሊናህን ከማበላሸትህም ባሕርይህም በአደገኛ ሁኔታ ይቦረቦራል፤ ዞሮ ዞሮ ግን በመጨረሻ እውነት አሸንፋ ትወጣለች። የቆሮንቶስ ሰዎች ደኅንነትን ያገኙት ጳውሎስና ጓደኞቹ ኢየሱስ ክርስቶስን ስለ ሰበኩላቸው ነበር። ታዲያ እግዚአብሔር እንዴት እውነትን በሐሰተኛ መምህራን አማካኝነት ሊገልጽ ይችላል? የምንሠራው ሥራ ከምንኖረው ሕይወት ስለሚፈልቅ፥ ምስክርነቱና የአገልጋዩ እርምጃ የግድ ጎን ለጎን ሊሄዱ ይገባል።

ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ምንም ዓይነት ሰብዓዊ አዎንታ ወይም አሉታ ሊኖር አይችልም። ለሚተማመኑበት እርሱ የእግዚአብሔር «ዘላለማዊ አዎንታ» ነው። «እግዚአብሔር ለሰጠው የተስፋ ቃል ሁሉ አዎን ማለት በእርሱ ነውና፥ ስለዚህ ለእግዚአብሔር ስለ ክብሩ ለእኛ የሚነገረው አሜን በእርሱ ደግሞ ነው» (ቁ. 20)። ኢየሱስ ክርስቶስ የተስፋ ቃሎቹን

ይገልጻል፤ ይፈጽማል፤ የተስፋ ቃሎቹ የእኛ እንደ ሆኑ አድርገን እንድንቀበልም ያስችለናል። ከንጹሕ ሕሊና በረከቶች አንዱ ወደ እግዚአብሔርም ሆነ ወደ ሰው ፊት ለመቅረብ ወይም እግዚአብሔር በቃሉ ውስጥ የሚሰጠንን የተስፋ ቃሎች የራሳችን አድርገን ለመቁጠር አለመፍራታችን ነው። ጳውሎስ የራሱን የኃጢአት ልምምዶች መዝገብ ለማጥራት በእግዚአብሔር ቃል «ያለ አግባብ የመጠቀም» ጥፋት አልፈጸመም ነበር (4፡2 ተመልከት)።

በመጨረሻም ልትረዳው የሚገባው ንጹሕ ሕሊና ሲኖርህ፥ ከእግዚአብሔር መንፈስ ጋር መልካም ግንኙነት እንደሚኖርህ ነው (1፡21-24)። ማጽናት የሚለው ቃል የንግድ ቃል ሲሆን፥ ለውለታው በትክክል መፈጸም የሚሰጥ መተማመኛ ነው። ሻጩ ለገዢው የሚሸጠው ዕቃ አስቀድሞ በማስታወቂያ እንደ ተነገረለት አስተማማኝ ለመሆኑ ወይም የሚሰጠው አገልግሎት በተገባው ቃል ኪዳን መሠረት የሚፈጸም ለመሆኑ የሚሰጠው ማረጋገጫ ነው።

መንፈስ ቅዱስም እግዚአብሔር ሊደገፉበት የሚቻልና ተስፋ የሰጠውን ሁሉ እንደሚፈጽም የሚያመለክት ማረጋገጫው ነው። ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስን ላለማሳዘን ይጠነቀቅ ነበር፤ እንዲሁም መንፈስ ቅዱስ ስለማይወቅሰው፥ አነሳሽ ምክንያቶቹ ትክክል እንደ ሆኑና ሕሊናውም ንጹሕ እንደ ነበር ያውቅ ነበር።

ክርስቲያኖች ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ተቀብተዋል (ቁ. 21)። በብሉይ ኪዳን ዘመን በእግዚአብሔር የሚቀቡት ነቢያት፥ ካህናትና ነገሥታት ብቻ ነበሩ። ቅብዓታቸውም ለአገልግሎት ያስታጥቃቸው ነበር። ራሳችንን ለመንፈስ ቅዱስ በምንሰጥበት ጊዜ፥ እግዚአብሔርን እንድናገለግልና ፈሪሃ-እግዚአብሔር ያለበትን ሕይወት እንድንኖር ያስችለናል። እግዚአብሔርን ተቀባይነት ባለው መንገድ እንድናገለግል ልዩ መንፈሳዊ የመለየት ስጦታ ይሰጠናል (1 ዮሐ. 2፡20፥ 27)።

በተጨማሪም የክርስቶስ ንብረት መሆናችንን ለማመልከትና በእርሱ እንደ ተጠራን ለማረጋገጥ መንፈስ ቅዱስ አትሞናል (ኤፌ. 1፡13፤ 2ኛ ቆሮ. 1፡22)። ከውስጣችን ያለው የመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት እውነተኛ የእግዚአብሔር ልጆች እንጂ ለማስመሰል እየጣርን እንዳለሆነ ዋስትና ይሰጠናል (ሮሜ 5፡5፤ 8፡9)። እንዲሁም መንፈስ ቅዱስ የእርሱ ንብረት ስለ ሆንን፥ እንደሚጠብቀን ያረጋግጥልናል።

በመጨረሻም፥ መንፈስ ቅዱስ ሌሎች ሰዎች ምን ማድረግ እንዳለባቸው ትዕዛዝ የምንሰጥ «መንፈሳዊ አምባዎች» ሳንሆን፥ ዳሩ ግን ሌሎች እንዲያድጉ ለመርዳት እንደሚሹ አገልጋዮች እናገለግል ዘንድ ያስችለናል (2ኛ ቆሮ. 1፡23-24)። የቆሮንቶስን ቤተ ክርስቲያን ያጨናነቁት የሐሰት አስተማሪዎች የአምባገነንነት ጥፋት ይፈጽሙ ስለ ነበር (2ኛ ቆሮ. 11 ተመልከት)፥ የሕዝቡ ልብ ብዙ መሥዋዕትነት ከከፈለላቸው ከጳውሎስ ሸፈተ።

መንፈስ ቅዱስ አንድ ቀን ከእርሱ ጋር በመንግሥተ-ሰማይ እንደምንሆንና የከበረውን አካል እንደምንለብስ የሚያረጋግጥልን የእግዚአብሔር «መያዣ» (ቀብድ፥ ዋስትና፥ ማስተማመኛ) ነው (ኤፌ. 1፡14 ተመልከት)። ዛሬም ቢሆን በልባችን በመንግሥተ ሰማይ በረከቶች ሐሤት እንድናደርግ ያስችለናል! በልቡ ውስጥ ካደረው መንፈስ ቅዱስ የተነሣ፥ ጳውሎስ ንጹሕ ሕሊና ስለ ነበረው በአሳብ አለመግባባት የተነሣ የሚፈጠሩ ችግሮችን በፍቅርና በትዕግሥት ለማስተናገድ ይችል ነበር። አንተም ብትሆን የሕይወት መመሪያህ ሰዎችን ለማስደሰት እስከ ሆነ፥ የአስተሳሰብ ግጭቶች ያስጨንቁሃል፤ ዳሩ ግን የምትኖረው እግዚአብሔርን ለማስደሰት ከሆነ፥ የአሳብ ልዩነቶችን ለማስወገድ በፍቅርና በብርታት ለመጋፈጥ ትችላለህ።

የሚራራ ልብ (2ኛ ቆሮ. 2፡1-11) የእግዚአብሔር ሕዝብ እንደ መሆናችን መጠን፥ በተደጋጋሚ ሊያጋጥሙን የሚችሉትን ችግሮች ሙሉ በሙሉ ይገልፃል የሚለውን አንድ ባልታወቀ ደራሲ የተቋረጠ ስንኝ ብዙ ጊዜ እጠቅስ ነበር።

ከምንናፍቃቸው ቅዱሳን ጋራ
ለዘለዓለም በላይ መኖር
አቤት ያለው ታላቅ ክብር!
ግን - ካወቅናቸው ቅዱሳን ጋር
ዕለት ዕለት በምድር ስንኖር
መቼም አንርቅ ከማማረር!

ከቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን አንዱ ጳውሎስን በእጅጉ አሳዝኖት ነበር። ይህ ሰው ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 5 ውስጥ የጠቀሰውና በግልጽ በዘማዊነት ኃጢአት የተጠመደው ሰው ይሁን፥ ወይም የጳውሎስን የሐዋርያነት ሥልጣን በይፋ የተፈታተነው ሌላው ሰው፥ በርግጠኛነት ልንናገር አንችልም። ጳውሎስ ይህንኑ ችግር ለመፍታት

በፍጥነት ወደ ቆሮንቶስ የገሰገሰ ሲሆን (2ኛ ቆሮ. 2፡14፤ 13፡1)፥ በተጨማሪም ስለ ሁኔታው የሚያሳዝን ደብዳቤ ጽፎላቸዋል። በዚህም ሁሉ፥ የርኅራኄ ልብ አሳይቷል። የጳውሎስን ፍቅር የሚያመለክቱትን የሚከተሉትን መረጃዎች ልብ በል።

በመጀመሪያ፥ ለሌሎች ቅድሚያ ሰጥቷል (2ኛ ቆሮ. 2፡1-4)። ስለ ራሱ ስሜቶች ሳይሆን፥ በመጀመሪያ ለሌሎች ሰዎች ስሜቶች ያስብ ነበር። በክርስትና አገልግሎታችን፥ ትልቅ ደስታ የሚያመጡልን ሰዎች ትልቅ ሐዘንም ሊፈጥሩብን ይችላሉ፤ ጳውሎስም እያለፈበት የነበረው ይህንኑ ዓይነት ልምምድ ነበር። ከልቡ ከተሰማው ጭንቀት የፈለቀና በክርስቲያን ፍቅር የታጀበ ጠንካራ ደብዳቤ ይጽፋል። ዓቢይ መሻቱም ቤተ ክርስቲያኗ የእግዚአብሔርን ቃሉን እንድታከብር፥ አጥፊውን እንድትቀጣና ለማኅበረ-ምዕመናኑም ንጽሕናና ሰላም እንድታመጣ ነበር።

«የወዳጅ ማቁሰል የታመነ ነው፤ የጠላት መሳም ግን የበዛ ነው» (ምሳሌ 27፡6)። ጳውሎስ የተጠቀማቸው ቃላት የሚወዳቸውን ወገኖች ሊያሳዝኑ እንደሚችሉ ያውቅ ስለነበር፥ ልቡ በሐዘን ተነክቶ ነበር። ዳሩ ግን (ማንኛውም አፍቃሪ አባት እንደሚያውቀው) ሰውን ስለ ፍቅር ብሎ በመጉዳትና በጠላትነት በማጥቃት መካከል ያለውንም ትልቅ ልዩነት ያውቅ ነበር። አንዳንድ ጊዜ የሚወዱን ሰዎች ራሳችንን እንዳንጎዳ ሲሉ ሊቀጡን ይገባል።

ጳውሎስ ሐዋርያዊ ሥልጣኑን በመጠቀም ሰዎች እንዲያከብሩትና እንዲታዘዙት ለማድረግ ይችል ነበር፤ ይሁንና በፍቅርና በትዕግሥት ማገልገሉን መረጠ። እግዚአብሔር የጳውሎስ ዕቅዶች መለወጥ ቤተ ክርስቲያንን ከተጨማሪ ሕመም የመጠበቅ ዓላማ እንደ ነበረው ያውቅ ነበር (2ኛ ቆሮ. 1፡23-24)። ፍቅር ሁልጊዜም የሌሎችን ስሜቶች በማጤን ከማንኛውም ነገር በፊት ለእነርሱ የሚበጀውን ያስቀምጣል።

እንዲሁም ፍቅር ለሌሎች ይሻሻሉና ያድጉ ዘንድ ለመርዳት ይሻል (2ኛ ቆሮ. 2፡5-6)። እዚህ ላይ ጳውሎስ የተቃወመውንና የቤተ ክርስትያንን ቤተሰብ የከፋፈለውን ሰው ስም እንዳልጠቀሰ ማስተዋል ጠቃሚ ነው። ይሁንና ጳውሎስ ለራሱ ለሰውየው ጥቅም ሲል ቤተ ክርስቲያኗ ይህንኑ ሰው እንድትቀጣ አሳስቧል። ይህ በ1ኛ ቆሮንቶስ 5 ውስጥ የተጠቀሰው ዘማዊው ሰው ከሆነ፥ ቤተ ክርስቲያን ጉባዔ ተቀምጣ እንደ ቀጣችውና እርሱም ከኃጢአቱ ንስሐ ገብቶ እንደ ተመለሰ እነዚሁ ቁጥሮች ያመለክታሉ።

እውነተኛ ቅጣት የፍቅርን መኖር ያመለክታል (ዕብ. 12 ተመልከት)። ልጆችን በማሳደጉ ረገድ «ዘመናዊ እይታ» ያላቸው አንዳንድ ወጣት ወላጆች ከመጠን በላይ እንደሚወዱ ቸው በመናገር፥ የማይታዘዙላቸውን ለመቅጣት አይፈልጉም። ዳሩ ግን በርግጥ ልጆቻቸውን ቢወዱ ኖሮ፥ ጥፋታቸውን በማሳየት እንዲታረሙ በረዷቸው ነበር።

የቤተ ክርስቲያን የሥነ-ሥርዓት እርምጃ ተወዳጅነት ያለው ወይም በስፋት የሚሠራበት ዓይነት አይደለም። እጅግ በርካታ አብያተ ክርስቲያናት ይህን ዓይነቱ ሁኔታ ሲያጋጥማቸው ቅዱሳት መጻሕፍትን በመታዘዝ፥ «እውነትን በፍቅር በመናገር» (ኤፌ. 4፡15) ምትክ፥ ብሎም ሁኔታውን በድፍረት ከመጋፈጥ የሚመርጡት፥ ነገሩ ወደ ጎን ገሸሽ አድርገው መተውን ነው። ንጽሕና ሳይኖር፥ እውነተኛ መንፈሳዊ ሰላም ሊኖር ስለማይችል፥ «የሆነውን ሁሉ ዋጋ ከፍሎ በሰላም መኖር» የሚለው መርሆ ጨርሶ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም (ያዕ. 3፡15-18)። ወደ ጎን ገሸሽ ተደርገው የተተዉት ችግሮች፥ በኋላ የመባዛትና ከቀድሞውም የከፉ ችግሮችን የመፍጠር ዕድል አላቸው።

ጳውሎስ ያጋለጠውና ቤተ ክርስቲያን የቀጣችው ወንድም ፍቅር ያለበት አትኩሮት ተሰጥቶት ርዳታ አግኝቷል። ልጅ ሳለሁ፥ ምንም እንኳ ከተቀበልሁት የሚልቅ ቅጣት እንደሚገባኝ መናዘዝ ቢኖርብኝም፥ ቤተሰቦቼ የሚሰጡኝን ቅጣት ሁልጊዜም አልወድም ነበር። ዳሩ ግን አሁን ወደ ኋላ ተመልሼ ሳስብ፥ ራሴን ለባሰ ጥፋት እንዳላጋልጥ ለመከላከል ሲሉ ቤተሰቦቼ ከፍቅራቸው የተነሣ እስኪጎዱኝ ድረስ ጨክነው ሊቀጡኝ በመውደዳቸው እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። «ይህን ማድረጋችን አንተን ከሚጎዳው በላይ እኛንም ይጎዳናል» ሲሉ ይናገሩኝ የነበረው ምን ማለት እንደ ሆነ፥ አሁን በግልፅ ተረድቼዋለሁ።

በመጨረሻም፥ ፍቅር ይቅር ይላል፤ ያበረታታልም (2ኛ ቆሮ. 2፡7-11)። ጳውሎስ የቤተ ክርስቲያኗ ቤተሰብ ያንን ሰው ይቅር እንዲል ያበረታታ ሲሆን፥ ይህንኑ ምክር ከሥራ ላይ እንዲያውሉት ጠንካራ ምክንያቶችን ያቀርባል። በመጀመሪያ ደረጃ፥ ለሰውየው ይቅርታ መደረጉ «ከልክ ባለፈ ኃዘን እንዳይዋጥ» (ቁ. 7-8)፥ ለራሱ ጥቅም ሲባል ነበር። ይቅርታ የተሰበረውን ልብ ለመጠገን የሚረዳ መድኃኒት ነው። ቤተ ክርስቲያን ይህንኑ ንስሐ የገባ ሰው የፍቅሯ ተካፋይ የማድረጓን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነበር።

በራሴ የመጋቢነት አገልግሎት ውስጥ፥ የሥነ-ሥርዓት እርምጃ የተወሰደባቸው አባላት ይቅርታ ተደርጎላቸው ወደ ኅብረቱ በተቀላቀሉባቸው ጉባዔዎች ላይ መልእክት አካፍያለሁ፤ እነዚህም በሕይወቴ ውስጥ ከፍተኛና የተቀደሱ ሰዓታት ነበሩ። የቤተ ክርስቲያኗ ቤተሰቦች ይቅርታ ለተደረገለት ወንድም ወይም እህት ኃጢአታቸው እንደ ተዘነጋና ወደ ኅብረቱ እንደ ተመለሱ ሲያረጋግጡላቸው አካባቢው ድንቅ በሆነ በጌታ ሕልውና ይሞላል። ልጁን የሚቀጣ ወላጅ ሁሉ ከቅጣቱ አስከትሎ ፍቅርና ይቅርታው ከልብ የመነጨ ለመሆኑ ዋስትና መስጠት አለበት፤ ይህ ካልሆነ ግን ቅጣቱ ከማቃናት ይልቅ የባሰ ጠማማነትን ያስከትላል።

ክርስቲያኖች ለጌታ ሲሉ ይቅር ለተባለው ወንድም ፍቅራቸውን ያለማጓደል መለገስ አለባቸው (ቁ. 9-10)። እንዲሁም ቅጣት ለወንድም መስጠት ያለበት ግዴታ የመሆኑን ያህል፥ ለጌታም የመታዘዝ ኃላፊነትን ያቀፈ ጉዳይ ነው። ይህን የመሰለው ችግር የሚንፀባረቀው ባዘነው ሐዋርያና ኃጢአትን በፈጸመው ወንድም መካከል ብቻ ሳይሆን፥ ኃጢአትን በፈጸመው ወንድምና በሚያዝነው አዳኝ መካከልም ጭምር ነው። ያ ወንድም በእርግጥም በቤተ ክርስቲያን እና በጳውሎስ ላይ በደል ቢፈጽምም፥ ዳሩ ግን ከሁሉም በላይ በጌታ ላይ ኃጢአትን ሠርቷል። ፍርሃት የሚያጠቃቸው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ይህን የመሳሰለውን ሁኔታ በታማኝነት በመጋፈጥ ምትክ «አለባብሰው» ሲያልፉት፥ የጌታን ልብ ያሳዝናሉ።

ጳውሎስ ሦስተኛ ምክንያትም ሰጥቷል፡- ጥፋት የፈጸመውን ወንድም ለቤተ ክርስቲያኗ ደኅንነት ሲሉ ይቅር ማለት ነበረባቸው (ቁ. 11)። ለኃጢአት ተገቢ የሆነ መጽሐፈ ቅዱሳዊ መፍትሔ እንዳይገኝለት ከምዕመናኑ አንዱ እንቅፋት ሲሆንና ይቅርታ ለማድረግ ሳይፈቅድ ሲቀር፥ ሰይጣን በማኅበረ-ምዕመናን ውስጥ ተልዕኮውን የሚፈጽምበት ቀላል «መንሻ» ያገኛል። ይቅርታን የማያደርግ መንፈስ ካለን፥ መንፈስ ቅዱስን በማሳዘን «ለዲያብሎስ ፈንታ» (ኤፌ. 4፡27-32) እንሰጣለን።

ከሰይጣን «ማታለያ ዘዴዎች» አንዱ ኃጢአት የሠሩ አማኞች ፍጹም ተስፋ እንዲቆርጡ መክሰስ ነው። በእኔም በኩል፥ ከሰይጣን ጭቆናና ክስ በታች በመውደቃቸው ምክንያት እርዳታ ሽተው ደብዳቤ የጻፉልኝ ወይም ስልክ የደወሉልኝ ሰዎች በብዛት አጋጥመውኛል። መንፈስ ቅዱስ የሚወቅሰን፥ ኃጢአታችንን ተናዝዘን ለመንጻት ወደ

ክርስቶስ እንድንመለስ ሲሆን፥ ዳሩ ግን ሰይጣን ተስፋ ቆርጠን የእምነት ጉዞአችንን እንድንተው ይከሰናል።

ያጠፋው ወንድም ወይም እህት ከመጽሐፍ ቅዱስ መመሪያ አኳያ ከተቀጡና ንስሐ ከገቡ በኋላ፥ የቤተ ክርስቲያኒቱ ቤተሰብ ይቅርታ በማድረግ እንደ ቀድሞው ሊያቅፏቸው ይገባል፤ ነገሩም ዳግመኛ ላይታወስ መደምደም አለበት። (ዳግም ላይወሳ)። የቤተ ክርስቲያኒቱ ቤተሰብ ወይም ከቤተሰቡ ውስጥ ማንኛውም ሰው ይቅርታን የማያደርግ መንፈስ ካለው፥ ሰይጣን በቤተ ክርስቲያን ላይ አዳዲስ ጥቃቶችን ለማስከተል በዚሁ ቀዳዳ ይጠቀማል።

ጳውሎስ ንጹሕ ሕሊናና የሚራራ ልብ ስለ ነበረው፥ ከፊቱ የተጋረጡትን ችግሮች ለማሸነፍ ችሏል። ዳሩ ግን ለድል ያበቃው ሦስተኛው መንፈሳዊ ሀብት ቀጥሎ የተጠቀሰው ነበር፡-

## ድል-ነሺ እምነት (2ኛ ቆሮ. 2፡ 12-17)

በእስያ የተዘረጉት የጳውሎስ ዕቅዶች ሙሉ ለሙሉ የከሸፉ ይመስል ነበር። ቲቶ የት ነበር? በቆሮንቶስ ያለውስ ሁኔታ ምን ይመስል ነበር? ጳውሎስ በጢሮአዳ ለአገልግሎት የተከፈቱ በሮች ቢኖሩም፥ በእነዚያ በሮች ውስጥ እንደምኞቱ ለመመላለስ የልብ ሰላም አልነበረውም። በሰብዓዊ አባባል፥ ጦርነቱ በሰይጣን ድል-አድራጊነት የተፈጸመ ይመስል ነበር።

የቀረው ነገር ቢኖር የጳውሎስ ድል-አድራጊ እምነት ብቻ ነበር! በእርግጥም የነበረበትን ሁኔታ ተቋቁሞ፥ «ለአምላክ ምስጋና ይሁን!» (ቁ. 14) ለማለት ቻለ። ይህ የምስጋና መዝሙር የፈለቀው ጳውሎስ ጌታን በመተማመን ካገኘው ዋስትና ውስጥ ነው።

እግዚአብሔር እየመራው እንዳለ እርግጠኛ ነበር (2ኛ ቆሮ. 2፡14) ሁኔታዎቹ አመቺ ባለመሆናቸው፥ ጳውሎስ ማብቂያ ያልነበራቸውን ችግሮችና ኃዘኖች ለመግለጽ አይችልም ነበር፤ ዳሩ ግን እግዚአብሔር ሁኔታዎቹን እየተቆጣጠረ እንዳለ እርግጠኛ ነበር። አንድ አማኝ እግዚአብሔርን እስከ ወደደውና ፈቃዱን ለማድረግ እስከ ፈለገበት ጊዜ ድረስ፥ እግዚአብሔር ነገርን ሁሉ ለበጎ እንደሚያደርግለት ሁልጊዜም እርግጠኛ ሊሆን ይችላል (ሮሜ 8፡28)። ይህም ለግድየለሽነት የተሰጠ የማመካኛ የተስፋ ቃል ሳይሆን፥ ለመተማመኛ የሚረዳ ማበረታቻ ነው።

አንድ ወዳጄ በሶሻሊስት አገር ውስጥ ከሚገኝ ከአንድ ክርስቲያን መሪ ጋር ሊገናኝና ስለ አንድ መጽሐፍ ሕትመት ሊወያይ ፈልጎ ነበር። ይሁንና ከሰውየው ጋር ለመገናኘት የነበረው ዕቅድ ሳይሳካለት ቀረ። ወዳጄም በአደገኛ ሥፍራ ብቻውን ተቀምጦ የሚያደርገው ጠፍቶት ግራ ተጋብቶ ሳለ፥ አንድ የማያውቀው እንግዳ ሰው አጋጠመው። ይሁንና ያ እንግዳው ሰው ወደሚፈልገው መሪ ሊያደርሰው ቻለ! ይህም የእግዚአብሔር ፈቃድ በሥራ ላይ እንደ ነበር የሚያመለክትና ለሮሜ 8፡28 ተፈፃሚነት ማረጋገጫ ነበር።

እንዲሁም ጳውሎስ እግዚአብሔር በድል እየመራው ለመሆኑ እርግጠኛ ነበር (2ኛ ቆሮ. 2፡14)። በዚህ ጥቅስ ውስጥ የምናገኘው ሥዕል፥ ሮም ከጦር ሜዳ በአሸናፊነት ለሚመለሱ ጀነራሎችዋ የምታዘጋጀውን ዓይነት «የድል አቀባበል» የሚያመለክት ነበር።

አንድ ሮማዊ ጠቅላይ አዛዥ በባዕድ ምድር ላይ ሙሉ ለሙሉ ድል ከተቀዳጀ፥ ቢያንስ 5000 የጠላት ወታደሮችን ከገደለና ለንጉሠ ነገሥቱ ተጨማሪ ግዛት ካስገኘ፥ ያ ጠቅላይ አዛዥ ለሮማዊ ድል አድራጊ የሚሰጥ የክብር ሥርዓት ይደረግለታል። ከሚደረጉት የአቀባበል ሥርዓቶችም ውስጥ አንዱ ጠቅላይ አዛዡ በባልደረቦቹ ታጅቦና በወርቅ ሰረገላ ላይ ተቀምጦ የሚያልፍበት ትርዒት ነበር። በተጨማሪም የማረካቸው የጠላት ወታደሮችና የበዘበዛቸው ንብረቶች ለዕይታ ይቀርቡ ነበር። የሮም ካህናትም ድል ለነሣው ሠራዊት ባለውለተኛነታቸውን ለመግለጽ ዕጣን እያጤሱ በሥነ-ሥርዓቱ ላይ በድምቀት ይካፈሉ ነበር።

ሰልፉም በከተማዪቱ ውስጥ የተለየ መንገድ ይዞ በመጓዝ፥ ምስኪኖቹ ምርኮኞች ከአራዊት ጋር በመታገል ሕዝቡን ወደሚያዝናኑበት የትርዒት ማሳያ መድረክ (ሰርከስ ማክሲመስ) ሲደርስ ያቆማል። ያም ዜጎቹ በሙሉ ሮማዊውን ድል አድራጊ በክብር የሚቀበሉበት ዕለት በሮም ታሪክ ውስጥ እንደ ልዩ ዕለት የሚቆጠር ነበር።

ይህ የታሪክ ምዕራፍ ዛሬ ሸክም ከተጫነው አማኝ ሕይወት ጋር የሚዛመደው እንዴት ነው? ታላቁ ጠቅላይ አዛዣችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ባዕድ ምድር (ወደዚህች ዓለም) መጥቶ፥ ጠላትን (ሰይጣንን) ሙሉ ለሙሉ ድል አድርጓል። 5000 ሰዎችን በመግደል ፈንታ፥ ከ5000 ለሚልቁ ሰዎች ሕይወትን ሰጠ - በዕለተ-ጴንጠቆስጤ የዳኑትን 3000 እና ብዙም ሳይቆይ ወደ መዳን የመጡትን 2000 ሰዎች ጨምሮ (የሐዋ. 2፡41፤ 4፡4)። ኢየሱስ ክርስቶስ የሰይጣንና የኃጢአት ባሪያዎች

የነበሩትን የጠፉ ነፍሳት ማርኮ ወደ መዳን አምጥቷል (ሉቃ. 11፡14-22፤ ቆላ. 2፡15፤ ኤፌ. 4፡8)። ምንኛ የሰመረ ድል ነው!

የድል-ነሺ ጄነራል ልጆች የድሉ ተካፋይ በመሆን፥ ከአባታቸው ሰረገላ ኋላ ኋላ ይከተሉ ነበር፤ ዛሬም የአማኞች ሕይወት እንዲሁ ነው - የክርስቶስን ድል መከተል። እኛ ገና ለገና ለድል አንዋጋም፤ ዳሩ ግን ድልን ተላብሰን እንዋጋለን። ለጳውሎስ በእስያም ሆነ በቆሮንቶስ የነበረው ሁኔታው ከቶውንም ድልን የሚያቀዳጀው አልነበረውም፤ ዳሩ ግን እርሱ በእግዚአብሔር ስላመነ፥ እግዚአብሔር ሽንፈትን ወደ ድል አድራጊነት ለወጠው።

በመጨረሻም፥ ጳውሎስ እግዚአብሔር ሲመራው ሳለ እየተጠቀመበት እንደ ሆነ እርግጠኛ ነበር (2ኛ ቆሮ. 2፡14-17)። የሮም ካህናት በሥርዓቱ ላይ ዕጣን በሚያጤሱበት ጊዜ፥ ከዚያ የሚመጣው ሽታ በተለያዩ ሰዎች ላይ የተለያየ ስሜት ያሳድር ነበር። ለድል-ነሺ ወታደሮች፥ ይህ የሕይወትና የድል ሽታ ሲሆን፥ ዳሩ ግን ድል ለተመቱት ወታደሮች የሽንፈትና የሞት ሽታ ነበር። በአራዊት ተቦጫጭቀው የሚሞቱበት ጊዜ እየተቃረበ ነውና።

ጳውሎስ ይህንን የዕጣን ምስል በመጠቀም፥ የክርስትናን አገልግሎት ገልጿል። አማኞችን በሕይወታቸውና በሥራቸው የኢየሱስ ክርስቶስን መልካም መዓዛ እንደሚያመነጩ ዕጣኖች አድርጎ ይመለከታቸዋል። ለእግዚአብሔር አማኞች የኢየሱስ ክርስቶስ መልካም መዓዛዎች ናቸው። ለሌሎች አማኞች የሕይወት ሽታዎች ስንሆን፥ ዳሩ ግን ለማያምኑ ሰዎች የሞት ሽታዎች ነን። በሌላ አባባል፥ የክርስትና ሕይወትና አገልግሎት የሕይወትና የሞት ጉዳዮች ናቸው። የምንኖርበት ወይም የምንሠራበት ሁኔታ ዙርያችንን ለከበበን የተጎሳቆለ ዓለም የሕይወት ወይም የሞት ትርጉም ሊኖረው ይችላል።

ጳውሎስ፥ «ለዚህ ነገር የሚበቃ ማን ነው?» (ቁ. 16) ብሎ መጮኹ የሚያስደንቅ አይሆንም። በቀጣዩ ምዕራፍ ውስጥ የዚህን ጥያቄ ምላሽ ይሰጣል፡- «ብቃታችን ከእግዚአብሔር ነው» (3፡5)። ለቆሮንቶስ ሰዎች ልቡ ንጹሕ እንደ ሆነና አነሳሽ ዓላማዎቹም ታማኝ እንደ ሆኑ ይገልጽላቸዋል። እንደዚሁም የድል-ነሺውን አዳኝ ፈለግ ተከትሎ ሲመላለስ ሳለ በብልጠት ተጠቅሞ በእግዚአብሔር ቃል «የሚነግድበት» ምክንያት አልነበረውም። እነርሱ የእርሱን አሳብ ላይረዱ ቢችሉም፥ ዳሩ ግን እግዚአብሔር ልቡን ያውቅ ነበር።

«እወድቃለሁ» ብለን ተስፋ መቁረጥ የለብንም! ሁኔታዎች ተስፋ ሊያስቆርጡን፥ ሰዎች ሊቃወሙንና አሳባችንን ላይረዱልን ይችላሉ፤ ዳሩ ግን ውጊያውን ድል ለመንሣት በክርስቶስ መንፈሳዊ ሀብቶች አሉን፡- ንጹሕ ሕሊና፥ የሚራራ ልብና ድል የሚነሳ እምነት።

«እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል? ... በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን» (ሮሜ 8፡31፥37)።

- 3 -

# ከክብር ወደ ክብር

## 2ኛ ቆሮንቶስ 3

እውነተኛ ነገር በሚኖርበት ጊዜ ሁሉ፥ ሰዎች የማስመሰል ተግባር ሲፈጽሙ ይታያል። ሌላው ቀርቶ የኪነ-ጥበብ ሃያሲያን እንኳ «ምርጥ ሥራዎች» ተብለው በቀረቡ አስመሳይ የሥዕላ ሥዕል ቅቦች ተሞኝተዋል፤ እንደዚሁም እውነተኛ አሳታሚዎችም «ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸው መዛግብት» እንደ ሆኑ በመቁጠር የገዙዋቸው ንብረቶች በማስመሰል የተሠሩ መሆናቸውን ዘግይተው ይረዳሉ። ይህን የመሳሰለውን ማጭበርበር ስንመለከት፥ ሄንሪ ዎርድ ቢቸር የተባሉት ሰው «ለውሸት ምንጊዜም ምርኩዙ እውነት ነው» በማለት የተናገሩትን ነገር ሐቀኝነት ያስታውሰናል።

የእግዚአብሔር የጸጋ ወንጌል በአሕዛብ መካከል መሠራጨት ከጀመረ ብዙም ሳይሰነብት፥ የጸጋና የሕግ ቅልቅል የሆነው የማስመሰል «ወንጌል» ብቅ ማለት ጀመረ። ይህም ተግባር የተከናወነው «አይሁዳውያን ወግ አጥባቂዎች» ብለን በምንጠራቸው ቀናተኛ ቡድኖች ነበር። ጳውሎስ የገላትያ ሰዎች እምነታቸውን ውድቅ እንዲያደርጉባቸው የጻፈላቸው ሲሆን፥ በ2ኛ ቆሮንቶስም ውስጥ ስለ እነዚህ ወገኖች ብዙ ጊዜ ይጠቅሳል።

የእነዚህ ቡድኖች ዓቢይ መልእክት ያተኮረው ደኅንነት የሚገኘው በክርስቶስ በማመንና ሕግን በመጠበቅ እንደ ሆነ በማስገንዘብ ላይ ነበር (የሐዋ. 15 ከቁ. 1 ጀምሮ)። እንደዚሁም አማኙ በእምነቱ ፍጹም የሚሆነው የሙሴን ሕግ በመጠበቅ እንደ ሆነ ያስተምሩ ነበር። እንዲሁም ደካማው ሰብዓዊ ተፈጥሮ ክርስቶስን ከመታመንና መንፈስ ቅዱስ እንዲሠራ ከመፍቀድ ይልቅ፥ ቀደምትነቱን ሃይማኖታዊ ግቦችን ለመጨበጥ በመስጠቱ፥ «የሕጋዊነት ወንጌላቸው» ከፍተኛ ተወዳጅነትን ሊያተርፍ ችሎ ነበር። ለሰብዓዊው ሚዛን፥ ከእውነተኛ ጽድቅ ይልቅ «ሃይማኖት»ን መለካት በጣም ቀላል ነው።

ጳውሎስ እነዚህን የሐሰት አስተማሪዎች የእግዚአብሔር ቃል «ሸቃጮች» አድርጎ ይመለከታቸዋል (2ኛ ቆሮ. 2፡17 ተመልከት) - አላዋቂዎችን የሚበዘብዙ «ሃይማኖታዊ ቀማኞች» ማታለል

የተሞላበትን የመጽሐፍ ቅዱስ ማስተማሪያ ዘዴዎቻቸውን ከመነሻው አውግዟል (4፡2)፤ ነፍሳትን እንደ ማረኩ በመግለጽ ለመመካት የቃጡበትንም ሁኔታ አናንቋል (10፡12-18)። የቆሮንቶስ ሰዎች ጳውሎስ ያሳሰባቸውን ልዩ እርዳታ በመሰብሰብ በኩል ወደ ኋላ ከቀሩባቸው ምክንያቶች አንዱ እነዚህ ቀናተኛ አይሁዳውያን ቤተ ክርስቲያንን ስለ ዘረፉ ነበር (11፡7-12፥ 20፤ 12-14)።

ለመሆኑ ጳውሎስ የነዚህን ሕጋውያን የሐሰት አስተማሪዎች የእምነት ትምህርቶችና ልምምዶች እርባና-ቢስነት ያረጋገጠው እንዴት ነበር? የእግዚአብሔርን የጸጋ አገልግሎት የላቀ ክብር በማሳየት ነበር። በ2ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 3 ጳውሎስ የአሮጌውን ቃል ኪዳን አገልግሎት (ሕግ) ከአዲሱ ኪዳን አገልግሎት (ጸጋ) ጋር በማነጻጸር፥ የአዲሱን ኪዳን አገልግሎት የበላይነት አረጋግጧል። እነሆ ያቀረባቸውን ማነጻጸሪያዎች ተመልከት፡-

## የድንጋይ ጽላት - የሰው ልብ ጽላት (2ኛ ቆሮ. 3፡1-3)

እነዚህ አይሁዳዊነትን ለማስፋፋት የሚታገሉ ወገኖች፥ በኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሚገኙ «ታላላቅ ሰዎች» «የምስጋና ደብዳቤ» (ቁ. 1 አዲስ ትርጉም) እንደ ተቀበሉና ጳውሎስ ግን ይህን ያህል አስፈላጊ ከበሬታዎች እንዳልነበሩት በትምክህት ይናገራሉ። አንድ ሰው የግል ከበሬታውን እግዚአብሔር ስለ እርሱ በሚያውቀው ሳይሆን፥ ሰዎች ስለ እርሱ በሚናገሩት ነገር መለካቱ የሚያሳዝን ነው። ጳውሎስ ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሚያሞካሽ ደብዳቤ አላስፈለገውም፡- አስፈላጊዎቹ ምስጋናዎቹ ሕይወቱና አገልግሎቱ ብቻ ነበሩ።

እግዚአብሔር ሕግን ሲሰጥ፥ በድንጋይ ጽላቶች ላይ የቀረጻቸው ሲሆን፥ እነዚያም ጽላቶች በቃል ኪዳኑ ታቦት ውስጥ ተቀምጠው ነበር። ምንም እንኳ እስራኤላውያን ሁለቱን የድንጋይ ጽላቶች ለማንበብ ቢችሉም፥ ሆኖም ግን ይኸው ልምምድ በራሱ ሕይወታቸውን ሊለውጥ አይችልም ነበር። ሕግ ውጫዊ ነገር ሲሆን፥ የሰዎች ሕይወት እንዲለወጥ ከተፈለገ፥ ውስጣዊ ኃይል ያስፈልጋቸዋል። አንድ የሕግ ሰው «ይህን አድርግ!» ወይም «ይህን አታድርግ!» የሚል ትዕዛዝ ይሰጠናል እንጂ፥ የምንታዘዝበትን ኃይል አያጎናጽፈንም። ብንታዘዝ እንኳ፥ ከልብ የመነጨ ስለማይሆን፥ ማብቂያችን ከቀድሞው ሁኔታችን የከፋ ይሆናል!

የጸጋ አገልግሎት ግን ልብን ይለውጣል። የእግዚአብሔር መንፈስ የእግዚአብሔርን ቃል በመጠቀም ከልብ ውስጥ ይጽፋል። የቆሮንቶስ ሰዎች ጳውሎስ ወደ እነርሱ በመጣ ጊዜ የከፉ ኃጢአተኞች ነበሩ፤ ዳሩ ግን የእግዚአብሔር የጸጋ አገልግሎት ሕይወታቸውን ሙሉ ለሙሉ ለወጠው (1ኛ ቆሮ. 6፡9-11 ተመልከት)። ይህም የእግዚአብሔር የጸጋ ልምምዳቸው የሐሰት አስተማሪዎች ተሸክመው ከሚዞሩዋቸው የምስጋና ደብዳቤ የላቀ ትርጉም ይሰጣቸው ነበር። የቆሮንቶስ አማኞች በጳውሎስ ልብ ውስጥ በፍቅር የተጻፉ ሲሆን፥ በዚያው መጠን ደግሞ የእግዚአብሔር መንፈስ «የክርስቶስ ሕያው መልእክተኞች» አድርጎ፥ እውነትን በእነርሱም ልብ ላይ ጽፎት ነበር።

የአገልግሎት መፈተኛው የተለወጠ ሕይወት እንጂ፥ ይህን ያህል ሠርቻለሁ በማለት የሚቀርብ የመረጃ ጋጋታ አይደለም። ለሕግ አጥባቂው ሰው ግን አገልግሎቱን «በውጫዊ» መመዘኛዎች ስለሚለካ፥ ራሱን ለማወደስ ይቀለዋል። በእግዚአብሔር መንፈስ ላይ ተደግፎ የሚያገለግል አማኝ ውጤቶቹን ለጌታ መልቀቅ አለበት። እንግዲህ የቆሮንቶስ ሰዎች ትምክህተኞቹን የአይሁዳዊነት አስተማሪዎች ተከትለው፥ ከፍርድ ያዳናቸውን ሰው ልብ በሐዘን መስበራቸው እንደ ምን የሚያሳዝን ነገር ነው!

## ሞት - ሕይወት (2ኛ ቆሮ. 3፡4-6)

ጳውሎስ ምን ጊዜም ቢሆን ክብሩን ለራሱ ሳይሆን፥ ለእግዚአብሔር ለመስጠት የፈጠነ ነበር። መተማመኛው እግዚአብሔር እንደ መሆኑ፥ ብቃቱም የሚመጣለት ከእግዚአብሔር ነበር። ጳውሎስ ንቁና በሚገባ የተማረ ሰው ቢሆንም፥ በጌታ እንጂ በራሱ ብቃት ላይ አልተደገፈም።

በርግጥ የሕግ መምህራን፥ ማንኛውም ሰው ሕግን በመጠበቅ መንፈሳዊ ሊሆን እንደሚችል አስተምረዋል። ዳሩ ግን የሕግ ትምህርት የሰዎችን ራስ-ወዳድነት አዝማሚያ የሚያጎላብት ነው። በእግዚአብሔር ጸጋ ላይ የምናተኩር ከሆን፥ ሰዎች ራሳቸውን ለማዳን የማይችሉ የጠፉ ኃጢአተኞች መሆናቸውን መናገር አለብን። የጳውሎስ ምስክርነት «ነገር ግን አሁን የሆንሁትን የሆንሁት በእግዚአብሔር ጸጋ ነው» (1ኛ ቆሮ. 15፡10 - አዲስ ትርጉም) የሚል ነበር። ማንም ሰው በራሱ ከሰዎች ልብ ዘልቆ የሚደርስ አገልግሎት የማቅረብ ብቃት የለውም። ያ ብቃት ሊመጣ የሚችለው ከእግዚአብሔር ዘንድ ብቻ ነው።

ይህን ምዕራፍ ስታነብ ሳለ፥ ጳውሎስ አሮጌውንና አዲሱን ቃልኪዳን በሚያነጻጽርበት ወቅት የሚሰጣቸውን ስያሜዎች በጥንቃቄ አስተውል። በቁጥር 6 ውስጥ፥ «ፊደል» የሚለው ቃል የአሮጌውን ቃል ኪዳን ሕግ የሚያመለክት ሲሆን፥ «መንፈስ» ደግሞ አዲሱን የጸጋ መልእክት ያሳያል። እዚህ ላይ ጳውሎስ ሁለት የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎሞችን ማለትም «ቃል በቃል ትርጉም» እና «መንፈሳዊ ትርጉም» እያነጻጸረ አልነበረም። በምትኩ፥ የብሉይ ኪዳን ሕግ ሕይወት ሊሰጥ እንደማይችልና የሞት አገልግሎት እንደ ሆነ ለአንባቢዎቹ እያስታወሰ ነበር (ገላ. 3፡21 ተመልከት)። ኢየሱስ በመስቀል ላይ ከፈጸመው ሥራ የተነሣ፥ ወንጌሉ ለሚያምኑት ሕይወት ይሰጣል።

ጳውሎስ ሕግ ስህተት እንደ ሆነ ወይም አገልግሎቱ አላስፈላጊ እንዳልሆነ እየገለጸ አልነበረም። አሳቡ ከዚህ የራቀ ነው! ጳውሎስ አንድ ኃጢአተኛ በእግዚአብሔር ጸጋ ከመዳኑ በፊት፥ በሕግ ሊገደልና ተስፋ በሌለው ሁኔታ ሊኮነን እንደሚገባው ጥምር ያውቅ ነበር። መጥምቁ ዮሐንስ ለኢየሱስና የሚያድን ጸጋ ላለበት መልእክቱ መንገድ የሚጠርግ፥ የፍርድ መልእክት ይዞ ነበር የመጣው።

የሕግ አገልግሎት ሞትን ያመጣል። በሕግጋት ትምህርቶች የሚመረቁ ሰባኪዎች ማህበሮቻቸውን ጽልመት ባጠላበት የበደለኛነት ደመና ውስጥ ሸሽገው ያኖራሉ፤ ይህም ደስታቸውን፥ ኃይላቸውንና ለክርስቶስ የሚኖራቸውን ፍሬያማ ምስክርነት ይገድለዋል። የየግል ችሎታቸውን ባለማቋረጥ የሚያነፃፅሩ፥ «ውጤቶቻቸውን» የሚያወዳድሩ፥ ብሎም እርስ በርስ የሚቀናኑና የሚፎካከሩ ክርስቲያኖች ብዙም ሳይቆይ በሥጋ እንጂ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንደማይደገፉ ይረዳሉ። አሥርቱን ትዕዛዛት ጨምሮ፥ የሰውን ሕይወት የሚለውጥ መመዘኛ ከቶውንም ሊገኝ አልቻለም። የጠፉትን ኃጢአተኞች ኢየሱስ ክርስቶስን ወደሚያስከብሩ መልእክተኞች ሊለውጥ የሚችለው፥ በእግዚአብሔር መንፈስ የሚስተናገደው የእግዚአብሔር ጸጋ ብቻ ነው።

ጳውሎስ የአዲሱን ቃል ኪዳን ትምህርቱን ለአጋጣሚው እንዲስማማ ብሎ የፈጠረው አልነበረም። እንደ ጥንቁቅ የቅዱሳት መጻሕፍት ተማሪነቱ፥ ጳውሎስ ኤርምያስ 31፡27-34፥ እንዲሁም ሕዝቅኤል 11፡14-21ን አንብቦ ነበር። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ዕብራውያን ምዕራፍ 8-10 መጠናት ያለበት ቁልፍ ምንባብ ነው። በውጫዊ ታዛዥነት ላይ የሚያተኩረው አሮጌው ኪዳን፥ ለአዲሱ የጸጋ መልእክትና ለውስጣዊ የልብ ለውጥ ቅድመ ዝግጅት ነበር።

## የሚደበዝዝ ክብር - የሚበዛ ክብር (2ኛ ቆሮ. 3፡ 7-11)

ይህ አንቀጽ የምዕራፉ እምብርት ስለ ሆነ፥ ከዘጸአት 34፡29-35 ጋር ተያይዞ መጠናት አለበት። የሕግ መሰጠት፥ የድንኳንና የቤተ መቅደስ አገልግሎት ውስጥ በትክክል ክብር ያልተለየው ስለ ነበረ፥ ጳውሎስም ቢሆን ይህን የአሮጌውን ኪዳን ክብር አልካደም። ዳሩ ግን እርሱ ለማጠናከር የፈለገው የአዲሱ ኪዳን የጸጋ ኪዳን ክብር እጅግ የሚበልጥ መሆኑንና ለዚሁም በርካታ ምክንያቶች እንዳሉት ነበር።

1. የአዲሱ ኪዳን ክብር ማለት መንፈሳዊ ሕይወት እንጂ፥ ሞት አይደለም (2ኛ ቆሮ. 3፡ 7-8)። ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር ከተነጋገረ በኋላ ከተራራው ላይ ሲወርድ፥ ፊቱ በእግዚአብሔር ክብር ያበራ ነበር። ይህም ከሕግ መስጠት ክብር አንዱ አካል ስለ ነበር፥ ሕዝቡን አስደንቆአቸዋል። ከዚያም ጳውሎስ፥ ሞትን ባመጣው የሕግ መስጠት ውስጥ ክብር ከነበረ፥ ሕይወትን በሚያመጣው አገልግሎት ውስጥ ምንኛ የበለጠ ክብር ይኖር ይሆን! በማለት ይሞግታል።

እንደ አይሁዳዊነት ወግ አክራሪዎች ሁሉ ሕግ-አጥባቂዎችም የሕግን ክብር አጉልተው ለማሳየትና ደካማ ጎኑን ለመሸፈን ይጥራሉ። ጳውሎስ በገላትያ ለሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት በጻፈው ደብዳቤ፥ የሕግን ደካማነት በሚገባ አመልክቷል፡- ሕግ የጠፉን ኃጢአተኛ ሊያጸድቅ (ገላ. 2፡ 16፤ 2፡21)፥ መንፈስ ቅዱስን ሊሰጥ (3፡2)፥ ርስትን ሊሰጥ (3፡ 18)፥ ሕይወትን ሊሰጥ (3፡21)፥ ወይም ነጻነትን ሊሰጥ አይችልም (4፡8-10)። ዳሩ ግን የሕግ ክብር ለሙታን እንደሚደረገው አገልግሎት ዓይነት ክብር ነው።

2. የአዲሱ ኪዳን ክብር ማለት ጽድቅ እንጂ ኩነኔ አይደለም (2ኛ ቆሮ. 3፡9-10)። ለሕግ በመታዘዝ ደኅንነት ስለማይገኝ፥ ሕግ የተሰጠው ለደኅንነት ዓላማ አልነበረም። ሆኖም ሕግን መተላለፍ ኩነኔ ስለሚያመጣ፥ ፊታችን ምንኛ እንዳደፈ እንደሚያሳይ መስተዋት ነው ለማለት ይቻላል። ዳሩ ግን በመስተዋቱ ውስጥ ፊታችንን ልንታጠብ አንችልም።

የአዲሱ ኪዳን አገልግሎት ጽድቅን የሚያመጣ ሲሆን፥ ሕይወትን ለእግዚአብሔር ክብር ይለውጣል። ለሰው እጅግ የሚያስፈልገው ጽድቅ ሲሆን፥ እግዚአብሔርም የሚሰጠው ከሁሉም የላቀው ስጦታ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኘው ጽድቅ ነው። «ጽድቅስ በሕግ በኩል ከሆነ፥ እንኪያስ ክርስቶስ በከንቱ ሞተ!» (ገላ. 2፡21)። ከሕግ በታች ለመኖር የሚሞክር ሰው ይበልጥ የበደለኛነት ስሜት እየተጫነው ይሄዳል፤ ይህም

ተስፋ የመቁረጥንና የመገለልን ስሜት ሊያስከትል ይችላል። የተቀባይነት ስሜትና ደስታ ሊኖረን የሚችለው በክርስቶስ ስንታመንና በእግዚአብሔር ጸጋ አምነን ስንመላለስ ብቻ ነው።

ሁለተኛ ቆሮንቶስ 3፡10 ሕግ እጅግ የበለጠ ክብር ካለው የእግዚአብሔር የጸጋ አገልግሎት ጋር ሲነጻጸር «ክብሩን እንዳጣ» ያህል እንደሚቆጠር ይናገራል። ባጭሩ ሊወዳደሩ አይችሉም ማለት ነው። የሚያሳዝነው የበደለኛነትን ስሜት እስካላነገቡ ጊዜ ድረስ፥ «መንፈሳዊነት የማይሰማቸው» አንዳንድ ሰዎች መኖራቸው ነው። ሕግ የዕዳን ሰንሰለትና (ቆላ. 2፡14) የሚቀጣንን ተቆጣጣሪ (ገላ. 4፡1-5) የሚመስል፥ ብሎም ለመሸከም የማይሞከሩት ብርቱ ቀንበር ስለ ሆነ፥ በደልና ኩነኔ ያመጣል (ገላ. 5፡1፤ የሐዋ. 15፡10)።

3. የአዲሱ ኪዳን ክብር ቋሚ እንጂ ጊዜያዊ አይደለም (2ኛ ቆሮ. 3፡11)። በዚህ ሥፍራ የተጠቀሰው የጊዜ አመልካች ግስ (አንቀጽ) በጣም አስፈላጊ ነው፡- «ያ ይሻር የነበረው» ጳውሎስ የጻፈው ወደ ፍጻሜ የሚነጉደውና አዲስ የሚያቆጠቁጠው ዘመን የጋርዮሽ ሚና በሚጫወቱበት የታሪክ ወቅት ነበር። አዲሱ የጸጋ ዘመን የተጀመረ ቢሆንም፥ ዳሩ ግን የቤተ መቅደስ አገልግሎቶች አሁንም የቀድሞውን መልክ ይዘው ይከናወኑ ነበር፤ ሕዝበ - እስራኤልም ገና ከሕግ በታች ይኖር ነበር። በ70 ዓ.ም. የኢየሩሳሌም ከተማና ቤተ መቅደሱ በሮም ተደመሰሱ፤ ያም የአይሁድን የሃይማኖት ዘይቤ ከፍጻሜ አደረሰው።

የአይሁድ እምነት አስፋፊዎች የቆሮንቶስ አማኞች የኋሊት ተጉዘው ከሕግ በታች እንዲኖሩና ሁለቱን ኪዳኖች «እንዲቀላቅሉ» ፈለጉ። ጳውሎስም፥ «ወደ ኋላ ተመልሳችሁ፥ ጊዜያዊና ጠፊ ወደ ሆነው ነገር ለምን ትሄዳላችሁ? ይበልጥ እየደመቀና እየመጠቀ በሚሄደው በአዲሱ ኪዳን ክብር ውስጥ ኑሩ» ይላቸዋል። የሕግ ክብር ያለፈ ታሪክ ክብር ብቻ ሲሆን፥ የአዲሱ ኪዳን ክብር የአሁኑ ልምምድ ክብር ነው። አማኞች እንደ መሆናችን፥ «ከክብር ወደ ክብር» (3፡18) ልንለወጥ እንችላለን፤ ይህንን ደግሞ ሕግ ከቶውንም ሊሠራው የማይችለው ነገር ነው።

በጳውሎስ ዘመን የሕግ ክብር እየደበዘዘ ነበር፤ ዛሬ ያ ክብር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብቻ ተመዝግቦ ይገኛል። ዛሬ የእስራኤል ሕዝብ ቤተ መቅደስም ሆነ የካህናት አገልግሎት የለውም። ደግሞም ሕዝቡ አዲስ ቤተ መቅደስ ቢሠራ እንኳን፥ በቅዱሰ-ቅዱሳን ውስጥ

የሚያድረው የእግዚአብሔር መለኮታዊ ክብር አሁን ሊኖር አይችልም። የሙሴ ሕግ ከዚህ ቀደም ከፍተኛ ክብር የነበረው ሃይማኖት ነበር፤ ዛሬ ግን ያ ክብር የለውም። ብርሃኑ ሥፍራውን ለቅቆአል፡- የቀረው ነገር ቢኖር ጥላው ብራ ነው (ቆላ. 2፡ 16-17)።

ጳውሎስ የጸጋ አገልግሎት ሕይወትን እንደሚያስገኝ (ቁ. 4-6)፥ እየደመቀና እየጨመረ የሚሄድ ክብር ያዘለ መሆኑንና (ቁ. 7-11) ውስጣዊ ጠቀሜታ (2ኛ ቆሮ. 3፡ 1-3) እንዳለው ገልጿል። የዚህኑ የአዲሱን ኪዳን የጸጋ አገልግሎት የበላይነት ለማረጋገጥ አንድ የመጨረሻ ማነጻጸሪያ ያቀርባል፡-

## ስውርነት - ግልጽነት (2ኛ ቆሮ. 3፡ 12-18)

መጽሐፍ ቅዱስ መልእክቱን ለማስተላለፍ በተምሳሌቶች፥ በዘይቤዎችና በሌሎችም ሥነ ጽሑፋዊ ዘዴዎች ስለሚጠቀም፥ በመሠረቱ «(ሥዕላዊ) ገላጭ መጽሐፍ» ነው። ጳውሎስ በዚህ አንቀጽ ውስጥ፥ ክብር የሞላበትን ነጻነትና ግልጽነት ተጎናጽፎ ከጸጋ ሥር የሚገኘውን የክርስትና ሕይወት ለማብራራት፥ በሙሴና በፊት መጋረጃው ዓይነ-ርግብ ታሪክ ይጠቀማል። ጳውሎስ ከሙሴ ልምምድ ውስጥ ያገኘው ግንዛቤ፥ እኔና አንተ በዘጸአት 34፡29-25 ያለውን ክፍል በማንበብ ልናገኝ ከምንችለው በላይ የጠለቀ መንፈሳዊ ትርጉም ያዘለ ነው።

1. ታሪካዊ ክስተት (2ኛ ቆሮ. 3፡ 12)። በአገልግሎትህ ላይ የእግዚአብሔር ክብር እያበራ ሲሄድ ለምትናገረው ነገር ድፍረት ሊኖርህ ይችላል፤ ጳውሎስ ደግሞ ይህንን ድፍረቱን አልሸሸገውም። ከሙሴ በተቃራኒ፥ ጳውሎስ የሚሸሽገው አንዳችም ነገር አልነበረውም።

ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር ሲነጋገር ቆይቶ ሲመለስ፥ ፊቱ የእግዚአብሔር ክብር በማንጸባረቅ ያበራ ነበር። ለሰዎች ንግግር በሚያደርግበት ጊዜ፥ ከፊቱ ላይ ክብሩን ያዩና ይደነቁ ጀመር። ዳሩ ግን ሙሴ ክብሩ እንደሚደበዝዝ ያውቅ ነበረና ሕዝቡን አስተምሮ ሲያበቃ፥ ፊቱን በዓይነ-ርግብ ይሸፍን ነበር። ይህም ክብሩን ከእርሱ መለየት እንዳይመለከቱ አደረጋቸው። ታዲያ ክብሩን እያጣ ያለውን መሪ መከተል የሚፈልግ ሰው ይኖር ይሆን?

በቁጥር 13 ላይ «መጨረሻ» ተብሎ የተተረጎመው ቃል ሁለት ትርጉሞች አሉት - «ዓላማ» እና «ፍጻሜ» የሚሉ። ዓይነ-ርግቡ ሰዎቹ የሙሴ ክብር እየደበዘዘ ሂዶ «ከፍጻሜ» የሚደርስበትን ሁኔታ

እንዳይመለከቱ ማዕቀብ ጣለባቸው። እንዲሁም ደግሞ ይኸው ዓይነ-ርግብ ከሚደበዝዘው ክብር በስቲያ ያለውን «ዓላማ» እንዳይረዱ አሁንም ጋረዳቸው። ከዚህ በተጨማሪም ሕጉ በቅርቡ የተሰጠ ስለ ነበር፥ ሕዝቡ ይህ የከበረው ሥርዓት ጊዜያዊ ስለ መሆኑ ይነገራቸው ዘንድ አልተዘጋጁም ነበር። የሕጉ ቃል ኪዳን ወደፊት ለሚከሰት ለአንድ ከዚያ በላይ ለላቀ ነገር መዘጋጃ የመሆኑ እውነት አልተገለጸላቸውም ነበር።

2. ብሔራዊ ተዛምዶ (2ኛ ቆሮ. 3፡ 14-17)። ጳውሎስ ለእስራኤል ልዩ ፍቅር የነበረው ሲሆን፥ ወገኖቹ በክርስቶስ አምነው ሲድኑ ለማየት ከፍተኛ ሸክም እንዳለበትም ይሰማው ነበር (ሮሜ 9፡ 1-3)። ዳሩ ግን የአይሁድ ሕዝብ መሲሐቸውን ያልተቀበሉት ለምን ነበር? ጳውሎስ የአሕዛብ ሚሲዮናዊ እንደ መሆኑ፥ በርካታ አሕዛቦች በጌታ ሲታመኑና ዳሩ ግን አይሁዶች - የራሱ ወገኖች - እውነትን በመግፋት እርሱንና ቤተ ክርስቲያንን ሲያሳድዱ ይመለከት ነበር።

ለዚህስ ምክንያቱ ምን ይሆን? ምክንያቱ፥ አእምሮአቸውንና ልባቸውን የከለለው «መንፈሳዊ መጋረጃ» ስለ ነበረ ነው። «መንፈሳዊ ዓይኖቻቸው» ስለ ታወሩ፥ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ሲያነቡ፥ ስለ ገዛ መሲሐቸው የተገለጸውን እውነት ለማየት አይችሉም ነበር። ምንም እንኳ ቅዱሳት መጻሕፍት በምኩራቦች ውስጥ ሥርዓት ባለው መንገድ ቢነበቡም፥ አይሁዳውያን ግን እግዚአብሔር የሰጣቸውን መንፈሳዊ መልእክት አልተረዱም ነበር። በገዛ ሃይማኖታቸው ታውረው ነበር።

ከደኅንነት ርቀው ለባዘኑት የእስራኤል ልጆች አንዳች ተስፋ ይኖር ይሆን? አዎን፥ አለ! «ወደ ጌታ (ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ) ግን ዘወር ባለ ጊዜ ሁሉ መጋረጃው ይወሰዳል» (2ኛ ቆሮ. 3፡ 16)።

በመጋቢነት ባገለገልሁባቸው በሦስት አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ያመኑትን አይሁዳውያን ማጥመቅ ደስ ይለኝ ነበር። ዳግም ከተወለዱ በኋላ አእምሮአቸው በሚያስደንቅ ሁኔታ ለቅዱሳት መጻሕፍት ይከፈታል። አንድ ሰው ስለዚሁ ልምምዱ ሲያጫውተኝ «ልክ ቅርፊት ከዓይኔ እንደሚወድቅ ያህል ማለት ነው። እንዲያውም እኔ የማየውን ነገር ሁሉም ሰዎች ለምን እንደማያዩት በማሰብ እደነቃለሁ!» ብሎኛል። መጋረጃው በእግዚአብሔር መንፈስ አማካኝነት ስለሚወገድ፥ መንፈሳዊ ዕይታን ያገኛሉ።

ዳሩ ግን ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ውጭ ማንኛውም ኃጢአተኛ - አይሁዳዊ ወይም አሕዛብ - ወደ ክርስቶስ ሊመለስ አይችልም። «ጌታ ግን መንፈስ ነው» (ቁ. 17)። ይህ ዓረፍተ

ነገር መንፈስ ቅዱስ አምላክ መሆኑን የሚያመለክት ነው። በቆሮንቶስ ውስጥ ቤተ ክርስቲያንን የሚያውኩ የአይሁድ ትምህርት አጥባቂዎች የሰዎችን ሕይወት ለመለወጥ በሕግ ላይ ይመረኩዙ ነበረ፤ ዳሩ ግን መንፈሳዊ መለወጥን የሚያመጣው የእግዚአብሔር መንፈስ ብቻ ነው። ሕግ የሚሰጠን ነገር ቢኖር እስራትን ብቻ ነው፤ ዳሩ ግን መንፈስ ቅዱስ ወደ ነጻነት ሕይወት ያስገባናል። «አባ አባት ብለን የምንጮህበትን የልጅነትን መንፈስ ተቀበላችሁ እንጂ፥ እንደገና ለፍርሃት የባርነትን መንፈስ አልተቀበላችሁምና» (ሮሜ 8፡ 15)።

ዛሬ የእስራኤል ሕዝብ በመንፈሳዊ ዕውርነት ይኖራል። ዳሩ ግን ይህ ማለት ደግሞ ከአይሁዶች መካከል አንዳንድ ግለሰቦች አይድኑም ማለት አይደለም። ዛሬ ቤተ ክርስቲያን ባለውለታዋ ለሆነው ለእስራኤል ሕዝብ ሊኖራት የሚገባውን ሸክም እንደገና ማንሣት አለባት። ይህ ሁሉ ያገኘነው መንፈሳዊ በረከት በእስራኤል በኩል ስለ መጣልን፥ የእነርሱ ባለዕዳዎች ነን። «መዳን ከአይሁድ ነውና» (ዮሐ. 4፡ 22)። ይህንን ዕዳ «ልንከፍል» የምንችለበት ብቸኛው መንገድ ወንጌሉን ለእነርሱ በማካፈልና ይድኑ ዘንድ በመጸለይ ነው (ሮሜ 10፡ 1)።

3. ግላዊ ተዛምዶ (2ኛ ቆሮ. 3፡ 18)። «እኛም ሁላችን በመጋረጃ በማይከደን ፊት የጌታን ክብር እንደ መስተዋት እያብለጨለጭን መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደሚደረግ ያን መልክ እንመስል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን።» ይህ ጥቅስ የምዕራፉን ፍሬ አሳብ የምንጨብጥበት ከፍተኛ ደረጃ ሲሆን፥ በበኩሌ ብዙ አማኞች ስተውታል ወይም ገሸሽ አድርገውታል ብዬ የምደነቅበትን ታላቅ እውነት ያዘለ ነው። እኔና አንተ የኢየሱስ ክርስቶስን አምሳል ተቀብለን፥ በእግዚአብሔር መንፈስ አገልግሎት አማካኝነት «ከክብር ወደ ክብር» ልንለወጥ እንችላለን።

በአሮጌው ኪዳን ዘመን፥ ወደተራራው በመውጣት ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት ያደረገው ሙሴ ብቻ ሲሆን፥ ዳሩ ግን በአዲሱ ኪዳን አማኞች ሁሉ ከእርሱ ጋር ህብረት የማድረግ ዕድል አላቸው። በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት፥ ወደ ቅድስተ-ቅዱሳን ልንገባ እንችላለን (ዕብ. 10፡ 19-20) - ገደል እየቧጠጥን ከተራራ ራስ መውጣት ሳያስፈልገን!

መስተዋት የእግዚአብሔር ቃል ተምሳሌት ነው (ያዕ. 1፡ 22-25)። ወደ እግዚአብሔር ቃል በመመልከት የእግዚአብሔርን ልጅ በምናይበት ጊዜ፥ መንፈስ ቅዱስ ወደ እግዚአብሔር ቅድስና ይለውጠናል። ይሁንና ምንም ነገር ከእግዚአብሔር መሸሽግ የለብንም።

ከእርሱ ጋር ግልጽና ታማኝነት ያለበት ህብረት ማድረግ እንጂ፥ ማንነታችንን «መሸፋፈን» የለብንም።

በዚህ ስፍራ መለወጥ ተብሎ የተተረጎመው ቃል፥ በተራራው የጌታችን መልክ ያንጸባረቀበትን ሁኔታ ከሚገለጸው ቃል ጋር አንድ ዓይነት ነው (ማቴ. 17፤ ማር. 9)። ቃሉም አንድ ኃይል ከውስጥ ፈልቆ በመውጣት በውጭ የሚታየውን ለውጥ ማስከተሉን የሚገልጽ ነው። ይህም የዕድገት ሂደትን «መለወጥን» (ሜታሞርፎሲስ) የሚያመለክት የግሪክ ቃል ሲሆን፥ ይኸውም አንድ እንደ ቢራቢሮ ያለ በራሪ ፍጡር፥ እንዴት ከዕንቁላልነት ወደ ሽጋትነትና እጭነት ከዚያም ወደ ብስል እንስሳነት እንደሚለወጥና ቀጥሎ ወደ መብረር ደረጃ የሚደርስበትን የዕድገት ሂደት ሁሉ ይወክላል። ለውጦቹ በሙሉ የሚመጡት ከውስጥ ነው።

ሙሴ የእግዚአብሔርን ክብር ያንጸባርቅ እንጂ፥ ዳሩ ግን እኔና አንተም የእግዚአብሔርን ክብር በውስጣችን ማስተላለፍ እንችላለን። የእግዚአብሔር ቃል በማሰላሰል በውስጡ የእግዚአብሔርን ልጅ በምንመለከትበት ጊዜ፥ መንፈስ ቅዱስ ይለውጠናል! «ከክብር ወደ ክብር» ስንሸጋገር ሳለ፥ ይበልጥ ጌታ ኢየሱስን እየመሰልን እንሄዳለን። ይህ አስደናቂ ሂደት ሕግን በመጠበቅ ሊመጣ አይችልም። የሕግ ክብር ደብዝዞ ጠፍቷል፤ ዳሩ ግን የእግዚአብሔር የጸጋ ክብር በሕይወታችን ውስጥ እየጨመረ ይሄዳል።

ጳውሎስ የሚያነጻጽረው አሮጌውንና አዲሱን ኪዳን ብቻ ሳይሆን፥ የአሮጌውን ኪዳን አገልግሎት ከጸጋው አገልግሎት ጋር ጭምር መሆኑን ከልብ አጢነው። የአሮጌው ኪዳን አገልግሎት ግብ ለውጫዊ መመዘኛ መታዘዝ ሲሆን፥ ዳሩ ግን ይህ መታዘዝ የሰውን ባሕርይ ሊለውጥ አይችልም። የአዲሱ ኪዳን አገልግሎት ግብ ኢየሱስ ክርስቶስን መምሰል ነው። ሕግ ወደ ክርስቶስ ሊያመጣን ሲችል (ገላ. 3፡24)፥ ዳሩ ግን ክርስቶስን እንድንመስል የሚያደርገው ጸጋ ብቻ ነው። የሕግ አስተማሪዎችና ሰባኪዎች አድማጮቻቸውን እስከ ተወሰነው መመዘኛ ድረስ ሊያስኬዱዋቸው ቢችሉም፥ ዳሩ ግን የእግዚአብሔርን ልጅ እንዲመስሉ ለመለወጥ በፍጹም አይችሉም።

የአሮጌው ኪዳን አገልግሎት መሣሪያ ሕግ ሲሆን፥ ዳሩ ግን የአዲሱ ኪዳን አገልግሎት መሣሪያ የእግዚአብሔርን ቃል በመጠቀም የሚሠራው የእግዚአብሔር መንፈስ ነው። (የ«ሕግ» ስል ብሉይ ኪዳንን ማለቴ ሳይሆን፥ ዳሩ ግን በሙሴ የተሰጡትን ሕግጋት በሙሉ ማለቴ

ነው። በርግጥ፥ መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስ ክርስቶስን ለእኛ ለመግለጽ በአሮጌውና በአዲሱ ኪዳን በሁለቱም ሊጠቀም ይችላል።)

ቃሉን የጻፈው መንፈስ ቅዱስ ስለ ሆነ፥ ሊያስተምረን የሚችለው እርሱ ነው። ከዚህም በላይ፥ መንፈስ ቅዱስ ከውስጣችን ስለሚኖር፥ በልባችን ቃሉን እንድንታዘዝ ሊረዳን ይችላል። ይህም ከፍርሃት የመነጨ የሕግ መታዘዝ ሳይሆን፥ ከፍቅር የመነጨ የልጅነት መታዘዝ ነው።

በመጨረሻም፥ የአሮጌው ኪዳን አገልግሎት ውጤት ባርነት ሲሆን፥ ዳሩ ግን የአዲሱ ኪዳን አገልግሎት ውጤት በመንፈስ አርነት መውጣት ነው። ሕጋዊነት ሰውን በእንጭጭነት ደረጃ የሚያቆይ ስለ ሆነ፥ ከሕግ ሥር መኖር ያለባቸውም ያልበሰሉ ሰዎች ናቸው (ገላ. 4፡ 1-7)። እግዚአብሔር ልጆቹ እንዲታዘዙት የሚፈልገው፥ ከውጫዊ ፊደል (ሕግ) የተነሣ ሳይሆን፥ ከውስጣዊ ባሕርይ የተነሣ ነው። ክርስቲያኖች ከሕግ በታች ባይሆኑም ዳሩ ግን ይህን ማለት ደግሞ ሕግ-አልባዎች ነን ማለት አይደለም! የእግዚአብሔር መንፈስ የእግዚአብሔርን ቃል ከልባችን ላይ ስለሚጽፍ፥ በውስጣችን ካስቀመጠው አዲስ ሕይወት የተነሣ አባታችንን እንታዘዛለን።

ዛሬም ቢሆን የሕጋዊነት መስህብ ከእኛ ጋር አብሮ ያለ ነው። በጳውሎስ ዘመን የአይሁድን ሃይማኖት የሚያስፋፉ ሰዎች እንዳደረጉት፥ ዛሬም በመናፍቃን ትምህርቶች የታወቁ ክርስቲያኖችና የቤተ ክርስቲያን ምዕመናን ይነጠቃሉ። ስለ ሆነም የሐሰት ትምህርቶችን ልንለይና አንገዋለን ልንጥላቸው ይገባል። እንዲሁም ደግሞ ላይ ላዩን ወንጌል-ሰባኪ አብያተ ክርስቲያናት ቢመስሉም፥ ዳሩ ግን በሕግ-አጥባቂነት አዝማሚያቸው ምዕመኖቻቸውን አስተሳሰበ ጨቅላዎች፥ የበደለኛነት ስሜት የተጫናቸው መንፈስ፥ ኩልሽዎችና ፈሪዎች አድርገው የሚያኖሩ ብዙዎች አሉ። ጊዜያቸውን በአብዛኛው በውጫዊ ጉዳዮች ላይ ስለሚያጠፉ፥ ውስጣዊውን ሕይወት የማነጹን ተግባር ችላ ይላሉ። ሃይማኖታዊ መመዘኛዎችን ከፍ ከፍ ሲያደርጉና ኃጢአትን ሲኮንኑ፥ ዳሩ ግን የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ታላቅነት ለመመስከር ይዘነጋሉ። በአንዳንድ የአዲስ ኪዳን አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የአሮጌው ኪዳን አገልግሎት ሲሰጥ መመልከቱ አሳዛኝ ነገር ነው።

ጳውሎስ የራሱን አገልግሎት ሁለት ገጽታዎች አብራርቷል፡- አገልግሎቱ ድል-ነሺ (ምዕራፍ 1-2) እና የከበረ (ምዕራፍ 3) ነው።

ሁለቱ አብረው ይሄዳሉ፡- «ስለዚህ ምክንያት ምህረት እንደ ተሰጠን መጠን፥ ይህ አገልግሎት ስላለን አንታክትም» (4፡ 1)።

የአንተም አገልግሎት የእግዚአብሔርን ክብር የሚያንጸባርቅ እስከ ሆነ ድረስ፥ ሊታቆመው አትችልም!

## ለግጭቱ የሚያስፈልገው ብርታት

### 2ኛ ቆሮንቶስ 4፥1-5፥8

የዚህ ክፍል ዋናው መልእክት በቁጥር 1 እና 16 ውስጥ የተደጋገመ ሲሆን፥ ይኸውም «አንታክትም!» ወይም ጳውሎስ በቀጥታ እንዳስፈረው፥ «ተስፋ አንቆርጥም» የሚል ነው። እርግጥ በጳውሎስ ሁኔታ ውስጥ ተስፋ ለመቁረጥ የሚያበቁ በርካታ ምክንያቶች ቢኖሩም፥ ዳሩ ግን ታላቁ ሐዋርያ ከተልዕኮው አላፈገፈገም ነበር። ይህን በመሰለው የሕይወት ውጣ ውረድ ውስጥ ዝሎ እንዳይወድቅ ያበረታው ምን ነበር? ጳውሎስ ከኢየሱስ ክርስቶስ ምን እንዳገኘ ያውቅ ነበር! በመሆኑም ጳውሎስ በሌለው ነገር ከማጉረምረም ይልቅ፥ ባለው ነገር ተደሳች ነበር፤ እኔና አንተም እንደ እርሱ ልናደርግ እንችላለን።

### የከበረ አገልግሎት አለን (2ኛ ቆሮ. 4፥1-6)

ጳውሎስ የጻፈው ቃል በቃል ሲተረጎም «ስለዚህ፥ እንዲህ ዓይነት አገልግሎት ስላለን» የሚል ነው። ለመሆኑ ይህ አገልግሎት ምን ዓይነት አገልግሎት ይሆን? በቀደመው ምዕራፍ ውስጥ የተገለጸው ዓይነት አገልግሎት ነው፡- ለሰዎች ሕይወትን፥ ደኅንነትንና ጽድቅን የሚያመጣ የከበረ አገልግሎት፤ የሰዎችን ሕይወት ለመለወጥ የሚችል አገልግሎት። ይህ አገልግሎት ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚለገስና እኛም ከእርሱ የተቀበልነው ስጦታ ነው። የተሰጠንም ከእግዚአብሔር ምህረት የተነሣ እንጂ፥ ከእኛነታችን ወይም ካደረግነው አንዳች ነገር የተነሣ አይደለም (1ኛ ጢሞ. 1፥12-17 ተመልከት)።

አገልግሎትህ የምትመለከትበት መንገድ እንዴት እንደምትፈጽመው ለመወሰን ይረዳሃል። ለክርስቶስ ማገልገል እንደ መታደል ሳይሆን እንደ ሸክም የምትቆጥር ከሆነ፥ ፍላጎት ታጣና የሚጠበቅብህን ተግባር ብቻ ታከናውናለህ፤ እንዲያውም አንዳንድ ሰዎች አገልግሎትን ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደ ወረደ ቅጣት ይቆጥሩታል። ጳውሎስ የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይ የመሆኑን እውነታ ሲያስብ፥ የእግዚአብሔር ጸጋና ምህረት ከአእምሮው በላይ ሆነበት። ይህም በአገልግሎቱ ላይ የነበረው አዎንታዊ አመለካከት በሕይወቱ ውስጥ ተግባራዊ ውጤቶችን አስከትሎ ነበር።

በመጀመሪያ፤ ተስፋ ቆርጦ አገልግሎቱን ከማቋረጥ ጠብቆታል (2ኛ ቆሮ. 4:1)። በእስያ የተጋፈጣቸው መከራዎች እንዳስጨነቁት ለቆሮንቶስ ሰዎች ተናዞአል (1:8)። ጳውሎስ ከታላላቅ ስጦታዎቹና ሰፋፊ ልምዶቹ ባሻገር፥ ሰው እንደ መሆኑ ለሰብዓዊ ድክመቶችም ተጋልጦ ነበር። ዳሩ ግን እንዲህ ባለው አስደናቂ አገልግሎት ውስጥ እያለ እንደ ምን ተስፋ መቁረጥ ይችላል? እግዚአብሔርን ይህን አገልግሎት በኃላፊነት የሰጠው እንዲወድቅ ነውን? በርግጥ አይደለም! ከመለኮታዊው ጥሪ ጋር መለኮታዊ ብቃትም ተሰጥቶታል፤ እግዚአብሔር እስከ መጨረሻው እንደሚረዳው ያውቅ ነበር።

ተስፋ የቆረጠ አንድ የሜቶዲስት ቤተ ክርስቲያን ሰባኪ ምክር አስፈልጎት ኖሮ፥ የእስኮትላንድ ታላቁ ሰባኪ ለነበሩት አለክሳንደር ዋይት ደብዳቤ ጻፈ። አገልግሎቱን ትቶ መኮብለል ይሻለው ይሆን? ዋይት የመልስ ደብዳቤ ሲጽፉ፥ «ስብከትን ስለ መተው ከቶውንም እንዳታስብ! በእግዚአብሔር ዙፋን ዙሪያ ያሉት መላእክት እንኳን በዚህ ታላቅ አገልግሎትህ እየቀኑብህ ነው» በማለት አጽናንተውታል። ጳውሎስም ቢሆን የሚሰጠው የዚህ ዓይነቱን ምላሽ ነበር፤ ሁላችንም ሥራችን ከንቱ እንደ ሆነ በሚሰማን ጊዜ ሁሉ ልናስብበት የሚገባን አሳብ ይህ ነው።

ሁለተኛ፥ አታላይ ከመሆን ጠብቆታል (2ኛ ቆሮ. 4:2-4)። «ነገር ግን የሚያሳፍረውን ስውር ነገር ጥለናልና በተንኮል አንመላለስም፤ የእግዚአብሔርንም ቃል በውሸት አንቀላቅልም፤ እውነትን በመግለጥ ግን በእግዚአብሔር ፊት ለሰው ሕሊና ሁሉ ራሳችንን እናመሰግናለን» (ቁ. 2) ጳውሎስ እነዚህ ቃላት በሚጽፍበት ጊዜ ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ስለ አይሁድ ሃይማኖት አጥባቂዎች እየተናገረ ነበር። ዛሬ ማንኛውም የሐሰት አስተማሪ ትምህርቱን በእግዚአብሔር ቃል ላይ እንደሚመሠርት ይናገራል፤ ዳሩ ግን ሐሰተኛ አስተማሪዎች የእግዚአብሔርን ቃል በማታለል መንገድ ይጠቀሙበታል። አንተም ብትሆን ቅዱሳት መጻሕፍትን ከዓውድ ውጭ በመጠምዘዝና የራስህን የሕሊና ምስክርነት በማግለል፥ የማንኛውንም ነገር እውነትነት ወይም ውሸትነት በመጽሐፍ ቅዱስ ለማረጋገጥ ትችላለህ። መጽሐፍ ቅዱስ የሥነ-ጽሑፍ መጽሐፍ ስለ ሆነ፥ መሠረታዊ የአተረጓጎም ሕግጋትን በመከተል ሊተረጎም ይገባል። ሰዎች ሌሎች መጻሕፍትን መጽሐፍ ቅዱስን እንደሚያነቡት አድርገው ቢያነቡ፥ ምንም እውቀት ሊገበዩበት አይችሉም።

ጳውሎስ በግል ሕይወቱም ሆነ በስብከት ውስጥ የሚሸሽገው ነገር አልነበረውም። ሁሉም ነገር ግልጽና ታማኝነት ያለበት ነበር፤ የእግዚአብሔርን ቃል ለማታለል ወይም ለመጠምዘዝ የሞከረበት ጊዜ የለም። የአይሁድን ሃይማኖት የሚያጠብቁ ሰዎች ቅዱሳት መጻሕፍትን ከራሳቸው የቀድሞ ግንዛቤ ጋር ለማስማማት የሚጠመዝዙ ሲሆኑ፥ እውቀት የሌላቸው ሰዎች ይከተሉዋቸው ነበር።

እንግዲህ ጳውሎስ ለቃሉ ይህን ያህል ታማኝ አስተማሪ ከሆነ ዘንዳ፥ ብዙ ሰዎች መልእክቱን ያልተቀበሉት ለምንድን ነበር? ለሐሰተኛ አስተማሪዎች ነፍሳትን በቀላሉ የመማረኩ ተግባር የሚሳካላቸው በምን ምክንያት ነበር? ምክንያቱ፥ ደኅንነትን ያላገኘ ኃጢአተኛ ሰው አእምሮው በሰይጣን ስለሚታወርና ለእንደዚህ ዓይነቱም የተሰናከለ ሰው ከእውነት ይልቅ ውሸትን ማመን ስለሚቀለው ነው። «ወንጌላችን የተከደነ ቢሆን እንኳ የተከደነባቸው ለሚጠፉ ነው። ለእነርሱም የእግዚአብሔር ምሳሌ የሆነ የክርስቶስ የክብሩ ወንጌል ብርሃን እንዳያበራላቸው፥ የዚህ ዓለም አምላክ የማያምኑትን አሳብ አሳወረ» (ቁ. 3-4)።

ጳውሎስ አስቀድሞ የአይሁዶች አእምሮ ከልባቸው ዕውርነት የተነሣ «እንደ ተጋረደ» ገልጾአል (3፡14-16፤ ሮሜ 11፡25)። የአሕዛቦች አእምሮም ጨልሞአል! ደኅንነትን ያላገኙ ሰዎች («የሚጠፉ») የወንጌሉን መልእክት ለመረዳት አይችሉም። የከበረው የደኅንነት ብርሃን በሕይወታቸው ውስጥ እንዲያበራ ሰይጣን ጨርሶ አይፈልግም። ሰይጣን የዚህ ዓለም አምላክና አለቃ በመሆኑ (ዮሐ. 12፡31)፥ ከደኅንነት የራቁትን ኃጢአተኞች በጨለማ ውስጥ ያቆያቸዋል። የሚያሳዝነው ደግሞ ሰይጣን ሰዎችን ለማታለል (የአይሁድን ትምህርት ያስፋፉ የነበሩትን ዓይነት) በሃይማኖት መሪዎች መጠቀሙ ነው። ዛሬ ለኑፋቄ ከተጋለጡት ሰዎች ብዙዎቹ በመጀመሪያ የክርስቲያን አብያተ ክርስቲያናት አባላት ነበሩ።

ጳውሎስ ይህንን አገልግሎት ከክርስቶስ የመቀበሉ የሚያስገርም እውነት ግን ከክህደትና ከማታለል ጠብቆታል፤ እንዲሁም ደግሞ ስለ ራሱ ብዙ ከመናገርም ጠብቆታል (2ኛ ቆሮ. 4፡5-6)። «ራሳችንን አንሰብክምና!» (ቁ. 5)። የአይሁድን ትምህርት የሚያስፋፉ መምህራን ስለ ራሳቸው መስበክንና በፈጸሙዋቸው ተግባራት መከበርን ይወዱ ነበር (10፡12-18)። ሕዝቡን ለመርዳት የሚጥሩ አገልጋዮች ሳይሆኑ፥ ሕዝቡን የሚበዘብዙ አምባገነኖች ነበሩ።

ጳውሎስ ያለ አንዳች ጥርጥር ትሑትና ራስን ዝቅ የማድረግ ሕይወት የሚመራ ሰው ነበር። በራሱ ማንነት የማይታመን (1፥9)፥ ወይም ራሱን የማያመሰግን (3፥1-5)፥ ወይም ስለ ራሱ የማይሰብክ (4፥5) ሰው ነበር። የሚፈልገው ነገር ቢኖር ሰዎችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ መምራትና በእምነት ማነጽ ብቻ ነበር። ለነገሩማ ለጳውሎስ «የአድናቂዎች ክበብ» በማቋቋም ከታላላቅ ሰዎች ጋር ለመጎዳኘት ጉጉት ከነበራቸው ደካማ ሰዎች ጥቅም ማግኘቱ በቀለለውም ነበር። የአይሁድ ሃይማኖት አስፋፊዎች የሚሠሩት በዚህ መልኩ ሲሆን፥ ዳሩ ግን ጳውሎስ ለዚህ ዓይነቱ አገልግሎት አምሮቱም፥ ፍላጎቱም አልነበረውም።

አንተስ የኢየሱስ ክርስቶስን አዳኝነት ላላወቁት ሰዎች በምታካፍልበት ጊዜ የሚከሰተው ነገር ምንድን ይመስልሃል? ብርሃኑ ማብራት ይጀምራል! ጳውሎስ ደኅንነትን በዘፍጥረት 1፥3 ላይ ከተገለጸው ከፍጥረት ታሪክ ጋር አወዳድሮታል። ልክ በዘፍጥረት 1፥2 ላይ እንደምንመለከታት ምድር፥ ደኅንነትን ያላገኘ ኃጢአተኛ ቅርጽ የሌለውና ባዶ ነው፤ ይሁንና በክርስቶስ በሚታመንበት ጊዜ፥ አዲስ ፍጥረት ይሆናል (2ኛ ቆሮ. 5፥17)። ከዚያም እግዚአብሔር በክርስቶስ ለሚታመነው ሰው ሕይወት ቅርጽ በመስጠት ባዶነቱን መሙላት ይጀምራል፤ ሰውየውም ለጌታ ፍሬያማ መሆን ይጀምራል። «ብርሃን ይሁን!» ያለው የእግዚአብሔር ቃል ሁሉንም ነገር አዲስ ያደርገዋል።

ውድ መዝገብ አለን (2ኛ ቆሮ. 4፥7-12) ጳውሎስ ንጽጽሩን ከአዲስ ፍጥረት ክብር ወደ ሸክላው ዕቃ ውርደት ያሸግራል። አማኙ «የሸክላ ዕቃ» ሲሆን፥ ውድ የሚያደርገው በሸክላው ውስጥ የተቀመጠው ዕቃ (መዝገብ) ክቡርነት ነው። የዕቃው ምስል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተደጋግሞ የተገለጸ በመሆኑ፥ ከዚህ ውስጥ ብዙ ነገሮችን ልንማር እንችላለን።

በመጀመሪያ ደረጃ፥ እግዚአብሔር በእኛነታችን የፈጠረን፥ እንድንፈጽመው የሚፈልግብንን ሥራ ለማከናወን እንድንችል ነው። እግዚአብሔር ስለ ጳውሎስ ሲናገር፥ «ይህ በአሕዛብ ... ዘንድ ስሜን ይሸከም ዘንድ ለእኔ የተመረጠ ዕቃ ነውና» (የሐዋ. 9፥15) ብሏል። ማንኛውም ክርስቲያን ስጦታዎች ወይም ችሎታዎች እንደ ሌሎች በመግለጽ፥ ወይም በውስንነቶቹ ወይም በአካለ-ስንኩልነቱ ምክንያት በእግዚአብሔር ላይ ማንጎራጎር የለበትም። መዝሙር (139)፥13-16

የዝርያ መዋቅራችን በእግዚአብሔር እጆች ውስጥ እንዳለ ይናገራል። እያንዳንዳችን እኛነታችንን ተቀብለን በእኛነታችን መኖር አለብን።

ስለ ዕቃው የሚፈለገው ነገር ቢኖር ንጹሕ፥ ባዶና ለአገልግሎት ተዘጋጅቶ መቅረቡ [መገኘቱ] ነው። እያንዳንዳችን «ለክብር የሚሆን፥ የተቀደሰም [የተለየ]፥ ለጌታውም የሚጠቅም ለበጎም ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ዕቃ» (2ኛ ጢሞ. 2፡21) ለመሆን መጣር አለብን። እኛ እግዚአብሔር የሚጠቀምብን ዕቃዎች ነን። ሸክላ ዕቃዎች ስለ ሆንን፥ በእግዚአብሔር እንጂ በራሳችን ኃይል አንደገፍም።

በመሆኑም በዕቃው ውስጥ ባለው መዝገብ ላይ እንጂ በዕቃው ላይ ማተኮር የለብንም። እንግዲህ ጳውሎስ በበኩሉ መዝገቡን እስከ ጠበቀ ጊዜ ድረስ፥ እግዚአብሔር ዕቃውን እንደሚጠብቅ ስለሚያውቅ፥ የሚደርስበትን ሥቃይ ወይም መከራ አልፈራም ነበር (1 ጢሞ. 1፡11፤ 6፡20 ተመልከት)። እግዚአብሔር መከራዎች እንዲመጡ ይፈቅዳል፤ እግዚአብሔር መከራዎችን ይቆጣጠራል፤ እንዲሁም እግዚአብሔር መከራዎችን ለራሱ ክብር ይጠቀምባቸዋል። እግዚአብሔር በደካማ ዕቃዎች በኩል ክብርን ያገኛል። የቻይናን ማዕከላዊ ክፍል ለወንጌል የከፈቱት ሚስዮናዊ ጄ. ሃድሰን ቴይለር፥ «የእግዚአብሔርን ሥራ ያከናወኑት ሰዎች ሁሉ እርሱ ከእነርሱ ጋር እንዳለ በመተማመን ብቻ ታላላቅ ተግባራትን የፈጸሙ ደካማ ሰዎች ነበሩ» ብለዋል።

አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ዕቃዎቹ ከያዟቸው መዛግብት ጢቂት በመፍሰስ ሌሎችን እንዲያንጹ ዕቃዎቹ እንዲጋጩ ይፈቅዳል። መከራ የሰውን ደካማነት ብቻ ሳይሆን፥ ዳሩ ግን የእግዚአብሔርንም ክብር ይገልጻል። ጳውሎስ በዚህ በተጠቀሰው አንቀጽ ውስጥ የተቃራኒ ነገሮችን ዝርዝር ያስቀምጣል: - ሸክላ ዕቃዎች - የእግዚአብሔር ክብር፤ የኢየሱስ ሞት - የኢየሱስ ሕይወት፤ ሞት በሥራ ላይ - ሕይወት በሥራ ላይ። ይሁን እንጂ ተፈጥሮአዊ አእምሮ የዚህ ዓይነቱን መንፈሳዊ እውነት ሊረዳ ስለማይችል፥ ለምን ክርስቲያኖች በመከራ ላይ ድልን እንደሚቀዳጁ ለመረዳት ያዳግተዋል።

በዕቃው ሳይሆን በመዝገቡ ላይ ማተኮር እንደሚገባን ሁሉ፥ እንደዚሁም በአገልጋዩ ላይ ሳይሆን በጌታ ላይ ማተኮር አለብን። መከራ ብንቀበል፥ ስለ ኢየሱስ ብለን ነው። እኔነታችንን የምንገድለው፥ የክርስቶስ ሕይወት እንዲገለጽብን ነው። በመከራ ውስጥ ብናልፍ፥ ክርስቶስ እንዲከብርብን ነው። ይህ ሁሉ ደግሞ ለሌሎችም ጥቅም ነው።

ክርስቶስን ስናገለግል፥ ሞት በእኛ ላይ ይሠራል፤ ዳሩ ግን ለምናገለግላቸው ሰዎች ሕይወት ይሆንላቸዋል።

ዶክተር ጆን ሄንሪ ጆውት፥ «ምንም ዋጋ የማያስከፍል አገልግሎት፥ ምንም ነገር አይሠራም» ብለዋል። ትክክል ናቸው። አንድ ጊዜ እኔና በመጋቢነት የሚያገለግሉ ወዳጄ አንድ ወጣት ግሩም ስብከት ሲያቀርብ ሰምተን ነበረ፤ ሆኖም ስብከቱ አንድ የሚጎድለው ነጥብ ስለ ነበረ፥ ለወዳጄ፥ «አንድ ነገር ይጎድለዋል» ስል አሳቤን አካፈልኩት። እርሱም፥ «አዎን» ብሎ መለሰና በማከልም፥ «የወጣቱ ልብ እስካልተሰበረ ድረስ ጉድለቱ ሊሟላ አይችልም። ለአፍታ ያህል መከራ ከተቀበለ በኋላ ግን፥ ተስማሚ ስብከት የማዘጋጀት ብቃት ይኖረዋል» በማለት መለሰልኝ።

የአይሁድ ሃይማኖት አስፋፊዎች መከራ አልተቀበሉም። በመሆኑም ደኅንነት ያላገኙትን ነፍሳት ለመማረክ በመጣር ፈንታ፥ ጳውሎስ በመሠረታቸው አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የሚገኙትን የዳኑትን ሰዎች በአቋራጭ ይሰርቁ ነበር። ለሕዝቡ መሥዋዕት በመሆን ፈንታ፥ ሕዝቡ ለእነርሱ መሥዋዕትነት እንዲከፍል ያደርጉ ነበር (11፡20)። እነኝህ የሐሰት አስተማሪዎች ለሌሎች የሚያካፍሉት መዝገብ አልነበራቸውም። ከእጃቸው ውስጥ የሚገኙ ነገሮች ቢኖሩ ስለ ቀድሞው ኪዳን የሚያወሩ አንዳንድ የመዘከር ቁርጥራጮች፥ የሰውን ሕይወት ሊመግቡ የማይችሉ የደበዘዙ ቅርሳ ቅርሶች ብቻ ነበሩ።

በበኩሌ፥ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት አንድ መጋቢ ሕዝቡን በሚያገለግልበት ጊዜ ለጌታ ታማኝ ለመሆን ስለሚከፍለው ዋጋ ምንም ነገር እንደማያውቁ ተገንዝቤአለሁ። ይህም ርዕስ በ2ኛ ቆሮንቶስ ውስጥ ከተጠቀሱትና የጳውሎስን መከራዎች ከሚዘረዝሩት ሦስት ክፍሎች አንደኛው ነው። ሌሎቹ ሁለቱ ክፍሎች 6፡1-10 እና 11፡16-12፡10 ናቸው። የእውነተኛ አገልግሎት መፈተኛው ሽልማት ሳይሆን ጠባሳ ነው። «እኔ የኢየሱስን ማኅተም [ጠባሳዎች] በሥጋዬ ተሸክሜአለሁና ከእንግዲህ ወዲህ አንድ ስንኳ አያድክመኝ» (ገላ. 6፡17)።

ተስፋ ቆርጦ ከማቆም እንዴት እንድናለን? የምንድነው፥ በሸክላ ዕቃዎቻችን ውስጥ የወንጌሉ መዝገብ እንዲቀመጥ ዕድል እንደ ተሰጠን በማስታወስ ነው!

## አስተማማኝ እምነት አለን (2ኛ ቆሮ. 4፡ 13-18)

የእምነት መንፈስ የሚለው ሐረግ «የእምነት እይታ ወይም አመለካከት» ማለት ነው። ጳውሎስ ወደ ልዩ የእምነት ስጦታ ሳይሆን (1ኛ ቆሮ. 12፡9)፥ ዳሩ ግን አማኝ ሁሉ ሊኖረው ወደሚገባ የእምነት አመለካከት እያመለከተ ነበር። ጳውሎስ ራሱን፥ «አመንሁ፤ ስለዚህም ተናገርሁ» የሚለውን የመዝሙር (116)፡ 10 መልእክት ከጻፈው ሰው ጋር ይመሳሰላል። ለእግዚአብሔር የሚሰጠው እውነተኛ ምስክርነት በእግዚአብሔር በማመን ላይ የተመሠረተ ሲሆን፥ ይህም እምነት የሚመጣው ከእግዚአብሔር ቃል ነው (ሮሜ 10፡ 17)። አለማመንን ያህል የአንድን አማኝ አፍ የሚለጉም ነገር የለም (ሉቃ. 1፡20 ተመልከት)።

ጳውሎስ የተማመነው በምን ነበር? ለሞት ወይም ለሕይወት የሚያሰጋው ምንም ነገር ባለመኖሩ ነው! የሕይወቱና የአገልግሎቱ አካል የነበሩትን መከራዎች ቀደም ብሎ ስለ ዘረዘረ፥ አሁን ደግሞ እምነቱ በእነዚህ ሁሉ ላይ ድልን እንዳቀዳጀው ያረጋግጣል። ከእምነቱ የተነሣ የሚተማመንባቸው ነገሮች ቀጥለን እንመልከት፡-

1. በመጨረሻ ላይ ድልን እንደሚቀዳጅ እርግጠኛ ነበር (2ኛ ቆሮ. 4፡ 14)። ኢየሱስ ክርስቶስ የመጨረሻውን ጠላት ሞትን ካሸነፈ፥ ሌላውን ነገር መፍራት ለምን ያስፈልጋል? ሰዎች የሞትን ትርጉም ለማግኘትና በዚያውም አንጻር ለመዘጋጀት የሚችሉትን ጥረት ሁሉ ቢያደርጉም፥ ዓለም ግን ለዚህ ጥያቄ ምንም ምላሽ አላገኘችም። አንድ ሰው ለመሞት እስካልተዘጋጀ ድረስ፥ በርግጥም ለመኖር አልተዘጋጀም። የጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን አስደሳች መልእክት ኢየሱስ ክርስቶስ በሞት ላይ ስለ ተቀዳጀው ድል ሲሆን፥ እኛም ወደዚያው በድል ወዳሸበረቀ ምዕራፍ መመለስ ያስፈልገናል። እንዲሁም ደግሞ፥ ጳውሎስ «ከእናንተም ጋር እንዲያቀርበን» ሲል፥ ወደ ፊት የእግዚአብሔር ሕዝብ የሚኖረውን አንድነት እንደ ተመለከተ መገንዘብ ያሻል። ሞት ታላቁ አከፋፋይ ሲሆን፥ ዳሩ ግን እርሱ ራሱ ባለበት ስፍራ ሕዝቡ ዳግም እንደሚሰባሰብ በኢየሱስ ክርስቶስ ዋስትና አለን (1ኛ ተሰ. 4፡ 13-18)።
2. እግዚአብሔር እንደሚከብር እርግጠኛ ነበር (2ኛ ቆሮ. 4፡ 15)። ይህ ምንባብ ከሮሜ 8፡28 ጋር የሚዛመድ ሲሆን፥ መከራዎቻችን እንበለ ከንቱ እንደማይቀሩ ያረጋግጥልናል፡- እግዚአብሔር ለሌሎች

ለማገልገልና ለስሙ ክብር ለማምጣት ይጠቀምባቸዋል። እግዚአብሔር በመከራችን የሚከበረው እንዴት ነው? ጉዞው አስቸጋሪ በሚሆንበት ጊዜ፥ በደስታና በብርታት የምንሻገርበትን «የተትረፈረፈ ጸጋ» በመስጠቱ ነው። በጸጋ የሚጀመር ማንኛውም ነገር፥ ወደ ክብር ይመራል [መዝ. (84)፡ 11፤ 1ጴጥ. 5፡ 10 ተመልከት]።

3. መከራዎቹ የሚፈጸሙት ለእርሱ ጥቅም እንጂ ሊጎዱት እንዳልሆነ እርግጠኛ ነበር (2ኛ ቆሮ. 4፡ 16-17)። «እንታክትም» (ቁ. 1 ተመልከት) የሚለው የጳውሎስ አስተማማኝ ምስክርነት ነበር። የአንድ ሰው «የውስጥ ሰውነቱ» ዕለት በዕለት መንፈሳዊ ተሐድሶ እስካገኘ ድረስ፥ «የውጭው ሰውነቱ» ቢጠፋ ምን ችግር ያስከትልበታል? ጳውሎስ ይህንን በመናገሩ ሰውነት አስፈላጊ አይደለም ለማለት፥ ወይም የሰውነትን ማስጠንቀቂያዎችና መሻቶች ማግለል እንዳለብን ማመልከቱ አልነበረም። ሰውነታችን የእግዚአብሔር ቤተ-መቅደስ ስለ ሆነ፥ እንክብካቤ ልናደርግለት ይገባል፤ ዳሩ ግን የሰብዓዊ ተፈጥሮ ተፈጥሮአዊ ድክመት የሆኑትን አንዳንድ ባሕርያት ተቆጣጥረን ልናስወግዳቸው አንችልም። ጳውሎስ የዳነባቸውን ሥጋዊ መከራዎች ሁሉ ስንመለከት፥ እንደዚህ ብሎ መጻፉ አያስገርመንም።

ክርስቲያኖች እንደ መሆናችን፥ በአንድ ጊዜ አንድን ቀን መኖር አለብን። ምንም ያህል ስጦታ ወይም ሀብት ቢኖረው፥ ማንኛውም ሰው በአንድ ጊዜ ሁለት ቀናትን አይኖርም። እግዚአብሔር ወደ እርሱ ስንጸልይ (ሉቃ. 11፡ 3)፥ «ዕለት-በዕለት» የሚያስፈልገንን ይሰጠናል። እርሱ ለየዕለቱ የሚያስፈልገንን ብርታት ይሰጠናል (ዘዳ. 33፡ 25)። እግዚአብሔር የሚያስፈልገንን ጸጋ የሚሰጠን በተፈለገው ጊዜ ስለ ሆነ (ዕብ. 4፡ 16)፥ ምናልባት በወደፊት ለሚያጋጥመን ችግር ያገለግለናል በማለት «ጸጋውን ለማከማቸት» የመሞከር ስንፍናን ልንፈጽም አይገባም። በአንድ ጊዜ አንድን ቀን ብቻ መኖርን እስከ ተለማመድን በእግዚአብሔር እንክብካቤ ላይ የሚኖረን እርግጠኛነት፥ የሕይወታችንን ውጥረት ባመዛኙ ያስወግደዋል።

አንተም በክርስቶስ በማመን እስከ ተመላለስህ፥ መከራን በተመለከተ ትክክለኛ አመለካከት ይኖርሃል። እስቲ ጳውሎስ በ2ኛ ቆሮንቶስ 4፡ 17 ላይ ያቀረባቸውን ንጽጽሮች እንመልከት፡- ቀላል መከራ - ብዙ ክብር፤ ጊዜያዊ - ዘላለማዊ፤ ያደርግብናል -

ያደርግልናል። ጳውሎስ በዘላለማዊ እሴቶች ላይ ተመርኩዞ ይጽፋል። ያሁኑን መከራ ከሚመጣው ክብር ጋር በማመዛዘን፥ መከራዎቹ ለጥቅሙ እንደ ሆኑ ይገነዘባል (ሮሜ 8፡ 18 ተመልከት)።

የዚህን መመሪያ አሳብ በመሳት፥ ክርስቲያን ደስ እንዳለው ሊኖርና በመጨረሻው ሁሉም ነገር ወደ ክብር እንደሚለወጥለት ተስፋ ሊያደርግ ይችላል ብለን ማሰብ የለብንም። ጳውሎስ የሚጽፈው የእግዚአብሔርን ሥራ በሚሠራበት ጊዜ፥ በእግዚአብሔር ፈቃድ ስለሚመጡ መከራዎች ነበር። እግዚአብሔር መከራን ወደ ክብር ሊለውጥ ይችላል - ይለውጣልም፤ ዳሩ ግን ኃጢአትን ወደ ክብር ሊለውጥ አይችልም። በኃጢአት ውስጥ ክብር ስለሌለ፥ ኃጢአት ፍርድን መቀበል አለበት።

ሁለቱም ቁጥሮች ስለ እግዚአብሔር ልጅ መንፈሳዊ ተሐድሶ ስለሚናገሩ፥ 2ኛ ቆሮንቶስ 4፡ 16 እና 3፡ 18 ሊዛመዱ ይገባል። መከራ በራሱ የተቀደሰን ወንዶችና ሴቶች አያደርገንም። እንዲያውም ራሳችንን ለጌታ እስካልሰጠን፥ ወደ ቃሉ እስካልተመለከትንና እንደሚሠራ እስካልተማመን ድረስ፥ መከራችን የበለጠ የከፋን ክርስቲያኖች ሊያደርገን ይችላል። በራሴ የመጋቢነት አገልግሎት ውስጥ፥ አንዳንድ የእግዚአብሔር ሰዎች ግትርና መራራ በመሆን፥ «ከክብር - ወደ - ክብር» በመሻገር ፈንታ፥ «ከማጡ - ወደ - ድጡ» የወደቁበትን ሁኔታ ተመልክቻለሁ። በመሆኑም ጳውሎስ በቁጥር 13 ላይ የጠቀሰው «የእምነት መንፈስ» ያሻናል።

4. የማይታየው ዓለም እውነተኛ ስለ መሆኑ እርግጠኛ ነበር (2ኛ ቆሮ. 4፡ 18)። ዶክተር ኤ. ደብልዩ. ቶዘር የተባሉት፥ በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሰው የማይታይ ዓለም ብቸኛው «እውነተኛ ዓለም» እንደ ሆነ ተናግረዋል። በዙርያችን የሚገኘውን ገሀዱን ዓለም እግዚአብሔር እንድንመለከተው በሚፈልገው ዓይነት ሁኔታ ብቻ እስከ ተመለከትነው፥ በውስጡ በሚገኘው በማንኛውም ነገር አንማረክም (1 ዮሐ. 2፡ 15-17)። በዕብራውያን 11 ውስጥ የተጠቀሱት ታላላቅ የእምነት ሰዎች፥ ከዚያ ደረጃ የደረሱት «የማይታየውን እንደሚታይ አድርገው ስለ ተመለከቱ» ነው (ዕብ. 11፡ 10፥ 13-14፥ 27)።

የዚህን ዓለም ነገሮች ልናያቸውና ልንዳስሳቸው ስለምንችል፥ በጣም እውነተኛ ይመስላሉ። ዳሩ ግን ሁላቸውም ጊዜያዊና ለሕልፈት የተወሰኑ ናቸው። ለዘለቄታው የሚኖሩት የመንፈሳዊ ሕይወት ዘላለማዊ ነገሮች ብቻ ናቸው። እዚህ ላይ ማጤን ያለብን ይህን እውነት እጅግ በማስፋት፥ «ቁሳዊ» እና «መንፈሳዊ» ነገሮች እንደሚቃረኑ አድርገን

ማሰብ እንደማይገባን ነው። ቁሳዊውን ነገር በእግዚአብሔር ፈቃድ ስንጠቀምበት ወደ መንፈሳዊነት ይለወጥና በሰማይ ያለው መዝገባችን አካል ይሆናል። (በምዕራፍ 8-9 በዚህ ጉዳይ ላይ በይበልጥ እናተኩራለን።) ለቁሳዊ ነገሮች ስፍራ የምንሰጠው፥ መንፈሳዊውን ነገር ለማሳደግ ሊረዳን ስለሚችል እንጂ፥ በራሱ ስለሚሰጠን ጥቅም አይደለም።

ለመሆኑ የማይታዩትን ነገሮች እንዴት ልታያቸው ትችላለህ? የእግዚአብሔርን ቃል ስታነብ ሳለ በእምነት ልትመለከታቸው ትችላለህ። ክርስቶስን ወይም መንግሥተ-ሰማይን አይተን አናውቅም፤ ይሁንና የእግዚአብሔር ቃል ስለሚነግረን በእውነት እንዳሉ እናውቃለን። እምነት «የማናየውን ነገር የሚያስረዳ ነው» (ዕብ. 11፡ 1)። አብርሃም ሰማያዊቷን ከተማ ስለ ተመለከተ፥ ከሰዶም ተለየ፤ ዳሩ ግን ሎጥ በእምነት ሳይሆን በማየት ስለ ተመላለሰ፥ ሰዶምን መረጠ (ዕብ. 11፡ 10፤ ዘፍ. 13)።

በርግጥ፥ ደኅንነትን ያላገኘው ዓለም እኛን የተለየንና የማንረባ ሰዎች እንደ ሆንን አድርጎ ይቆጥረናል፤ ምናልባትም እብዶች እንደ ሆንንም ጭምር ሊያስብ ይችላል - ይኸውም በማይታየው ዓለም መንፈሳዊ በረከት እውነታ ስለምናምን ነው። ይሁንና የክርስቲያኖች እርካታ ሕይወታቸውን በዘላለማዊ እሴቶች መምራት እንጂ፥ ጊዜያዊ ነገሮችን መከተል አይደለም።

የወደፊት ተስፋ አለን (2ኛ ቆሮ. 5፡ 1-8) «ይህ አገልግሎት አለን ... ይህ መዝገብ ... አለን ... ያው አንዱ የእምነት መንፈስ አለን ... ከእግዚአብሔር የተሠራ ሕንፃ (አለን)» (4፡ 1፥ 7፥ 13፤ 5፡ 1)። ይህ ጳውሎስ ስለ ክርስትና እምነት እውነታ የሰጠው ምስክርነት ምንኛ ድንቅ ነው!

በጥቅሱ ውስጥ «የእግዚአብሔር ሕንፃ» ተብሎ የተገለጸው በዮሐንስ 14፡ 1-6 ውስጥ የምናገኘው ቃል የተገባለት የአማኙ ሰማያዊ ቤት ሳይሆን፥ የሚለብሰው የከበረ አካል ነው። ጳውሎስ ድንኳን ሠሪ ሲሆን (የሐዋ. 18፡ 1-3)፥ በዚህ ስፍራ ድንኳንን የአሁኑ ምድራዊ ሕይወታችን መግለጫ አድርጎ ተጠቅሞበታል። ድንኳን ደካማ፥ መሠረቱ ጊዜያዊ የሆነና ብዙም ውበት የሌለው ሲሆን፥ ዳሩ ግን ወደፊት የምናገኘው የከበረው አካል፥ ዘላለማዊ፥ ውብና የድካም ወይም የመበስበስ ምልክት የማይታይበት ነው (ፊልጵ. 3፡ 20-21 ተመልከት)። ጳውሎስ የሰውን ሰውነት እንደ ምድራዊ ዕቃ (2ኛ ቆሮ. 4፡ 7) እና

ጊዜያዊ ድንኳን አድርጎ ይመለከታል፤ ዳሩ ግን አማኞች አንድ ቀን ከድንቅኛው የመንግሥተ ሰማይ ድባብ ጋር የሚስማማ ውብና የከበረ አካል እንደሚለብሱ ያውቅ ነበር።

በዚህ አንቀጽ ውስጥ የጳውሎስን ምስክርነት መመልከት አስደሳች ነው።

እናውቃለን (2ኛ ቆሮ. 5፡10)። እንዴት እናውቃለን? በእግዚአብሔር ቃል ስለምንተማመን። ማንኛውም ክርስቲያን ወደፊት ምን እንደሚሆን ወይም ከሞት በኋላ ስለሚሆነው ነገር ለማወቅ፥ ዕድል-ተንባይ፥ ጨሌጣይ፥ መናፍስት ጠሪ፥ ወይም ሞራ ገላጭ ማማከር አያሻውም። እግዚአብሔር ማወቅ የሚያስፈልገንን ነገር ሁሉ በሰፈረባቸው ገጾች ላይ አስቀምጧል። ጳውሎስ «እናውቃለን» የሚለው በ4፡14 ላይ ከሚገኘው «እውቀት» ጋር የተያያዘ ሲሆን፥ ከኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ይዛመዳል። እርሱ ሕያው ስለ ሆነ፥ ሞት በእኛ ላይ እንደማይሰለጥን እናውቃለን። «እኔ ሕያው ነኝና እናንተ ደግሞ ሕያዋን ትሆናላችሁ» (ዮሐ. 14፡19)።

ድንኳናችን «ቢወድቅ» መሥጋት የለብንም። ሰውነት የምንኖርበት ቤት ብቻ ነው። አንድ አማኝ በሚሞትበት ጊዜ፥ ሰውነቱ ወደ መቃብር ይገባል፤ ዳሩ ግን መንፈሱ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ለመኖር ወደ ሰማይ ይሄዳል (ፊልጵ. 1፡20-25)። ኢየሱስ ክርስቶስ በክብር ሲመለስ፥ የሞተውን ሰውነት በክብር ያስነሣውና፥ ሰውነትና መንፈስ በመንግሥተ ሰማይ ለዘላለም በክብር ለመኖር ይዋሃዳሉ (1ኛ ተሰ. 4፡13-18፤ 1ኛ ቆሮ. 15፡35-58)።

እንቃትታለን (2ኛ ቆሮ. 5፡2-5)። ጳውሎስ ለመሞት ያለውን ከፍተኛ መሻት እየገለጸ አልነበረም። እንዲያውም ዓረፍተ ነገሩ የዚህ ተገላቢጦሽ ነው። የከበረውን አካል «ይለብስ ዘንድ» ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲመለስ ያለውን ጉጉት የሚያሳይ ነበር። ጳውሎስ ሰውነትን በድንኳን በመመሰል ሦስት አስተያየቶችን አቅርቦአል፡- 1) ሕያው - በድንኳን ውስጥ የሚኖር፤ 2) ምውት - እርቃኑን ያለ፥ ከድንኳን ውጭ የወጣ፥ 3) ልብስ የደረበ - ክርስቶስ ሲመለስ የሚፈጸመው የሰውነት መለወጥ። ጳውሎስ ኢየሱስ ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ ሕያው ሆኖ በምድር ላይ እንደሚኖርና በሞት ልምምድ ውስጥ እንደማያልፍ ተስፋ ያደርግ ነበር። ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 15፡51-58 ውስጥ በተመሳሳይ መግለጫ የተጠቀመ ሲሆን፥ በሮሜ 8፡22-26 ውስጥ ደግሞ የ«መቃተት»ን አሳብ አቅርቧል።

የከበረው አካል በ2ኛ ቆሮንቶስ 5፡1 ላይ «በሰማይ ያለ በእጅ ያልተሠራ ... ከእግዚአብሔር የተሠራ ሕንጻ» ተብሎ ሲጠራ፥ በቁጥር 2 ላይ ደግሞ «ከሰማይ የሚሆነው መኖሪያችን» ተብሏል። ይህ ከምድር አፈር ከተሠራው ሟች ሥጋችን ጋር የሚቃረን ነው። «የዚያን የመሬታዊውን መልክ እንደ ለበስን የሰማያዊውን መልክ ደግሞ እንለብሳለን» (1ኛ ቆሮ. 15፡49)። ጳውሎስ የሚቃትተው ሰብዓዊ ሰውነት ለብሶ ስለሚኖር ሳይሆን፥ ዳሩ ግን ኢየሱስ ክርስቶስን ለማየትና የከበረ አካል ለማግኘት ስለ ናፈቀ መሆኑን መረዳት አስፈላጊ ነው። ለክብር እየቃተተ ነበር!

ይህም አባባሉ ሞት ክርስቲያኖችን ለምን እደማያሸብር ግልጽ ያደርግልናል። ጳውሎስ ምድራዊ ሞቱን «መለየት» ብሎታል (2ኛ ጢሞ. 4፡6)። የዚሁ የግሪክ ቃል አንድኛው ትርጉም፥ «ድንኳን ነቅሎ ወደ ሌላ ስፍራ መጓዝ» የሚል ነው። ሆኖም ግን እኛ አንድ ቀን የጌታችንን የከበረ አካል የሚመስል አዲስ አካል እንደሚኖረን እንዴት እርግጠኞች መሆን እንችላለን? እርግጠኞች መሆን የምንችለው መንፈስ ቅዱስ ከውስጣችን ስለሚኖር ነው። ጳውሎስ በ2ኛ ቆሮንቶስ 1፡22 ላይ የመንፈስ ቅዱስን ማተምና መያዣነት ጠቅሶአል (በተጨማሪም ኤፌ. 1፡13-14 ተመልከት)። በአማኙ ውስጥ የሚኖረው መንፈስ ቅዱስ፥ የከበረውን አካል ጨምሮ፥ የወደፊቱን ውርስ የሚያረጋግጥ «መያዣ» ነው። በዘመናዊ የግሪክ ቋንቋ፥ መያዣ ተብሎ የተተረጎመው ቃል «የእጮኛ ቀለበት» ማለት ነው። ቤተ ክርስቲያን ለኢየሱስ ክርስቶስ የታጨች ስትሆን፥ ሙሽራው መጥቶ ወደ ሠርጉ ሥነ-ሥርዓት እንዲወስዳት እየተጠባበቀች ነው።

ሁልጊዜም ተማምነን እንኖራለን (2ኛ ቆሮ. 5፡6-8)። የእግዚአብሔር ሕዝብ ሊገኝ የሚችለው ከሁለቱ በአንድኛው ስፍራ ነው - በሰማይ ወይም በምድር (ኤፌ. 3፡15)። ከእግዚአብሔር ሕዝብ ውስጥ አንድም ሰው ቢሆን በመቃብር፥ በሲኦል፥ ወይም በሰማይና በምድር መካከል በሚገኝ በማንኛውም «መካከለኛ ስፍራ» ሊኖር አይችልም። በምድር ላይ የሚኖሩት አማኞች «በሥጋ ያድራሉ»፥ የሞቱት አማኞች ደግሞ «ከሥጋ ተለይተዋል»። በምድር ላይ የሚኖሩ አማኞች «ከጌታ ተለይተው በስደት የሚኖሩ» ሲሆኑ፥ በሰማይ ላይ ያሉት አማኞች ግን «በጌታ ዘንድ የሚያድሩ» ናቸው።

ጳውሎስ የዚህ ዓይነት መተማመኛ ስለ ነበረው፥ ለመከራና ለሥቃይ፥ ወይም ደግሞ ለአደጋዎች አይሠጋም ነበር። ይህ ማለት ደግሞ አጓጉል የድፍረት እርምጃዎች በመውሰድ ጌታን ተፈታተነ ማለት ሳይሆን፥ ዳሩ ግን ለክርስቶስና ለወንጌሉ አገልግሎት «ሕይወቱን ለማጣት» ፈቃደኛ ነበር ማለት ነው። በእምነት እንጂ በማየት አልተመላለሰም። ለዘላለም የሚኖረውን የማይታይ ነገር እንጂ፥ ለጊዜው የሚታየውን አልመረጠም (2ኛ ቆሮ. 4፡ 18)። ለጳውሎስ፥ መንግሥተ ሰማይ የመድረሻው ግብ ብቻ ሳይሆን የሚያነቃቃውም ተስፋ ጭምር ነበር። በዕብራውያን 11 ውስጥ እንደምናገኛቸው የእምነት ጀግኖች ሁሉ፥ ሰማያዊቷን ከተማ በመመልከት ሕይወቱን ከዘላለማዊ እሴቶች አንጻር መርቷል።

ይህንን የ2ኛ ቆሮንቶስ ክፍል በምንከልስበት ጊዜ፥ ጳውሎስ የገጠሙትን ችግሮች ለመቋቋም እንዴት ብርታት እንደ ነበረውና ተስፋ እንዳልቆረጠ ልንመለከት እንችላለን። ሕይወትን የለወጠ ክቡር አገልግሎት ነበረው። በሰውነቱ ምድራዊ ዕቃ ውስጥ ውድ መዝገብ ነበረውና ያንኑ መዝገብ ለሚጠፋው ዓለም ለማጋራት ፈለገ። ፍርሃትን ድል የሚነሣ አስተማማኝ እምነትና መድረሻና ማነቃቂያ ሆኖ ያገለገለው ብሩህ የወደፊት ተስፋ ነበረው።

ስለዚህ ጳውሎስ «ከአሸናፊዎች የሚበልጥ» መሆኑ (ሮሜ 8፡ 37) ያን ያህል የሚያስደንቅ አይሆንም!

በኢየሱስ ክርስቶስ ያለው እያንዳንዱም አማኝ ከጳውሎስ ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ድንቅ በረከቶች ስላሉት፥ ማንኛውንም የሚያጋጥመውን ችግር በእነርሱ አማካኝነት በብርታት ሊወጣ ይችላል።

# የአገልግሎት መንስዔዎች

## 2ኛ ቆሮንቶስ 5፡9-21

ምን ጊዜም ቢሆን እምነታችንና አካሄዳችን ጎን ለጎን ሊሄዱ ይገባል። እግዚአብሔር ያደረገልንን በጎ ነገር ለእርሱም በአፀፋው መልካምን እንድናደርግ ሊያነቃቃን ስለሚገባ፥ ጳውሎስ ተግባርንና የእምነት ትምህርትን አይነጣጥላቸውም ነበር። ፊልፕስ ብሩክስ፥ «ክርስትና የፍቅር ልጅና የተግባር ወላጅ ያልሆነውን እውነት አይቀበልም» ብለዋል።

አንዲት ሴት ለሰባኪው፥ «በስብከትህ መጨረሻ ላይ ‹ስለዚህ› በሚለው ቃል ደጋግመህ ባትጠቀም ኖሮ ግሩም ሰባኪ በወጣህ ነበር» ስትል ተናግራዋለች።

ጳውሎስ በመልእክቶቹ ውስጥ አዘውትሮ «ስለዚህ» እና «በመሆኑም» በሚሉት ቃላት እየደጋገመ ይጠቀምባቸው ስለ ነበር፥ ከመጋቢው አሳብ ጋር የሚስማማ እውነት ነው። እንዳውም በዚሁ የሁለተኛ ቆሮንቶስ ክፍል ውስጥ እንኳን እነዚሁ ቃላት በቁ. 9፥ 11፥ 16 ና 17 ውስጥ ተደጋግመው ተጠቅሰው ይገኛሉ። ይህም ጳውሎስ ከገለጻ ወደ ተግባራዊነት መሸጋገሩን የሚያመለክት ነው። የመልእክቱም ጭብጥ ለአገልግሎት የሚገፋፉትን መንስዔዎች በግልፅ በማሳወቅ ላይ ያተኰረ ነው። የጳውሎስ ጠላቶች የወንጌል አገልግሎቱን የራስ-ወዳድነት ዓላማዎቹን ለማራመድ በግሉ እንደ ተጠቀመበት አድርገው ከሰውት ነበር፤ እንደ እውነቱ ከሆነ ግን የወንጌሉን እውነት «በውሸት የሚቀላቅሉት» (4፡2፤ 2፡17) ራሳቸው ነበሩ።

የክርስቲያን አገልግሎት ምንድነው? ኃጢአተኞችን ከእግዚአብሔር ጋር እንዲታረቁ ማሳመን ነው (5፡11፥ 20)። ሆኖም ሰዎች በክርስቶስ እንዲያምኑ ማስገደድ ወይም በማታለያ ዘዴዎች ጨርሶ መጠቀም የለብንም። «... እኛ የመከርናችሁ በስህተት ወይም በርኩስ ዓላማ ተመርተን አይደለም፤ እናንተን ለማታለል ያደረግነው ምንም ነገር የለም» (1ኛ ተሰ. 2፡3 - አዲሱ ትርጉም)። ክርስቲያን አገልጋይ፥ ለአገልግሎቱ ትክክለኛ ዓላማና ትክክለኛ መልእክት ሊኖረው ይገባል።

ጳውሎስ በዚህ ክፍል ውስጥ፥ ለአገልግሎት የሚጠቅሙ ሦስት ዓላማዎች አስቀምጧል።

የጌታ ፍርሃት (2ኛ ቆሮ. 5፡9-13) «የጌታን ፍርሃት አውቀን» (ቁ. 11)። የዚህ ዓይነቱ አመለካከት ብዙውን ጊዜ በአገልግሎት ውስጥ አይታይም። የታወቁት የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁር፥ ቢ.ኤፍ. ዌስትኮት፥ አንድ ጊዜ፥ «ሰዎች በመንፈሳዊ ጉዳዮች ላይ ደፍረው የሚናገሩበትን ሁኔታ ሳጤነው፥ እያንዳንዱን ዓመት በበለጠ እንድፈራው ያደርገኛል» በማለት ጽፈዋል። እንዲሁም ፊልፕስ ብሩክስ የተባሉት ሰው፥ እንዴት አንዳንድ «ቀልደኛ ሰባኪዎች» በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ በመቀለድ፥ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የተጻፈውን ቃል ኃይልና ክብር እንደሚያሳጡት አስጠንቅቀው ነበር። ብዙውን ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ይፋዊ ጉባዔዎች ውስጥ ፈሪሃ-እግዚአብሔር መታጣቱ በእጅጉ የሚያሳዝን ከመሆኑም፥ ወጣቱም ትውልድ ለእግዚአብሔር ቃል ክብደት አለመስጠቱ ከዚሁ የመነጨ ለመሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም።

ጳውሎስ በሦስት ጠንካራ ዓረፍተ ነገሮች የራሱን ምስክርነት ከማቅረቡም፥ መንስዔውንም ገልጾልናል።

እንቀናለን (2ኛ ቆሮ. 5፡9) የሚለው «እንሻለን» ማለት ነው። ራስ-ወዳድነትና ዓለማዊነት የነገሠበት መሻት ቢኖርም፥ ዳሩ ግን ጌታን የሚያስከብር ቅዱስ መሻትም አለ። የጳውሎስ ትልቅ መሻት ለኢየሱስ ክርስቶስ እጅግ - ደስ የሚያሰኝ ሆኖ መገኘትን ነበር። የአይሁድ ሃይማኖት አስፋፊዎች ሰዎችን ለማስደሰት ብለው ያገለገሉና ተከታይ ያበጁ ሲሆን፥ ዳሩ ግን ጳውሎስ ኢየሱስ ክርስቶስን ብቻ ለማስደሰት አገልግሏል (ገላ. 1፡10)። ሰውን ለማስደሰት የሚደረግ አገልግሎት ሥጋዊና ታማኝነት የጐደለው አገልግሎት በመሆኑ፥ እግዚአብሔር ሊባርከው አይችልም።

ተቀባይነት ያለው («ደስ የሚያሰኝ») ተብሎ የተተረጎመው ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ በበርካታ ሥፍራዎች ስለ ተጠቀሰ፥ እነዚህ ማጣቀሻዎች ጌታን ደስ የሚያሰኘው ምን እንደ ሆነ የበለጠ ለመረዳት ይረዱናል። ሰውነታችንን ሕያው መሥዋዕት አድርገን ስናቀርብ፥ ይኼ ጌታን ደስ ያሰኘዋል (ሮሜ 12፡1)፤ ሌሎችን ስንረዳና የማሰናከያ ዓለት ከመሆን ስንታቀብ ደስ ይለዋል (ሮሜ 14፡18)። እግዚአብሔር ልጆቹ በዙርያቸው ካለው ክፉ ነገር ራሳቸውን ሲለዩ (ኤፌ. 5፡10)፥ እንዲሁም ስጦታዎቻቸውን ሲያቀርቡለት (ፊልጵ. 4፡18) ደስ ይለዋል። እርሱ ለወላጆቻቸው በሚታዘዙ ልጆችና (ቆላ. 3፡20) ኢየሱስ

ክርስቶስ ፍጹምነት ያለበት ፈቃዱን በሕይወታቸው ውስጥ እንዲፈጽም በሚፈቅዱ ቅዱሳን ደስ ይለዋል።

ፈሪሃ-እግዚአብሔር የሚንጸባረቅበት መሻት ክፉ አይደለም። በሮሜ 15፡20 ላይ ጳውሎስ፥ «ወንጌልን ለመስበክ ተጣጣርሁ [ፈለግሁ]» በማለት ምስክርነቱን ይሰጣል። መልእክቱን ተሰብኮ ወደማያውቅበት ሥፍራ ለማዳረስ ያስገደደው ይኸው ፈሪሃ-እግዚአብሔር ያለበት መሻት ነበር። ጳውሎስ የተሰሎንቄን አማኞች «በጸጥታም ትኖሩ ዘንድ ልትቀኑ (ልትፈልጉ) ... (1ኛ ተሰ. 4፡11) አዝዘናችኋል» ይላል። አማኞች በመንፈስ ተመርተው፥ ለስፖርት ውድድር ወይም ለሥራ የሚያደርጉትን ያህል ጥረት በክርስትና ሕይወታቸውና አገልግሎታቸው ላይ ቢያክሉ ኖሮ፥ ወንጌል በጠፋው ዓለም ላይ የላቀ አዎንታዊ ተጽዕኖ ባስከተለም ነበር። አንድ በቅርብ ጊዜ ወደ ጌታ የተመለሰ ክርስቲያን፥ «ለዲያብሎስ የቀናሁትን ያህል፥ ለእግዚአብሔር ለመቅናት እፈልጋለሁ» ብሎኝ ነበር፤ በርግጥም እግዚአብሔር በዚህ ወንድም ሕይወት በሚገባ ተጠቅሞበታል።

ሁላችንም መቅረብ አለብን (2ኛ ቆሮ. 5፡10)። ሁሉም አማኝ ለጌታ ሥራ ጉጉ አይደለም፤ ዳሩ ግን ሁሉም አማኝ በጌታ ፊት ይቀርባል፤ በመሆኑም የዝግጅቱ ጊዜ አሁን ነው። የክርስቶስ የፍርድ ወንበር፥ የእግዚአብሔር ሕዝቦች እንደየሥራቸው መጠን ሽልማትን ለማግኘት፥ በአዳኙ ፊት የሚቀርቡበት የወደፊት ክስተት ነው (ሮሜ 14፡8-10 ተመልከት)። ጳውሎስ ጌታን በድፍረት እንጂ በኀፍረት ሊገናኝ ባለመፈለጉ፥ ለሥራው ፍፁም ታማኝነት ነበረው (1ኛ ዮሐ. 2፡28)።

የፍርድ ወንበር የሚለው ቃል በግሪክ «ቤማ» የሚል ሲሆን፥ ይህም በግሪክ ከተማ ውስጥ ዲስኩር የሚደረግበት ወይም ገዢዎች ውሳኔ የሚያስተላልፉበት መድረክ ነው (ማቴ. 27፡19፤ የሐዋ. 12፡21፤ 18፡12 ተመልከት)። ይህ ስፍራ በዓመታዊ የኦሎምፒክ ውድድር ወቅት ላሸነፉ ተወዳዳሪዎች ሽልማት የሚሰጥበትም ነበር። ይህ «የፍርድ ወንበር» ክርስቶስ በኃጢአተኞች ላይ ከሚፈርድበት ከታላቁ የነጭ ዙፋን ፍርድ ጋር መምታታት የለበትም (ራእ. 20፡11-15)። በመስቀል ላይ ከተፈጸመው የክርስቶስ የቸርነት ሥራ የተነሣ፥ አማኞች ኃጢአታችን ቢሰረዝልንም፥ (ሮሜ 8፡1፤ ዮሐ. 5፡24)፥ ዳሩ ግን የሥራችንንና የአገልግሎታችንን ምላሽ ለጌታ መስጠት አለብን።

የክርስቶስ የፍርድ ወንበር የመገለጫ ሥፍራ ይሆናል፤ «መቅረብ» የሚለው ቃል የሚያመለክተው መገለጥን ነው። በዚህች ምድር ላይ እስከ ኖርንና እስከ ሠራን ድረስ፥ ነገሮችን መሸሸግና ማስመሰል በአንጻሩ ቀላል ነው፤ ዳሩ ግን በአዳኙ መርማሪ ዓይኖች ፊት የሥራዎቻችን እውነተኛ ባሕርይ ይጋለጣል። እርሱ ሥራዎቻችን መልካም ወይም ክፉ እንደ ነበሩ ይገልጣል። የአገልግሎት ባሕርያችን (1ኛ ቆሮ. 3፡13)፥ እንዲሁም ደግሞ የገፋፉን ውስጣዊ መንስዔዎችም (ዓላማዎች) ይገለጣሉ (1ኛ ቆሮ. 4፡5)።

እንዲሁም ደግሞ የአገልግሎት ዘገባችንን በምናቀርብበት ጊዜ ስለ ድርጊታችን ሁሉ መልስ የምንሰጥበት ስፍራ ይሆናል (ሮሜ 14፡10-12)። ታማኞች ከነበርን፥ ይህ ሥፍራ በሽልማትና በእውቂያ የምናሸበርቅበት ይሆናል (1ኛ ቆሮ. 3፡10-15፤ 4፡1-6)። በታማኝነት ላገለገልን ሰዎች፥ ያ ጊዜ ሽልማቶቻችንን በአምልኮአችንና በውዳሴአችን አማካይነት ለጌታ መልሰን የምንሰጥበት በመሆኑ፥ በደስታ የምንፍለቀለቅበት ወቅት ይሆናል።

ሽልማትን መሻት፥ አገልግሎት ለማበርከት ወሳኙ መንስዔ ነውን? ምንም እንኳ ይህ እጅግ የላቀው አነሳሹ ምክንያት ባይሆንም፥ እግዚአብሔር ሽልማቶችን እንደሚሰጥ የተስፋ ቃል በመግባቱ ሽልማትን መሻት ኃጢአት እንዳልሆነ ያረጋግጥልናል። ልክ ወላጆች ልጆቻቸው እውቂያን ሲያተርፉ እንደሚደሰቱ ሁሉ፥ ጌታችንም ሕዝቡ ለእውቂያና ለሽልማት ሲበቁ በማየት ደስ ይሰኛል። አስፈላጊው ነገር ሽልማቱ ራሱ ሳይሆን፥ ዳሩ ግን ክርስቶስን ከማስደሰትና ከማስከበር ሐሴት ነው።

ለሰዎች እናስረዳለን (2ኛ ቆሮ. 5፡11)። እግዚአብሔር በገዛ ሕዝቡ ላይ የሚፈርድ ከሆነ፥ ደኅንነትን ያላገኙ ኃጢአተኞች ምን ይሆናሉ? «ጻድቅም በጭንቅ የሚድን ከሆነ ዓመፀኛውና ኃጢአተኛው ወዴት ይታይ ዘንድ አለው?» (1ኛ ጴጥ. 4፡18)። ፍርሃት የሚለው ቃል መንቀጥቀጥ ወይም መሥጋት ወይም ድንጋጤ ማለት አይደለም። አዳኛችንን ልናየው ወደዚያው መጓዛችን የማይቀር ነው - እርሱም ይወደናል። እርግጥ ጳውሎስ ይህን ሁኔታ ጨርሶ እንደማያስፈራ አድርጎ አልቆጠረውም። በክርስቶስ ፊት ልንቆም ይገባናል፤ «ለሰው ፊትም አድልዎ የለም» (ቆላ. 3፡23-25)። ክርስቶስ ወንጌሉን ለሕዝቦች ሁሉ እንድናዳርስ አዞናል - እናም መታዘዝ አለብን። አንድ ሰው የዌሊንግተንን ዱክ (መስፍን) ስለ ውጭ አገር የሚሲዮን አገልግሎቶች

ምን እንደሚያስቡ ጠይቆአቸው ነበር። እርሳቸውም «የዘመቻችሁ ትእዛዞች በቅድሚያ ምንድን ናቸው?» በማለት መልሰውለታል።

ክርስቲያን በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት ለመቅረብ እንዴት ሊዘጋጅ ይችላል? በመጀመሪያ ደረጃ፥ ንጹሕ ሕሊና ሊኖረው ይገባል (2ኛ ቆሮ. 5፡11)። በቆሮንቶስ ከተማ ከሚገኙ የጳውሎስ ጠላቶች አንዳንዶቹ፥ «ጳውሎስ በጌታ ፊት እስኪቆም ድረስ ብቻ ጠብቁ» ይሉ እንደ ነበር አይጠረጠርም። ዳሩ ግን ጳውሎስ ሕሊናው ንጹሕ እንደ ሆነ ያውቅ ስለ ነበር (1፡12 ተመልከት)፥ አልፈራም ነበር። ስለ እያንዳንዳችን እውነቱ ስለሚገለጽ፥ ኢየሱስ ክርስቶስም ስለነዚያ እርሱን ደስ ስላሰኙት ነገሮች ያመሰግነናል።

ሁለተኛ፥ በሰዎች ምስጋና ላይ እንዳንደገፍ መጠንቀቅ አለብን (5፡12)። ይህ ቁጥር ጳውሎስ የአይሁድ መምህራን በከፍተኛ ደረጃ የሚመለከቱዋቸውን «የምስጋና ደብዳቤዎች» ከሚጠቅሱበት ከ3፡1 ጋር ይዛመዳል። የሰዎችን ምስጋና ለማግኘት ብለን ብቻ የምንኖር ከሆነ፥ በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት የእግዚአብሔርን ምስጋና ልናተርፍ አንችልም። ከሰው ምስጋና ለማግኘት ብሎ መኖሩ ከባሕርይ ይልቅ ዝናን ለማትረፍ የሚደረግ ጥረት ከመሆኑም፥ በክርስቶስ ፊት በምንቀርብበት ጊዜ ዋጋ የሚሰጠው ለባሕርይ መሆኑን አለመረዳት ነበር። እንደ እውነቱ ከሆነ የቆሮንቶስ ሰዎች ጳውሎስን ማመስገን በተገባቸውም ነበር፤ ዳሩ ግን ከልባቸው መንፈሳውያን ያልሆኑትንና፥ በሥጋቸው ከብረው የሚታዩትን የአይሁድ መምህራን ለማሞገስ መረጡ (11፡18 ተመልከት)።

በመጨረሻም፥ የሰዎችን ትችት ማግለል አለብን (5፡13)። የጳውሎስ ባላንጣዎች ማስተዋል የሌለው ሰው እንደ ሆነ ይናገሩ ነበር። ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያንን በሚያሳድድበት ወቅት፥ «እብድ» እንደ ነበር ይናገራል፤ ዳሩ ግን ጠላቶቹ እንዳውም አማኝ ከሆነ በኋላ «እንዳበደ» ይናገራሉ (የሐዋ. 26፡24)። ይሁንና ሰዎች ጌታችንን እንኳን «አብደሃል» ብለውት ስለ ነበረ፥ ጳውሎስ ለእብደቱ ብቸኛ ሳይሆን መልካም ደባልም ነበረው ማለት ነው (ማር. 3፡21 ተመልከት)። ጳውሎስም፥ «እኔ እብድ ከሆንሁ፥ ለናንተ ጥቅምና ለእግዚአብሔር ክብር ነው - ይህም የእብደቴን ጠቃሚነት ያጎላዋል!» ይል ነበር።

ጵዋይት ኤል ሙዲ በሺካጎ ውስጥ በሚገኘው ሰፌ የሰንበት ትምህርት ቤትና ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚያገለግሉበት ጊዜ፥ ብዙውን ጊዜ ሰዎች «ጅሉ ሙዲ» እያሉ ይጠሩዋቸው ነበር። ሙዲ

የሰንበት ትምህርት ቤት ሠራተኛና ወንጌላዊ ለመሆን የተዋጣለትን የንግድ ሥራቸውን በመተዋቸው፥ ደኅንነትን ባላገኘው ዓለም ፊት «ጅል» ነበሩ። ይሁንና ያደረጉት ውሳኔ የአዋቂነት እንደ ነበር በጊዜ ማረጋገጫነት ታውቋል። ዛሬ፥ በእኚህ ሰው ላይ የተሳለቁትን ሰዎች ስም አናውቅም፤ ዳሩ ግን የዲ. ኤል. ሙዲን ስም አሳምረን እናውቃለን - በአክብሮትም እናስታውሳቸዋለን።

ለእያንዳንዱ ክርስቲያን ለክርስቶስ የፍርድ ወንበር መዘጋጀቱን ለመረዳት፥ ዘወትር ሕይወቱን መመርመሩ አስፈላጊ ነው። በክርስቶስ ፊት መልካም ዘገባ ለማቅረብ መሻቱ፥ ለክርስቲያናዊ አገልግሎት ተገቢ መንስዔ ነው።

## የክርስቶስ ፍቅር (2ኛ ቆሮ. 2፡14-17)

ፍርሃትና ፍቅርን የመሳሰሉ የሚቃረኑ ስሜቶች በአንድ ልብ ውስጥ እንዴት ሊኖሩ ይችላሉ? በመሠረቱ እነዚህ ስሜቶች ወላጆቻቸውን በሚወዱና ዳሩ ግን ወላጆቻቸውን በወላጅነታቸው በሚያከብሩና ለሥልጣናቸውም በሚገዙ ሕፃናት ልጆቻቸው ሕይወት የሚታዩ ናቸው። «ለእግዚአብሔር በፍርሃት ተገዙ፤ በረዓድም (በመንቀጥቀጥ) ደስ ይበላችሁ» (መዝ. 2፡11)።

«የክርስቶስ ፍቅር» የሚለው ሐረግ፥ በመሥዋዕትነት ሕይወቱን ለእኛ ብሎ በሰጠ ጊዜ የታየው ለእኛ ያለው ፍቅሩ ማለት ነው። «እርሱ አስቀድሞ ወዶናልና፥ እኛ እንወደዋለን» (1ዮሐ. 4፡19)። እርሱ የማንወደድ ሳለን ወደደን፤ እንዲያውም ፈሪሃ-እግዚአብሔር የራቀን፥ ኃጢአተኞችና ጠላቶቹ ሳለን ነበር የወደደን (ሮሜ 5፡6-10 ተመልከት)። ክርስቶስ በመስቀል ላይ በሞተ ጊዜ፥ ለዓለም (ዮሐ. 3፡16)፥ ለቤተ ክርስቲያን (ኤፌ. 5፡25)፥ ብሎም በኃጢአት ለጠፉ ግለሰቦች (ገላ. 2፡20) ያለውን ፍቅር አሳይቷል። ክርስቶስ የሞተባቸውን ምክንያቶች በትክክል በምትረዳበት ጊዜ፥ እርሱን ከመውደድ በቀር ሌላ አማራጭ አይኖርህም።

እኛ እንድንሞት ሞተልን (2ኛ ቆሮ. 5፡14 - «እንግዲያስ ሁሉ ሞቱ»)። ይህ የአማኙ ከክርስቶስ ጋር የመተባበር እውነት በሮሜ 6 ውስጥ በዝርዝር ተገልጾአል። ክርስቶስ በሞተ ጊዜ በእርሱና ከእርሱ ጋር ሞትን። ስለ ሆነም አሮጌው ሕይወት ዛሬ በእኛ ላይ ሊሰለጥን አይገባም። «ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ» (ገላ. 2፡20)።

በሕይወት እንድንኖር ሞተልን (2ኛ ቆሮ. 5፡ 15)። ይህ ከክርስቶስ ጋር የመተባበራችን አዎንታዊ ገጽታ ነው - ከርሱ ጋር መሞት ብቻ ሳይሆን፥ ዳሩ ግን «በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ» (ሮሜ. 6፡4)፥ ከርሱ ጋር ተነሥተናል። ከክርስቶስ ጋር ስለ ሞትን፥ ኃጢአትን ልናሸንፍ እንችላለን፤ እንዲሁም ከክርስቶስ ጋር በሕይወት ስለምንኖር፥ ለእግዚአብሔር ክብር ፍሬ ልናፈራ እንችላለን (ሮሜ 7፡4)።

በእርሱ አማካኝነት በሕይወት እንድንኖር ሞተልን፡- «በእርሱ በኩል በሕይወት እንኖር ዘንድ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደ ዓለም ልኮታልና» (1ኛ ዮሐ. 4፡9)። ይህ የደኅንነት ልምምዳችን ነው፥ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የዘላለምን ሕይወት ማግኘት። ዳሩ ግን ለእርሱ እንጂ፥ ለራሳችን እንዳንኖርም ሞቷል (2ኛ ቆሮ. 5፡15)። ይህም የአገልግሎት ልምምዳችን ነው። «ሕይወቱን ለእርሱ እንድንኖርለት ክርስቶስ ሞታችንን ሞተልን» የሚለው አባባል እውነትነት ያለው ነው። አንድ ከደኅንነት የራቀ ኃጢአተኛ ወደ መስቀሉ ከመጣና ከዳነ በኋላ፥ ቀሪ ሕይወቱን እንደ ምን በራስ-ወዳድነት ሊያሳልፍ ይችላል?

በ1858 ዓ.ም. ፍራንሲዝ ሪድሊ ሐቬርጌል የተባለችው ወጣት የተጎዳ ዓይናቸውን በመታከም ላይ ከሚገኙ አባቷ ጋር ጀርመንን ጎብኝታ ነበር። በአንድ መጋቢ ቤት ውስጥ ሳለችም፥ «እኔ ላንተ ይህን አደረግሁ። አንተስ ምን አድርገህልኛል?» የሚሉ ቃላት የሰፈሩበትን የስቅለት ሥዕል ከግድግዳው ላይ ትመለከታለች። ወዲያውም ቁራጭ ወረቀት ወስዳ፥ በዚያ መልእክት ላይ የተመሠረተ ግጥም ጻፈች፤ ዳሩ ግን የጻፈችው ግጥም ስላላረካት፥ ወረቀቱን ጨምድዳ እሳት ውስጥ ከተተችው። ይሁንና ወረቀቱ ሳይቃጠል ቀረ። በኋላም አባቷ ያንን ግጥም እንድታሳትመው ገፋፏትና ዛሬ በፊሊፕ ፒ. ብሊስ ዜማ ወጥቶለት በመላው ዓለም በሚገኙ እንግሊዝኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ዘንድ በመዘመር ላይ ይገኛል።

ሕይወቴን ለወጥሁልህ ልገዛ ነፍስህን፥ ሰማይን ልከፍትልህ ልሰጥህ ርስትህን። ትድን ዘንድ ደሜ ፈሶአል፤ ምን መልሰህልኛል?

ክርስቶስ የሞተው በእርሱ አማካኝነትና ለእርሱ፥ እንዲሁም ከእርሱ ጋር እንድንኖር ነው። «የምንነቃም ብንሆን፥ የምናንቀላፋም ብንሆን፥ ከእርሱ ጋር አብረን በሕይወት እንኖር ዘንድ፥ ስለ እኛ ሞተ» (1ኛ ተሰ. 5፡10)። በጎልጎታ ላይ ከተፈጸመው ነገር የተነሣ፥ አማኞች ለዘላለም ከክርስቶስ ጋር ለመኖር ወደ ሰማይ ይሄዳሉ።

እኛ እንድንሞትና በሕይወት እንድንኖር ሞተልን። ዳሩ ግን የሞተው የአዲሱ ፍጥረት ተካፋይ እንድንሆንም ጭምር ነው (2ኛ ቆሮ. 5፡16-17)። ከክርስቶስ ጋር ያለን አዲስ ግንኙነት ከዓለምና በዙሪያችን ከሚገኙ ሰዎች ጋር አዲስ ግንኙነት እንዲኖረን አድርጓል። ከእንግዲህ ሕይወትን እንደ ቀድሞው አንመለከትም። ክርስቶስን «በሥጋ ማወቅ» ማለት፥ እርሱን በሰብዓዊ እይታ መገመት ማለት ነው። ዳሩ ግን ወደ ሰማይ ስላረገና አሁን በአብ ቀኝ በክብር ስለሚኖር፥ «የሥጋው ወራት» አብቅተዋል (ዕብ. 5፡7)።

አዳም የአሮጌው ፍጥረት ራስ ሲሆን፥ ክርስቶስ (የኋለኛው አዳም - 1ኛ ቆሮ. 15፡45) ደግሞ የአዲሱ ፍጥረት ራስ ነው። ከአዳም አለመታዘዝ የተነሣ፥ አሮጌው ፍጥረት ለኃጢአትና ለኩነኔ ተገዝቶአል። ከኢየሱስ ክርስቶስ መታዘዝ የተነሣ፥ አዲሱ ፍጥረት ግን ጽድቅና ደኅንነት ነው። (ስለ «ሁለቱ አዳሞች» ማብራሪያ ሮሜ 5፡12-21 ተመልከት።) እኛ የአዲሱ ፍጥረት አካል ስለ ሆንን፥ ሁሉም ነገር አዲስ ሆኗል።

ክርስቶስን በተመለከተ አንድ አዲስ አስተሳሰብ (አመለካከት) አለን። ዕለት በዕለት እንደምናየው፥ በተለይ በመዝሙሮችና በሥዕሎች አማካይነት ለክርስቶስ «ሥጋዊ ሕይወት» የሚሰጠው ልዩ ትኩረት በመሠረቱ አሳዛኝ ነው። እርግጥ የክርስቲያን መልእክት በታሪክ መሠረት ላይ የተደገፈ ስለ ሆነ፥ የኢየሱስን ምድራዊ ሕይወት እውነታዎች ማወቅ አስፈላጊ ነው። ዳሩ ግን ግርግሙን (የቤተልሔሙን በረት) በዙፋን መተርጎም አለብን። ዛሬ የምናመልከው በግርግም የሚተኛውን ሕፃን ሳይሆን፥ በዙፋን ላይ ከብሮ የተቀመጠውን አዳኝ ነው።

«ሁሉም ነገር ስለ ታደሰ»፥ በዙርያችን ለሚኖሩ ሰዎች የተለየ አመለካከት አለን። ክርስቶስ እንደ ሞተላቸው ኃጢአተኞች አድርገን እንመለከታቸዋለን። ከእንግዲህ እንደ ወዳጆች ወይም ጠላቶች፥ እንደ ገዢዎች ወይም አጋዥ-ሠራተኞች አድርገን አንመለከታቸውም። ልክ ክርስቶስ እረኛ እንደሚያስፈልጋቸው ተቅበዝባዥ በጎች አድርጎ እንደሚመለከታቸው ሁሉ እኛም በዚያው ዓይን እናያቸዋለን። የክርስቶስ ፍቅር ግድ የሚለን እስከሆንን፥ እኛም የእርሱን ፍቅር ለሌሎች ከማጋራት ወደ ኋላ አንልም።

የተለየ ውዝግብ ባስከተለ በአንድ ፕሬዝደንታዊ ምርጫ ወቅት፥ አንድ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ከተወዳዳሪዎቹ አንዱን የሚደግፍ የደረት ምልክት አድርጎ ወደ ሰንበት ትምህርት ክፍል ገባ። መጋቢውም

አስቆመውና ከቤተ ክርስቲያን ግቢ እስኪወጣ ድረስ ምልክቱን ከደረት ኪሱ ላይ እንዲያወርድ ጠየቀው።

ሰውየውም፥ «ለምን አወርዳለሁ? ሰውየው እኮ በጣም ጥሩ ተወዳዳሪ ነው!» በማለት ሙግት ገጠመ።

መጋቢውም፥ «ይሁን እሺ፥ ግን አንድ ደጎንነትን ያላገኘ የሌላ ፓርቲ አባል ምልክቱን አድርገህ ቢያይህና ከብስጭት ላይ ቢወድቅ፥ ቃሉን ሰምቶ ከመዳን የማያግደው አይመስልህም?» በማለት መለሰለት።

ሰውየውም በዝግታ ምልክቱን ካወለቀ በኋላ፥ ፈገግ ብሎ፥ «ሰዎች ሪፓብሊካን ወይም ዲሞክራቶች ሳይሆኑ፥ አዳኝ የሚያስፈልጋቸው ኃጢአተኞች መሆናቸውን ማስታወስ በተገባኝ ነበር፤ ይህም ምርጫውን ከማሸነፍ የላቀ ነገር ነው» አለ።

እንደዚሁ ሁሉ እኛም ሌሎች ክርስቲያኖችን የአዲሱ ፍጥረት አካላት እንደ ሆኑ አድርገን መመልከት እንጂ፥ ባላቸው ትምህርት፥ ዘር፥ ሀብት፥ ወይም ማህበራዊ እሴት ላይ ተመርኩዘን ማናናቅ ወይም ማንገሥ የለብንም። «አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፤ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም፤ ወንድም ሴትም የለም፤ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና» (ገላ. 3፡28)።

## የክርስቶስ ተልዕኮ (2ኛ ቆሮ. 5፡18-21)

በዚህ አንቀጽ ውስጥ ቁልፉ አሳብ ዕርቅ ነው። ሰው ከዓመፁ የተነሣ፥ የእግዚአብሔር ጠላትና ከእርሱ ጋር ከሚኖረው ኅብረት የራቀ ነበር። ከመስቀሉ ሥራ የተነሣ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ደግሞ ሰውንና እግዚአብሔርን ወደ አንድነት አመጣ። እግዚአብሔርም ከሰው ጋር በመታረቅ፥ ፊቱን በፍቅር ወደ ጠፋው ዓለም መለሰ። የዕርቅ መሠረታዊ ትርጉም «ሙሉ ለሙሉ መለወጥ» የሚል ሲሆን፥ በእግዚአብሔርና በጠፋው ዓለም መካከል የተደረገውን የግንኙነት ለውጥ ያመለክታል።

የዕርቅ ሥራ በመስቀል ላይ ስለ ተፈጸመ፥ ለእግዚአብሔር ከሰው ጋር ዕርቅን ማድረግ አያሻውም። ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ ያለበት ኃጢአተኛው ሰው ነው። «ሃይማኖት» ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ለመታረቅ የፈጠረው ደካማ ዘዴና ከንቱም ልፋት ነው። ከእግዚአብሔር ጋር የሚያስታርቀን አካል ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሆን፥ የመታረቂያ በታውም ከመስቀሉ ሥር ነው።

በዚህ ክፍል ውስጥ ሌላው ቁልፍ አሳብ መቁጠር የሚለው ሲሆን (ለምሳሌ የእኛ ኃጢአት በክርስቶስ ላይ ተቆጠረ)፥ አሳቡ በባንክ ቤት ውስጥ ገንዘብ ከማከማቸት ጋር የሚዛመድ ነው። «በአንድ ሰው የሂሳብ ደብተር ውስጥ ገንዘብ ማስቀመጥን» ያመለክታል። ገንዘብ በባንክ ቤት ውስጥ ስታስቀምጥ፥ ኮምፒውተሩ (ወይም ሠራተኛው) ያንኑ የገንዘብ መጠን በሂሳብ ደብተርህ ውስጥ ይመዘግባል። ኢየሱስ በመስቀል ላይ በሞተ ጊዜ፥ ኃጢአታችን በሙሉ ወደ እርሱ ተላለፈ - በርሱ ደብተር ላይ ተመዘገበ። እግዚአብሔርም እነዚያን ሁሉ ኃጢአቶች ክርስቶስ ራሱ እንደ ፈጸማቸው አድርጎ ቆጠረ።

ውጤቱስ? ክርስቶስን እንደ አዳኛችን አድርገን ስላመንን፥ እግዚአብሔር የእነዚያ ሁሉ ኃጢአቶች ዋጋ እንደ ተከፈለ በመቁጠር፥ ከእንግዲህ በእኛ ላይ ኃጢአቶችን አይዝም። ከዚህም በላይ፥ እግዚአብሔር በእኛ መዝገብ ውስጥ የክርስቶስን ጽድቅ አስቀምጦታል! «እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን [ክርስቶስን] ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው» (ቁ. 21)።

ዕርቅ [ኃጢአትን] በመሸከም ላይ የተመሠረተ ነው:- ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቅዱስ ሕግ መጠይቆች በመስቀሉ ላይ ሙሉ ለሙሉ ስለ ተፈጸሙ፥ እግዚአብሔር ከኃጢአተኞች ጋር ሊታረቅ ይችላል። ኢየሱስ ክርስቶስን አዳኛቸው አድርገው የሚያምኑ ሰዎች፥ ኃጢአታቸውን ዳግም አይቆጠርባቸውም [ሮሜ. 4፡1-8፤ መዝ. (32)፡1-2]። መዝገባቸውንም በተመለከተ፥ የኢየሱስ ክርስቶስን ጽድቅ ለመጋራታቸው ተረጋግጦላቸዋል።

ጳውሎስ ለወዳጁ ለፊልሞና በጻፈው አነስተኛ መልእክት ውስጥ ይህንኑ እውነታ የሚያብራራ ግሩም መግለጫ አለ። የፊልሞና ባሪያ የነበረው አናሲሞስ ከጌታው ዘንድ ገንዘብ ሰርቆ ወደ ሮም ሸሽቶ ነበር። በዚህ ወንጀሉም ሊገደል ይችል ነበር። ይሁንና እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ፥ አናሲሞስ ከጳውሎስ ጋር ተገናኝና ደኅንነትን ተቀበለ። ከዚያም ጳውሎስ አናሲሞስን ይቅር ብሎ ወደ ቤት ያስገባው ዘንድ ለማበረታታት ለወዳጁ ለፊልሞና ደብዳቤ ይጽፍለታል። ጳውሎስ፥ «እንደ እኔ አድርገህ ተቀበለው ... ብድር ያለበት እንደ ሆነ፥ ይህን በእኔ ላይ ቁጠር» (ፊል. ቁ. 17 ና 18) ይለዋል። ጳውሎስ አናሲሞስና ፊልሞና እንዲታረቁ ዕዳውን ለመክፈል ፈቃደኛ ነበር።

ይህ አስደናቂ የዕርቅ ትምህርት ክርስቶስን እንድናገለግል እንዴት ያነሣሣናል? እኛ መልእክት ያለን አምባሳደሮች ነን። እግዚአብሔር የዕርቅን አገልግሎት (2ኛ ቆሮ. 5፡18) እና የዕርቅን ቃል (ቁ. 19) ሰጥቶናል።

በሮም መንግሥት ውስጥ ሴናቶሪያልና ኢምፔሪያል የሚባሉ ሁለት የግዛት ዓይነቶች ነበሩ። ሴናቶሪያል የሚባሉት ከሮም ጋር መዋጋትን አቁመው በሰላም የሚኖሩቱ ናቸው - እጃቸውን በመስጠት ተገዝተው የሚኖሩ። ዳሩ ግን ኢምፔሪያሎቹ አቅሙ ከፈቀደላቸው በሮም ላይ ለማመፅ ይፈልጉ ስለ ነበር፥ አደገኞች ነበሩ። በመሆኑም ዓመፁ እንዳይነሣሣ ሮም ወደ ኤምፔሪያል ግዛቶች አምባሳደሮችን መላክ ያስፈልጋት ነበር።

በዚህ ዓለም ውስጥ ክርስቲያኖች የክርስቶስ አምባሳደሮች ስለ ሆኑ፥ ዓለም በእግዚአብሔር ላይ በማመፅ ላይ ነች ማለት ነው። ይህች ዓለም ለእግዚአብሔር «የኢምፔሪያል ግዛት» ነች። እርሱም አምባሳደሮቹን ወደ ዓለም የላከው ጦርነትን ሳይሆን፥ ሰላምን እንዲያውጁ ነው። «ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ!» ብለን ኢየሱስ ክርስቶስን እንወክላለን (2ኛ ቆሮ. 4፡5፤ ዮሐ. 20፡21)። ኃጢአተኞች እኛንና መልእክታችንን ቢገፉ፥ በመሠረቱ የተገፋው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ለዚህ ዓለም ዕመፀኛ ኃጢአተኞች የሰማይ አማባሳደር ሆኖ መሾም ምንኛ ታላቅ ዕድል ነው!

ገና ወጣት መጋቢ በነበርሁበት ጊዜ፥ ሰዎችን ለመጎብኘትና ስለ ክርስቶስ አዳኝነት ለመመስከር ኃፍረት ይሰማኝ ነበር። በኋላ ግን የነገሥታት ንጉሥ አማባሳደሩ ሆኜ በመሾም፥ ዕድለኛ መሆኔን ተረዳሁ። ምንም የሚያሳፍረኝ ነገር አልነበረም። እንዲያውም፥ የምጎበኛቸው ሰዎች፥ ከክርስቶስ አምባሳደሮች አንዱ ሊጠይቃቸው በመምጣቱ መደሰት ነበረባቸው።

እግዚአብሔር በዓለም ላይ ጦርነትን አላወጀም፤ ይልቁንም በመስቀሉ ላይ ሰላምን አውጇል። ይሁንና አንድ ቀን ጦርነትን ያውጃል፤ በዚያን ጊዜም አዳኙን ለገፉት ሰዎች ጊዜው ይመሽባቸዋል (2ኛ ተሰ. 1፡3-10)። ሰይጣን በዓለም ውስጥ ነገሮችን ሁሉ ለመበታተን እየጣረ ነው፤ ዳሩ ግን ክርስቶስና ቤተ ክርስቲያኑ ነገሮችን ወደ አንድነት በማምጣቱና ወደ እግዚአብሔር ዘንድ በመመለሱ የዕርቅ አገልግሎት ላይ ተሰማርተዋል።

አገልግሎት ቀላል አይደለም። በአገልግሎታችን ስኬታማ ለመሆን ከፈለግን፥ አነሣሽ ምክንያታችን ፈሪሃ-እግዚአብሔር፥ አፍቅሮተ-ክርስቶስና እንዲሁም እርሱ የሰጠን ተልዕኮ መሆን አለበት። እርሱን ማገልገል ምንኛ መታደል ነው!

# ልብ ለልብ

## 2ኛ ቆሮንቶስ 6-7

እነዚህ ሁለት ምዕራፎች ጳውሎስ ስለ አገልግሎቱ ለሚሰጠው ማብራሪያ እውነተኛ ማጠቃለያ ያቀርባሉ። ባለፍንባቸው ምዕራፎች ውስጥ ለአንባቢዎቹ፥ ከመከራዎቹ ባሻገር አገልግሎቱ ድል-ነሺ (ምዕ. 1-2) እና የከበረ (ምዕ. 3) መሆኑን በመግለጽ፥ ከመታከት የተነሣ ከዓላማው ከቶውንም ዝንፍ እንደማይል ተናግሯል። ባላንጣዎቹ አገልግሎቱን ለግል ጥቅም ማግኛ እንዳዋለ አድርገው የከሰሱት ቢሆንም፥ ዳሩ ግን አገልግሎቱ እውነተኛ (ምዕ. 4) እና በእግዚአብሔር ላይ በተጣለ እምነት የተመሠረተ (ምዕ. 5) መሆኑን አረጋግጧል። አሁን የቀረው ነገር ቢኖር የቆሮንቶስን ሰዎች ልብ ማነሣሣትና እንደሚያፈቅራቸው ማረጋገጥ ብቻ ነበር። ይህንንም ለማሳካት ሲል የሚከተሉትን ሦስት የፍቅር ልመናዎችን ያቀርባል።

### ለምስጋና የቀረበ ልመና (2ኛ ቆሮ. 6፡ 1-10)

የሥነ-ልቦና መመሪያዎች በሚል ርዕስ የተዘጋጀው የዊልያም ጀምስ መጽሐፍ፥ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠውና በመስኩም ቀደምትነት ያለው ሥራ ነበር። ዳሩ ግን ደራሲው ከመጽሐፉ ውስጥ አንድ «ትልቅ ነገር እንደ ጎደለ» አምኖ ነበር። «የሰብዓዊ ባሕርይ እጅግ የጠለቀ መሻት ምስጋናን ማትረፍ» እንደ ሆነ ይገልጹና ዳሩ ግን በመጽሐፋቸው ውስጥ ይህንን ጉዳይ እንዳላነሡት ይናገራሉ።

የ2ኛ ቆሮንቶስን መልእክት በምናነብበት ጊዜ ቤተ ክርስቲያኗ በጳውሎስ ራሱም ሆነ በመካከላቸው በሠራቸው ሥራዎች ጭምር ተደስታ ምስጋና እንዳላቀረበች ያለ ጥርጥር እንረዳለን። እነርሱ ለጳውሎስ ሊሟገቱለት እንጂ፥ እርሱ ለራሱ እንዲሟገት ሊያስገድዱት ባልተገባቸውም ነበር። የቆሮንቶስ ሰዎች ቤተ ክርስቲያኒቱን ስለወረሩ የአይሁድ ሃይማኖት አስፋፊዎች በመኩራራት ቢናገሩም፥ እነዚህ ሰዎች ግን ምንም አልፈየዱላቸውም ነበር። ስለ ሆነም እግዚአብሔር በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ዘንድ ስለ ሰጠው አገልግሎት ጳውሎስ ያስታውሳቸዋል።

ወንጌላዊው ጳውሎስ (2ኛ ቆሮ. 6፡ 1-2)። የወንጌሉን የምሥራች ይዞ ወደ ቆሮንቶስ የሄደው ጳውሎስ ነበር፤ በዚህም አገልግሎት ቤተ

ክርስቲያን ተመሠረተች። በ2ኛ ቆሮንቶስ 5፡ 18-21 የተገለጸውን «የአምባሳደርነቱን» ተልዕኮ በሚገባ ተወጥቶት ነበር። እነርሱንም ወደ ክርስቶስ የመለሳቸው ጳውሎስ እንጂ፥ የአይሁድ ሃይማኖት አስፋፊዎች አልነበሩም።

ይህም ሆኖ ግን ጳውሎስ፥ «ድኛለሁ» በማለት በቤተ ክርስቲያኗ የታቀፉትን ሁሉ እውነተኛ የእግዚአብሔር ልጆች ስለ መሆናቸው እርግጠኛ አልነበረም (13፡5 ተመልከት)። የእግዚአብሔርን ጸጋ ይቀበሉ ዘንድ፥ ኢሳይያስ 49፡8ን እንደ ልመና አድርጎ ጠቅሶላቸዋል። በመስቀል ላይ ከተፈጸመው የክርስቶስ የዕርቅ ሥራ የተነሣ (2ኛ ቆሮ. 5፡18-19)፥ በርግጥም «የመዳን ቀን» ዛሬ ነው በማለትም አሳስቧቸዋል። ለማንኛውም ኃጢአተኛ ነገ የመዳን ዕድል ሊኖረው እንደሚችል የሚያረጋግጥ ምንም ዓይነት ዋስትና የለም። «እግዚአብሔር... ቀርቦ ሳለ ጥሩት» (ኢሳ. 55፡6)።

አንድ መጋቢ ኢየሱስ ክርስቶስን ለመቀበል ገና ብዙ ጊዜ እንዳላት በመግለጽ ከምትሟገት ወጣት ሴት ጋር ይነጋገር ነበር። መጋቢውም ቁራጭ ወረቀት ሰጣትና፥ «ደኅንነትን በአንድ ዓመት ለማዘግየት ፈቃደኛ መሆንሽን በመግለጽ ጽፈሽ ትፈርሚበታለሽ ወይ?» አላት። «አይ፥ ፈቃደኛ አልሆንም» አለች። ለስድስት ወራትስ? አሁንም አይሆንም። ለአንድ ወር? አመነታችና «አይሆንም» አለች። ከዛሬ በስተቀር ሌላ ቀን ዕድል እንደሚኖራት የሚያረጋግጥ ዋስትና ስላላገኘች፥ የሙግቷን እርባና-ቢስነት ተመለከተችና ክርስቶስን ያኔውኑ ተቀበለች።

ምሳሌ የሆነው ጳውሎስ (2ኛ ቆሮ. 6፡3-10)። ለወንጌል መስፋፋት እንቅፋት ከሚሆኑ ነገሮች አንዱ ክርስቲያኖች ነን የሚሉት ሰዎች እኩይ ምሳሌነት ነው። ደኅንነትን ያላገኙ ሰዎች የቅዱሳንን - በተለይም የሰባኪዎችን - የቃልና የተግባር መለያየት፥ ኢየሱስ ክርስቶስን ላለመቀበል ማመካኛ ለማድረግ ይሻሉ። ጳውሎስ በኃጢአተኞች ወይም በቅዱሳን ጎዳና ላይ መሰናክል የሚፈጥር ማንኛውንም ነገር ላለማድረግ ይጠነቀቅ ነበር (ሮሜ 14 ተመልከት)። ከግል ሕይወቱ ግድፈት የተነሣ አገልግሎቱ በማንኛውም መንገድ ዋጋ እንዳያጣ («እንዳይነቀፍ») ይጠነቀቅ ነበር።

ጳውሎስ ለአንባቢዎቹ ለእነርሱ ብሎ የተቀበላቸውን መከራዎች ያስታውሳቸዋል (2ኛ ቆሮ. 6፡4-5)። ጳውሎስ የጽናት («የትዕግሥት») ሰው ስለ ነበር፥ ነገሮች አቀበት ሲሆኑበት ጥሎ አልፈረጠጠም።

መከራዎች ስንል፥ በአካባቢ ተፅዕኖዎች የተነሣ በሕይወታችን ላይ የሚደርሱ ጫናዎችና ፈተናዎች ሊሆኑ ይችላሉ። መሠረታዊ ፍላጎቶችን በማጣት የሚመጡ ችግሮች ዕለታዊ የሕይወት ጉብታዎች ሲሆኑ፥ ጭንቀት ማምለጫ የሌለበት ወደሚመስለን ጥግ የሚገፉንን ልምምድ ያመለክታል። የግሪኩ ቃል «በጠባብ ማነቆ» ይመስለዋል።

ምንም እንኳን እነዚህ መከራዎች የማያምኑም ሰዎች የሚያልፉባቸው ልምምዶች ቢሆኑም፥ ጳውሎስ ግን ከሕዝቡ ተቃውሞ የተነሣ አንዳንድ የደረሰባቸውን መከራዎች ብቻ ዘርዝሮአል - መገረፍ፥ ወኅኒ መግባት፥ ሁከት እነዚህን ችግሮች በሕይወቱ ውስጥ ማሳለፉ ጌታን በታማኝነት ያገለግል ስለ ነበር ነው። ከዚያም ለአገልግሎቱ ብሎ በፈቃደኛነት የከፈላቸውን አንዳንድ መሥዋዕቶች ዘርዝሮአል - ድካም (ከመንገድና ከሥራ ብዛት)፥ እንቅልፍ ማጣት፥ ጾም (በፈቃደኛነት አለመመገብን መምረጥ)። በርግጥ ጳውሎስ እነዚህን ነገሮች በይፋ እያወጀ አልነበረም። በዚህ ደብዳቤ ውስጥ የጠቀሰበት ብቸኛው ምክንያት ለቆሮንቶስ ሰዎች ያለውን ፍቅር ለማረጋገጥ ነበር።

በተጨማሪም በአገልግሎቱ ስለ ተገለገለባቸው መሣሪያዎች ያስታውሳቸዋል (6፡6-7)። ንጽሕና የሚለው «ከትዳር ውጭ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት አለመፈጸምን» የሚያመለክት ነው (11፡2 ተመልከት)። ጳውሎስ የራሱን ግብረ-ገባዊ ሕይወት በንጽሕና ጠብቋል። ትዕግሥት አስቸጋሪ ሰዎችን መታገሥ ሲሆን፥ መጽናት (6፡4) በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ መጽናናትን ያመለክታል። ጳውሎስ እንደ ቸርነትና እውነተኛ ፍቅር ያሉትን የመንፈስ ፍሬዎች ለማፍራት የተደገፈው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ላይ ነበር። መንፈሳዊ እውቀትን ለማስተላለፍ የእግዚአብሔርን ቃል ይጠቀማል፤ ከሰይጣናዊ ጥቃቶች ለመከለልም የእግዚአብሔርን የጦር ዕቃ ይለብሳል (ኤፌ. 6 ከቁ. 10 ጀምሮ)።

በመጨረሻም፥ የሕይወት ምስክርነቱን ያስታውሳቸዋል (2ኛ ቆሮ. 6፡8-10)። ጳውሎስ ሁሉም ሰዎች እርሱንና አገልግሎቱን በትክክል እንዳልተረዱ በማወቁ፥ የተቃራኒ ነገሮችን ዝርዝር ያቀርባል። የጳውሎስ ባላንጣዎች ስሙን ለማጥፋት እንደለየለት አጭበርባሪ አድርገው ዘገባ አቅርበውበት ነበር። ዳሩ ግን እግዚአብሔር ጳውሎስ ክብር የሚገባውና እውነተኛ መሆኑን የሚያመለክት መልካም ዘገባ አቀረበለት። ጳውሎስ በአንድ በኩል በሚገባ የታወቀ ሲሆን፥ በዚያው መጠን ደግሞ በሌላ በኩል ያልታወቀ ሰው ነበር።

ጳውሎስ በአገልግሎቱ ታማኝ ለመሆን የከፈለው ዋጋ ምንኛ ውድ ነበረ! ይሁንና የቆሮንቶስስ ሰዎች ላደረገላቸው መልካም ነገር ሁሉ የሰጡት ምስጋና ምንኛ አናሳ ነው! ልቡን በኃዘን አደሙበት፤ ይሁንና እርሱ «ሁልጊዜም» በኢየሱስ ክርስቶስ «ይደሰት» ነበር። እነርሱ ሀብታም እንዲሆኑ፥ እርሱ ድሀ ሆነ (1ኛ ቆሮ. 1፡5፤ 2ኛ ቆሮ. 8፡9 ተመልከት)። ድሀ ተብሎ የተተረጎመው ቃል «ፍጹም የሆነ የለማኝነት ደረጃ» ማለት ነው።

ጳውሎስስ እንዲያመሰግኑት በመፈለጉ ጥፋተኛ ይሆን ይሆን? አይመስለኝም። እርግጥ እጅግ በርካታ ክርስቲያኖች የመጋቢዎችን፥ የሚሲዮናውያንንና፥ ታማኝ የቤተ ክርስቲያን ሠራተኞችን አገልግሎት የዋዛ አድርጎ የመመልከት ዝንባሌ አላቸው። ደግሞም እኮ ጳውሎስም ቢሆን እንዲያመሰግኑት እየለመናቸው አልነበረም፤ ዳሩ ግን በቆሮንቶስ ለነበሩት ወዳጆቹ ያበረከተላቸው አገልግሎት ውድ ዋጋ እንዳስከፈለው ሊያስታውሳቸው ብቻ ነበር የፈለገው።

በርግጥ በዚህ ሁሉ የግል ምስክርነቱ፥ ጳውሎስ የአይሁድ ሃይማኖት አስፋፊዎች ያስነሡበትን የሐሰት ክሶች እያፈራረሰባቸው ነበር። እነዚህ ሰዎች በቆሮንቶስ ለነበሩ ወገኖች ምን ያህል መከራ ተቀብለዋል? ለአገልግሎታቸው ምን ያህል ዋጋ ከፍለዋል? ዛሬ እንደምናያቸው በርካታ «ኑፋቄዎች» ሁሉ፥ እነዚያም የሐሰት አስተማሪዎች በሌላው ሰው ምስክርነት የዳኑትን ሰዎች ሰረቁ እንጂ፥ ራሳቸው ወደ ጠፉት በጎች ተጉዘው ነፍሳትን አልማረኩም ነበር።

«ምስጋናን ብትሻ የምታገኘው ከመዝገበ-ቃላት ውስጥ ብቻ ነው» የሚለው አባባል እውነትነት ያለው ነው። እኛስ አገልግሎት ላበረከቱልን ሰዎች ምስጋናችንን ከልብ እየገለጽንላቸው ይሆን?

## የመለየት ልመና (2ኛ ቆሮ. 6፡ 11-7፡ 1)

ምንም እንኳን ቤተ ክርስቲያኗ በጳውሎስ ላይ የተለያዩ ችግሮችና ልብን የሚሰብሩ ሐዘኖች ብታደርስበትም፥ እርሱ ግን በቆሮንቶስ ውስጥ የሚገኙትን አማኞች በጣም ይወዳቸው ነበር። አስቀድሞ በታማኝነትና በፍቅር ተናግሮአቸው ነበር፤ አሁን ደግሞ ልባቸውን ይከፍቱለት ዘንድ በፍቅር ይጠይቃቸዋል። ጳውሎስ የወለዳቸው ልጆቹ የሚገባውን ፍቅር እንደ ነፈጉት አባት ያህል ሐዘኔታ ተሰምቶት ነበር (1ኛ ቆሮ. 4፡ 15 ተመልከት)።

ፍቅራቸውን የሚነፍጉት ለምን ነበር? ምክንያቱም የተከፋፈለ ልብ ስለ ነበራቸው ነው። የሐሰት አስተማሪዎች ልባቸውን ስለሰረቁባቸው፥ ለጳውሎስ የነበራቸው ፍቅር ቀዝቅዞ ነበር። ልክ ለጋብቻ የታጨችና ዳሩ ግን በሌላ ሰው ማባበል የተማረከችን ልጃገረድ ይመስሉ ነበር (2ኛ ቆሮ. 11፡ 1-3)። የቆሮንቶስ ሰዎች ከዓለም ጋር ለመስማማት ይከጅሉ ነበርና፥ ጳውሎስ ራሳቸውን ለእግዚአብሔር እንዲለዩ ይለምናቸዋል፥ ታማኝ ሚስት ራስዋን ለባልዋ እንደምትለይ ዓይነት።

የመለየት ትምህርት አስፈላጊ እውነት መሆኑ ጉልቶ እየታየ፥ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ጠቀሜታው እየተዘነጋና እየተናቀ መምጣቱ አሳዛኝ ነው። አንዳንድ ቀናዒና ሐቀኛ ክርስቲያኖች፥ ከራሳቸው ጋር እንኳ ለማበር እስኪሳናቸው ድረስ ኅብረታቸውን አጥብበው፥ መለየትን ወደ መገንጠል ለውጠውት ይታያሉ። ከዚህ እጅግ ከተስፈነጠረ አቋም በተቃራኒ ያሉ ሌሎች አማኞች ደግሞ ስለሚያምኑበት ወይም ስለሚኖሩበት የሕይወት ዘይቤ ግድ ሳይኖራቸው የመለያየት ግድግዳዎችን ሁሉ አፍርሰው፥ ካገኙት ከማንኛውም ሰው ጋር ኅብረት ያደርጋሉ። ምንም እንኳ የእነዚህን ወገኖች ክርስቲያናዊ ፍቅርን የመለማመድ መሻት በአንድ በኩል ብንደግፈውም፥ ዳሩ ግን በክርስቲያናዊ ፍቅርም ውስጥ ቢሆን መቼ መለየት ወይም አለመለየት እንደሚያስፈልግ ማስተዋል እንዳለባቸው ለማሳሰብ እንወዳለን (ፊልጵ. 1፡9-11)።

ጳውሎስ እንዚህ አማኞች ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር ከሚቃረን ነገር እንዲለዩ ሦስት የማሳመኛ አሳቦችን ያቀርባል።

1. የአማኙ ባሕርይ (2ኛ ቆሮ. 6፡ 14-16)። ኅብረትን የሚወስነው ባሕርይ ነው። አሣማ የአሣማ ባሕርይ (ተፈጥሮ) ስላለው፥ ከሌሎች አሣማዎች ጋር በጭቃ ውስጥ ኅብረት ያደርጋል። በግ የበግ ባሕርይ ስላለው፥ ከሌሎች በጎች ጋር በመስክ ሣር ያመነዥካል። ክርስቲያን መለኮታዊ ባሕርይ ስላለው (2ኛ ጴጥ. 1፡ 3-4)፥ ጌታን ከሚያስደስት ነገር ጋር ብቻ መተባበር አለበት።

«በማይመች አካሄድ አትጠመዱ» የሚለው አሳብ ከዘዳግም 22፡ 10 የተወሰደ ነው፤ «በሬንና አህያን በአንድ ቀንበር ጠምደህ አትረስ» (አዲስ ትርጉም)። ለአይሁዶች በሬ ንጹሕ እንስሳ ሲሆን፥ ዳሩ ግን አህያ ንጹሕ አልነበረም (ዘዳ. 14፡ 1-8)። ስለ ሆነም ሁለቱን በአንድ ላይ ማጣመዱ ትክክል አልነበረም። በተጨማሪም፥ ሁለቱም ሁለት የተለያዩ ባሕርያት ስላሉዋቸው፥ ለሥራውም ቢሆን የማይመች ነበር።

ሁለቱን ማጣመድ የጭካኔ ተግባር ይሆን ነበር። እንደዚሁም፥ የአማኞች ከማያምኑ ሰዎች ጋር መጠመድ ትክክል አይደለም።

እስቲ ጳውሎስ የተጠቀማቸውን ስያሜዎች ልብ ብለህ ተመልከት፡- ተካፋይነት፥ ኅብረት፥ መስማማት፥ ክፍል፥ መጋጠም። እነዚህ ቃላት ሁሉ የጋርዮሽን አሳብ ያንጸባርቃሉ። ስምምነት የሚለው ቃል የ«ዝማሬ»ን አሳብ ያዘለ ሲሆን፥ መዘምራን አንድን የዜማ ጽሑፍ እያነበቡና በአንድ መሪ እየተመሩ የሚያሰሙትን የግሩም ዝማሬ መዋጣት ያመለክታል። ዳሩ ግን እያንዳንዱ የመሣሪያ ተጫዋች የራሱን ዜማ በራሱ የአጨዋወት ዘይቤ ቢያቀርብ ምን ዓይነት ሁከት በተፈጠረ ነበር!

በእነዚህ ቃላት ውስጥ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያሉት መሻቶች ታይተዋል። እርስ በርሳችን ያለንን እንድንከፋፈል (ኅብረት) እና የክርስትናን ሕይወት በረከቶች በጋርዮሽ እንድንቋደስ ይፈልጋል። አብረን ስንሠራና ስንኖር ሳለ በአንድነትና በመስማማት ደስ እንድንሰኝ ይሻል። ይህ ሳይሆን ቀርቶ ግን በአንድ ጊዜ ከእግዚአብሔር እና ከዓለም ጋር ለመራመድ ከሞከርን፥ የተገኘውን መንፈሳዊ ኅብረት በማፍረስ መለያየትን እናመጣለን።

ጳውሎስ አማኞችና የማያምኑ ሰዎች በግልጽ እንደሚቃረኑ ይመለከታል፡- ጽድቅ -፥ ብርሃን - ጨለማ፥ ክርስቶስ - ቤልሆር (ሰይጣን)፥ እምነት - ክህደት፥ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ - የጣዖት መስገጃዎች። እነዚህን ተቃራኒ ነገሮች እንዴት ወደ አንድነት ለማምጣት ይቻላል? ክርስቲያን ካልተቀደሰው ነገር ይለይ ዘንድ ባሕርዩ ያስገድደዋል። አንድ በክርስቶስ አምኖ የዳነ ሰው (ሴት) በዚህ ልምምድ ውስጥ ያላለፈ የትዳር ጓደኛ በሚመርጥበት ጊዜ፥ የማይዘለቅ አቀበት ይፈጠራል፤ በንግድ ሽርኮችና በሃይማኖታዊ «አንድነቶች» መካከል የሚፈጠረውም አለመግባባት ከዚህ ያልተለየ ይሆናል።

በ2ኛ ቆሮንቶስ 6፡ 16 ውስጥ «እናንተ» የሚለው ቃል ብዙኃንን እንደሚወክል ልብ ማለት ያሻል። በዚህ ሥፍራ ጳውሎስ አጥቢያዪቱን ቤተ ክርስቲያን በጥቅል እያመለከተ እንጂ፥ እንደ 1ኛ ቆሮንቶስ 6፡ 19-21 አማኞችን በግል እየጠቀሰ አልነበረም። አማኞች የእግዚአብሔር ሕዝብ ስለ ሆኑ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር የመኖሪያ ሥፍራ ነች (ሕዝ. 37፡26-27፤ ዘሌ. 26፡12፤ ዘፀ.6፡7፤ 25፡8)። ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ምስክርነቷን መበረዝ ማለት ቅዱስ ቤተ መቅደስን ማርከስ እንደ ማለት ነው።

2. የመጽሐፍ ቅዱስ ትዕዛዝ (2ኛ ቆሮ. 6፡ 17)። የዚህ ጥቅስ አቢይ ክፍል የተወሰደው ከኢሳይያስ 52፡ 11 ሲሆን፥ ዳሩ ግን የሕዝቅኤል 20፡ 34፥ 41 ጥቅሶችም እንደ ገደል ማሚቴዎች በላዩ ላይ ያስገመግሙበታል። በኢሳይያስ ውስጥ የሚገኘው ማጣቀሻ የሚያመለክተው፥ ባቢሎንን ለቀው ወደ ገዛ አገራቸው የሚመለሱትን ምርኮኞች ሲሆን፥ ዳሩ ግን በመንፈሳዊ ተዛምዶነቱ የሚያመለክተው፥ ዛሬም ቢሆን የእግዚአብሔር ሕዝብ ከዓለም መለየት እንዳለበት ነው።

እግዚአብሔር ሕዝቡን «ውጡ» እያለ ያዛል፤ ይህም በበኩላቸው ሊወስዱት የሚገባቸውን ግልጽ እርምጃ ያመለክታል። «የተለያችሁ ሁኑ» የሚለው ለተለየ ዓላማ ለእግዚአብሔር መሰጠትን ያሳያል። መለየት አሉታዊ የመገንጠል ተግባር ብቻ ሳይሆን፥ አዎንታዊ ለእግዚአብሔር የመሰጠት ተግባርም ነው። ከኃጢአት ወደ እግዚአብሔር መለየት አለብን። «ርኩስንም አትንኩ» የሚለው ከርኩሰት እንድንርቅ የተሰጠን ማስጠንቀቂያ ነው። አንድ የብሉይ ኪዳን አይሁዳዊ አስከሬን ወይም የከፋ ቁስል ከነካ ይረከስ ነበር። በርግጥ ዛሬ በንኪኪ ምክንያት በክርስቲያኖች ላይ የሚደርስ ርኩሰት የለም፤ ዳሩ ግን መመሪያው ያው ነው፡- ምስክርነታችንን ሊያበላሽ ወይም ወዳለመታዘዝ ከሚመራን ነገር ጋር መተባበር የለብንም።

እግዚአብሔር እንድንለይለት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከዳር እስከ ዳር ያዘናል። እስራኤላውያን በከነዓን ምድር ከጣዖት አምላኪዎች ጋር እንዳይተባበሩ አስጠንቅቆአቸዋል (ዘኁል. 33፡ 50-56)፤ ዳሩ ግን በተደጋጋሚ ቃሉን ተላልፈው ለቅጣት ተዳርገዋል። ነቢያት ሕዝቡ ጣዖት ማምለካቸውን ትተው፥ ሙሉ ለሙሉ ራሳቸውን ለእግዚአብሔር እንዲሰጡ ይማጸኑዋቸው ነበር። በመጨረሻም፥ እግዚአብሔር እስራኤልን ለአሦራውያን፥ ይሁዳን ደግሞ ለባቢሎናውያን ምርኮ አሳልፎ መስጠት ግድ ሆኖበት ነበር። ጌታችን የፈሪሳውያንን የውሸት «መለየት» የተቃወመ ሲሆን፥ ዳሩ ግን ደቀ መዛሙርቱን ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን እርሾ (ሐሰተኛ ትምህርት) እንዲጠበቁ አስጠንቅቆአቸዋል። እንዲሁም ከዓለም ርኩሰት እንዲጠበቁም ጸልዮላቸዋል (ማቴ. 16፡6፥ 11፤ ዮሐ. 17፡ 14-17)።

ሐዋርያትም ለአብያተ ክርስቲያናት በጻፍአቸው ደብዳቤዎች ውስጥ የእምነት ትምህርትና በግል ሕይወት ንጽሕና ላይ ትኩረት አድርገዋል። አማኙ በዓለም ውስጥ ቢኖርም፥ ዳሩ ግን ዓለምን

ላለመምሰል መጠንቀቅ አለበት። እንዲሁም ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስና በሐዋርያት የተሰጠውን ትምህርት ከሚገፉ ሰዎች መለየት አለባት (ሮሜ 12፡1-2፤ 16፡17-20፤ ቆላ. 3፡1-2፤ 1ኛ ጢሞ. 6፡10-11፤ ቲቶ 2፡14፤ 1ኛ ጴጥ. 4፡3-6፤ 1ኛ ዮሐ. 4፡6)። በዮሐንስ ራእይ ውስጥ እንኳ፥ የእግዚአብሔር ሕዝብ ከሐሰተኛና የረከሰ ሕይወት ከሚመሩ ወገኖች ስለ መለየታቸው አስፈላጊነት ልዩ ትኩረት ተሰጥቶታል (ራእ. 2፡14-16፥ 20-24፤ 18 ከቁ. 4 ጀምሮ)።

እንዲህም ስለ ተባለ ደግሞ ለእምነት ትምህርትና ለግል ሕይወታችን ንጽሕና በሚኖረን መሻት ምክንያት፥ በዙርያችን የሚገኘውን ምስኪን ዓለም እስክንዘነጋ ድረስ ራስ-ወዳዶች መሆን የለብንም። ጌታችን «ቅዱስና ያለ ተንኰል፥ ነውርም የሌለበት፥ ከኃጢአተኞችም የተለየ» (ዕብ. 7፡26) ሲሆን፥ ዳሩ ግን «የቀራጮችና የኃጢአተኞች ወዳጅ» ነበር (ሉቃ. 7፡34)። እንደ ጥበበኛ ሐኪም፥ «በሽታው ሳይተላለፍብን መገናኘትን» መለማመድ አለብን። ይህማ ካልሆነ፥ አገልግሎታችን እጅግ ከሚያስፈልጋቸው ሰዎች ራሳችንን መነጠላችን ነው።

3. የእግዚአብሔር የበረከት ተስፋ (2ኛ ቆሮ. 6፡17-7፡1)። ኢየሱስ ክርስቶስን አዳኛችን አድርገን በምንቀበልበት ጊዜ፥ እግዚአብሔር አባታችን ይሆናል፤ ዳሩ ግን እስካልታዘዝነውና ከእርሱ ጋር ኅብረት እስካላደረግን ጊዜ ድረስ አባታችን ሊሆን አይችልም። እርሱ በፍቅር ሊቀበለንና እንደ ውድ ልጆቹ አድርጎ ሊንከባከበን ይናፍቃል። ደኅንነት ማለት የአብን ሕይወት መጋራታችን ሲሆን፥ ዳሩ ግን መለየት ማለት ደግሞ ሙሉ በሙሉ ወደ አብ ፍቅር ውስጥ ዘልቀን ገብተናል ማለት ነው። ኢየሱስ ይህን «የጠለቀ ፍቅር» እንደሚሰጠን በዮሐንስ 14፡21-23 ውስጥ ተስፋ ሰጥቶናል።

እግዚአብሔር ራሳቸውን ከኃጢአት ለእርሱ የሚለዩትን ሰዎች ይባርካቸዋል። አብርሃም ራሱን ከከለዳውያን ዑር ለየና እግዚአብሔርም ባረከው። ሆኖም አብርሃም የመለየቱን ነገር ችላ ብሎ ወደ ግብፅ በመሔዱ፥ እግዚአብሔር ጥፋቱን ማሳየት ነበረበት (ዘፍ. 11፡31-12፡20)። እስራኤላውያን በከነዓን ከሚገኙ ኃጢአተኛ ሕዝቦች እስከ ተለዩ ድረስ እግዚአብሔር ይባርካቸው ነበር፤ ዳሩ ግን ከጣዖታት ጋር መዳራት በሚጀምሩበት ጊዜ፥ የቅጣት አለንጋውን ማውረድ ነበረበት። ዕዝራና ነህምያ ሁለቱም የመለየትን ትርጉም ደግሞ

ማስተማር አስፈልጎአቸው ነበር (ዕዝ. 9-10፤ ነህ. 9፡2፤ 10፡28፤ 13፡1-9፥ 23-31)።

ከእግዚአብሔር የቸርነት የተስፋ ቃሎች የተነሣ፥ እኛም በበኩላችን ልናሟላቸው የሚገባ መንፈሳዊ ኃላፊነቶች አሉን (2ኛ ቆሮ. 7፡1)። ራሳችንን ከሚያረክሰን ከማንኛውም ነገር ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ማንጻት አለብን። እግዚአብሔር እንዲያነጻን መጠየቅ ብቻ በቂ አይደለም፤ ዳሩ ግን የራሳችንን ሕይወት ልናነጻና በቀላሉ ከኃጢአት አዘቅት ውስጥ እንድንወድቅ ከሚያደርጉን ነገሮች መለየት አለብን። ማንኛውም አማኝ ለሌላው አማኝ ውሳኔ ሊያስተላልፍ አይችልም፤ እያንዳንዱ የልቡንና የሕይወቱን ችግር ያውቃል።

ብዙውን ጊዜ ክርስቲያኖች የሚታገሉት ከተፈጠረው ችግር ምልክቶቹ ጋር እንጂ ከመነሻ ምክንያቶቹ ጋር አይደለም። የችግሩን ሥር ስላላገኘንና «ሕይወታችንን ስላላነጻን»፥ አንዱን ኃጢአት ደጋግመን ስንናዘዝ እንኖራለን። ምናልባት አሮጌውን ባሕርይ «የሚቀልብ» አንድ ተወዳጅ ኃጢአት ይኖርና «የሥጋችን እድፈት» ሊቀጥል ይችላል (ሮሜ 13፡14)፤ ወይም ደግሞ የኃጢአትን አመለካከት የተላበሰ፥ «መንፈሳዊ እድፈት» ሊኖርብን ይችላል። የጠፋው ልጅ የሥጋ ኃጢአቶች ቁራኛ ሲሆን፥ «ሥነ-ምግባራዊ» ብቃት የነበረው ታላቅ ወንድሙ ግን ለመንፈሳዊ ኃጢአቶች ሰለባ ነበር። ከአባቱ ጋር እንኳ ሊስማማ አልቻለም ነበር (ሉቃ. 15፡11-21 ተመልከት)።

ዳሩ ግን ራሳችንን ማንጻት የኃላፊነቱን ግማሽ አካል ከመወጣት የሚልቅ አይደለም - በተጨማሪም «በእግዚአብሔር ፍርሃት ቅድስናን ፍጹም» ማድረግ አለብን (2ኛ ቆሮ. 7፡1)። በጸጋና በእውቀት እያደግን ስንሄድ፥ ይህ የማያቋርጥ ሂደት ይሆናል (2ኛ ጴጥ. 3፡18)። ሚዛናዊነትን መጠበቅ መልካም ነው። ፈሪሳውያን ኃጢአትን ለማስወገድ ቢጓጉም፥ ዳሩ ግን ቅድስናን ፍጹም ለማድረግ አልተጉም ነበር። ይሁንና የታወቀ ኃጢአት በሕይወታችን ውስጥ ተቀምጦ እያለ፥ ቅድስናን ፍጹም ለማድረግ መጣር ሞኝነት ነው።

ጳውሎስ ለምስጋናና ለመለየት ልመና አቅርቧል። በተጨማሪም የቆሮንቶስን አማኞች ፍቅርና መሰጠት መልሶ ለማምጣት አንድ የመጨረሻ ልመናም አክሏል።

## የዕርቅ ልመና (2ኛ ቆሮ. 7፡2-16)

«ልባችሁን ክፈቱልን» (6፡13 - አዲስ ትርጉም)። «በልባችሁ ሥፍራ አስፉልን» (7፡2)። «በውኑ ሁለት ሰዎች ሳይስማሙ በአንድነት ይሄዳሉን?» (አሞ. 3፡3)። እግዚአብሔር የሚቀበላቸውና ደግሞ ከጳውሎስ ጋር ኅብረት ሊኖራቸው የሚችለው፥ የቆሮንቶስ አማኞች ሕይወታቸውንና የቤተ ክርስቲያን ኅብረታቸውን ሲያነጹ ብቻ ነበር።

በዚህ ክፍል ውስጥ አጽንኦት የተሰጠው፥ እንዲህ ያሉ ታላላቅ መከራዎችን በእስያና በጢሮአዳ ከተቀበለ በኋላ፥ እግዚአብሔር ጳውሎስን ባጽናናበት ሁኔታ ላይ ነው (1፡8-10፤ 2፡12-13 ተመልከት)። በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ሦስት የመጽናናት ሁኔታዎች ይገኛሉ።

1. ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያንን ያጽናናል (2ኛ ቆሮ. 7፡2-4)። ቤተ ክርስቲያኗ ቲቶን ስለ ተቀበለች፥ አሁን ጳውሎስን መቀበል ነበረባት (ቁ. 13)። ጳውሎስ እነርሱን ለመበደል ብሎ ያደረገው ምንም ነገር ስላልነበረ፥ እንዲተማመኑበት ይጠይቃቸዋል። ይህ በተለይም «ማጭበርበር» («መበዝበዝ» 11፡20 ተመልከት) በሚለው ቃል የሐሰት አስተማሪዎች እርሱን ለመወንጀል እንደ ተጠቀሙበት የሚያመለክት ነው። «ጳውሎስ ይህን የእርዳታ ስጦታ የሚሰበስበው፥ ራሱ ሊጠቀምበት ሲል ነው» ሲሉ ስሙን ያጠፉት ነበር።

ሰዎችን እንደምንወዳቸው በመግለጽ ስለ ፍቅራችን ማረጋገጥ አቀበት የሚሆንብን ለምንድነው? ጳውሎስ እነርሱን ለማሳመን ከዚህ የበለጠ ምን ሊያደርግ ይችል ነበር? እነርሱ ከልቡ ውስጥ ሥፍራ ተሰጥቶአቸው ስለ ተቀመጡ፥ ካስፈለገ ሊሞትላቸው እንኳ ይፈቅድ ነበር (3 ከቁ. 1 ጀምሮ፤ 6፡11-13 ተመልከት)። እርሱ ስለ እነርሱ መልካምነት በመመካት ለሌሎች «በልዩ አክብሮት» ይናገርላቸው እንጂ እነርሱ ግን የትችት ዶፍ እያወረዱበት ነበር።

ዳሩ ግን ከእነዚህ ችግሮች ባሻገር፥ የቲቶ ጉብኝት ስኬታማ ስለ ነበር፥ ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያኒቱን ለማጽናናት አመቺ መንገድ አግኝቶ ነበር፤ በመሆኑም አሁን «ያዘመመውን ቅጥር ለመጠገንና» ኅብረትን ለማደስ በር ተከፍቶ ነበር። ይህም ወደ ሁለተኛው መጽናናት ያሸጋግረናል።

2. ቲቶ ጳውሎስን ያጽናናዋል (2ኛ ቆር. 7፡5-10)። ጳውሎስ በመጀመሪያ የተጽናናው፥ ከረጅም ጊዜ መለያየት በኋላ ከቲቶ ጋር ግንኙነት ለማድረግ በመቻሉ ነበር። በዚያን ዘመን ራቅ ባለ አካባቢ ከሚኖር ሰው ጋር መገናኘት ወይም እንደ ልብ መጓጓዝ የዋዛ አልነበረምና፥ ጳውሎስ የቲቶን የቆሮንቶስ ጉብኝትም ሆነ የዕቅዶቹን ከዳር መድረስ በተመለከተ በእግዚአብሔር ፈቃድ ላይ መደገፍ ነበረበት። (ዘመናዊ መገናኛና መጓጓዣ ባለበት በአሁኑ ጊዜ ቢሆንም በእግዚአብሔር ፈቃድ ላይ መደገፍ አለብን።)

ዳሩ ግን ጳውሎስ ቲቶ በቆሮንቶስ የተደረገለትን አቀባበል ሲናገር ተጽናና። የጳውሎስን «አሳዛኝ ደብዳቤ» አንብበው ከኃጢአታቸው ንስሐ ገቡ፤ ችግሮቹን የቀሰቀሱትንም ምዕመናን ቀጡዋቸው።

ጳውሎስ ጠንካራ ደብዳቤ ጽፎ ነበርና በዚያ ምክንያት ተጸጽቶ ነበር። ይሁንና ደብዳቤው ግቡን ስለ መታና የቆሮንቶስ ሰዎች ንስሐ ስለ ገቡ፥ ጳውሎስ ደስ ተሰኘ። ንስሐቸውም እንዲያው አላፊ «ጸጸት» ብቻ ሳይሆን፥ ፈሪሃ-እግዚአብሔር ያደረበት ኃዘን ነበር። «እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ኃዘን ጸጸት የሌለበትን ወደ መዳንም የሚያደርሰውን ንስሐ ያደርጋልና፤ የዓለም ኃዘን ግን ሞትን ያመጣል» (7፡10)። የሐዘን የልዩነቱ ደረጃ በይሁዳና በጴጥሮስ ሕይወት ውስጥ ተስተውሏል። ይሁዳ በኃጢአቱ ተጸጸተና ራሱን ገደለ፤ ጴጥሮስ ግን ስለ ውድቀቱ አንብቶ ንስሐ ገባ (ማቴ. 26፡75-27፡5)።

ክርስቲያኖች ንስሐ መግባት ያስፈልጋቸዋል ወይ? ኢየሱስ እንደሚያስፈልገን ይናገራል (ሉቃ. 17፡3-4)፤ ጳውሎስም ከእርሱ ጋር ይስማማል (2ኛ ቆር. 12፡21)። በራእይ ምዕራፍ 2-3 ውስጥ ከተዘረዘሩት የትንሹ እስያ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ አራቱ ንስሐ እንዲገቡ ታዘዋል። ንስሐ መግባት ማለት «አእምሮን መለወጥ» ማለት ሲሆን፥ ባለመታዘዝ የሚመላለሱ ክርስቲያኖች ይህንኑ ማድረግ አለባቸው - ደኅንነትን ለማግኘት ሳይሆን፥ ከእግዚአብሔር ጋር ያደርጉት የነበረውን የቅርብ ግንኙነት ለማደስ።

3. የቆሮንቶስ አማኞች ቲቶን አጽናንተዋል (2ኛ ቆር. 7፡11-16)። የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም ትልቅ እርምጃዎችን ወሰዱ። በመጀመሪያ፥ ቲቶን አገኙትና ከእርሱ ጋር ባደረጉት አንድነት አጽናኑት (ቁ. 13)። ጳውሎስ ሲመካባቸው በነበረው ሁኔታ አሁንም

በመገኘታቸው፥ በዚህም የቲቶ ልብ በፍስሐ ተሞልቶ ነበር። በተጨማሪም ከጳውሎስ የተጻፈውን መልእክት ስላመኑበት፥ በዚያው መሠረት መንቀሳቀስ ያዙ።

በቁጥር 11፥ ጳውሎስ አሠራራቸውን ገልጾአል። «እነሆ፥ ይህ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ኃዘን እንዴት ያለ ትጋት፥ እንዴት ያለ መልስ፥ እንዴት ያለ ቁጣ፥ እንዴት ያለ ፍርሃት፥ እንዴት ያለ ናፍቆት፥ እንዴት ያለ ቅንዓት፥ እንዴት ያለ በቀል፥ በመካከላችሁ አደረገ። በዚህ ነገር ንጹሐን እንደ ሆናችሁ በሁሉ አስረድታችኋል።» ጳውሎስ ንስሐ የገቡበትንና ትክክል የሆነውን ነገር ለማድረግ ያሳዩትን አሳቢነትና ቅንዓት ከቲቶ ሲሰማ ልቡ ዐረፈ - ተጽናና። የጳውሎስ የደብዳቤው ዓላማ በደለኛውን ሰው ለመገሠጽና ለመርዳት ብቻ ሳይሆን፥ ዳሩ ግን ለቤተ ክርስቲያን ያለውን ፍቅር ለመግለጽ ጭምር መሆኑን ያረጋግጣል። ጳውሎስ ከዚህ ነገር የተነሣ ብዙ ተሰቃይቷል፤ ዳሩ ግን አሁን ችግሩ ስለ ተቃለለ ስቃዩ ዋጋ አላጣም ነበር።

እጅግ ከሚያጻግቱ ነገሮች አንዱ የሻከረን ግንኙነት መልሶ መገንባት ነው። ጳውሎስም በበኩሉ ይህንን ለማድረግ መሞከሩን በ2ኛ ቆሮንቶስ በተለይ በምዕራፍ 6 እና 7 ላይ እናያለን። ሆኖም የሚያሳዝነው ነገር፥ ዛሬም ቢሆን በርካታ ሻካራ ግንኙነቶች በቤት፥ በቤተ ክርስቲያን፥ ብሎም በአገልግሎት ውስጥ መታየታቸው ሲሆን ሊወገዱ የሚችሉት ደግሞ ሰዎች ችግሮችን በእውነተኛነት፥ በመጽሐፍ ቅዱስ እውነት በመመራትና በፍቅር ሲጋፈጡና ከእግዚአብሔር ጋር ለመስማማት ሲፈልጉ ነው።

እኔና አንተ የግል ሕይወታችንን ስንመረምር፥ የመፍትሔው እንጂ የችግሩ አካል እንዳንሆን መወሰን አለብን። እግዚአብሔር በተቃቃሩ ወገኖች መካከል ስምምነትን ለማስገኘት በእኛ እንዲጠቀምብን እስከ ፈለግን፥ አክብሮት ያለበትን አመስጋኝነትን ማሳየት መለየትን መለማመድና ዕርቅን ማበረታታት አለብን።

# የመስጠት ጸጋ - ክፍል 1

## 2 ቆሮንቶስ 8

ከጳውሎስ ሦስተኛ የሚሲዮናዊነት ጉዞ አበይት አገልግሎቶች አንዱ በይሁዳ ለሚኖሩ ድሀ ክርስቲያኖች ልዩ «የርዳታ ስጦታ» ማድረግ ነበር። ጳውሎስ ከዚህ በፊት አንድ ጊዜ የዚህ ዓይነት አገልግሎት ያበረከተ ሲሆን (የሐዋ. 11፡27-30)፥ አሁንም ተመሳሳይ ግልጋሎት ለመስጠት ደስተኛ ነበር። የተዘነጋውንና «ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብፁዕ ነው» (የሐዋ. 20፡35) የሚለውን የጌታችን ብፅዕና ያስታወሰው ጳውሎስ እንደ ነበር መረዳት አስፈላጊ ነው።

ይሁንና ድሆችን በገንዘብ ከመርዳትም በተጨማሪ በጳውሎስ አእምሮው ውስጥ የሚመላለሱ ሌሎችም በረከቶች ነበሩ። ከባሕር ማዶ ለሚገኙ የአይሁድ ማኅበራት የአሕዛብ አብያተ-ክርስቲያናት የሚያደርጉትን እርዳታ በማስታወስ፥ ይህ የቤተ ክርስቲያን አንድነት በበለጠ እንዲጠናከር ይፈልግ ነበር። ጳውሎስ አሕዛብ የአይሁድ «ባለ ዕዳዎች» እንደ ሆኑ አድርጎ ይመለከታል (ሮሜ 15፡25-28)፤ ልዩ የርዳታ አሰባሰቡም ያንኑ ዕዳ ለመክፈል አንድኛው መንገድ ነበር።

እንዲሁም ይህ ስጦታ ለአይሁድ አማኞች (አሁንም አንዳንዶቹ ለሕጉ ይቀኑ ነበር) ጳውሎስ እንደሚወራበት የአይሁዶች ወይም የሙሴ ጠላት እንዳልነበር የሚያረጋግጥ ማስረጃ ነበር (የሐዋ. 20 ከቁ. 17 ጀምሮ)። ጳውሎስ በአገልግሎቱ መጀመሪያ አካባቢ ድሆችን ለማሰብ ተስፋ የሰጠ ሲሆን (ገላ. 2፡6-10)፥ ያንኑ የተስፋ ቃል ለመጠበቅ በትጋት ይሠራ ነበር፤ ሆኖም ግን እግረ መንገዱንም የአይሁዶችን የቅናት መንፈስ ለመስበር በማሰብ ከአሕዛቦች የሚደረግላቸው እርዳታ እንዲጠናከር ያበረታታ ነበር።

የሚያሳዝነው፥ የቆሮንቶስ ሰዎች የበኩላቸውን ድርሻ እየተወጡ አልነበረም። እንደ ብዙዎቹ ሰዎች፥ የተስፋ ቃሎችን ቢሰጡም፥ ዳሩ ግን አልፈጸሙም ነበር። እንዲያውም፥ አንድ ዓመቱ በሙሉ በከንቱ ባክኗል (2ኛ ቆሮ.8፡10)። ለዚህ ምክንያቱ ምን ነበር? የቤተ ክርስቲያኗ በዝቅተኛ መንፈሳዊ ደረጃ ላይ መገኘቷ ነበር። ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ እስካልሆነች፥ በልግስና ልትሰጥ አትችልም። ሌላው ምክንያት ደግሞ

የሚችሉትን ያህል ገንዘብ ከቤተ ክርስቲያን ሳይዘርፉ ያልቀሩት የአይሁድ ሃይማኖት አስፋፊዎች ወረራ ነበር (11፡7-12፥ 20፤ 12፡14)።

ጳውሎስ ክርስቲያኖችን ለዚህ የልግስና ስጦታ ተካፋይ ማድረጉ ቀላል እንደማይሆን ስለ ተረዳ፥ ልመናውን ወደ ከፍተኛ መንፈሳዊ ደረጃ ያሳድገዋል፡- መስጠት የጸጋ ተግባር እንደ ሆነ ያስተምራቸዋል። ጳውሎስ ስጦታውን ለማመልከት በዘጠኝ የተለያዩ ቃላት ቢጠቀምም፥ ዳሩ ግን ከሁሉም በላይ የተገለገለበት «ጸጋ» በሚባለው ቃል ነበር። መስጠት በመሠረቱ ሌሎችን የሚረዳ አገልግሎትና ኅብረትን የሚያሳይ (8፡4) ቢሆንም፥ ዳሩ ግን የመመንጫው ምክንያት በልብ ውስጥ ያለው የእግዚአብሔር ጸጋ ሊሆን ይገባል። ጳውሎስ ይህ የርዳታ አሰባሰብ የአሕዛቦች ዕዳ መቅረፊያና (ሮሜ 15፡27) የክርስቲያናዊ ሕይወታቸው ፍሬ (ሮሜ 15፡27) ፍሬ እንደ ሆነ ቢያውቅም በሌላ በኩል ደግሞ ከዚህም የላቀ ምክንያት እንደ ነበረው ተረድቶ ነበር፤ ከሁሉም በላይ የእግዚአብሔር ጸጋ በሰው ልብ ውስጥ የመሥራቱ ውጤት መሆኑን ያምንበት ነበር።

ስለዚህ ክርስቲያኖች ከልብ መስጠት ከመቀበል ይልቅ የተባረከ መሆኑን አምነው፥ ወደ መስጠት ጸጋ በሚገቡበት ጊዜ አስደናቂ ነገር ይሆናል። ጥያቄው ግን «በጸጋ መስጠትን» እየተለማመድን መሆኑን እንዴት ልናውቅ እንችላለን? የሚለው ነው። ጳውሎስ ስጦታችን በጸጋ የተነቃቃ ለመሆኑ ማስረጃ የሚሆኑ ምልክቶች እንዳሉ አመልክቷል።

## በሁኔታዎች ሳንገደብ ስንሰጥ (2ኛ ቆሮ. 8፡1-2)

ጳውሎስ በምሳሌነት የጠቀሳቸው የመቄዶንያ አብያተ ክርስትያናት፥ የራሳቸው የሆኑ ከፍተኛ ችግሮች ቢኖሩባቸውም፥ ዳሩ ግን በልግስና ለመስጠት ወደ ኋላ አላሉም ነበር። «በብዙ መከራ ተፈትነው» (ቁ. 2) ነበር እንጂ፥ እንዲሁ በ«መከራ» ውስጥ ብቻ ያለፉ አልነበሩም። በከፍተኛ ድህነት ማለትም «በመናጢነት» ደረጃ ላይ ነበሩ። በዚህ ሥፍራ የተጠቀሰው ቃል ምንም ነገር የሌለውንና ለወደፊትም ምንም ነገር የማግኘት ተስፋው የመነመነን ለማኝ የሚገልጽ ነው። ይህ አስቸጋሪ ሁኔታቸው የመነጨው ምናልባትም ክርስቲያን በመሆናቸው የተነሣ፥ ከሥራቸው በመፈናቀላቸው ወይም ከጣዖት አምልኮ ጋር ለመተባበር ባለመፈለጋቸውና ከንግድ ማኅበራት በመገለላቸው ምክንያት ሊሆን ይችላል።

ይሁንና የነበሩባቸው ሁኔታዎች ከመስጠት አላቀቡዋቸውም ነበር። እንዲያም፥ በደስታና በልግስና ሰጡ። ማንኛውም ኮምፒውተር ይህንን የሚከተለውን አስደናቂ ስሌት ሊገነዘብ አይችልም፡- ትልቅ መከራና ጥልቅ ድህነት ሲደመር ጸጋ ለ ብዙ ደስታና ብዙ ልግስና! ይህም በጳውሎስ አገልግሎት ውስጥ የነበረውን የተቃራኒ ነገሮች ዝርዝር ያስታውሰናል፡- «ድሆች ስንሆን ብዙዎችን ባለጠጎች እናደርጋለን» (6:10)። በተጨማሪም የመገናኛው ድንኳን (ዘጸ. 35:5-6) እና ቤተ መቅደሱ (1ኛ ዜና 29:6-9) በተሠሩ ጊዜ የተሰጡትን የልግስና ስጦታዎች ያስታውሰናል።

አንተም የእግዚአብሔርን ጸጋ በሕይወትህ ውስጥ እስከ ተለማመድህ ድረስ ለሌሎች ለመስጠት አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ማመካኛ አድርገህ አትጠቀምባቸውም። ለነገሩማ እንዲያውስ ሁኔታዎች የመስጠት አገልግሎታችንን ያበረታቱበት ወቅት ጨርሶ ይኖር ይሆን? በመጀመሪያው የመጋቢነት አገልግሎቴ ወቅት፥ አዲስ ቤተ ክርስቲያን ማነጽ በጣም ያስፈልገን ነበር፤ ዳሩ ግን አንዳንድ ሰዎች «ከኢኮኖሚው ሁኔታ» የተነሣ ተቃወሙት። በዚያን ወቅት የብረትና የሌሎችም ፋብሪካዎች ሥራቸውን በአድማ ለማቆም የተነሣሡበት ነበር። በተጨማሪም የባቡር ሐዲዶችና የነዳጅ ማደያዎችም ችግር ፈጥረው ነበር ...ስለሆነም ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ የማይቻል ይመስል ነበር። ዳሩ ግን «በጸጋ መስጠት»ን የሚያምኑ በቂ ሰዎች ስለ ነበሩ፥ ቤተ ክርስቲያኗ አዲስ ሕንፃ ለማሠራት ቻለች - ያንን ሁሉ የኢኮኖሚ ችግር በመወጣት! በጸጋ መስጠት ማለት በሁኔታዎች ሳይገደቡ መስጠት ማለት ነው።

## በፍላጎት ስንሰጥ (2ኛ ቆሮ. 8:3-4)

በልግስና መስጠትና ደግሞም ያለ ፍላጎት መስጠት፥ ሁለቱም ይቻላሉ። አንድ ቆንቋና ምዕመን፥ «ሰባኪው እስኪጎዳኝ ድረስ መስጠት እንዳለብኝ ይናገራል፤ ለእኔ ግን፥ ስለ መስጠት ማሰቡ ራሱ ይጎዳኛል» እስከ ማለት መድረሱ ይነገራል። የመቄዶንያ አብያተ ክርስቲያናት፥ እንደ ቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን መቀስቀስ ወይም ማስታወስ አላስፈለጋቸውም። እንዲያውም ከሚሰባሰበው ገንዘብ ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ ለማዋጣት ፈቃደኞች ነበሩ። ይህም ዕድል እንዲሰጣቸው እስከ መማጸን ደርሰዋል። ለመሆኑ አንድ ክርስቲያን ስጦታውን ሌላው እንዲቀበለው እስከ መለመን የደረሰበት ሁኔታ ስንት ጊዜ አጋጥሞህ ይሆን?

ስጦታቸው ፈቃደኝነትና ግብታዊነት የሚታይበት ነበር። የጸጋ እንጂ፥ ከመገደድ የተነሣ የተፈጸመ አልነበረም። ለልግስናው የተሽቀዳደሙት የእግዚአብሔርን ጸጋ ስለ ተለማመዱና ለመስጠት ስለፈለጉ ነበር። ጸጋ ከኃጢአት ማንጻት ብቻ ሳይሆን፥ ከራሳችንም ያነጻናል። የእግዚአብሔር ጸጋ ልብህንና እጅህን ይፈታዋል። የምትሰጠውም በቀዝቃዛ የሂሳብ ስሌት ተመርተህ ሳይሆን፥ ዳሩ ግን ከሙቅ ልብ በሚመነጭ ሐሤት ነው።

## እንደ ኢየሱስ ስንሰጥ (2ኛ ቆሮ. 8፡5-9)

በአገልግሎትም ይሁን በመከራ፥ ወይም ራስን በመሠዋት ሁሉ አማኙ ሊከተለው የሚገባው ከሁሉም የላቀውን የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌነት ነው። የኢየሱስ ክርስቶስን ፈለግ በመከተል የመቄዶንያ ክርስቶያኖችም ራሳቸውን ለእግዚአብሔርና ለሌሎች አሳልፈው ሰጥተዋል (ቁ. 5)። ራሳችንን ለእግዚአብሔር ከሰጠን፥ ንብረታችንን ለእግዚአብሔር መስጠቱ ብዙም አይከብደንም። እንዲሁም ራሳችንን ለእግዚአብሔር ከሰጠን፥ ለሌሎችም ደግሞ ራሳችንን እንሰጣለን። እግዚአብሔርን እየወደዱ የባልንጀራችንን ችግር ችላ ማለት የማይቻል ነገር ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን ለእኛ ሲል ሰጥቶአል (ገላ. 1፡4፤ 2፡20)። እኛስ ራሳችንን ለእርሱ መስጠት የለብንም? የሞተልን ለራሳችን ሳይሆን፥ ዳሩ ግን ለእርሱና ለሌሎች እንኖር ዘንድ ነው (2ኛ ቆሮ. 5፡15)።

የመቄዶናውያን ስጦታ፥ ልክ እንደ ክርስቶስ በፍቅር አነሣሽነት የተከናወነ ነበር (8፡7-8)። ይህ በመንፈሳዊ በረከቶች ለበለጸጉት የቆሮንቶስ ሰዎች ምንኛ ተግሣጽ ነበር (1ኛ ቆሮ. 8፡4-5)። እነርሱ ግን በመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ዙሪያቸውን ታጥረው ስለ ነበር፥ የመንፈስ ቅዱስን የጸጋ ስጦታዎችንም ሆነ በጸጋ ተነሣሥተው መለገስን ዘንግተው ነበር። የመቄዶንያ አብያተ - ክርስቲያናት «ጥልቅ ድህነት» (2ኛ ቆሮ. 8፡2) ደርሶባቸው ሳለ፥ ዳሩ ግን አብዝተው ሊሰጡ ችለዋል። የቆሮንቶስ ሰዎች ግን በርካታ መንፈሳዊ ስጦታዎች ቢኖሯቸውም፥ ዳሩ ግን ተስፋ የሰጡትን ቃል ለመጠበቅና በሚሰበሰበው ገንዘብ ውስጥ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ለማበርከት ግድ የለሾች ነበሩ።

የመንፈሳዊ ስጦታዎችን አገልግሎት በልግስና ለማከናወን የመስጠት ተግባር ምትክ ሊሆን ይችላል ብለን ልንከራከር አይገባም። «በሰንበት ትምህርት ቤት ውስጥ ስለማስተምር፥ መስጠት አያስፈልገኝም» የሚለው ማመካኛ እንጂ፥ አጥጋቢ የማሳመኛ ነጥብ

አይደለም። ስጦታዎቹ በእርግጥም ስጦታዎች እንደ ሆኑ የሚያስብ ክርስቲያን ምን ጊዜም የሚነሣው ለሌሎች ለመስጠት እንጂ በጌታ አገልግሎት ሽፋን «ልደበቅ» አይልም። እኔንም ቢሆን፥ አንዳንድ ሙሉ ጊዜያቸውን ለጌታ አገልግሎት በማዋላቸው፥ ለመስጠት እንደማይገደዱ በመግለጽ የተከራከሩኝ መጋቢዎችና ሚሲዮናውያን አጋጥመውኛል። ጳውሎስ ከዚህ የሚቃረን አሳብ ነበረው:- ከእግዚአብሔር ዘንድ ግሩም ስጦታ ስለ ተሰጣችሁ፥ አብልጣችሁ ለመስጠት መሻት አለባችሁ።

ከዚህም ሌላ ጳውሎስ እንዲሰጡ ያዘዛቸው ራሱ እንዳልሆነ በግልጽ እንዲያውቁት ይጠነቀቅ ነበር። እንዲያውም የቆሮንቶስን ሰዎች አመለካከትና ከመቄዶንያ ሰዎች ጋር እያነጻጸረ ነበር። የመቄዶንያ ክርስቲያኖች የጌታን ምሳሌ እየተከተሉ መሆናቸውን በግልጽ መሰከረ:- ድሆች ሆነው ሳሉ ሰጡ። ከዚህም በመነሣት የቆሮንቶስ ሰዎች ጳውሎስን እንደሚወዱት ይናገሩ ስለ ነበር፥ በሚሰበሰበው ገንዘብ ውስጥ ተካፋይ በመሆን ፍቅራቸውን እንዲያረጋግጡለት ይጠይቃቸዋል። በጸጋ መስጠት የፍቅርን መኖር የሚያረጋግጥ ነው - ለክርስቶስ፥ ላገለገሉ የእግዚአብሔር ባሪያዎችና እኛ ልናቃልላቸው የምንችለው ልዩ ችግር ላለባቸው ሰዎች ያለንን ፍቅር የምናሳይበት ነው።

በመጨረሻም፥ ስጦታቸው እንደ መሥዋዕትነት የሚቆጠር ነበር (ቁ. 9)። ኢየሱስ ባለጸጋ የሆነው በምን መንገዶች ነበር? በመሠረቱ ዘላለማዊ አምላክ እንደ መሆኑ፥ በስብዕናው ባለጸጋ ነበር። የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ እንደ መሆኑ፥ ባሉት ነገሮችና ባለው ሥልጣን ባለጸጋ ነበር። ማንኛውንም ነገር ለማድረግ ስለሚችል፥ በኃያሉ ባለጸጋ ነበር። ይሁንና እነዚህም ሆኑ ሌሎችም አያሌ ብልጽግናዎች እያሉት ድሀ ሆነ።

የአንቀጹ የጊዜ አመልካች እንደሚያሳየው፥ በዚህ ሥፍራ ድህነት የተባለው ሥጋ መልበሱ፥ በቤተልሔም መወለዱ ነው። ራሱን ወደ ሰው ደረጃ ዝቅ አደረገና ሰብዓዊ ባሕርይ ተላበሰ። ባሪያ ለመሆን ዙፋኑን ለቆ መጣ። ያለውን ነገር ሁሉ ወደ ጎን ስለ ተወ፥ ራሱን የሚያስጠጋበት ስፍራ እንኳ አልነበረውም። ከሁሉም በላቀው ጉስቁልና ውስጥ ያለፈው፥ ስለ እኛ በመስቀል ላይ እንደ ኃጢአተኛ በተቆጠረ ጊዜ ነበር። ገሃነመ እሳት ዘላለማዊ የድህነትና የጉስቁልና ስፍራ በመሆኑ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የድሆች ሁሉ ድሀ ሆነ።

ለምን ይህን አደረገ? እኛ እንበለጽግ ዘንድ ነው! ይህም ኢየሱስ ክርስቶስን ከማግኘታችን በፊት ድሆችና ሙሉ ለሙሉ ጎስቋሎች እንደ ነበርን ያመለክታል። ይሁንና አሁን በእርሱ ስላመንን፥ የብልጽግናዎቹ ሁሉ ተካፋዮች ሆነናል! አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ከሆንን፥ «የእግዚአብሔር ወራሾች ነን፤ ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች ነን» (ሮሜ 8፡17)። ይህ እውነት ሆኖ ሳለ፥ እንዴት ለሌሎች ከመስጠት እንቆጠባለን? እኛን ለማበልጸግ እርሱ ድሀ ሆነ። ሲበዛ ድሀና ጎስቋላ ቢሆኑ፥ የመቄዶንያ አብያተ ክርስቲያናት የእርሱን ፈለግ በመከተል አብዝተው እንደ ሰጡ፥ እኛስ ምሳሌነቱን ልንከተል አንችልም ይሆን?

## በፈቃደኝነት ስንሰጥ (2ኛ ቆሮ. 8፡10-12)

ቃል ኪዳን በመግባትና የተገባውን ቃል ከተግባር ላይ በማዋል መካከል ትልቅ ልዩነት አለ። የቆሮንቶስ ሰዎች ከአንድ ዓመት በፊት በልዩው የርዳታ አሰባሰብ ውስጥ የበኩላቸውን ድርሻ እንደሚያበረክቱ ለቲቶ በትምክህት ተናግረው፤ ዳሩ ግን ቃላቸውን አላከበሩም ነበር (ቁ. 6)። ጳውሎስ ከቁጥር 10-12 በፈቃደኛነት ላይ ትኩረት እንዳደረገ ልብ በል። በጸጋ የመስጠት ተግባር ከልብ መመንጨት አለበት እንጂ፥ በግድ ወይም በጉልበት የሚከናወን አይደለም።

በአገልግሎት ላይ ባሳለፍኋቸው ዓመታት ውስጥ ብዙ ልመናዎች ታግሼአለሁ። ለማመን ስለሚያዳግቱ የድህነት ታሪኮች አሳዛኝ ገጽታም ሰምቻለሁ። ገንዘቤን እንዳካፍል ሁኔታዎችን ለማመቻቸት በቀረቡልኝ የተለመዱ የማታለያ ዘዴዎችም ለመሳቅ ተገድጃለሁ። ተግሣጽ፥ አሳፋሪ ሁኔታና ዛቻም ሳይቀር ተሰንዝሮብኛል፤ ዳሩ ግን ከእነዚህ ዘዴዎች አንዳቸውም ከዕቅዱ በላይ እንድሰጥ አላነሣሡኝም። እንዲያውም፥ የገንዘብ ፈላጊዎቹ ዓለማዊ አቀራረብ ስላሳዘነኝ፥ ከዕቅዱ በታች የሰጠሁባቸው ጊዜያትም ነበሩ። (ዳሩ ግን ከተንዛዛ የልመና ተግባር የተነሣ፥ በመበሳጨቱ፥ ለመስጠት ያቀደውን መከልከል ብቻ ሳይሆን፥ ከሙዳይ ምፅዋቱ ገንዘብ ቀምቶ መውሰዱን እንደ ተናገረው ማርክ ትዌይን ዓይነት የሚያስገርም አላደረግሁም!)

መፍቀድና ማድረግ ጎን ለጎን የሚሄዱ ስለ ሆኑ፥ እዚህ ላይ መደናገር የለብንም። ለመስጠት ያለው ፈቃደኝነት እውነተኛና በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ የሚገኝ ከሆነ፥ «በተግባር መገለጹ» የማይቀር ነው (ቁ. 11፤ ፊልጵ. 2፡12-13)። ጳውሎስ ፈቃደኛነት የማድረግ ምትክ ነው በማለት አልተናገረም፤ አይደለምም። ዳሩ ግን

ስጦታችን በጸጋ የተነሣሣ ከሆነ፥ ስለ ተገደድን ሳይሆን፥ በፈቃዳችን እንሰጣለን።

እግዚአብሔር የሚመለከተው «የልብን ስጦታ» እንጂ «የእጅን ስጦታ» አይደለም። ልብ ብዙ ለመስጠት ቢፈልግና ዳሩ ግን ይህንኑ ለማድረግ ባይችል፥ እግዚአብሔር ሁኔታውን ተመልክቶ በዚያው መሠረት ይመዘግባል። ዳሩ ግን እጅ ልብ ሊሰጥ ከሚፈልገው በላይ ቢሰጥ፥ እጅ የሰጠው ገንዘብ ምንም ያህል ቢበዛ፥ እግዚአብሔር የሚመዘግበው በልብ ውስጥ የተቀመጠውን ነው።

አንድ ወዳጇ ለሥራ ወደ ሌላ አገር ሊሄድ ተነሥቶ ነበርና ወደ ቤተ ክርስቲያን ከመሄዳቸው በፊት ባለቤቱ ለቤት ወጪ የተወሰነ ተጨማሪ ገንዘብ እንደምትፈልግ አስታወሰችው። እርሱም ልክ መባው ሊሰበሰብ ሲል፥ የተወሰነ ገንዘብ ከእጇ ላይ ጣል አደረገ፤ እርሷም የሰጣት ለሳምንታዊው የመባ አስተዋፅኦ ስለ መሰላት፥ በመባ መሰብሰቢያው ሙዳይ ውስጥ ጨመረችው። ዳሩ ግን ያ ገንዘብ ለሳምንቱ የሰጣት የቤት ወጪ ነበር።

ወዳጇም «የሰጠነው ለጌታ ነውና እርሱም መዝግቦ ያቆየዋል» አለ።

መጋቢያቸው ግን፥ «ምን ያህል ለመስጠት ወስናችሁ ነበር» ሲል ጠየቀ። ቁጥሩን ነገረው።

መጋቢውም «እንግዲህ እግዚአብሔር የመዘገበው ይህንኑ ይሆናል፤ የልባችሁን መሻት አይቶአልና» በማለት መለሰ።

እግዚአብሔር የሚመለከተው የምንሰጠውን ሳይሆን፥ የምንሰጠውን መጠን ነው። ከለገስነው በላይ ልንሰጥ የምንችል ብንሆንና ዳሩ ግን ባናደርገው፥ እግዚአብሔር ያንን ያያል። የበለጠ ለመስጠት ፈልገን ባይሞላልን ደግሞ ያንኑ ይመለከታል። ባለን አቅም በፈቃደኝነት ስንሰጥ፥ በጸጋ መስጠትን እየተለማመድን ነው ማለት ነው።

## በእምነት ስንሰጥ (2ኛ ቆሮ. 8፡ 13-24)

ጳውሎስ ድሀው ይበለጽግ ዘንድ ሀብታሙ እንዲደኸይ እየተናገረ አልነበረም። አንድ ክርስቲያን የሌላውን ሰው ዕዳ ለመክፈል ብሎ ለራሱ በዕዳ ውስጥ ቢዘፈቅ ይኼ አዋቂነት አይሆንም - የገባበትን ዕዳ መልሶ ለመክፈል እስካልቻለ ድረስ ስህተት ፈጽሟል። ጳውሎስ በሂደቱ ሁሉ ውስጥ «ሚዛናዊነትን» ይሻል፡- አሕዛብ በአይሁዶች አማካይነት በመንፈሳዊ ሀብት ስለ በለጸጉ፥ አይሁዶችም በተራቸው በቁሳዊ ነገሮች በአሕዛብ መበልጸግ ነበረባቸው (ሮሜ 15፡25-28 ተመልከት)።

በተጨማሪም፥ በወቅቱ በይሁዳ የሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት በጭቆና ቀንበር ሥር ወድቀው ሳለ፥ የአሕዛብ አብያተ ክርስቲያናት ግን በቁሳዊ ሀብት በልጽገው ነበር። ያ ሁኔታ አንድ ቀን ሊለወጥ ይችል ነበር። የአይሁድ አማኞች አሕዛብን የሚረዱበት አንድ ወቅት ወደ ፊት ሊከሰት ይችላል።

ዳሩ ግን ይህን ሁኔታ የሚያስተካክለው ማነው? እግዚአብሔር ነው! ይህን ለማብራራት ጳውሎስ የመናን ተአምርና መመሪያ በመጥቀስ በምሳሌነቱ ተጠቅሞበታል (ዘጸ. 16፡18)። አይሁዶች በየዕለቱ የቱንም ያህል መና ቢሰበስቡም፥ ዳሩ ግን ለሁሉም የሚያስፈልጋቸውን ያህል ያገኙ ነበር። መናውን ለማከማቸት የሚሞክሩ ሰዎች ቢኖሩ እንኳን ይህን ለማድረግ እንደማይቻል ተረድተው ነበር። መናው አንድ ቀን ካደረ ይበሰብስና ይሸት ነበር (ዘጸ. 16፡20)። ትምህርቱ ግልጽ ነው፡- የሚያስፈልግህን ያህል ሰብስብ፤ የሚችሉትን ያካፍሉ፤ የእግዚአብሔርን በረከቶች ለማከማቸት አይሞክሩ። እግዚአብሔር እርሱን ከተማመኑና ቃሉን ከጠበቅህ፥ በችግር ውስጥ እንዳትወድቅ ይጠነቀቅልሃል።

ለመስጠት የሚያነሣሣን በሕይወታችን ውስጥ ያለው የእግዚአብሔር መንፈሳዊ በረከት ሲሆን፥ ዳሩ ግን ለመስጠት መለኪያ የሚሆነን የእግዚአብሔር ቁሳዊ በረከት ነው። ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው በመጀመሪያ ደብዳቤው፥ «ከእናንተ እያንዳንዱ በየሳምንቱ በፊተኛው ቀን እንደ ቀናው መጠን እያስቀረ በቤቱ ያስቀምጥ» (1ኛ ቆሮ. 16፡2) በማለት አሳቡን በግልጽ አካፍሏቸዋል። በጸጋ የመስጠቱ ተግባር በአሥራት (ከ10 እጅ አንድ እጅ) ስለማይወሰን፥ ጳውሎስ ምንም የሒሳብ ስሌት መመሪያ ለማስቀመጥ አልሞከረም። በጸጋ መስጠት እንዴት እንደምንሰጥ የምንወስነው እንጂ በሕግ መልክ የሚደነገግ አይደለም። በጸጋ መስጠት እንችላለን ብለን በሕሊናችን በምናስላው የገንዘብ መጠን ምን ጊዜም አይረካም።

«የገቢያችንንና ወጪያችንን ሚዛናዊነት» የሚጠብቀው እግዚአብሔር ስለ ሆነ፥ ጳውሎስን ከኮሚኒዝም ጋር የተመሳሰለ ትምህርት ስለ ማስተማሩ አንወቅሰውም። እንዲያውም፥ 2ኛ ቆሮንቶስ 8፡13 ኮሚኒዝምን በቀጥታ የሚቃወም ክፍል ነው። «ኮሚኒዝም» የሚባለው የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ሁኔታ (የሐዋ. 2፡44-47፤ 4፡32-37) ዛሬ ከሚታወቀው ኮሚኒስታዊ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ዘይቤ ጋር ምንም ዝምድና የለውም። የጥንቱ ክርስቲያኖች (እንደ ዛሬዎቹ

በርካታ ክርስቲያኖች) የነበራቸውን ነገር በፈቃዳቸው ለሌሎች አካፈሉ እንጂ፥ ሰዎች በዚህ ተግባር ላይ እንዲሳተፉ አላስገደዱዋቸውም። ዕቅዱም ራሱ ጊዜያዊ ነበር፤ ጳውሎስ በወቅቱ ችግር ላይ የነበሩትን ክርስቲያኖች ሁኔታ ለማሻሻል የተለየ የርዳታ ገንዘብ አሰባስቦ የመውሰዱ እውነታ፥ ዕቅዱ በኋለኞቹ የክርስቲያን ትውልዶች እንዲዘወተር ታስቦ እንዳልተደረገ የሚያረጋግጥ ነው።

በጸጋ መስጠት የእምነት ጉዳይ ነው:- የሌሎችን ጉድለት በምናሟላበት ጊዜ እግዚአብሔር የእኛንም ጉድለት እንደሚያሟላልን እናምናለን - እንታዘዘዋለንም። አይሁዶች በየቀኑ መና ይሰበስቡ እንደነበር እኛም «የዕለት እንጀራችንን» እንዲሰጠን በእግዚአብሔር ላይ መደገፍ አለብን (ማቴ. 6፡11)። እግዚአብሔር የሚሰጠንን ነገር ማባከንም ሆነ ማከማቸት የለብንም። በእግዚአብሔር ፈቃድ መቆጠቡ ትክክል ነው። (አይሁዶች ዓርብ ዕለት የወረደውን መና ለሰንበት ዕለት (ቅዳሜ) ይቆጥቡ ነበር፤ መናውም አይበሰብስም ነበር [ዘጸ. 16፡22-26]።) ዳሩ ግን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ ሆነን የምናከማቸው ሀብት ይጎዳን እንደሆን እንጂ አይጠቅመንም (ያዕ. 5፡1-6 ተመልከት)።

ጳውሎስ ከቁ. 16 ጀምሮ፥ ዋንኛውን መንፈሳዊ መመሪያ መስጠቱን በመግታት፥ ልዩ መዋጮው ስለሚሰበሰብበት ሁኔታ አንዳንድ ተግባራዊ ምክሮችን ወደ መስጠቱ ይመለሳል። በጸጋ መስጠት በእምነት መስጠት መሆኑ እውነት ሆኖ ሳለ፥ በጸጋ መስጠት በዘፈቀደ መስጠት እንዳለሆነም እውነት ነው። ለሌሎች የሚያካፍለው ክርስቲያን፥ የሚሰጠው ነገር በታማኝነት መከናወኑን ማረጋገጥ አለበት።

እኔም ለዓመታት ያህል ምዕመናን ታማኝ ለሆኑት የእግዚአብሔር አገልጋዮች ድጋፍ እንዲያደርጉ ለማበረታታት ሞክሬአለሁ። በዚያው መጠን ታማኝነት ለሚጎድላቸው ድርጅቶች ምዕመናን እርዳታ እንዳያደርጉ አስጠንቅቄአለሁ። ዳሩ ግን ማስጠንቀቂያዬን ችላ ብለው የሰጡት አንዳንዶቹ፥ ከጥቂት ወራት በኋላ ወደ እኔ መጥተው፥ «ለዚያ ድርጅት ቼክ ልኬ ነበርና አሁን ግን መታለሌን ተረድቻለሁ» ይሉኛል። እኔም ተከዝ ብዬ፥ «እንዳታደርጉት አስጠንቅቄአችሁ ነበር» እላለሁ።

«እንግዲህ፥ ጌታ ልቤን ያውቀዋል፤ ገንዘቡ ቢባክንም ቅሉ፥ ትርፌን በመንግሥተ ሰማይ አገኘዋለሁ» ሲሉ ይከራከሩኛል።

በጸጋ መስጠት ማለት በሞኝነት መስጠት ማለት አይደለም። በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንኳ፥ የመዋዕለ-ንዋይ ጉዳይ የሚያከናውኑ ሰዎች የተወሰኑ ብቃቶች ቢኖሯቸው መልካም ነው። ጳውሎስ የ«ሃይማኖታዊ ሌብነት»ን ዝና ስላልፈለገ፥ ከእጁ የገባውን የአደራ ገንዘብ በጥንቃቄ ስለሚይዝበት ሁኔታ በብርቱ ይጨነቅበት ነበር። በመሆኑም በሚሰበሰበው መዋጮ ውስጥ አስተዋጽኦ ያደረጉ አብያተ ክርስቲያናት የተወሰኑ ወኪሎች ከእርሱ ጋር እንዲሄዱ ያስመርጥ ስለ ነበር፥ ሁሉም ነገር በታማኝነት፥ በአግባብና በሥርዓት ይፈጸም ነበር።

በመጋቢነት ባገለገልሁበት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሚገኙ የሰንበት ትምህርት ክፍሎች በአንድኛው፥ አንድ ወጣት ምጽዋቱን ሲሰበስብ፥ ሲቆጥር፥ ብሎም አሁንም ራሱ ሲመዘግብና ከዚያም ወደ ሰንበት ትምህርት ቤት ቢሮ ሲወስድ ታዝቤአለሁ። በመሆኑም ለማስፈራራት ብዬ ሳይሆን፥ አንድ ሰው የከሰሰው እንደ ሆነ አደገኛ ሁኔታ እንደሚደርስበት ገለጽሁለት፡- ገንዘቡን በታማኝነት ስለ ማስረከቡ ሊያረጋግጥ የሚችልበት መንገድ ወይም ምስክር የለውምና! እኔም «በበኩሌ አምንሃለሁ፤ ዳሩ ግን ሊከታተሉህና የትችት ቀዳዳ ሊያገኙብህ የሚሹትን ሰዎች አላምናቸውም» አልሁት። ሰውየው አሳቤን ተቀብሎ በመጠቀም ፈንታ፥ በጣም ተቆጣና ቤተ ክርስቲያኒቱን ጥሎ ሄደ።

በየትኛውም መንፈሳዊ ዘርፍ - አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን፥ የሚሲዮን ድርጅት፥ የወንጌላውያን ስብሰባ ውስጥ የሚገኙ ወንድሞችና እህቶች፥ የእግዚአብሔርን ገንዘብ የሚይዙ ከሆነ፥ የሚከተሉት ባሕርያት ሊኖሯቸው ይገባል።

1. ከእግዚአብሔር የተሰጠ የማገልገል መሻት (2ኛ ቆሮ. 8፡16-17)። ጳውሎስ ቲቶን አላዘዘውም፤ ወጣቱ በልዩ መዋጮው ውስጥ የማገልገል መሻት በልቡ ውስጥ አድሮ ነበር። ሆኖም ግን ብዙውን ጊዜ በአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ እንደሚታየው፥ በዚህ መስመር ጌታን የማገልገል እውነተኛ መሻት የሌላቸው ሰዎች በመዋዕለ-ንዋይ ኮሚቴ ውስጥ ይሰየማሉ። ከሁሉም በላይ፥ የጌታን ገንዘብ የሚይዝ ሰው ከእግዚአብሔር አሳብ ጋር የሚስማማ ልብ ሊኖረው ይገባል።

2. ለጠፉት ነፍሳት የሚሰማው ሸክም (2ኛ ቆሮ. 8፡18)። ይህ ወንድም ማን እንደ ነበር ባናውቅም፥ ዳሩ ግን ወንጌሉን የማጋራት ምስክርነት ስለ ነበረው እግዚአብሔርን እናመሰግናለን። ወንጌላዊ ሳይሆን ባለመቅረቱም፥ ቢያንስ በአብያተ ክርስቲያን አካባቢ፥ ነፍሳትን

ለማዳን ሸክም የሚሰማው በመሆኑ የሚታወቅ ነው። ዳሩ ግን በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዕጩዎችን የሚመርጡ ኮሚቴዎች «ነፍሳት በመማረኩ» ረገድ መልካም ተስጥኦ ያላቸውን ሰዎች፥ በወንጌል አገልግሎት ኮሚቴ ወይም በሚሲዮን ኮሚቴ ውስጥ ያስቀምጣሉ፤ እርግጥ ይህም ቢሆን ተገቢ ነው። ሆኖም ከእነዚህ መካከል አንዳንዶቹ በመዋዕለ-ንዋይ ኮሚቴ ወይም በንብረት ተቆጣጣሪ ቦርድ ውስጥ መግባት አለባቸው። ለምን? ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮች ለማቃናት! ነፍሳትን ለመማረክ አገልግሎት የሚውል ወጪ ለመመደብ በጅ የማይሉ ኮሚቴዎች፥ ለሕንፃዎች ግንባታና ለቁሳቁስ መግዣ ከፍተኛ አኀዝ ያዘለ ገንዘብ ሲመድቡ ተመልክቻለሁ።

አንድ ዕለት አንድ ተስፋ የቆረጠ ወጣት መጋቢ ምክር ጠይቆኝ ነበር። «የመዋዕለ-ንዋይ ኮሚቴአችን ለመወሰን ድፍረት በማጣቱ እያሳሰበኝ ነው። የኢኮኖሚ ሁኔታ ማናቸውንም ወጪ ለመመደብ እጃቸውን አሥሮታል። ጨርሶ ገንዘብ አይደማቸውም - በባንክ ቤት ደግሞ ብዙ ትርፍ ገንዘብ አለን» በማለት አጫወተኝ። ከዚህ ኮሚቴ ጋር ተገናኝቼ ባላውቅም፥ ይሁን እንጂ ስለ እነዚህ ሰዎች አንድ ነገር ለመረዳት ችያለሁ። የኃጢአተኞችን ሰዎች ሸክም የመጋፋት ስሜት ሊኖራቸው ይገባል።

3. እግዚአብሔርን ለማስከበር መሻት (2ኛ ቆሮ. 8፡ 19)። ብዙውን ጊዜ የመዋዕለ-ንዋይ ዘገባዎች ቤተ ክርስቲያንን፥ ወይም የተለዩ የርዳታ ሰጪ ቡድኖችን እንጂ፥ እግዚአብሔርን አያስከብሩም። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሥራ ዘርፍ ውስጥ «ለዓለማዊና ለተቀደሰ» ተግባር ወይም «ለንግድና ለአገልግሎት» የሚባል ክፍፍል የለም። የምናደርገው ነገር ሁሉ ለጌታ «የተቀደሰ ሥራ» እና አገልግሎት ብቻ ነው። አንድ የቤተ ክርስቲያን መተዳደሪያ ደንብ፥ ዲያቆናት (ወይም ሽማግሌዎች) «መንፈሳዊ ጉዳዮችን እንደሚይዙ» እና ንብረት ክፍሎች ደግሞ «ቁሳዊና የመዋዕለ-ንዋይ ጉዳዮችን እንደሚያከናውኑ» በሚናገርበት ጊዜ፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የሌለውን ገደብ ማበጀቱ ነው። ቤተ ክርስቲያን ልታደርግ የምትችለው ከሁሉም የላቀው ነገር በጥበብ ገንዘቧን ለመንፈሳዊ አገልግሎት ማዋል ነው።

እግዚአብሔር የሚሰጠንን ነገር እርሱ በሚፈልገው መንገድ በመጠቀም እናከብረዋለን። የቤተ ክርስቲያንን መዋዕለ-ንዋይ የሚቆጣጠሩ ሰዎች እግዚአብሔርን የማስከበር ተጨማሪ ሸክም

እስከሌላቸው፥ ብዙም ሳይቆይ ገንዘቡን የእግዚአብሔርን ስም በሚያሰድብ መንገድ መጠቀሚያ ሊያደርጉት ይጀምራሉ።

4. በታማኝነት መልካምን ስም ማግኘት (2ኛ ቆሮ. 8፡20-22)። ጳውሎስ ከአብያተ-ክርስቲያናት የተወከሉትን ሰዎች በደስታ እንደ ተቀበለ ገልጾአል። ምንም ዓይነት ነቀፋ እንዲሰነዘርበት አልፈለገም ነበር። «ጌታ እኛ የምንሠራውን ይመለከታል!» ማለቱ ብቻ በቂ አይደለም። ሰዎች የምንሠራውን ነገር ለማየት እንደሚችሉ መረዳት አለብን። ጄ. ቢ. ፊልጵስ ቁጥር 21ን በጥሩ ሁኔታ ተርጉመውታል፡- «በመዋጮው ክፍፍል ውስጥ ምንም ዓይነት ትችት እንዲነሣ አንፈልግም፤ እንዲሁም በእግዚአብሔር ፊት ብቻ ሳይሆን፥ በሰዎች ፊት ጭምር ሙሉ ለሙሉ ከነቀፋ ነጻ ለመሆን እንሻለን።»

በበኩሌ መልካም ስም ካለው ኮሚቴ ወይም ቦርድ፥ ወይም ድርጅት ጋር በሆነ መንገድ ኅብረት የማያደርገውን ክርስቲያን አገልጋይ ወይም ሚሲዮናዊ አልደግፍም። እንዲሁም የሒሳብ መዝገቡ ተመርምሮ ለረጂዎቹ ዘገባ የማይቀርብበትንም አገልግሎት አልደግፍም። ይህን ስል በግል የሚሠሩ ክርስቲያን አገልጋዮች ሁሉ ታማኞች አይደሉም ማለቴ ሳይሆን፥ ዳሩ ግን የመዋዕለ-ንዋይ ድጋፋቸውን ከሚቆጣጠር ቦርድ ወይም ድርጅት ጋር ኅብረት ቢያደርጉ የበለጠ በአገልግሎታቸው ላይ መተማመን ይኖረኛል ማለቴ ነው።

በቁጥር 22 ላይ ትጋትን አስመልክቶ የተሰጠውን አጽንኦት አስተውል። መዋዕለ-ንዋይን ለመያዝ የሚያስፈልግ አንድ ነገር ቢኖር፥ ትጋት ነው። የገቢና ወጪን ወቅታዊ ዘገባዎች በትክክል ስለማያቀርቡትና «ምንም ጊዜ እንደ ሌላቸው» በማመካኘት፥ ዓመታዊ ዘገባዎችን በግድየለሽነት ስለሚያከናውኑ የቤተ ክርስቲያን ገንዘብ ያዦች ብዙ ጊዜ ሰምቻለሁ። እንግዲህ በዚያ ክፍል ውስጥ ባይሠሩ ምንኛ መልካም ነበር!

5. ተባባሪ መንፈስ (2ኛ ቆሮ. 8፡23-24)። ቲቶ ለዚህ አገልግሎት ልቡን መስጠት ብቻ ሳይሆን (ቁ. 16)፥ እንዴት መልካም «የቡድን አባል» መሆን እንደሚቻልም ያውቅ ነበር። ጳውሎስ ቲቶን «አብሮኝ የሚሠራ» በማለት ይጠራዋል። ቲቶ፥ ገና በመጀመሪያው ስብሰባ ላይ፥ «በዚህ ኮሚቴ ውስጥ እስካለሁ ድረስ፥ በሙሉ ድምፅ ድጋፍ የሚተላለፍ ውሳኔ አይኖርም» ሲል እንደሰማሁት የኮሚቴ አባል አልነበረም።

የመዋዕለ-ንዋይ ኮሚቴ አባላት የገንዘቡ ባለቤቶች አይደሉም፡-ገዘነቡ የጌታ ነው። ኮሚቴው ገንዘቡን በታማኝነትና በጥንቃቄ ለጌታ አገልግሎት ከማዋል የበለጠ ኃላፊነት የለውም። እንዲሁም ጳውሎስ ኮሚቴውን የአብያተ ክርስቲያናት ልዩ አገልጋዮች አድርጎ እንደ ተመለከተ ልብ በል። ይህ የተለየ «የርዳታ ገንዘብ» የአሕዛብ አብያት-ክርስቲያናት በመተባበር ለሚያከናውኑት ተግባር የሚውል እንጂ፥ ጳውሎስና ተወካዮቹ የአብያተ ክርስቲያናት «መልእክተኞች» ከመሆን ውጪ፥ ውሳኔ የሚሰጡ አልነበሩም። «ለተለየ ተልዕኮ የተላከ - ሐዋርያ» የሚለውን ቃል የሚተካልን የግሪኩ ቃል «አፖስቶሎስ» የሚል ነው። እነዚህ ራሳቸውን የሰጡ ክርስቲያኖች፥ ለአብያተ ክርስቲያናት ሥራቸውን በታማኝነትና በስኬታማነት ማከናወንን ግዴታቸው መሆኑን አምነው ተቀብለውት ነበር።

በጸጋ መስጠት ደስ የሚያሰኝ ልምምድ ነው። «በእምነት አማካኝነት በጸጋ» መስጠትን ስትለማመድ (ልክ በዳኑበት መንገድ - ኤፌ. 2፡8-9)፥ ከነገሮችና ከሁኔታዎች በሚያስደንቅ ሁኔታ ነጻ መውጣት ትጀምራለህ። ለነባራዊ ሁኔታዎች ተገዢ በመሆን ፈንታ፥ አዳዲስ እሴቶችንና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች ወዲያውኑ የመፈጸም ልምድ ታዳብራለህ። ከእንግዲህም ሕይወትን ወይም ሌሎች ሰዎችን በገንዘብ ወይም በንብረት ላይ ተመሥርተው አትለካም። ገንዘብ ከሁሉም የሚልቀው የስኬታማነት መለኪያ ቢሆን ኖሮ፥ ኢየሱስ ድሀ ስለ ነበር፥ ከውዳቂዎች በተቆጠረ ነበር!

በጸጋ መስጠት ሌሎችን የማበልጸጉን ያህል አንተንም ያበለጽጋል። በጸጋ መስጠት ይበልጥ ኢየሱስ ክርስቶስን እንድትመስል ያደርግሃል። በጸጋ የመስጠትን ደስታ ተረድተኸው ይሆን?

# የመስጠት ጸጋ - ክፍል 2

## 2ኛ ቆሮንቶስ 9

እኛ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር አብዝቶ ከሰጠን በኋላ፥ ለሌሎች ለመስጠት የሚገፋፋን ሌላ ሰው መፈለጋችን ግራ የሚያጋባ ነገር ነው። እግዚአብሔር የቆሮንቶስን ሰዎች በድንቅ ሁኔታ ቢያበለጽጋቸውም፥ ዳሩ ግን ያላቸውን ነገር ለሌሎች ለማካፈል ያመነቱ ነበር። በጸጋ መስጠትን አልተለማመዱም ነበርና ጳውሎስ ይህንኑ አሳብ ለእነርሱ ማብራራት ነበረበት። ጳውሎስ በጸጋ መስጠትን ከገለጸላቸው በኋላ፥ በልዩ መዋጮው ውስጥ አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ሊያነሣሣቸው ይሞክራል። ይህንንም ያደረገው በጸጋ ከመስጠት ጋር የተያያዙትን አምስት ማበረታቻዎች (መጽናኛዎች) በማቅረብ ነው።

### ያንተ መስጠት ሌሎችንም ያነሣሣቸዋል (2ኛ ቆሮ. 9፡ 1-5)

ክርስቲያኖች ለክርስቶስ በምናቀርበው አገልግሎት እርስ በርስ መወዳደር ባይኖርብንም፥ ጳውሎስ «ለፍቅርና ለመልካም ሥራ እንድንነቃቃ እርስ በርሳችን እንተያይ» (ዕብ. 10፡24) እንዳለው ልንፈጽም ይገባል። እግዚአብሔር በሌሎች አማኞች ውስጥና በእነርሱም በኩል የሚሠራውን ነገር ስንመለከት፥ እኛም በበለጠ ለማገልገል መጣጣር አለብን። በሥጋዊ አድራጎት ኩረጃና በመንፈሳዊ ሕይወት ቅጂ መካከል እስከዚያ ልዩነት እንደሌለ ልንገነዘብና በዚህም በኩል ጥንቃቄ ልናደርግ ይገባል። በመሆኑም ቀናተኛ ክርሲትያን ቤተ ክርስቲያንን ለማነቃቃትና ምዕመኑንም ለጸሎት፥ ለሥራ፥ ለምስክርነትና ለስጦታ ለማነሣሣት መሣሪያ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል።

የሚያስገርመው ነገር ግን የሚከተለው ነው፡- ጳውሎስ የመቄዶንያን አብያተ ክርስቲያናት ለማበረታታት በቆሮንቶስ ሰዎች ቅንዓት ተጠቅሞ ነበር፤ ግን አሁን ደግሞ የቆሮንቶስን ሰዎች ለማበረታታት በመቄዶንያ ሰዎች ይጠቀማል። ከአንድ ዓመት በፊት፥ የቆሮንቶስ ሰዎች በመዋጮው ውስጥ ተካፋይ እንደሚሆኑ በከፍተኛ ፍላጎት ገልጠውለት ነበር፤ ከዚያ በኋላ ግን ምንም አላደረጉም ነበር። የመቄዶንያ ሰዎች ደግሞ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ አበርክተው ነበርና

ጳውሎስ ስለ ቆሮንቶስ ሰዎች የተናገረው ትምክህት ከንቱ እንዳይሆንበት ሠጋ።

ስለ ሆነም የቆሮንቶስ ሰዎች በመዋጮው አሰባሰብ ውስጥ የድርሻቸውን እንዲወጡ ያነቃቃቸው ዘንድ፥ ጳውሎስ ቲቶንና ሌሎች ወንድሞችን ወደ ቆሮንቶስ ላከ። ከገንዘቡ ይልቅ አጅግ የሚልቀው፥ በሕይወታቸው ውስጥ ላለው የእግዚአብሔር ጸጋ ምላሽ በመስጠት ያላቸውን በሚያካፍሉበት ጊዜ ቤተ ክርስቲያኗ የምታገኘው መንፈሳዊ በረከት ነበር። ጳውሎስ አስተዋጽኦውን ስለሚያሰባስቡበት ሁኔታ ለቤተ ክርስቲያኒቱ አስቀድሞ ስለ ጻፈ (1ኛ ቆሮ. 16፡ 1-4)፥ ለመዘግየታቸው የሚያመካኙበት ነገር አልነበራቸውም። ጳውሎስ ባለቀ ሰዓት ላይ ተሰብስበው ችግር የሚፈጥሩ መዋጮዎች እንዳይኖሩ ሲል፥ እርሱና «የመዋዕለ-ንዋይ ኮሚቴው» በሚደርሱበት ጊዜ ሁሉም ነገር ተሰናድቶ እንዲጠብቀው ይፈልግ ነበር።

ጳውሎስ ለማስወገድ የፈለገው ነገር ምን ነበር? የፈለገው መዋጮው ካልተሰናዳ በራሱና በቤተ ክርስቲያን ላይ የሚደርሰውን ኀፍረት ለማስወገድ ነበር። በይበልጥም ኀፍረቱ ያሳሰበው ከመቄዶንያ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ተውክለው ከልዩ ኮሚቴው ጋር የሚሄዱ በርካታ ሰዎች በመኖራቸውም ጭምር ነበር (የሐዋ. 20፡ 4 ተመልከት)። ጳውሎስ ስለ ቆሮንቶስ ሰዎች ለመቄዶናውያን ተናግሮ ስለ ነበር የነገራቸው ነገር ከንቱ ሆኖ እንዳይቀር በእርግጥም ፍርሐት ገብቶት ነበር።

ጳውሎስ ሰዎች ለመስጠት ቃል እንዲገቡ መጠየቅን፥ ስህተት ወይም መንፈሳዊነት የጎደለው ተግባር አድርጎ ያልተመለከተ ይመስላል። እያንዳንዳቸው ምን ያህል መስጠት እንደሚገባቸው አልተናገራቸውም፤ ዳሩ ግን የተስፋ ቃላቸውን መፈጸማቸውን ይጠብቅ ነበር። አንድ ሰው ለቤቱ ስልክ ሲያስገባ፥ በየወሩ የተወሰነ ገንዘብ ለመክፈል ቃል ይገባል። እንደ ስልክ፥ መኪናና የዱቤ መውሰጃ መዝገብ ለመሳሰሉ ነገሮች ገንዘብ ለመስጠት ቃል መግባቱ ተቀባይነት ካለው፥ ለጌታም ሥራ ቃል የምንገባው ቅሬታ የሚያሳድርበት ምክንያት አይኖርም።

ጳውሎስ ስለ መዋጮው ሲጽፍ ምን እንዳለ ተመልከት። ይህ «ለቅዱሳን የሚሆን አገልግሎት» ነበር። እንዲሁም ደግሞ ስጦታው «በረከት» (2ኛ ቆሮ. 9፡5) ማለትም «የልግስና ስጦታ» ነበር። ምናልባት ጳውሎስ የቆሮንቶስ ሰዎች ካቀዱት በላይ እንዲሰጡ እየገፋፋቸው ይሆን?

ጳውሎስ ምንም ዓይነት ጫና ላለማሳደር ይጠነቀቅ ነበር። ጳውሎስ ስጦታቸው «እንደ በረከት (ልግስና) ሆኖ ከስስት (ከውጥረት) ነጻ» እንዲሆን ይፈልግ ነበር። ከፍተኛ ጫና የታከለባቸው የስጦታ ልመናዎች በጸጋ ከመስጠት ጎን ሊሰለፉ አይችሉም።

ለመስጠት ከሁሉም በላይ የሚያበረታታን ነገር ስጦታችን ጌታን የሚያስደስት መሆኑ ነው፤ ይሁንና ሌሎችን ለመስጠት የሚያነሣሣ ዓይነት የስጦታ ልምምድ ማድረጉም ስህተት አይደለም። እንዲህም ስለ ተባለ በግል የምንሰጠውን ነገር እንደማስታወቂያ ለሁሉም ማወጅ አለብን ማለት አይደለም - ይኸውም የዚህ ዓይነቱ መስጠት ከመስጠት መሠረታዊ መመሪያዎች አንደኛውን ስለሚያፋልስ ነው (ማቴ. 6፡1-4)። ይሁንና ጳውሎስ የሚጽፈው ለአብያተ ክርስቲያናት ስለ ሆነ፥ ማኅበረ - ምዕመናን የሰጡትን ነገር ቢያሳውቁ ስህተት አይሆንም። ዓላማችን ያደረግነውን ለሌሎች በመግለጽ ለመመካት ከሆነ፥ በጸጋ የመስጠትን ልምምድ እያደረግን አይደለም። ዳሩ ግን መሻታችን ሌሎችም ያላቸውን እንዲያካፍሉ ለማነሣሣት ከሆነ፥ የእግዚአብሔር ጸጋ ሌሎችን ለመርዳት በእኛ በኩል ሊሠራ ይችላል።

## ያንተ መስጠት ለራስህ በረከት ይሆናል (2ኛ ቆሮ. 9፡6-11)

የጌታችን የተስፋ ቃል «ስጡ፤ ይሰጣችሁማል» የሚል ነበርና ይህ ቃል አሁንም በእውነትነቱ ጸንቶ ያለ ነው (ሉቃ. 6፡38)። መልሶ የሚሰጥበትም «መልካም መስፈሪያ» ሁልጊዜም ገንዘብ ወይም ቁሳዊ ነገር የተመለከተ ባይሆንም፥ ዳሩ ግን ሁልጊዜም እኛ ከሰጠነው አብልጦ የሚልቅ ነው። መስጠት የእኛነታችን ማረጋገጫ እንጂ፥ እኛ የምናደርገው ነገር አይደለም። የእግዚአብሔርን ጸጋ ለሚገነዘብ ክርስቲያን፥ መስጠት የሕይወት ዘይቤ ነው። ዓለም እንደ ምሳሌ 11፡24 የመሳሰለውን አሳብ አትረዳም፡- «ያለውን የሚበትን ሰው አለ፤ ይጨመርለታልም፤ ያለ ቅጥ የሚነፍግ ሰውም አለ፤ ይደኸያልም።» በጸጋ በምንሰጥበት ጊዜ ዓላማችን «አንድን ነገር ማግኘት» አይደለም፤ ዳሩ ግን የእግዚአብሔርን በረከት ማግኘት «እናገኛለን» ብለን የማናስበው ምርቃት ነው።

መስጠታችን እንዲባርከንና እንዲያንጸን ከተፈለገ፥ ጳውሎስ በዚህ ክፍል ውስጥ የገለጻቸውን መመሪያዎች ለመከተል ልንጠነቀቅ ይገባል።

1. የዕድገት መመሪያ - የምንዘራውን ያህል እናጭዳለን (2ኛ ቆሮ. 9፡6)። ይህ መመሪያ በዕለታዊ ሕይወታችን ውስጥ የሚንጸባረቅ ስለ ሆነ፥ በመጠኑ ማብራራት አስፈላጊ ነው። ብዙ ዘር የሚዘራ ገበሬ

ብዙ ምርት ለመሰብሰብ የሰፋ ዕድል ይኖረዋል። በባንክ ውስጥ ከፍተኛ ገንዘብ ያስቀመጠ ባለ ሀብት፥ ብዙ ወለድ ያገኛል። በጌታ ሥራ ውስጥም ብዙ ትርፋማ ተግባር ባከናወንን መጠን፥ በመዝገባችን ውስጥ የበለጠ «ፍሬ» ይገኛል (ፊል. 4፡ 10-20)

ይህን መመሪያ ለመዘንጋት በምንፈተንበት ጊዜ ሁሉ፥ እግዚአብሔር በስጦታው ቁጥብ እንዳለሆነ ልናስታውስ ይገባል። «ለገዛ ልጁ ያልራራለት፥ ነገር ግን ስለ ሁላችን አሳልፎ የሰጠው፥ ያው ከእርሱ ጋር ደግሞ ሁሉን ነገር እንዲያው እንዴት አይሰጠንም?» (ሮሜ 8፡32)። በተፈጥሮም ይሁን በጸጋ፥ እግዚአብሔር ለጋስ ሰጪ ነው፤ እንዲሁም ፈሪሃ-እግዚአብሔር የነገሠበትን ሕይወት ለመምራት የሚፈልግ ሰው መለኮታዊውን ምሳሌ መከተል አለበት።

2. የመሻት መመሪያ - በትክክለኛ ልብ እንደ ዘራን እንዲሁ እናጭዳለን (2ኛ ቆሮ. 9፡7)። ለአንድ ገበሬ ግብርናውን ለማካሄያድ ልዩ የሆኑ አነሣሽ ምክንያቶች እምብዛም ፋይዳ አይኖራቸውም። ጥሩ የዘር እህል ካለውና በጥሩ ወቅት ላይ ከዘራ፥ ለትርፍም ይሁን ለብልጽግና፥ ወይም ለኩራት ቢሠራ፥ ዞሮ ዞሮ ፍሬ ማግኘቱ አይቀርም። ከምርቱ የሚያገኘውን ገንዘብ ለመጠቀም የሚያቅድበትም ሁኔታ በምርቱ ላይ ልዩነት አይፈጥርም። እንደ ዘመኑ ሁኔታ ምድሪቱ ያፈራችለትን ሰብል ይሰበስባል።

ዳሩ ግን ለክርስቲያን ነገሩ እንዲህ አይደለም - በመስጠት (ወይም በሌላ በማንኛውም እንቅስቃሴ) ውስጥ፥ አነሣሹ ምክንያት «ዓላማው፥ መንስኤው) ወሳኝ ነው። የምንሰጠው ከልባችን መሆን አለበት፤ ከልባችን ውስጥ ያለው አነሣሽ ምክንያት ደግሞ እግዚአብሔርን ሊያስደስተው ይገባል። የልብ ፈቃደኛነት ሳይታከል «በኃዘኔታ እንደሚሰጡ» ወይም «በእብደት ያላቸውን እንደሚበትኑ» ሰዎች መሆን የለብንም፤ ዳሩ ግን የእግዚአብሔርን ጸጋ ስለ ተለማመድን፥ ያለንን በደስታ የምናካፍል «ደስተኛ ሰጪዎች» መሆን አለብን። እንዲህ ያለው «ርኅሩኅ የተባረከ ይሆናል» (ምሳ. 22፡9)።

በደስታ መስጠት አቀበት ከሆነብን፥ ልባችንን ወደ አምላካችን እንሥተን፥ ጸጋውን እንዲሰጠን መጠየቅ አለብን። በርግጥ እግዚአብሔር በኃላፊነት ስሜት የተሰጠውን ስጦታ ሊባርክ ይችላል፤ ዳሩ ግን ልቡ እስካልተስተካከለ ድረስ፥ ሰጪውን ሊባርክ አይችልም። በጸጋ መስጠት ማለት እግዚአብሔር ስጦታውንም ሰጪውንም ይባርከዋል ማለት ነው - ሰጪውም ለሌሎች በረከት ይሆናል።

3. የፈጣን ውጤታማነት መመሪያ - እየዘራን ሳለ እንኳ ልናጭድ እንችላለን (2ኛ ቆሮ. 9፡8-11)። ገበሬ የመከሩን ጊዜ መጠባበቅ አለበት፤ ዳሩ ግን በጸጋ መስጠትን የሚለማመድ አማኝ ወዲያውኑ መከሩን መሰብሰብ ይጀምራል። ከስጦታችን የሚገኙ የረዥም ጊዜ ጥቅሞች ቢኖሩም፥ ዳሩ ግን ወዲያውኑ የሚከሰቱ በረከቶችም አሉ።

አስቀድሞ እግዚአብሔር ከሚያበዛልን ጸጋው መካፈልን እንጀምራለን (ቁ. 8-9)። በዚህ ጥቅስ መሠረቱ «ሁሉም» የቃሉ አጠቃቀም ሁላችንም ከምናስተውለው በላይ ነው፤ በጸጋ ሁሉ፥ ሁልጊዜ፥ ብቃትን ሁሉ፥ ለበጎ ሥራ ሁሉ ይላል። ይህም ማለት እግዚአብሔር ሁሉንም ክርስቲያን በቁሳዊ ነገሮች ያበለጽገዋል ማለት ሳይሆን፥ ዳሩ ግን በጸጋ መስጠትን የሚለማመድ ክርስቲያን ሁልጊዜም በሚያስፈልገው ጊዜ ሁሉ የሚያስፈልገው ነገር ይኖረዋል ማለት ነው። በተጨማሪም፥ የእግዚአብሔር ጸጋ በግብረ-ገባዊና በመንፈሳዊ ሁኔታው ስለሚያበለጽገው፥ በክርስቲያናዊ ባሕርዩ ያድጋል። በአካሄዱና በሥራው ሁሉ፥ ሙሉ ለሙሉ በእግዚአብሔር ብቃት ላይ ይደገፋል።

በዛሬው ጊዜ ምን ያህል ሰዎች ለመንፈሳዊ ጽናታቸው በሌሎች ሰዎች ላይ ሙሉ በሙሉ እንደሚደገፉ ማየት ከማስደነቅም የሚያሳዝን ነገር ነው። ሰባኪዎቹ የሚሰብኩትን ትምህርት ከመጽሐፍ ወይም ከካሴት እስካልተዋሱ ድረስ የሚያስተላልፉት ስብከት አይኖራቸውም። እንዲሁም የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ምክር ፍለጋ ለሁለት ወይም ለሦስት እውቅ ሰባኪዎች እስካልደወሉ ድረስ፥ ችግራቸውን እንዴት እንደሚፈቱት አያውቁም። እጅግ ብዙ የቤተ ክርስቲያን አባላት በሳምንት ቢያንስ አንድ ጊዜ ከመጋቢያቸው ምክር መጠየቅ ያስፈልጋቸዋል - አለበለዚያ ግን መንፈሳዊ ውድቀት ይደርስባቸዋል።

ብቃት የሚለው ቃል «ከውስጥ የሚገኘውን በቂ ሀብት» የሚያመለክት ነው (ፊልጵ. 4፡11 ተመልከት)። በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት፥ ለሕይወት የሚያስፈልጉንን ነገሮች ለማሟላት የሚበቃ ሀብት አለን። ክርስቲያኖች እንደ መሆናችን፥ እርስ በርሳችን መረዳዳትና መበረታታት አለብን፤ ዳሩ ግን አንዳችን በሌላችን ላይ መደገፍ (ጥገኛ መሆን) የለብንም። ጥገኛነታችን በጌታችን ላይ መሆን አለበት። ለሕይወት ብቁ የሚያደርገንን ያንን «የውኃ ምንጭ» ከልባችን ሊያመነጭ የሚችለው እርሱ ብቻ ነው (ዮሐ. 4፡14)።

የእግዚአብሔር ጸጋ መጋራት ብቻ ሳይሆን፥ ዳሩ ግን ጽድቁንም ደግሞ እንካፈላለን (2ኛ ቆሮ. 9፡9)። ጳውሎስ አሳቡን ለማረጋገጥ

መዝሙር (112)፡9ን ይጠቅሳል። መዝሙሩ ልቡ ለጌታ እውነተኛና ታዛዥ በመሆኑ ምክንያት ሥጋት ስለሌለበት ሰው ይናገራል። ጽድቅን የማግኛ ብቸኛው መንገድ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንደ መሆኑ፥ ጳውሎስ በመስጠታችን ጽድቅን እናገኛለን አላለም። ይሁንና ልባችን ቅን ከሆነ፥ እግዚአብሔር ባሕርያችንን ለማቅናት በመስጠታችን ይጠቀማል። በጸጋ መስጠት ክርስቲያናዊ ባሕርይን ያንጻል።

የምንዘራውን ያንኑ ስለምናጭድ፥ ለምንሰጠውና ለምናደርገው ነገር የእግዚአብሔርን የተአምራት ብዛት እንጋራለን (2ኛ ቆሮ. 9፡10)። ገበሬው ምን ያህል ዘር ለምግብነት እንደሚያውልና ምን ያህሉን እንደሚዘራ መወሰን አለበት። ምርቱ ከቀነሰ፥ ለምግብነትም ሆነ ለቀጣዩ የአዝመራ ወቅት የሚኖረው እህል አናሳ ይሆናል። ዳሩ ግን በጸጋ በመስጠት የሚያምን ክርስቲያን፥ ስለዚህ ውሳኔ ከቶውንም መጨነቅ የለበትም - እግዚአብሔር የሚያስፈልገውን ሁሉ ይሞላለታል። ሁልጊዜም ለምግብነት የሚውል መንፈሳዊና ቁሳዊ «እንጀራ» አለ፤ ሁልጊዜም ለመዝራት የሚያገለግል መንፈሳዊና ቁሳዊ «ዘር» አለ።

ጳውሎስ በዚህ ስፍራ፥ የእግዚአብሔርን ቃልና የእርሻውን መስከ የመከር ፍሬ ለማመልከት «ዘር» እና «እንጀራ» የሚሉትን ቃላት የሚጠቀመውን የኢሳይያስ 55፡10-11 የምንባብ ክፍል ይጠቅሳል። በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ «ዓለማዊ» እና «የተቀደሰ» የሚባል ነገር የለም። ገንዘብን መስጠት፥ መዝሙር የመዘመርን ወይም የወንጌል ስርጭት በራሪ ወረቀት (ትራክት) የማከፋፈልን ያህል የሚቆጠር መንፈሳዊ ተግባር ነው። ገንዘብ ዘር በመሆኑ፥ በጸጋ መመሪያዎች አንጻር እስከ ሰጠነው ድረስ፥ ለእግዚአብሔር ክብርን ሊያበረክትና ብዙ ጉድለቶችን ሊሞላ ይችላል። ከዚህ ዓላማው ውጪ ከተጠቀምንበት ግን የዘራነው አዝመራ ፍሬ-አልባ ይሆናል።

በመጨረሻም፥ ስንዘራ ለራሳችን እንበለጽጋለን፤ ሌሎችንም እናበለጽጋለን (2ኛ ቆሮ. 9፡11)። ገበሬው በእርሻ ቦታው ላይ ሲሠራ፥ ወዲያው ሥጋዊ ጥቅሞችን ያገኛል፤ ይሁንና የመከሩን ጊዜ መጠበቅ አለበት። በጸጋ የተነሣሣ ክርስቲያን በራሱ ሕይወት ውስጥ ለግል ብልጽግናው የሚጠቅሙትን በረከቶች ያጭዳል፤ ይህም ብልጽግና ለሌሎች ይተርፋል። የዚህም ነገር የመጨረሻ ውጤት ሌሎች በሚያመሰግኑበት ጊዜ ለእግዚአብሔር የሚመጣው ክብር ነው። ጳውሎስ በጸጋ መስጠት እግዚአብሔርን ከሚያስከብር በቀር፥ ለእኛ የሚያስገኝልን ምስጋና እንደሌለ በጥንቃቄ ይገልጻል። እኛ

እግዚአብሔር የሌሎችን ጉድለት ለመሙላት የሚጠቀምብን አሸንዳዎች እንጂ፥ ማንም ምንም አይደለንም።

ይሁንና ቁጥር 11 ሌላም እውነት ያስተምረናል - እግዚአብሔር የሚያበለጽገን ከዚህ አብልጠን እንድንሰጥ ነው። በጸጋ ከመስጠት ደስታዎች አንዱ አብልጦ መስጠት ነው። ገቢያችን ብቻ ሳይሆን፥ ማንኛው ያለን ንብረት ሁሉ የእግዚአብሔር፥ ለእግዚአብሔር የተሰጠና ሥራውን ይፈጸምበት ዘንድ እርሱ የሚጠቀምበት ነው። ሁሉንም ነገር ከእርሱና ከሌሎች ጋር ስለምናካፍል፥ በነገር ሁሉ በልጽገናል ማለት ነው።

መጋቢ እንደ መሆኔ፥ ወጣት ክርስቲያኖች እነዚህን በጸጋ የመስጠት መመሪያዎች ተከትለው ማደግ ሲጀምሩ ተመልክቻለሁ። የመስጠት ተግባራቸው በጸጋ እንደ መነሣሣቱ ሁሉ፥ በእግዚአብሔር ሲታመኑ መመልከት እጅግ ደስ ያሰኘኝ ነበር። ሆኖም በዚያው በተመሳሳይ ጊዜ ደግሞ፥ ሌሎች በእነዚህ መመሪያዎች ላይ በማፌዝ፥ ቀስ በቀስ ወደ ጉስልቁልና አዘቅት ሲያመሩ ተመልክቻለሁ። ከእነዚህ መካከል አንዳንዶቹ የመዋዕለ-ንዋይ «ሀብት» ቢያገኙም፥ ገቢያቸው ግን ውድቀታቸው ነበር - እውነተኛውን ብልጽግና አልለገሳቸውም። ዋጋቸውን (ሽልማታቸውን) እዚሁ ተቀብለዋልና መንፈሳዊ ባለጸግነት የሚያገኙባቸውን ዕድሎች አጥተዋል።

በጸጋ መስጠት ማለት እግዚአብሔር ታላቁ ሰጪ መሆኑን በትክክል በመረዳት፥ ቁሳዊና መንፈሳዊ ሀብቶቻችንን በተመሳሳይ መንገድ ለሌሎች ጥቅም ማዋል ማለት ነው። ዳሩ ግን የእኛ ስጦታ በእግዚአብሔር ስጦታዎች ዓይን ምን ያህል አናሳ ነው!

## ያንተ መስጠት የሌሎችን ጉድለት ይሞላል (2ኛ ቆሮ. 9፡ 12)

አሁን ደግሞ ጳውሎስ መስጠትን አገልግሎት በሚለው ሌላ ቃል ሲገልጸው እንመለከታለን። ይህም አገልግሎት «የክህነት አገልግሎት»ን የሚመለከት ሲሆን ጳውሎስ የስጦታን ገጽታ እጅግ ከፍ ወዳለው ደረጃ አሳድጎታል። ጳውሎስ ይህንን መዋጮ፥ አንድ ካህን ብዙ ገንዘብ የፈሰሰበትን መሥዋዕት በመሠውያ ላይ እንደሚያቀርበው፥ ለእግዚአብሔር እንደ ቀረበ «መንፈሳዊ መሥዋዕት» አድርጎ ተመልክቶታል።

ክርስቶስ በመስቀል ላይ የፈጸመው ሥራ የሌዋውያንን ሥርዓት ከፍጻሜ ስላደረሰው (ዕብ. 10፡ 1-14)፥ ክርስቲያኖች ከእንግዲህ

እንስሳትን ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አድርገው አያቀርቡም። ይሁንና ለጌታ የምናመጣቸው ቁሳዊ ስጦታዎች፥ በኢየሱስ ስም ከተሰጡ፥ «መንፈሳዊ መሥዋዕቶች» ይሆናሉ (1ኛ ጴጥ. 2፡5፤ ዕብ. 13፡15-16፤ ፊልጵ. 4፡10-20)።

ዳሩ ግን በ2ኛ ቆሮንቶስ 9፡12 ላይ ትኩረት የተሰጠው፥ ስጦታቸው በይሁዳ የሚገኙትን ድሆች ጉድለት በሚሞላበት ሁኔታ ላይ ነው። «የዚህ ረድኤት አገልግሎት ለቅዱሳን የሚጎድላቸውን በሙሉ የሚሰጥ ብቻ አይደለምና፥ ነገር ግን ደግሞ በብዙ ምስጋና ለእግዚአብሔር ይበዛል» (ቁ. 12)። የአሕዛብ አማኞች ገንዘባቸውን ላለመስጠት የመሰላቸውን የማመካኛ ምክንያቶች ሊያቀርቡ ይችሉ ነበር። ከማመካኛዎቹም አንዱ፥ «ረሃብ የደረሰባቸውና የደኸዩት በእኛ ጥፋት አይደለም» የሚለው ሊሆን ይችላል። ወይም፥ «በይሁዳ አቅራቢያ የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ሊረዷቸው ይገባ ነበር።» በሌላም በኩል፥ «መስጠት አስፈላጊ መሆኑን እናምናለን፤ ዳሩ ግን በመጀመሪያ ደረጃ ለራሳችን ድሆች እንክብካቤ ማድረግ አለብን» ለማለት ይችሉ ነበር።

አንድ ክርስቲያን ላለመስጠት ብሎ ማመካኛዎችን ማሰባሰብ ሲጀምር፥ ከመቅጽበት በጸጋ ከመስጠት ክልል ይወጣል። ጸጋ የሚፈልገው የሚያገለግልበትን ዕድል እንጂ፥ የሚያመካኝበትን ምክንያት አይደለም። መሸፈን የሚገባው ቀዳዳ ካለ፥ በጸጋ ቁጥጥር ሥር የሚመላለሰው ክርስቲያን ቀዳዳውን ለመድፈን የሚችለውን ሁሉ ያደርጋል። «እንግዲያስ ጊዜ ካገኘን ዘንድ ለሰው ሁሉ ይልቁንም ለሃይማኖት ቤተ ሰዎች መልካም እናድርግ» (ኤፌ. 6፡10)። ጳውሎስ ሀብታም ክርስቲያኖች፥ «በበጎም ሥራ ባለጠጎች እንዲሆኑ፥ ሊረዱና ሊያካፍሉም የተዘጋጁ እንዲሆኑ» ይመክራቸዋል (1ጢሞ. 6፡18)። ብዙዎቻችን ራሳችንን «ሀብታሞች» አድርገን አንመለከትም፤ ዳሩ ግን የተቀረው ዓለም የሚመለከተን እንደ ባለጠጎች አድርጎ ነው።

ይሁንና ክብሩን የምንወስደው እኛ ሳንሆን፥ የሚከበረው ጌታችን ነው (ማቴ. 5፡16)። ብዙ ሰዎች ጉድለታቸውን በመሙላቱ በኩል ተካፋዮች በመሆናችን በሰማይ፥ እግዚአብሔርን ያመሰግናሉ። ምናልባት ዛሬ ያንን የምስጋና ድምፅ ላንሰማ ብንችልም፥ ዳሩ ግን ቤተ ክርስቲያን በምትሰባሰብበት ጊዜ እንሰማለን።

እዚህ ላይ ጳውሎስ ይህንን መልእክት በሚጽፍበት ወቅት መብዛት የሚለውን ቃል ስለ ተጠቀመበት ሁኔታ መመልከቱ ጠቀሜታ

ይኖረዋል። መልእክቱን የጀመረው ከብዙ መከራ ጋር በተመጣጠነ ብዙ መጽናናት ነበር (2ኛ ቆሮ. 1፡ 5)። እንዲሁም ብዙ ጸጋን (4፡ 15)፥ ብዙ ደስታንና ልግስናን (8፡ 2) ገልጸአል። ከእግዚአብሔር ጸጋ ብዛት የተነሣ፥ ሁልጊዜም በመልካም ሥራ ሁሉ ልንበዛ እንችላለን (9፡ 8)። ኢየሱስ ክርስቶስ ለማንኛውም ሁኔታ ብቁ ሊያደርገን ስለሚችል፥ ጳውሎስ የክርስትናን ሕይወት ከመትረፍረፍ እንደ አንዱ አድርጎ ይመለከታል።

መስጠታችን መሠረታዊ ጉድለቶችን ለማቅረብ እንጂ፥ ለተቀናጣ ሕይወት ማሟያ ሊውል አይገባም። ልንቋቋማቸው የሚገባ ብዙ ችግሮች እያሉ፥ ውስን የሆነውን ሀብታችንን ለሆን ላልሆነው ማባከን አይገባንም። ችግር በራሱ ለመስጠት ብቸኛው ምክንያት አለመሆኑ የታወቀ ከመሆኑም፥ ደግሞም ማንኛውም አንድ በጎ አድራጊ ክርስቲያን ወይም ቤተ ክርስቲያን ሊሸፍኗቸው የማይችሏቸው የችግር ዓይነቶችም አሉ። ይሁንና ለመስጠት፥ የችግር መኖር አስፈላጊ ነው። አንዳንድ ችግሮች ከሌሎች የላቁ ሲሆኑ፥ አንዳንዶቹ ችግሮች ደግሞ በመሟላታቸው ከሌሎቹ የተለየ ብዙ ጥቅም ይሰጣሉ። ዛሬ የሚጫኑን በርካታ ችግሮች ለመወጣት በምንነሣሣበት ጊዜ፥ ስለ ችግሮቹ ትክክለኛ መረጃና መንፈሳዊ መረዳት ሊኖረን ይገባል።

## ያንተ መስጠት እግዚአብሔርን ያስከብራል (2ኛ ቆሮ. 9፡ 13)

ጌታችን፥ «መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ» ብሏል (ማቴ. 5፡ 16)። ይህ ከቤተ ክርስቲያን የመስጠት ውብ ገጽታዎች አንዱ ነው - ለእግዚአብሔር ብቻ የሚገባውን ክብር የሚቀበል ግለሰብ የለም።

መልካም ነገር የተደረገላቸው የአይሁድ አማኞች እግዚአብሔርን ስለ ምን ያመሰግኑ ነበር? የሚያመሰግኑት የአሕዛብ አብያተ ክርስቲያናት ሥጋዊና ቁሳዊ ጉድለቶቻቸውን ለእግዚአብሔር ሲሉ በማሟላታቸው ነበር። እንዲሁም ደግሞ ለአሕዛብ መንፈሳዊ መገዛትንና የመስጠትን ፍላጎት በልባቸው ስላሳደረው የእግዚአብሔር መንፈስ እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ነበር። «እነዚያ አሕዛብ ወንጌሉን መስበክ ብቻ ሳይሆን፥ በወንጌሉ ይኖራሉ» ለማለት ይችሉ ነበር።

## በዚህ ቁጥር ውስጥ (2ኛ ቆሮ. 9፡ 13)

«ሁሉንም» የምትለው ቃል አስፈላጊ ነች። የአይሁድ አማኞች ሌሎችም በአሕዛብ አብያተ ክርስቲያናት ስለ መረዳታቸው እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ነበር። እርዳታ የተደረገላቸው አነስተኛ ማኅበረ ምዕመናን ሁሉ ስለ እርዳታውና እርዳታው ለሌሎች ስለ መስጠቱ ጭምር ያመሰግኑ ነበር። «ለእኛ ለምን ብዙ አልተሰጠንም?» በማለት ፈንታ፥ በችግር ውስጥ ያሉት ሌሎችም እየተረዱ በመሆናቸው፥ እግዚአብሔርን ለማመስገን ይችሉ ነበር። በጸጋ መስጠት የሚሠራው በዚህ መንገድ ነው።

እያንዳንዳችን ስለ መታዘዛችንና ስለልግስናችንም እግዚአብሔርን የሚያመሰግኑ እንዳሉ እንደሌሉ ለመረዳት አብያተ ክርስቲያናት ግምገማ ቢያካሂዱ መልካም ነው። የቱንም ያህል የጎላ የወንጌል አገልግሎት ቅንዓት ቢኖረን፥ ወይም የአምልኮ ተግባራትን ብናከናውን እነዚህ በራሳቸው ሌሎችን ለማገልገልና ተጨባጭ ችግሮቻቸውን በማስወገድ ረገድ ያመለጡንን አጋጣሚዎች ሊተኩ አይችሉም። በእኛ ዘንድ አንዱን የመምረጥና ሌላውን የማግለል ጉዳይ ሊኖር አይገባም። ብርሃናችን ያለ ማቋረጥ በድምቀት እንዲያበራ ከተፈለገ፥ ወንጌል የማካፈልንና ሰዎችን ከችግራቸው የማላቀቅን ኃላፊነት ሚዛናዊ ልናደርጋቸው ይገባል። ለተራበ ሰው ወንጌል መስበኩ አስቸጋሪ ነው የሚለው አባባል ትክክለኛ ነው። (ያዕ.2፡ 15-16 ተመልከት።)

አንድ ሀብታም ሰው በቤተሰቡ የግል የጽሞና ጊዜያት ሁሉ፥ ቤተ ክርስቲያኑ ለምትረዳቸው ሚሲዮናውያን ስለሚያስፈልጉ ነገሮች፥ በየዕለቱ ጸሎት ያደርግ እንደ ነበረ ማንበቤን አስታውሳለሁ። ታዲያ አንድ ቀን የጠዋት ጸሎታቸውን እንደ ጨረሱ ትንሽ ልጁ፥ «አባባ፥ የአንተ የባንክ ሒሳብ ደብተር የእኔ ቢሆን ኖሮ፥ ጸሎትህን ያለ ምንም ችግር በመለስሁልህ ነበር!» አለው ይባላል። እውነትም እንዴት ያለ አስተዋይ ልጅ ነው!

## ያንተ መስጠት የእግዚአብሔርን ሰዎች አንድ ያደርጋል (2ኛ ቆሮ. 9፡ 14-15)።

ጳውሎስ የአሕዛብ አብያተ ክርስቲያናት የአይሁድን አማኞች እንዲረዱ ሲጠይቅ፥ በልቡ ውስጥ ከነበሩት አበይት ዓላማዎች አንዱና መሠረታዊም ምክንያት ይህ ነበር። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበሩ

ዋንኞቹ ሕጋውያን ጳውሎስን ፀረ-አይሁዳዊና ብሎም ፀረ-ሕግ አድርገው ይከሱት ነበር። የአሕዛብ አብያተ ክርስቲያናት ከአገሩ ርቀትና ከባሕል ልዩነት የተነሣ በኢየሩሳሌም ውስጥ ከምትገኘው «እናት ቤተ ክርስቲያን» ተለይተው ነበር። ጳውሎስ ግን የቤተ ክርስቲያንን መከፋፈል ለመከላከል ይፈልግ ነበር፤ «እርዳታውም» የዚህ መርሐ-ግብር አካል ነበር።

ይህ እርዳታ የአይሁድና የአሕዛብ ማኅበረ-ምዕመናንን ሊያስተሳስር የሚችልባቸው መንገዶች የትኞቹ ናቸው? አንድኛው ነገር፥ ስጦታው የፍቅር መግለጫ መሆኑ ነው። (ምንም እንኳ ጳውሎስ ስጦታው «የመንፈሳዊ ዕዳ» ክፍያ እንደ ሆነ ቢናገርም - ሮሜ 15፡25-27) ይህንን ያደረጉት አሕዛብም ከእግዚአብሔር ጸጋ የተነሣ እንጂ፥ ግዴታቸው ስለ ነበረ አይደለም። አይሁዶችም በበኩላቸው፥ ለአሕዛብ ወንድሞቻቸውና እህቶቻቸው ባለውለታነትና አንድነት ይሰማቸው ነበር።

ሌላው በመንፈስ የሚያስተሳስራቸው ጸሎት ነው። «ራሳቸውም ስለ እናንተ ሲያማልዱ፥ በእናንተ ላይ ከሚሆነው ከሚበልጠው የእግዚአብሔር ጸጋ የተነሣ ይናፍቁአችኋል» (2ኛ ቆሮ. 9፡14)። የአሕዛብ አብያተ ክርስቲያናት የአይሁድ አብያተ ክርስቲያናትን የጸሎት ድጋፍ «እየገዙ» ይሆን? አይደለም! ጳውሎስ ስጦታውን ወደ ይሁዳ ሲያደርስ ሊስተዋል የሚችለውን ቅጽበታዊ የፍቅር፥ የምስጋናና የጸሎት መግለጫ በእዝነ-ሕሊናው ተመለከተ።

በርካታ የሚሲዮን ጣቢያዎችን የመጎብኘትና በዚያ የሚገኙ አማኞች፥ «እየጸለይንልህ ነበር» ሲሉ የመስማት ልምምድ ነበረኝ። ከምሥራቅ አውሮፓ ከመጣው አንድ መልካም ክርስቲያን ጋር ስንጫወት፥ «በአንዳንድ በኩል መንፈሳዊ ክርስቲያኖች ለመሆን ከእኛ የበለጠ ችግር ስላለባችሁ፥ በዩናይትድ እስቴትስ ለምትኖሩ ወገኖች እየጸለይንላችሁ ነበር» አለኝ። አሳቡንም እንዲያብራራልኝ በጠየቅሁት ጊዜ ፈገግ አለና፥ «ይህን ማለቴ ባንጻራዊ ሁኔታ ሲታይ ቀለል ያለ ሕይወት ስልምትኖሩና ምቾት ደግሞ የመንፈሳዊ ሕይወት ባላንጣ ስለ ሆነ ነው። በምሥራቅ አውሮፓ እነማን ወዳጆቻችን እንደ ሆኑና እነማንስ ጠላቶቻችን እንደ ሆኑ ጠንቅቀን እናውቃለን። እናንተ በምትኖሩበት ስፍራ ግን ለመሞኘት መንገዱ ቀላል ነው። በመሆኑም እንጸልይላችኋለን» አለኝ።

ሁለቱም የአይሁድና የአሕዛብ አብያተ ክርቲያናት ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ይበልጥ ይቀርቡ ነበር። «ስለማይነገር (ስለማይገለጽ) ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን» (ቁ. 15)። በኢየሱስ ክርስቶስ የሰብዓዊ ልዩነቶች በሙሉ ስለ ተወገዱ፥ ከእንግዲህ እርስ በርሳችን እንደ አይሁዶች ወይም አሕዛቦች፥ ድሆች ወይም ባለጠጎች፥ ሰጪዎች ወይም ተቀባዮች አንተያይም። «ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና» (ገላ. 3፡28)።

ዳሩ ግን መስጠታችን የሕይወታችን ምትክ ሲሆን መመልከቱ አሳዛኝ ነገር ነው። አንድ ጊዜ አንድ የቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣን፥ «ለሚሲዮን አገልግሎት የምትፈልጉትን ያህል ገንዘብ እሰጣችኋለሁ። የሚሲዮናዊን ንግግር ብቻ አታሰሙኝ!» ሲል አጉረምርሞብኛል። አንድ ክርስቲያን በጸጋ መስጠትን በሚለማመድበት ጊዜ፥ ገንዘቡ ለሌሎቹ ለማሰቡ ሆነ ለአገልግሎቱ ምትክ አይሆንም። በመጀመሪያ ራሱን ለእግዚአብሔር በመስጠት (2ኛ ቆሮ. 8፡5) - ቀጥሎም ያለውን ይሰጣል። ስጦታው የልቡን በቅድሚያ መሰጠት የሚያመለክት ነው። ስጦታው በእግዚአብሔር ጸጋ የተነሣሣ ከሆነ፥ ሰጪውንና ስጦታውን ለመለየት አይቻልም።

ወደ ኋላ ተመልሰህ 2ኛ ቆሮንቶስ 8 እና 9ን እንድታነብና በእግዚአብሔር ጸጋ ላይ የተደረገውን አጽንኦት እንድታስተውል እጠይቃለሁ። አብያተ ክርስቲያኖቻችንና ሌሎችም አገልግሎቶች በጸጋ ወደ መስጠት ቢመለሱ ኖሮ፥ በከፍተኛ ጫና የሚካሄዱት የስጦታ ልመናዎች፥ ገንዘብ ለማከማቸት የሚደረጉ የማታለያ ጥረቶችና ከእግዚአብሔር ሰዎች ዘንድ የሚደመጡ ማጉረምረሞች በእጅጉ በተቀነሱ ነበር። በምትኩም፥ የእግዚአብሔርን ጸጋ በእውነተኛ መንገድ ለሚያበለጽጉ አገልግሎቶትች በቂ ገንዘብ በኖረም ነበር። እንደ እኔም ግምት፥ በዓለም ያለው ያልዳነው ሰው የምንሠራውን ተአምር በአድናቆት በተከታተለም ነበር።

እግዚአብሔር በጸጋ በመስጠት በማመኑ፥ እኔና አንተ ድነናል። እኛስ በጸጋ በመስጠት ምን ያህል እናምናለን?

# በአገልግሎት ውስጥ የሚከሰቱ የአሳብ አለመግባባቶች

## 2ኛ ቆሮንቶስ 10

ከአንባብያን ወይም ከሬድዮ አድማጮች ጠጠር ያለ ደብዳቤ ሲደርሰኝ፥ ብዙውን ጊዜ ለመልሱ በብቃት እንደ ተዘጋጀሁበት እስከሚሰማኝ ድረስ በተለየ ፋይል ውስጥ አስቀምጠዋለሁ። በጥቂት አጋጣሚዎች፥ ለደብዳቤዎች እጅግ ፈጣን መልሶችን ሰጥቻለሁ፤ በኋላ ግን ተጸጽቼአለሁ። ቆይታ በማድረግ፥ ለማሰብና ለመጸለይ፥ ብሎም የደብዳቤውን አሳብ በትክክል ለመረዳት ለራሴ በቂ ጊዜ እሰጣለሁ። ይህም ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው ምላሽ ለመስጠት ስለሚያስችለኝ ነው።

ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በሚጽፍበት ጊዜ፥ ጥበብ ያለበትን እርምጃ እንዲከተል የእግዚአብሔር መንፈስ መርቶታል። የሚጽፈው ለተከፋፈለች (1ኛ ቆሮ. 1 ከቁ. 11 ጀምሮ)፥ ሐዋርያዊ ሥልጣኑን እየተገፋች ለነበረችና በሐሰተኛ መምህራን በማመረክ ላይ ለነበረች ቤተ ክርስቲያን ነበር። በመሆኑም፥ እውነተኛነቱን እንዳይጠራጠሩ በመጀመሪያ አገልግሎቱን ይገልጽላቸዋል። ከዚያም፥ የሚያቀርብላቸው የእርዳታ ጥያቄ ለመንፈሳዊ ሕይወታቸው ዕድገት እንደሚረዳቸው ስለሚያውቅ፥ በመዋጮው ውስጥ እንዲካፈሉ ያበረታታቸዋል። በጸጋ መስጠትና በጸጋ መኖር ጎን ለጎን ይሄዳሉ።

አሁን በመጨረሻው የደብዳቤው ክፍል፥ ሐሰተኛ አስተማሪዎችን ጨምሮ፥ ጳውሎስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሁከት የሚፈጥሩትን ሰዎች ይሞግታል - ሐዋርያዊ አገልግሎቱንም ያጠናክረዋል። ከምዕራፍ 10-13 ያለውን በምታነብበት ጊዜ፥ ጳውሎስ በቀጥታ ከሳሾቹን ሲጠቅስ (ለምሳሌ፥ 10፡7፥ 10-12፤ 11፡4፥ 20-23) እና ለሐሰት ክሶቻቸውም ምላሽ ሲሰጥ ትመለከታለህ። እንደዚሁም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበሩ የአይሁድ ሃይማኖት አስፋፊዎች የእግዚአብሔርን ሥራ ለማፍረስ የሚሠሩ የሰይጣን አገልጋዮች መሆናቸውን አልሸሸገም (11፡12-15)።

ጳውሎስ ከምዕራፍ 10-13 ውስጥ አንድን ቃል ሃያ ጊዜ ያህል ጠቅሶአል - መመካት ተብሎ የተተረጎመውን ቃል። እነዚህን ምዕራፎች በመጀመሪያ ስታነብ፥ ጳውሎስ ስለ ራሱ እንደሚመካ አድርገህ ታስብ

ይሆናል፤ ዳሩ ግን አይደለም። ጳውሎስ «የተመካው በኢየሱስ ክርስቶስ» ነው እንጂ፥ በራሱ ወይም ባደረጋቸው ነገሮች አልነበረም (ሮሜ 5፡11፤ ገላ. 6፡14፤ ፊልጵ. 3፡3)። እንዲሁም ስለ ቆሮንቶሶች ያለውን ትምክህት ለሌሎች ተናግሯል፤ ዳሩ ግን ትምክህቱ ከንቱ የሚቀር ይመስል ነበር (2ኛ ቆሮ. 7፡4፥ 14፤ 8፡24)።

ጳውሎስ ለአገልግሎቱና ለሐዋርያዊ ሥልጣኑ እንጂ፥ ለራሱ ሲል በግል እየተከላከለ እንዳልነበረ፥ ልብ በል። ከሌሎች አገልጋዮች ጋር «የዝና ውድድር» እያደረገ አልነበረም። ጠላቶቹ እርሱን በውሸት ለመክሰስ አልቦዘኑም ነበር፤ ራሳቸውንም ከፍ ከፍ ከማድረግ አልተመለሱም ነበር (11፡12)። ጳውሎስ ስለ ራሱና ስለ አገልግሎቱ በመግለጽ በግሉ እንዲከላከል ያስገደደው፥ የቆሮንቶስ ሰዎች ዓለማዊ አመለካከት ነበር። ጳውሎስ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ለመናገር አያቅማማም፤ ዳሩ ግን በቂ ምክንያት እስከሌለው ድረስ፥ ስለ ራሱ አይናገርም ነበር።

በመጨረሻም፥ ጳውሎስ በተመካበት ወቅት፥ እግዚአብሔር በሰጠው አገልግሎት ላይ ተወስኖ ነበር (10፡13)፤ ከዚያም አጽንኦቱን ያደረገው በመከራዎቹ ላይ እንጂ፥ በስኬቶቹ ላይ አልነበረም። ይህ ደብዳቤ በቆሮንቶስ ማህበረ-ምዕመናን ዘንድ በሚነበብበት ወቅት፥ ጳውሎስን በከሰሱት ሰዎች ልብ ውስጥ የኀፍረት ስሜት መጫሩ የማይቀር ነበር - የአይሁድ ሃይማኖት አስፋፊዎችንም ምኝነት ይፋ ማድረጉ የማይጠረጠር ነበር።

ጳውሎስ አገልግሎቱን የገለጸበት የመጀመሪያው ዓላማ፥ ከሥራው ጋር በተያያዘ መንገድ በሰዎች አእምሮ ውስጥ የሰረፀውን ውዥንብር (አለመግባባቶች) ማስወገድ ነበር። እነርሱም አስፈላጊ የሆኑትን ሦስት የአገልግሎት ክፍሎች አልተረዱም ነበር።

### መንፈሳዊ ውጊያን ስለ ማካሄድ (2ኛ ቆሮ. 10፡1-6)

1. የቀረበበትን ክስ (2ኛ ቆሮ. 10፡1-2) ለማግኘት የሚያዳግት አይደለም። (በአይሁድ ሃይማኖት አስፋፊዎች የሚመሩ) የቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዓመፀኞች፥ ጳውሎስ ከርቀት ሆኖ ደብዳቤ ሲጽፍ እንደሚደፍርና ዳሩ ግን ከቆሮንቶስ ሰዎች ጋር ፊት ለፊት በሚጋፈጥበት ጊዜ አልፈራም እንዲያውም በጣም ደካማ እንደ ሆነ አድርገው ያስወሩ ነበር (በተጨማሪም ቁ.9-11 ተመልከት)። ከበስተጀርባ ሆነው የሚገፋፏቸው የአይሁድ ሃይማኖት አስፋፊዎች በአመለካከታቸው ላይ ያላቋረጠ ተፅዕኖ ቢያሳድሩባቸውም፥

ሕዝቦቹ ግን ወደዋቸው ነበር (11፡20)። «አንድን መሥመር ያልተከተለው» የጳውሎስ የሕይወት ዘይቤ «አዎን እና አይደለም» ከሚለው የተስፋ ቃሉ ጋር ተጓዳኝ ነበር (1፡15-20)።

ጳውሎስ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ሲመሠርት፥ ዓላማው ክርስቶስን እንጂ ራሱን ማስከበር አልነበረም (1ኛ ቆሮ. 2፡1-5)። ብዙውን ጊዜ ክርስቲያኖች የሚያድጉት በተወለዱበት መንገድ ነው። አምባገነናዊ አገዛዝ በበዛበት ክልል ከተወለዱ፥ በሰው ጥበብና ብርታት ላይ ተደግፈው ያድጋሉ። ትህትናና ፍቅር በሰፈነበት አካባቢ ካደጉ፥ በጌታ ላይ መደገፍን ይማራሉ። ጳውሎስ አዲስ አማኞቹ በጌታ እንጂ በአገልጋዩ ላይ እንዳይተማመኑ ስለሚፈልግ፥ ሆን ብሎ ሥልጣኑንና ችሎታውን ዝቅ ያደርገዋል።

ጳውሎስ ያንን ሁሉ ካስተማራቸው በኋላ እንኳ፥ ክርስቲያኖቹ ግን አሁንም አላዋቂዎች ነበሩ። እውነተኛ መንፈሳዊ ኃይል የሚገኘው፥ በ«የዋህነትና ገርነት» እንጂ (2ኛ ቆሮ. 10፡1)፥ «ሥልጣንን አላግባብ በመጠቀም» እንዳልሆነ ለመረዳት አልቻሉም ነበር። በእነዚህ የመግቢያ ቁጥሮች ላይ የተጠቀሰው የጳውሎስ አመለካከት ባላንጣዎቹን ትጥቅ ያስፈታቸዋል። (እንዲያውም ጳውሎስ ማለት «ትንሽ» ማለት ስለ ሆነ፥ በዚህ ስፍራ ስሙን መጥቀሱም አስፈላጊ ነበር።) ጳውሎስ ደካማ ከነበር፥ ኢየሱስ ክርስቶስም እንዲሁ ነበር፤ ኢየሱስ ትሁትና ገር ነበርና (ማቴ. 11፡29)። ይሁንና አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ፥ ጌታችንም ብርቱና ብሎም ተቆጪ ነበር (ማቴ. 15፡1-2፤ 23፡13-33፤ ማር. 11፡15-17፤ ዮሐ. 2፡13-16 ተመልከት።) ጳውሎስ ፍቅር በተመላው መንገድ፥ «እባካችሁ መጥቼ እንዴት ደፋር ልሆን እንደምችል እንዳሳያችሁ አታስገድዱኝ!» በማለት እያስጠነቀቃቸው ነበር።

2. የሰጠው መልስ ደግሞ (2ኛ ቆሮ. 10፡3-6) መንፈሳዊ ውጊያ ምን እንደ ሆነ ይገልጻል። የቆሮንቶስ ሰዎች (በሐሰት መምህራን ተመርተው) በጳውሎስ አገልግሎት ላይ በውጫዊው ሁኔታው ስለ ፈረዱበት፥ ከውስጡ የነበረውን ኃይል አጥተው ነበር። ነገሮችን «ከሥጋ» አንጻር (ቁ.2) እንጂ፥ ከመንፈስ አንጻር አልገመገሙም ነበር። የአይሁድ ሃይማኖት አስፋፊዎች፥ ዛሬ እንደምናያቸው «አንዳንድ ታላላቅ የሃይማኖት ሰዎች»፥ በመግዛት ብቃታቸው፥ በርቱዕ አንደበታቸውና ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች በሚያገኟቸው «ሙገሳዎች» ያስደንቁዋቸው ነበር።

ጳውሎስ ምንም እንኳ እንደ ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ ፍጡር ቢሆንም የተደገፈው በመለኮታዊና ከጌታ ዘንድ በሚመጡ መንፈሳዊ የጦር ዕቃዎች እንጂ በሰብዓዊ ነገሮች ላይ ባለመሆኑ፥ የተለየ ፈለግ ተከትሏል። ከሥጋና ከደም ጋር ስለማይዋጋ፥ ውጊያው እንደ ሥጋ ፈቃድ አልነበረም (ኤፌ. 6 ከቁጥር 10 ጀምሮ ተመልከት)። ማንም ቢሆን መንፈሳዊ ውጊያዎችን በሥጋዊ የጦር ዕቃዎች ሊዋጋ አይችልም።

በቁጥር 4 ላይ የተጠቀሰው ጦር «ጦርነት» ወይም «ዘመቻ» ማለት ነው። ጳውሎስ በቆሮንቶስ አነስተኛ ጦርነት እየተጋፈጠ አልነበረም፤ በዚያ የነበረው የጠላት ጥቃት ከፍተኛ የሆነ ሰይጣናዊ ዘመቻ አካል ነበር። አሁንም ቢሆን የገሃነም ኃይላት የእግዚአብሔርን ሥራ ለማኮላሸት እየተጣጣሩ ስለ ሆነ (ማቴ. 16፡ 18)፥ ለጠላት ምንም ዓይነት ስፍራ አለመስጠታችን አስፈላጊው ነገር ነው፤ አንዲት ቤተ ክርስቲያን እንኳ መልቀቅ የለብንም!

በሰዎች አእምሮ የተቃወሞ ግድግዳዎች የሚገኙ በመሆኑ፥ (እንደ ኢያሪኮ ግንብ) እነዚህ ግድግዳዎች መናድ አለባቸው። ለመሆኑ «የአእምሮ ግድግዳዎች» የተባሉት ምንድን ናቸው? ግድግዳዎቹ፥ ከእግዚአብሔር ቃል እውነት ጋር የሚቃረኑ ፍልስፍናዎችና ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርገው በእውቀት መታበይ ናቸው። ጳውሎስ የሚቃወመው እውቀትን ሳይሆን፥ ዳሩ ግን ሰዎችን ከሚያውቁት በላይ እንደሚያውቁ አድርገው እንዲያስቡ የሚገፋፉቸውን የምሁርነት ወይም የሊቅነት አመለካከት ነው (ሮሜ 12፡ 16)። ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያኒቱን በሚመሠርትበት ጊዜ ይህንን «የሰዎች ጥበብ» የተጋፈጠ ሲሆን (1ኛ ቆሮ. 1፡ ከቁ. 18 ጀምሮ)፥ አሁን ደግሞ በአይሁድ ሃይማኖት አስፋፊዎች መምጣት የተነሣ ትግሉ እንደ ገና ሲጧጧፍ እናያለን።

ትዕቢት በሰይጣን እጅ እንደሚጥል ለተረዳው ጳውሎስ ከከፍተኛ የውጊያ መሣሪያዎቹ ውስጥ አንዱ ትህትና ነበር። ትሁቱ የእግዚአብሔር ልጅ ከጲላጦስ እጅግ የበለጠ ኃይል ነበረው (ዮሐ. 19፡ 11 ተመልከት)፤ ይህንኑም ደግሞ አረጋግጧል። ጳውሎስ ተቃውሞውን ለመጣል መንፈሳዊ የጦር ዕቃዎችን ተጠቅሞአል፡- ጸሎት፥ የእግዚአብሔር ቃል፥ ፍቅርና በሕይወቱ ውስጥ የሚሠራ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ናቸው። ጳውሎስ በራሱ ስብዕና፥ ወይም በችሎታዎቹ፥ ወይም በሐዋርያነቱ ሥልጣን ላይ አልተደገፈም ነበር። ይሁንና ማኅበረ-ምዕመናኑ አንድ ጊዜ ራሱን ለጌታ አስከ ሰጠ፥ ጳውሎስ አስፈላጊ ሆኖ ባገኘው ጊዜ አጥፊዎቹን ለመቅጣት ተዘጋጅቶ ነበር።

ዛሬ በርካታ አማኞች ቤተ ክርስቲያን በጦርነት ፍልሚያ ላይ እንዳለች አይገነዘቡም፤ የክርስትናን ጦርነት አደገኛነት የሚረዱትም ቢሆኑ፥ ብዙውን ጊዜ እንዴት መዋጋት እንዳለባቸው አያውቁም። አጋንንታዊ ኃይላትን ለመርታት ሰብዓዊ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ፤ እነዚህም ዘዴዎች ለውድቀት ይዳርጉዋቸዋል። ኢያሱና ሠራዊቱ የኢያሪኮን ግንብ ለሰባት ቀናት በዞሩበት ጊዜ፥ የኢያሪኮ ከተማ ታዛቢዎች አብደዋል የሚል አሳብ ነበራቸው። ይሁንና አይሁዶች በእግዚአብሔር ተማምነው ትዕዛዛቱን በመፈጸማቸው፥ ከፍ ያሉትን ቅጥሮች አፍርሰው፥ ጠላትን ድል ነሥተዋል (ኢያሱ 6፡ 1-20)።

በሺካጎ ከተማ በመጋቢነት ሳገለግል ሳለሁ፥ በየሳምንቱ ከሦስት መጋቢ ወዳጆቼ ጋር እየተገናኘን «በጸሎት ጦርነት» እንተባበር ነበር። ሰዎችን ለእግዚአብሔር ከመስጠት የሚከላከላቸውን የተሳሳተ አሳብ ለማስወገድ የሚያስችለውን የተስፋ ቃል በማሰብ ደጋግመን ጸለይን፤ እግዚአብሔርም በማለድንላቸው ሰዎች ሕይወት ውስጥ ታላላቅ ነገሮችን አደረገ። በአእምሮ ውስጥ የሚገኙ ግድግዳዎች ከፈራረሱ፥ ወደ ልብ የሚያደርሰው መንገድ ሊከፈት ይችላል።

## በመንፈሳዊ ሥልጣን ስለ መጠቀም (2ኛ ቆሮ. 10፡7-11)

የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ሊማሩት ከሚገባቸው እጅግ አስቸጋሪ ትምህርቶች አንዱ፥ ምድራዊ ሥልጣንና ሹመት በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ምንም ስፍራ እንደሌላቸው ነው። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ በሌሎች ላይ «ጌቶች» ተብለው ሊጠሩና ተፈላጊነታቸውን ሊያጋንኑ እንደማይገባቸውና የአሕዛብ ገዢዎችን ፈለግ በመከተል የመሪነት ተግባራቸውን በፈላጭ ቆራጭነት እንዳያከናውኑ አስጠንቅቆአቸዋል (ማር. 10፡35-45 ተመልከት)። ለእኛ ልንከተለው የሚገባን እንደ ባሪያ ሆኖ የመጣውንና ሌሎችን ያገለገለውን የኢየሱስ ክርስቶስን ምሳሌነት ነው። ጳውሎስ ያንን ምሳሌነት ተከትሏል።

ዳሩ ግን የቆሮንቶስ ሰዎች ጳውሎስ ያደርግ የነበረውን ነገር ለመመርመር በቂ መንፈሳዊ መረዳት አልነበራቸውም። የእርሱን ትህትና ከአይሁድ ሃይማኖት አስፋፊዎች «የባሕርይ ጥንካሬ» ጋር በማነጻጸር፥ ጳውሎስ ሥልጣን እንደሌለው አድርገው ደመደሙ። በመሆኑም ሥልጣኑን ለማረጋገጥ ኃይለኛ ደብዳቤ ጽፏል፥ ዳሩ ግን ሥጋዊ ሁኔታው ደካማ ከመሆኑም ሌላ ንግግሩም «የሚማርክ» አልነበረም። እነርሱም ከውጫዊ ገጽታ አኳያ እየፈረዱ እንጂ፥ መንፈሳዊ የመለየት ተግባር እያከናወኑ አልነበሩም።

አንድ ጊዜ ከጥቂት ወዳጆቼ ጋር ሆነን፥ አንድ ሰው በማራኪ «ታላላቅ ቃላት» የተሞላ፥ ባብዛኛው (ከዓውደ መልእክቱ ባፈነገጡ) በጥራዝ ነጠቅ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተደገፈና በዓለም ላይ ስለሚከሰቱ ነገሮች በሚገልጹ በርካታ ማጣቀሻዎችና «በዘመኑ ምልክቶች» ሙሉ በሙሉ የተጣበበ ስብከት ሲያቀርብ አድምጠናል። ከጉባዔው ወጥተን ስንሄድ ሳለ አንድኛው ወዳጃችን፥ «የዛሬው ስብከት በእርግጥም ‹እግዚአብሔር ግን በነፋሱ ውስጥ አልነበረም› የሚለውን የ1ኛ ነገሥት 19፡11 ምንባብ በደንብ ይገልጸዋል» አለን። ይሁንና ካጠገባችን የነበሩ ሰዎች እስካሁን ከሰሙዋቸው ስብከቶች ሁሉ እንደሚልቅ «አስደናቂ ስብከት» አድርገው ይናገሩ ነበር። በበኩሌ እነዚያ ሰዎች ከ10 ደቂቃዎች በኋላ ከሰባኪው መልእክት ውስጥ አንዲት ተጨባጭ ነገር ማስታወሳቸውን እጠራጠራለሁ።

ጳውሎስ ሥልጣን እንደ ነበረው አልካደም፤ ዳሩ ግን ያንኑ ሥልጣን መንፈሳዊነት በጎደለው መንገድ ሊጠቀምበት አልፈለገም ነበር። የሥልጣኑም ዓላማ እነርሱን ለማፈራረስ ሳይሆን፥ ለማነጽ ነበር፤ ማነጽ ደግሞ ማፍረስ ከሚጠይቀው እጅግ የላቀ ጥበብ ይጠይቃል። ማነጽ በተለይም ፍቅርን ይጠይቃል (1ኛ ቆሮ. 8፡1)፤ ይሁንና የቆሮንቶስ ሰዎች የጳውሎስን ፍቅርና ገርነት የደካማነት ምልክት አድርገው ወሰዱት።

በጳውሎስና በአይሁድ ሃይማኖት አስፋፊዎች መካከል የነበረው ዋናው ልዩነት፥ ጳውሎስ ሥልጣኑን ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ የተጠቀመበት ሲሆን፥ እነርሱ ግን ቤተ ክርስቲያን ሥልጣናቸውን እንድታንጽላቸው መጠቀሚያ በማድረጋቸው ነው።

የቤተ ክርስቲያናት መጋቢ በመሆንና ከስፍራ ወደ ስፍራ በመንቀሳቀስ ባገለገልሁባቸው በርካታ ዓመታት ውስጥ፥ አንዳንድ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት መጋቢዎቻቸውን በሚያስተናግዱበት ሁኔታ ተደንቄአለሁ። አንድ ሰው ፍቅርና እውነተኛ ትህትና ካሳየ፥ መሪነቱን በመቃወም ልቡን ያደማሉ። ሌላው ሰው «ቤተ ክርስቲያኒቱን የሚቆጣጠር» «አምባገነን» ይሆንና የሚፈልገውን ሁሉ ያገኛል። ሰዎችም ይወዱታል - ዝናውንም ያወሩለታል። ሆኖም ግን ጌታችንም የተስተናገደው በዚህ መንገድ በመሆኑ፥ በዚሁ ነገር ልንደነቅ አይገባም።

ጳውሎስ እውነተኛ ሐዋርያ ቢሆን ኖሮ፥ ሥልጣኑን በትክክል ባስመሰከረም ነበር በማለት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተቃውሞ ያስነሡበት ሰዎች በሐሰተኛነት ከሰውት ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ፥

ጳውሎስ በእርግጥም በሥልጣኑ ቢጠቀም ኖሮ አላግባብ ጨቁኖናል በማለት በወነጀሉት ነበር። ጳውሎስ የትኛውንም እርምጃ ቢወስድ፥ ሊከሱት ተዘጋጅተው ነበር። የቤተ ክርስቲያን አባላት መንፈሳዊ መረዳት ሲጎድላቸውና አገልግሎትን በዓለማዊ አመለካከት ሲገመግሙ፥ ሁልጊዜም ቢሆን የሚፈጸመው ይኸው ነው።

ይሁንና ክሳቸው በእነርሱ ላይ ተመልሶ የሚፈርድ ነበር። እንደ እነርሱ አባባል ጳውሎስ ሐዋርያ ባይሆን፥ በአስመሳይነት ተመላልሶአልና ተራ አማኝ እንኳ ሊሆን አልቻለም። ዳሩ ግን የጳውሎስ ሐዋርያነት እውነት ከሆነ፥ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን እውነተኛ ቤተ ክርስቲያን አልነበረችም ማለት ነው። ጳውሎስ ቀደም ብሎ ማንም ሰው አገልግሎቱንና የግል ሕይወቱን ሊነጣጠል እንደማይችል ገልጾአል (2ኛቆሮ.1፡12-14)። እርሱ አታላይ ከነበር፥ የቆሮንቶስ ሰዎች ተታለው ነበር ማለት ነው።

ጳውሎስ በተጨማሪም፥ በስብከቱና በጻፈው መልእክት መካከል ልዩነት እንዳልነበረ ገልጾአል። የጊዜውን ሁኔታ በማጤን፥ ጳውሎስ በደብዳቤዎቹ ውስጥ ጠንከር ያለ መልእክት አስተላልፎአል። በገርነት ለመጻፍ ቢቻል ኖሮ ምንኛ በይበልጥ ደስ ባለው ነበር። ይኼ ግን የተፈለገውን ዓላማ ከዳር ለማድረስ አያስችለውም ነበር። በመሆኑም፥ «ከባድና ኃይለኛ» ደብዳቤዎችን ቢጽፍም፥ ዳሩ ግን ከአፍቃሪ ልብ የመነጨ ነበር። «አስፈላጊ ከሆነ፥ እንዴት ኃይለኛ ልሆን እንደምችል አሳያችኋለሁና ለቀጣዩ ጉብኝቴ ብትዘጋጁ ይሻላል» እያላቸው ነበር።

ክርስቲያን ሥልጣንን የሚጠቀምበት ሁኔታ መንፈሳዊ ብስለቱንና ባሕርዩን ያመለክታል። ያልበሰለ ሰው በሥልጣኑ በሚጠቀምበት ጊዜ በኩራት ያብጣል፤ ዳሩ ግን በሳሉ ሰው በሥልጣን በመጠቀሙ ሂደት ውስጥ ያድጋል - ሌሎችም ከእርሱ ጋር ያድጋሉ። እንደ ጥበበኛ ወላጅ ሁሉ፥ ጥበበኛ መጋቢ መቼ ትዕግሥት በሞላበት ፍቅር በዝምታ እንደሚጠብቅና መቼስ በተወሰነ ኃይል ተግባሩን እንደሚያከናውን ያውቃል። ተቻኩሎ ከማጥቃት ይልቅ ትዕግሥትን ተላብሶ መጠበቅ የበለጠ ኃይል ያስፈልገዋል። በሳል ሰው ሥልጣንን የሚጠቀመው አክብሮትን ለማትረፍ ሳይሆን፥ ዳሩ ግን አክብሮቱ በተገቢው መንገድ ሥራ ላይ በማዋል ነው። በሳል መሪዎች እርምጃ ለመውሰድ ሲጠባበቁ ይሰቃያሉ፤ ያልበሰሉ መሪዎች ደግሞ ባለማስተዋል ቅጽበታዊ እርምጃ ይወስዱና ሌሎችን ለሥቃይ ይዳርጋሉ።

ሐሰተኛ አስተማሪዎች ሥልጣን ለመጨበጥ «በድጋፍ ደብዳቤ» ላይ ቢመኩም፥ ጳውሎስ ግን ከሰማይ የሆነ መለኮታዊ ተልዕኮ ነበረው። የእግዚአብሔር እጅ በሕይወቱ ላይ እንደ ነበረች እሙን በመሆኑ፥ ጳውሎስ የኖረው ሕይወትና የፈጸመው ተግባር ራሱ በቂ ማረጋገጫ ነበር። ጳውሎስ ቀጣዩን ዓረፍተ ነገር ለመጻፍ የሚያስችል ድፍረት ነበረው:- «በሰውነቴ ላይ ያለው የግርፋት ምልክት የኢየሱስ አገልጋይ መሆኔን ስለሚያመለክት ከእንግዲህ ወዲህ ማንም አያስቸግረኝ» (ገላ. 6፡17 አዲስ ትርጉም)።

እኔና ባለቤቴ በእንግሊዝ አገር ባገለገልንበት ጊዜ፥ ሁልጊዜም ለንደንን ለመጎብኘት በሚያስችል መልኩ ፕሮግራማችንን እናዘጋጅ ነበር። በተለይ በለንደን ውስጥ ከታወቁት ሁለት መደብሮች ማለትም ከሴልፍሪጅ እና ከሃሮድ ዕቃዎችን መግዛት ያስደስተን ነበር። ስማቸው የተጻፈበትን ታላቅ መደብር የገነቡት ኤች ጎርደን ሴልፍሪጅ፥ ድርጅቱን ለስኬታማነት ያበቁት መሪ እንጂ «አለቃ» ባለመሆናቸው መሆኑን አዘውትረው ይናገሩ ነበር። መሪው «እንሂድ!» ይላል። አለቃው ግን «ሂድ!» ይላል። አለቃው እንዴት እንደሚሠራ ያውቃል፤ ዳሩ ግን መሪው እንዴት እንደሚሠራ ያሳያል። አለቃ በጨፍሮቹ ላይ ፍርሃትን ያሳድራል፤ መሪው ግን በአክብሮትና በመልካም ፈቃድ ላይ የተመሠረተ የሥራ ፍላጎትን ያሳድራል። አለቃ ለተበላሸው ነገር ጥፋትን በሌሎች ላይ ያላክካል፤ እውነተኛ መሪ ግን የተበላሸውን ነገር ይጠግናል። አለቃ «እኔ» ሲል፥ መሪ ግን «እኛ» ይላል። የሚስተር ሴልፍሪጅ የአስተዳደር ፍልስፍና፥ ከሐዋርያው ጳውሎስ የመሪነት ፍልስፍና ጋር በትክክል ይስማማል።

መንፈሳዊ አገልግሎትን ስለ መለካት (2ኛ ቆሮ. 10፡12-18) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከማንኛውም እንቅስቃሴ በላይ «አገልግሎትን መለካት» በርካታ ችግሮችን እንዳስከተለ አስባለሁ። የቤተ ክርስቲያን ሥራ የእግዚአብሔር ከሆነና የእግዚአብሔርም ሥራ ተአምር ከሆነ፥ እንዴት አድርገን ተአምርን እንለካለን? ጌታችን ኢየሱስ በራእይ ምዕራፍ 2-3 ውስጥ የተጠቀሱትን አብያተ ክርስቲያናት ሲገመግም፥ እነርሱ ራሳቸውን ከለኩበት ሚዛን እጅግ ልዩ በሆነ መስፈርት ተጠቅሟል። ድሀ ነኝ ስትል የነበረችውን ቤተ ክርስቲያን፥ ሀብታም ነሽ አላት በሀታምነቷ የምትመካውና ደግሞ ድሀ (2፡8-11፤ 3፡14-22)።

አንዳንድ ሰዎች አገልግሎትን በአኀዛዊ ስሌቶች ብቻ ይለካሉ። የቀድሞዋ ቤተ ክርስቲያን አኀዛዊ ዘገባዎችን መጠቀሟ እውነት ቢሆንም (የሐዋ. 2፡41፤ 4፡4)፥ በዚያን ጊዜ ከቤተ ክርስቲያን ጋር መተባበር ይበልጥ አስቸጋሪ (አደገኛ) መሆኑም እውነት ነው (የሐዋ. 5፡13 ተመልከት)። ከጥቂት ዓመታት በፊት፥ ከአሜሪካ ታላላቅ የእምነት ክፍሎች አንዱ፥ «በ64 ዓ.ም. ከሚሊዮን የሚልቁ ነፍሳችን አባላታችን እንዳርጋለን። እያንዳንዱም አሥራቱን ይከፍላል» የሚል መፈክር ነበረው። ከዋንኛ ሰባኪዎቻቸውም አንዱ፥ «አሁንም የምናገኛቸው ሚሊዮን ሰዎች ከዚህ በፊት እንዳገኘናቸው ሚሊዮን ሰዎች ዓይነት ከሆኑ እግዚአብሔር ይርዳን!» የሚል አስተያየት ሲሰነዝር ሰማሁ። ብዛት ለጥራት ዋስትና አይሆንም።

1. የሐሰት መስፈሪያ (2ኛ ቆሮ. 10፡12)። ከውስጣዊ ለውጥ ይልቅ ውጫዊ እንቅስቃሴዎች የሚታዩበት ሃይማኖት ለመለካት እጅግ ስለሚቀል፥ የአይሁድ ሃይማኖት መሪዎች አገልግሎታቸውን በመለካቱ ረገድ ብርቱዎች ነበሩ። ሕግ አጥባቂው የሚያደርገውንና የማያደርገውን ሊለካ ይችላል፤ ዳሩ ግን በአማኝ ልብ ያለውን መንፈሳዊ እድገት ሊመለከተው የሚችለው ጌታ ብቻ ነው። አንዳንድ ጊዜ ከፍተኛ ዕድገት ያስገኙ አገልጋዮች ራሳቸውን እጅግ ከሚያንሱትም እንዳነሱ አድርገው ይቆጥራሉ።

እንደ እውነቱ ከሆነ፥ የአይሁድ ሃይማኖት አስፋፊዎች፥ መመዘኛዎቹን አውጥቶ በዚያው አንጻር ነገሮችን የሚለካ «የእርስ በርስ መሞካሻ ማኅበር» አባላት ነበሩ ለማለት ይቻላል። በመሆኑም የዚህ ቡድን አባላት የተሳካላቸው ተደርገው ሲቆጠሩ፥ ከዚያ ውጭ የሚገኙት ግን ተስፋ ቢሶች ተደርገው ይወሰዱ ነበር። ጳውሎስም ከዚህ ቡድን ውጭ ነበረና እንደ ውደቂ ተቆጠረ። የሚያሳዝነው ግን እነዚህ አጉል ተመፃዳቂዎች ራሳቸውን በኢየሱስ ክርስቶስ አይለኩም ነበር (ኤፌ. 4፡12-16 ተመልከት)። እንዲህማ ቢያደርጉ ኖሮ፥ ስህተታቸው ጎልቶ በታያቸውም ነበር።

2. እውነተኛ መለኪያ (2ኛ ቆሮ. 10፡13-18)። ጳውሎስ አገልግሎታችንን በእግዚአብሔር ፈቃድ ለመለካት ስንሻ፥ ራሳችንን ልንጠይቅ የሚገባንን ሦስት ጥያቄዎች ያቀርባል።

እግዚአብሔር በሚፈልገኝ ስፍራ ነው ያለሁት? (ቁ. 13-14) እግዚአብሔር ጳውሎስ የሚሠራበትን «ዳርቻ ወሰነ»፡- እርሱ የአሕዛብ ሐዋርያ ነበር (የሐዋ. 9፡15፤ 22፡21፤ ኤፌ. 3)። ከዚህ በፊት ሌላ ሐዋርያ ወዳላገለገለበት ስፍራ ተላከ።

ጳውሎስ በመከላከያው ጽሑፍ ውስጥ አነስተኛ በሆነ «የተቀደሰ ምፀት» ይጠቀማል። «እግዚአብሔር የወሰነልኝ ዳርቻ እናንተን የቆሮንቶስ ሰዎች ጭምር ያካልላል» (2ኛ ቆሮ. 10፡13 ተመልከት)። ወደ ቆሮንቶስ ወንጌልን ያዳረሱት የአይሁድ ሃይማኖት አስፋፊዎች አልነበሩም። ዛሬ እንደሚታዩ መናፍቃን ሁሉ፥ እነርሱም ቤተ ክርስቲያን ከተመሠረተች በኋላ ብቅ ብቅ ያሉ ነበሩ (ሮሜ 15፡15-22 ተመልከት)።

አብያተ ክርስቲያናትና አገልጋዮች ከራሳቸው ጋር እንጂ፥ እርስ በርስ እየተወዳደሩ አይደሉም። እግዚአብሔር ለቻርልስ እስፐርጀን ወይም ለቢሊ ሳንዳይ በሰጣቸው ስጦታዎችና ዕድሎች አንፃር አይለካንም። የእኔን ሥራ የሚለካው ለእኔ ከወሰነው የሥራ ድርሻ አኳያ ነው። እግዚአብሔር ከሁሉም በላይ ታማኝነትን ይሻል (1ኛ ቆሮ. 4፡2)።

የመጋቢያንን ጉባዔ ወይም የአንድን የእምነት ክፍል ስብሰባ ለመካፈል የሚያስፈራ አንድ ነገር አለ፤ ለዚህም ምክንያቱ በፕሮግራሙ ላይ የሚካፈሉት ሰዎች ከሁሉም የላቁ ውጤቶችን ያስመዘገቡ ታላላቅ ሰዎች በመሆናቸው ነው። ወጣት መጋቢያንና በዝቅተኛ የሥራ መደብ ላይ የሚያገለግሉ ሰዎች፥ በታማኝነት የሚያከናውኑት አገልግሎት የእነዚህን ታላላቅ ሰዎች ያህል ፍሬ የሚያፈራ ስለማይመስላቸው፥ በየዕለቱ በጥፋተኛነት ስሜት ተሸብበው ወደ ቤታቸው ይመለሳሉ። ከእነዚህ ተስፋ ከቆረጡት ሰዎች ጥቂቶቹ ፍሬያማ ለመሆን ሲሉ ባገኙት ዓይነት ፕሮግራምና ዘዴዎች ለመጠቀም ይሞክራሉ፤ ውጤቱ ግን የላቀ ኃዘኔታ ይሆናል። ከዚያም በመቀጠል አገልግሎቱን ለመልቀቅ ያስባሉ። ዳሩ ግን እግዚአብሔር አገልግሎታቸውን የሚለካው በያዙት የሥራ መደብ እንጂ፥ በሌላ የሥራ ክልል አንጻር እንዳልሆነ ቢረዱ፥ በሥራቸው ላይ ለመቆየትና በታማኝነት አገልግሎታቸውን ለመቀጠል መጽናናትን ያገኛሉ።

እግዚአብሔር በአገልግሎቱ ከብሯልን? (2ኛ ቆሮ. 10፡15-17)። ይህ ጥያቄ በሌሎች ሰዎች አገልግሎት የዳኑትን ሰዎች ሰርቀው ከወሰዱ በኋላ፥ የራሳቸው ደቀ መዛሙርት እንደ ሆኑ አድርገው ለሚመኩ የአይሁድ ሃይማኖት አስፋፊዎች የሚቀጠቅጥ ነቀፋ ነው። ጳውሎስ በሌላው ሰው ሥራ አይመካም፤ ወደ ሌላው ሰው ግዛትም ከስ አይገባም። ምንም ዓይነት ሥራ ቢሠራ፥ በእርሱ አማካኝነት የሠራው እግዚአብሔር ነው - ክብሩንም ሊወስድ የሚገባው እግዚአብሔር ብቻ ነው።

አንድ ጊዜ አንድ ሰው እንዴት ትልቅ የሰንበት ትምህርት ቤት መሥራት እንደሚቻል ሲያስተምር ሰምቼ ነበር። በትምህርቱ ውስጥ የሚገኘው አሳብ ሁሉ ትክክል ሲሆን፥ በተለይ በዩናይትድ እስቴትስ ውስጥ በሚገኙ በአንዳንድ ታላላቅ አገልግሎቶች አማካይነት በጥሩ ሁኔታ ከሥራ ላይ ውሏል። አንድ የሚያሳዝን ነገር ግን ሰውየው ራሱ ትልቅ የሰንበት ትምህርት ቤት ከዚህ በፊት ሠርቶ አለማወቁ ነበር። ትምህርቱን ለማበልጸግ ሲል ብዙዎቹ ታላላቅ የአገልግሎት ማዕከሎችን ጎብኝቷል፤ መጋቢዎችንና የሥራ ባልደረቦቻቸውን አነጋግሯል፤ በአጭሩ ትምህርቱ ሁሉ የተገኘው ከዚያ ነበር ለማለት ይቻላል። ታዲያ የዚያን ዕለቱን ሰበካውን ከፈጸመ በኋላ፥ ሰዎች ጥያቄ ለመጠየቅና ፊርማውን ለመቀበል ከበውት ነበር። እኔም በዚያን ጊዜ እንደ አጋጣሚ በአሜሪካ እጅግ ውብና ታላቅ ቤተ ክርስቲያን ከሠራ አንድ መጋቢ አጠገብ ቆሜ ነበርና፥

«እነዚህ ሰዎች ካንተ ጋር ቢነጋገሩ ይሻላቸው ነበር» አልሁት፤ «ምክንያቱም የሰንበት ትምህርት ቤት አሠርተህ ስላየኸው፥ ከእርሱ ይልቅ የተሻለ ዕውቀት አለህ ብዬ ስለምገምት ነው» ስል አከልሁበት።

መጋቢውም ፈገግ ብሎ፥ «ተወው፤ እባክህ ይደሰት!» አለና በመቀጠልም «ሁላችንም አንድን ሥራ እንሠራለን፤ ቁም-ነገሩ ግን የእግዚአብሔር መክበር ነው» በማለት አጫወተኝ።

ጳውሎስ «ከዚያ አልፎ ወደሚገኙ ስፍራዎች» እንዳይሄድ እንቅፋት የሆነው ብቸኛው ነገር የእነርሱ አለማመን እንደ ሆነ ሲናገር፥ አሁንም በሌላ መጠነኛ «የተቀደሰ ምፀት» እየተጠቀመ ነበር። ለመሪነቱ ቢገዙና ለቃሉ ቢታዘዙ ኖሮ፥ ሌሎችን ከደኅንነት የራቁ ነፍሳት ቀደም ሲል በወንጌል ለመድረስ ይችል ነበር፤ ዳሩ ግን በርካታ ችግሮች ስለ ፈጠሩበት፥ የቤተ ክርስቲያኗን የውስጥ ችግሮች ለመቅረፍ ሲል፥ የሚሲዮናዊነት አገልግሎቱን ጊዜ ማባከን ነበረበት። «የማቀርባቸው በርካታ አኅዛዊ ቀመሮች (ነፍሳት) ነበሩኝ - ዳሩ ግን እናንተው አግዳችሁኛል» እያለ ነበር።

ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 1፡31 ላይ የጠቀሰውን ኤርምያስ 9፡24 በቁጥር 17 ላይ በድጋሚ ይጠቅሳል። የቆሮንቶስ ሰዎች፥ በተለይም አሁን የአይሁድ ሃይማኖት አስፋፊዎች በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ስላንተንሰራፉ፥ ሰዎችን ወደማክበር ያዘነብሉ ነበር። የቆሮንቶስ ሰዎች እነዚህ መምህራን ያደረጉዋቸውን ነገሮች የሚያስረዱ «ዘገባዎችን» ሲሰሙና የያዙዋቸውንም «የድጋፍ ደብዳቤዎች» ሲመለከቱ፥ ሙሉ

ለሙሉ ተማረኩ። ከዚህም የተነሣ፥ ጳውሎስም ሆነ አገልግሎቱ እንደ ተናቀ ነገር ይቆጠር ጀምር።

ይሁንና የፍጻሜው ፈተና ውጤት የሚገለጸው ለዓመታዊ ስብሰባዎች ዘገባዎች ተዘጋጅተው በሚቀርቡበት ጊዜ አይደለም። የፍጻሜው ፈተና ውጤት የሚታወቀው በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት ነው - «በዚያን ጊዜም ለእያንዳንዱ ምስጋናው ከእግዚአብሔር ዘንድ ይሆናል» (1ኛ ቆሮ. 4፡5)። ሰዎች ክብሩን የሚወስዱ ከሆነ፥ እግዚአብሔር ክብርን ሊቀበል አይችልም። «እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ ስሜ ይህ ነው፤ ክብሬን ለሌላ፥ ምስጋናዬንም ለተቀረጹ ምስሎች አልሰጥም» (ኢሳ. 42፡8)።

እንዲህም ሲባል ስኬታማ ተግባር የሚያከናውኑ እጅግ የታወቁ አገልጋዮች የእግዚአብሔርን ክብር እየወሰዱ ናቸው ማለት አይደለም። እያደግንና «ብዙ ፍሬ» እያፈራን ስንሄድ፥ አብን እናስከብራለን (ዮሐ. 15፡1-8)። ይሁንና ይህ ከመንፈሳዊ ሕይወት ውስጥ የሚመነጭ «ፍሬ» እንጂ፥ በሰዎች ግፊትና በተጋነኑ አኃዛዊ ዘገባዎች ቀመር «ውጤት» እንዳልሆነ መገንዘብ አለብን።

ጌታ ሥራዩን ሊያመሰግነው ይችላል? (2ኛ ቆሮ. 10፡18)። ራሳችንን የምናመሰግን ወይም ሌሎች ሰዎች የሚያመሰግኑን ልንሆን እንችላለን። የሚያሳዝነው ግን የእግዚአብሔር ምስጋና የማይገባን ሰዎች ልንሆን መቻላችን ነው። እግዚአብሔር የሥራችንን መልካምነት የሚያጸድቀው እንዴት ነው? በመፈተን ነው! በቁጥር 18 ላይ የተፈተነ የሚለው ቃል፥ «በመፈተን ማረጋገጥ» ማለት ነው። ወደ ፊት በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት የሚደረግ ፈተና አለ (1ኛ ቆሮ. 3 ከቁጥር 10 ጀምሮ)፤ ዳሩ ግን አሁንም የምንሠራው ሥራ ይፈተናል። እግዚአብሔር ሥራቸው እንዲፈተንና እውነተኛነቱም እንዲረጋገጥ ሲል፥ ችግሮች ወደ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት እንዲመጡ ይፈቅዳል።

ለብዙ ዓመታት ያህል እንዳጤንኩት፥ ክርስቲያናዊ አገልግሎቶች በመዋዕለ-ንዋይ እጦት፥ በሐሰት ትምህርት ጣልቃ-ገብነት፥ «ቤተ ክርስቲያንን ለመቆጣጠር» በሚፈልጉ ኩራተኛ መሪዎችና በአጓጉል የለውጥ ጥያቄ ሲፈተኑ ተመልክቻለሁ። ሥራቸው መንፈሳዊነት ከማጣቱ የተነሣ፥ ወድቀው ወደ መክሰም የተቃረቡ አብያተ ክርስቲያናትም ነበሩ። ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ ከመከራዎቹ የተነሣ አድገው ተጠናክረዋል - በዚህም ሁሉ እግዚአብሔር ከብሯል።

በመሠረቱ የአገልግሎታችንን መረጃዎች ልንጠብቅና ዘገባዎችን ልንሰጥ ይገባል፤ ዳሩ ግን «በአኀዛዊ መረጃዎች ወጥመድ» ልንጠመድና አገልግሎት የሚለካው በአኀዞች ብቻ ነው ወደሚለው መደምደሚያ ልንደርስ አይገባም። እንደ እውነቱ እያንዳንዱን አብያተ ክርስቲያን የሚገጥመው ሁኔታ የተለያየ ሊሆን ስለሚችል፥ የአንዱን አገልግሎት በሌላው አገልግሎት መሠረት ለመገምገም አይቻልም። ቁም-ነገሩ፥ እግዚአብሔር በሚፈልገን ስፍራ መገኘታችንና እርሱ በሕይወታችን እንዲከብር፥ እናደርገው ዘንድ የሚፈልገውን ማድረጋችን ነው። መንስዔ የሆነን ምክንያት (ዓላማ) ልክ እንደምናስገኘው እድገት ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ ለሥራችን መለኪያ በመሆን ያገለግላል። እግዚአብሔርን ብቻ ለማስከበር የምንሻ ከሆነና እርሱም በልባችንና በሕይወታችን ውስጥ የሚካሄደውን ግምገማ ያለ ፍርሃት ከተቀበልን፥ የሰዎች ግምቶች ወይም ትችቶች ጭንቀት አያሳድሩብንም።

«የሚመካ ግን በጌታ ይመካ (ቁ. 17)።

# አባት ከሁሉም በላይ ያውቃል

## 2ኛ ቆሮንቶስ 11

ለምሳሌ አንተ ክርስቲያናዊ አገልጋይ ብትሆን፥ በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ የሚገኙትን ምዕመናን በርግጥ የምትወዳቸው መሆኑን እንዴት አድርገህ ልታሳምናቸው ትችላለህ?

ጳውሎስ ይህንን ደብዳቤ በሚጽፍበት ጊዜ ያጋጠመው ከዚህ ተመሳሳይ የሆነ ችግር ነበር። በመካከላቸው የፈጸመውን ሥራ ቢያስታውሳቸው፥ «ጳውሎስ በትምክህት እየተናገረ ነው» የሚሉ ዓይነት ሰዎች ነበሩ። በቆሮንቶስ ስለ ነበረው አገልግሎት ምንም ባይናገር ደግሞ፥ የአይሁድ ሃይማኖት አስፋፊዎቹ፥ «ተመልከቱ፥ ጳውሎስ ምንም ነገር እንዳልሠራ ነግረናችሁ አልነበር?» ማለታቸው የማይቀር ነው።

ስለዚህ ጳውሎስ ምን አደረገ? በግሩም መግለጫ ማወዳደርያ እንዲጠቀም የእግዚአብሔር መንፈስ መራው፤ ይህም ወደ ቆሮንቶስ አማኞች ልብ ጠልቆ እንደሚገባ የማያጠራጥር ነበር። በዚህም መግለጫው ውስጥ ያደረገው ራሱን ለቤተሰቡ ከሚጠነቀቅ «መንፈሳዊ አባት» ጋር በማወዳደር ማቅረብ ነበር። ከዚህ በፊት፥ እንደ «አባት» በወንጌሉ አማካኝነት እንደ ወለዳቸውና አስፈላጊ መስሎ ከተሰማው ሊቀጣቸው እንደሚችል ለማስታወስ፥ ይህንኑ ምሳሌ ተጠቅሟል (1ኛ ቆሮ. 4፡14-21)። እነርሱ የተወደዱ መንፈሳዊ ልጆቹ ነበሩና የሚመኝላቸው ሁሉ ከሁሉም የተሻለውን ነገር እንዲያገኙ ነበር።

ጳውሎስ ለነርሱ ስለ ነበረው አባታዊ ፍቅር ሦስት መረጃዎችን ይሰጣል። በቤተ ክርስቲያን ላይ የነበረው ቅንዓት (2ኛ ቆሮ. 11፡1-6፥ 13-15) እውነተኛ ፍቅር ከቶውንም አይመቀኝም፤ ዳሩ ግን በሚወዳቸው ላይ የመቅናት መብት አለው። ባል በሚስቱ ይቀናል፤ እርስ በርስ የሚኖራቸውን ፍቅር ለማሻከር በሚፎክር በማንኛውም ተቀናቃኝ ላይ ደግሞ ጥላቻና ተቃውሞ የማቅረብ መብቱን ማንም የማይነፍገው ነው። አንድ እውነተኛ የአገር ፍቅር ያለው ዜጋ በነጻነቱ ላይ የመቅናትና ይህንኑም ለማስጠበቅ የመዋጋት ሙሉ መብት አለው። እንደዚሁም፥

ማንኛውም አባት (ወይም እናት) በልጆቹ ላይ ስለሚቀና፥ ከሚጎዳቸው ከማንኛውም ነገር ሊጠብቃቸው ያላቋረጠ ክትትል ያደርጋል።

በዚህ ስፍራ የቀረበው መግለጫ፥ ለጋብቻ የታጨች ልጃ-ገረድ ልጅ ያለችውን አፍቃሪ አባት የሚያመለክት ነው። እርስዋን በንጽሕና መጠበቅና ለባሏ በኃዘን ሳይሆን በደስታ ማስረከቡ፥ መብቱና ሃላፊነቱ እንደ ሆነ ይሰማዋል። ጳውሎስ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን ኢየሱስ ክርስቶስን ለማግባት እንደ ታጨች ሙሽራ አድርጎ ይመለከታል (ኤፌ. 5 ከቁጥር 22 ጀምሮ እና ሮሜ 7፡4 ተመልከት)። ኢየሱስ ክርስቶስ ለሙሽራዪቱ እስኪመጣ ድረስ ያ ጋብቻ አይፈጸምም (ራእይ 19፡1-9)። እስከዚያው ድረስ፥ ቤተ ክርስቲያን (ማለትም ክርስቲያኖች) ወዳጇን ለመገናኘት ራስዋን አዘጋጅታ በንጽሕና መጠበቅ አለባት።

እንግዲህ ይህን በመሰለው ግንኙነት ላይ አደገኛ ሁኔታ የሚፈጠረው፥ ልጃገረዲቷ ለእጮኛዋ ሳትታመን ስትቀር ነው። የታጨች ሴት ፍቅሯንና ታማኝነቷን ሁሉ ለአንድ ሰው ብቻ ትሰጣለች - ለእጮኛዋ። ከሌላ ሰው ጋር ስትዳራ ብትገኝ፥ ታማኝነቷን ባለመጠበቋ በደለኛ ትሆናለች። በ2ኛ ቆሮንቶስ 11፡3 ላይ ቅንነት ተብሎ የተተረጎመው ቃል፥ «ታማኝነት፥ ለአንድ ወገን ራስን መስጠት» የሚል ትርጉም ይሰጣል። የተከፋፈለ ልብ ወደ ተበላሸ ሕይወትና ወደ ረከሰ ግንኙነት ያመራል።

የፍቅርና የጋብቻ መግለጫ፥ እንዲሁም የታማኝነት አስፈላጊነት፥ ብዙ ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጠቅሷል። ነቢዩ ኤርምያስ የእስራኤል ሕዝብ ለእግዚአብሔር የነበረውን ፍቅር እያጣ ሲሄድ ተመለከተና አስጠነቀቃቸው። «እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- የብላቴንነትሽን ምሕረት፥ የታጨሽበትንም ፍቅር፥ በምድረ በዳ ዘር ባልተዘራበት ምድር እንደ ተከተለኝ አስቤአለሁ» (ኤር. 2፡2)። የይሁዳ ሕዝብ «የጫጉላ ቤት ፍቅሩን» አጥቶ ጣዖታትን በማምለክ በደል ውስጥ ወደቀ። ኢየሱስም በኤፌሶን የነበረችውን ቤተ ክርስቲያን ሲያስጠነቅቅ፥ በተመሳሳይ መግለጫ ተጠቅሟል - «ዳሩ ግን የምነቅፍብህ ነገር አለኝ፤ የቀደመውን ፍቅርህን ትተሃልና» (ራእይ 2፡4)።

ጤናማውን ግንኙነት ከበስተጀርባ ሆኖ ያደፈረሰው ሰይጣን ሲሆን፥ በጥቅሱ ውስጥ በእባብ መልክ ተገልጾአል። ይህም የሚያመለክተው ወደ ዘፍጥረት ምዕራፍ 3 ነው። ጳውሎስ ይህንን ደብዳቤ ለቆሮንቶስ ሰዎች በሚጽፍበት ጊዜ፥ ስለ ከሳሹ ዲያብሎስ ብዙ

የሚለው ነገር እንደ ነበር መረዳቱ ጠቃሚ ነው። ሰይጣን አማኞችን ለማጥቃት በርካታ መሣሪያዎች እንደ ነበሩት በመግለጽ ያስጠነቅቃል። ኃጢአት የፈጸሙትን አማኞች ሕሊና ሊያከብድ (2ኛ ቆሮ. 2፡10-11)፥ የማያምኑትን አእምሮ ሊያሳውር (4፡4)፥ ወይም የአማኞችን አእምሮ ሊያሳስት (11፡3)፥ ብሎም የእግዚአብሔርን አገልጋዮች ሰውነት ሊጎስም (12፡7) ይችላል።

ሰይጣን ሐሰተኛ ስለ ሆነና ሐሰቶቹን እንድንሰማ፥ እንድናሰላስልና ከዚያም እንድናምንባቸው ስለሚፈልግ፥ ያለ የሌለው ትኩረቱ ሁሉ የአእምሯችንን አስተሳሰብ በመለወጥ ላይ ነው። ስለዚህም ነው በዚህ ክፍል ውስጥ በተለይ በአእምሯችን ላይ ለሚደርሰው ፈተና ልዩ ክብደት የተሰጠው ሰይጣንም በሔዋን ላይ የፈጸመው ይህንኑ ነበር። በመጀመሪያ፥ የእግዚአብሔርን ቃል እንድትጠራጠር አደረገ («እግዚአብሔር እንዲህ ብሎአልን ...?)፤ ከዚያም የእግዚአብሔርን ቃል ካደ («መሞትን አትሞቱም!»)፤ ቀጥሎም የራሱን ውሸት ምትክ አድርጎ አቀረበ («እንደ እግዚአብሔር ትሆናላችሁ ...») (ዘፍ. 3፡1፥ 4-5)።

በመሠረቱ ሰይጣን አታላይ ነው። አማኞች ውሸትን ወዲያው እንደማይቀበሉ ስለሚያውቅ፥ «ወጥመዱን በሚማርክ ነገር ማበጀትና» የሚሰጠንን ነገር እንድንቀበል ማድረግ መቻል አለበት። ከሰይጣን መሠረታዊ ባሕርያት አንዱ አስመሳይነት ነው - እግዚአብሔር የሚያደርገውን ነገር ይቀዳና የእርሱ ስጦታ በማስመሰል ከእግዚአብሔር እንደሚበልጥ አድርጎ ሊያሳምነን ይጣጣራል። ይህንን የሚያደርገው እንዴት ነው? እግዚአብሔርን የሚያገለግሉ መስለው ሰይጣንን በሚያገለግሉ አስመሳይ ሰዎች በመጠቀም ነው።

ሰይጣን፥ ሌላ አዳኝና ሌላ መንፈስ የሚገኝበት አስመሳይ ወንጌል አለው (ገላ. 1፡6-12)። የሚያሳዝነው የቆሮንቶስ ሰዎች የጸጋና የሕግ ድብልቅ የሆነውንና ከቶውንም እውነትነት የሌለበትን ይህንኑ «አዲስ ወንጌል» «መቀበላቸው» ነው። አንድ ወንጌል ብቻ ስላለ፥ ሊኖር የሚችለው አንድ አዳኝ ብቻ ነው (1ኛ ቆሮ. 15 ከቁጥር 1 ጀምሮ)። ስለዚህ አንተም በአዳኙ በምታምንበት ጊዜ በልብህ ውስጥ የእግዚአብሔር መንፈስ ገብቶ ያድራል፤ ያለውም አንድ መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው።

የዚህ የሐሰተኛ ወንጌል ሰባኪዎች (ዛሬም በእኛ መካከል የሚገኙ)፥ በ2ኛ ቆሮንቶስ 11፡13-15 ውስጥ ተገልጸዋል። እንደ እግዚአብሔር አገልጋዮች መለኮታዊ ሥልጣን እንዳላቸው ይናገሩ ነበር፤ ይሁንና ሥልጣናቸው ውሸት ነበር። እውነተኛ የእግዚአብሔር አገልጋዮችንም አስመሳዮች ናቸው ብለው በማሳጣት ወነጀሉ። ጳውሎስንም የከሰሱት በተመሳሳይ ሁኔታ ነበር። ራሳቸውንም ከጳውሎስ እጅግ ልቀው እንደሚገኙ «የመጠቁ-ሐዋርያት» አድርገው ያቀርቡ ነበር። በተራቀቀው የአነጋገር ችሎታቸው፥ አላዋቂ አማኞችን ሳቡዋቸው፤ ጳውሎስንም የመናገር ስጦታ የለውም በማለት ያሳጡት ጀመር (ቁ. 6፤ 10፡10)። በመሆኑም በእምነታቸው ወላዋይ የሆኑት አማኞች በታማኝ ሰባኪዎችና አስተማሪዎች በተሰጧቸው የወንጌሉ መሠረታዊ እውነቶች ጸንተ በመቆም ፈንታ፥ በሰይጣን አገልጋዮች «ማራኪ ንግግር» መደለላቸው ምን ያህል የሚያሳዝን ነገር ነበር!

ጳውሎስ፥ «እነርሱ ከቶውንም የመጠቁ-ሐዋርያት አይደሉም» በማለት ሕዝቡን ያስጠነቅቃል። «እነርሱ የውሸት ሐዋርያት ናቸው!» አነሳሽ ምክንያታቸውም እግዚአብሔርን ማስከበር ሳይሆን፥ ያመኑትን ሰዎች በማጥመድ የግል ጥቅም ማግኘት ነው። ዘዴዎቻቸው የማታለያ ብልሃቶች ናቸው (2፡17፤ 4፡2)። በዚህ ስፍራ ላይ የተመለከተው ዋንኛ አሳብ ዓሣን ለማጥመድ በወረንጦው ላይ የሚንጠለጠለው መታለያ ምግብ ነው። ለቤተ ክርስቲያን ምዕመናን በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከተገለጸው «የበለጠ» ክርስቲያናዊ ሕይወት እንዳለ በማስመሰል ያቀርባሉ፤ የመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት የሌለው የሕግና የጸጋ ድብልቅ ሕይወት ይሰብካሉ።

እነዚህ አገልጋዮች የሚሠሩት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሳይሆን በሰይጣን ኃይል ነው። ጳውሎስ ሥራቸውን በማስመልከት፥ ለሦስት ጊዜ ያህል መለወጥ በሚለው ቃል ተጠቅሟል (11፡13፥ 14፥ 15 ተመልከት)። የዚህ ቃል የግሪኩ ትርጉም «ማንነትን ላለማስነቃት በአልባሳት መጀቦን፥ ጭምብል ማጥለቅ» የሚል ነው። ከውጭ ለውጥ ይታያል፤ ዳሩ ግን ከውስጥ የተለወጠ ነገር የለም። እንደ ሰይጣን ሁሉ፥ የሰይጣን ሠራተኞችም እውነተኛ ባሕርያቸውን ይዘው አይቀርቡም፤ ሁልጊዜም እነርሱነታቸውን የሚሸሽግ አልባሳት ደርበውና በመጋረጃ ውስጥ ተጠልለው ይመጣሉ።

ይህን መጽሐፍ በምጽፍበት ወቅት፥ በርካታ «የሰይጣን አስመሳይ አገልጋዮች» ወደ ቤቴ መጥተው ነበር። ከነዚህ ሰዎች መካከል፥ አንዲት ውብ ወጣት ሴት፥ ለዓለም ሰላም እንደምትሠራ ልትነግረኝ ሞከራ ነበር። ዳሩ ግን ማንነቷን ስነግራት፥ የኑፋቄ ቡድን አባልነቷን አመነች። ሁለት አለባበሳቸውን ያሳመሩ ወጣት ወንዶች፥ «እኛ በዚህ ስፍራ የተገኘነው ኢየሱስ ክርስቶስን በመወከል ነው» በማለት ራሳቸውን አስተዋወቁኝ። እኔም የትኛውን ቡድን እንደሚወክሉ የማውቅ መሆኔን ወዲያውኑ ነገርኋቸውና በሩን ዘጋሁ። «ደህና ሁኑ» እንኳ አላልኋቸውም። ይህን በማድረጌ ቸርነት የጎደለብኝ የሚመስላችሁ ከሆነ፥ 2ኛ ዮሐንስ 5-11ን አንብቡና እንደ ትእዛዙ ፈጽሙ።

ጳውሎስ ከሐሰተኛ አስተማሪዎች ጥቃት በመጠበቅ ለቤተ ክርስቲያን የነበረውን ፍቅር አረጋግጧል፤ ይሁንና የቤተ ክርስቲያን ምዕመናን ለአይሁድ ሃይማኖት አስፋፊዎች ተታልለው በመቀበል ወደ ቤተ ክርስቲያናቸው እንዲገቡ በር ከፈቱላቸው። የቆሮንቶስ ሰዎች «የመጀመሪያ ፍቅራቸውን ስለ ተዉ»፥ ለኢየሱስ ክርስቶስ ከሙሉ ልብ የመነጨ አምልኮ እያቀረቡ አልነበረም። ፊታቸውን የመለሱት ከጳውሎስ ብቻ ሳይሆን ከክርስቶስም ጭምር ነበር፤ ይህ ደግሞ እጅግ የከበደ ጥፋት ነበር።

ለቤተ ክርስቲያን የሰጠው የልግስና ስጦታ (2ኛ ቆሮ. 11፡7-12) አፍቃሪ አባት ለቤተሰቡ የሚያስፈልጉትን ነገሮች ያሟላል፤ ጳውሎስም በቆሮንቶስ የነበረችውን ቤተ ክርስቲያን ለማገልገል መሥዋዕትነት ከፍሏል። ጳውሎስ እዚያ በነበረ ጊዜ፥ በእጆቹ ድንኳን የመሥራቱን ተግባር ከማከናወኑም በላይ (የሐዋ. 18፡ 1-3)፥ የቆሮንቶስ ሰዎች የዚህን ታላቅ የእግዚአብሔር ሐዋርያዊ አገልግሎት ለማግኘት ምንም ዋጋ አልከፈሉም ነበር ማለት ነው።

የቆሮንቶስ ሰዎች ጳውሎስ የከፈለላቸውን መሥዋዕት አደነቁት ይሆን? የለም - አብዛኛዎቹ አላደነቁትም። እንዲያውም የአይሁድ ሃይማኖት አስፋፊዎች ጳውሎስ ለገንዘብ የነበረውን አመለካከት ትክክለኛ ሐዋርያ አይደለም ለሚለው ክሳቸው «ማረጋገጫ» አድርገው ተጠቅመውበታል። እውነተኛ ሐዋርያ ቢሆን ኖሮ፥ ለመተዳደሪያው የገንዘብ አስተዋጽኦ በጠየቀና በተቀበለ ነበር ብለው ደመደሙ።

ጳውሎስ ግን ይህን በተመለከተ የነበረውን እምነት አብራርቷል (1ኛ ቆሮ. 9)። ከሞት የተነሣውን ክርስቶስን ስለ ተመለከተና በእርሱም ስለ ተላከ፥ እውነተኛ ሐዋርያ መሆኑን ገልጾአል። ዛሬ ታማኝ

የእግዚአብሔር አገልጋዮች እንደሚያደርጉት፥ ጳውሎስ የመዋዕለ-ንዋይ ድጋፍ የመጠየቅ መብት ነበረው፤ ይሁንና ማንም ሰው ወንጌሉን የገንዘብ ማግኛ ምንጭ አድርጎ እንደሚጠቀምበት በመቁጠር እንዳይነቅፈው፥ በመብቱ ሊገለገልበት አልፈለገም። እርሱም ለወንጌል ትምህርት ደኅንነትና ብሎም ከደኅንነት ርቀው የጠፉ ኃጢአተኞች በ«ሃይማኖታዊው ንግድ» የመሳተፍ ዝንባሌ እንዳያደናቅፉቸው ከመስጋቱ የተነሣ «የመዋዕለ-ንዋይ መብቱን» ለመተው መረጠ።

በሌላ በኩል ግን የአይሁድ ሃይማኖት አስፋፊዎች «ወንጌሉን» ለግል ጥቅማቸው እየተዘዋወሩ «ይሸቅሉበት» ነበር። ጳውሎስ በነጻ (2ኛ ቆሮ. 11፡7፥ ያለ ምንም ክፍያ) ወንጌሉን ሰብኮላቸዋል፤ ዳሩ ግን የሐሰት አስተማሪዎች ሐሰተኛ ወንጌል እያስተማሩ ቤተ ክርስቲያኒቱን ይዘርፉአታል (ቁ. 20)። ጳውሎስ በቁጥር 8 ላይ መጠነኛ ውስጠ ወይራ ቅኔ ይቀኛል - «አዎን፥ ‹ዘራፊ› ነኝ። ሆኖም እናንተን ‹እንዳልዘርፍ› ስል ሌሎች አብያተ ክርስቲያናትን ‹ዘረፍሁ›» ብሏል። አሁን ግን የአይሁድ ሃይማኖት አስፋፊዎች በእርግጥ እየዘረፉዋቸው ነበር።

አፍቃሪ አባት ሸክሞችን በልጆቹ ላይ አይጭንም። ይልቁንም፥ ልጆቹ የሚያስፈልጋቸውን ነገር እንዲሟላላቸው መሥዋዕትነትን ይከፍላል። ለልጆች በ«ዋጋዎች» እና «እሴቶች» መካከል የሚገኘውን ልዩነት ማስተማር አስቸጋሪ ነው። ለልጆች የወላጆቻቸው ወደ ሥራ መሄድና ለቤተሰቡ መሠረታዊ ፍላጎት ማሟያ ገንዘብ ማግኘት ምን ማለት እንደሆነ ለመረዳት የሚከብዳቸው ይመስላል። ከወንድሜ ልጆች አንደኛው በጣም ትንሽ ሳለ፥ ወላጆቹ ለቤታቸው አንድ ትልቅ መገልገያ ዕቃ መግዛት እንዳለባቸው ሲወያዩ ቢሰማም፥ ዳሩ ግን በቀጥታ በመሄድ የማይገዙበትን ምክንያት አልተረዳም ነበር። በመሆኑም፥ ወደ አባቱ የቼክ ደብተር እያመለከተ፥ «ለምን የምትፈልገውን ገንዘብ ያህል በአንደኛው ወረቀት ላይ ዝም ብለህ አትጽፍም?» በማለት ጠየቀ። በእነዚያ የደብተሩ «ወረቀቶች» ላይ የሚጻፈውን የገንዘብ ጥያቄ ተአማኒ ለማድረግ በቅድሚያ በባንክ ቤት ውስጥ ገንዘብ መቀመጥ እንደ ነበረበት አልተረዳም ነበር።

ጳውሎስ የገንዘብን ጉዳይ ያነሣው፥ የአይሁድን ሃይማኖት አስፋፊዎች ትምክህት ለማቀዝቀዝ የሚቻለውን ሁሉ ጥረት ለማድረግ እንጂ፥ ራሱን ለማሞካሸት ሲል አልነበረም። ጳውሎስ አንድም ሰው እንኳ በስግብግብነት ወይም በራስ-ወዳድነት እንደማይከሰው ያውቅ ነበር (ጳውሎስ ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን የሰጠውን ምስክርነት ከሐዋርያት

ሥራ 20፡33-35 ተመልከት)። እጆቹ ንጹሐን ነበሩ። ጠላቶቹ የሚከሱበትን ማንኛውንም መዘዝ ለማስወገድ ብርቱ ጥንቃቄ ያደርግ ነበር።

በ2ኛ ቆሮንቶስ 11፡9 ላይ መክበድ የሚለው ቃል በተለየ መንገድ መታየት የሚገባው ነው (12፡13-14ንም ተመልከት)። በግሪኩ፥ «መደንዘዝ» ማለት ነው። ቃሉም የተወሰደው ከውስጡ ከሚያስተላልፈው የኮረንቲ ኃይል ሳቢያ የሚበላቸውን ነገሮች አስቀድሞ ከሚያደነዝዘው «ኢል» ከሚባለው ዓሣ ምሳሌ ነው። ዓሣው ላጠመደው እንስሳ በኤሌክትሪክ ኃይል የደነዘዘው የአካል ክፍል ከባድ ሸክም ይሆንበታል። ጳውሎስ አማኞችን በማስደነቅ፥ በማጥቃት፥ ወይም በመዘረፍ ለመያዝ ምንም ዓይነት የማታለያ ብልሃቶችን አልተጠቀመም ነበር። በወንጌል ሰበካውም ሆነ በገንዘብ አያያዙ ግልጽና ታማኝ ነበር።

በራሴ የአገልግሎት ጉዞዎች ወቅት በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ እጅግ የሚያሳዝኑ ሁኔታዎች አጋጥመውኛል። ቤተ ክርስቲያኒቱ አድጋ ለማየት በመሥዋዕትነት ለሚሠሩ ታማኝ መጋቢዎች ማኅበረ-ምዕመናን ምንም ምስጋና ሲያቀርቡ አላየሁም። ከእነዚህ አገልጋዮች አንዳንዶቹ ጥቂት ደመወዝ እየተከፈላቸው ብዙ ሥራ የሚሠሩ ቢሆኑም፥ ዳሩ ግን አብያተ ክርስቲያናት ምንም ፍቅር የሚያሳዩዋቸው አይመስሉም። የእነርሱ ተተኪዎቻቸው ግን እንደ ነገሥታት ይታዩ ነበር። እዚህ ላይ የምንጽናናበት ነገር ቢኖር በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት ሁሉም ትክክለኛ ፍትሕና ዋጋ ማግኘቱ ነው።

በአንድ ወቅት ለአደን ወደ አፍሪካ መጥተው የነበሩት ፕሬዚዳንት ሩዝቬልት በመርከብ ወደ አሜሪካ በሚመለሱበት ጊዜ ስላጋጠሟቸው ሁለት ሐቀኛ ባልና ሚስት ሚሲዮናዊያን ታሪክ፥ ዶክተር ክሪስዌል ያጫወቱኝን አስታውሳለሁ። በርካታ ዜና ዘጋቢዎችና ፎቶግራፍ አንሺዎች በአደን ላይ የከረሙትን ለማግኘትና ቃለ-ምልልስ ለማድረግ በወደቡ ላይ ይጠባበቁ እንጂ፥ እነኛን ክርስቶስን በአፍሪካ በማገልገል ዘመናቸውን አሳልፈው ለተመለሱት ጀግና ሚሲዮናውያን ግን አቀባበል የሚያደርግላቸው አንድም ሰው አልተገኘም ነበር።

በዚያኑ ምሽት ባልና ሚስቱ በተከራዩበት መለስተኛ ሆቴል መኝታ ክፍላቸው ውስጥ ሆነው በኒው-ዮርክ ከተማ ወደብ ሲደርሱ ስለ ነበረው ሁኔታ በቴሌቭዥን ተመለከቱ። ባልዮዎም ባየው ነገር ኃዘን ተሰምቶት፥ «ትክክል አይደለም» አለ ለባለቤቱ፤ አክሎም፥ «ሚስተር ሩዝቬልት የተመለሱት ከአደን ጉዞ ነበር፤ እናም አገሩ በሙሉ እርሳቸውን

ለማግኘት ወጣ። እኛም ከብዙ ዓመታት የአገልግሎት ጊዜ በኋላ ወደ ቤት ተመለስን፤ ሰላም ሊለን የቀረበ ሰው ግን አልነበረም» አላት።

ባለቤቱ ግን ለዚህ ቅሬታው ትክክለኛ መልስ ነበራት:- «ፍቅሬ፥ እኛ ገና ወደ ቤታችን አልደረስንም» አለችው።

ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች የነበረውን ፍቅር ለማረጋገጥ ሁለት መረጃዎችን አቅርቧል:- ለቤተ ክርስቲያን የነበረው ቅንዓት - እነርሱን «ከመንፈሳዊ አለመታመን» መጠበቅና ለቤተ ክርስቲያን የነበረው ልግስና - ከእነርሱ የገንዘብ ድጋፍ አለመቀበል። ሦስተኛ መረጃም አቅርቦላቸዋል።

## ለቤተ ክርስቲያን የነበረው ሥጋት (2ኛ ቆሮ. 11:16-33)

የዚህ ረዥም ክፍል ቁልፍ አሳብ ቁጥር 28 ሲሆን፥ አሳቡን እንደሚከተለው ለመግለጽ ይቻላል:- «አዎን፥ በብዙ መከራዎች ውስጥ አልፌአለሁ፤ ይሁንና ከሁሉም የሚበልጠው መከራ፥ ከሁሉም የሚከብደው ሸክም፥ ለአብያተ ክርስቲያናት ያለኝ አሳብ ነው!» አሳብ ተብሎ የተተረጎመው ቃል፥ «ውጥረት፥ ጭንቀት፥ ሥጋት» ማለት ነው። ሌሎች መከራዎች ውጫዊና ወቅታዊ ሲሆኑ፥ ዳሩ ግን የአብያተ ክርስቲያናት ሸክም ውስጣዊና ዘለቄታነት ያለው ነበር።

ሄንሪ ዎርድ ቢቸር፥ «ራሳችን ወላጆች እስክንሆን ድረስ የወላጆችን ፍቅር በፍጹም አንረዳም» ብለው ነበር፤ ትክክል ናቸው። ታላቁ ልጃችን ሕፃን በነበረ ጊዜ፥ አንድ አሻንጉሊት ከኤሌክትሪክ ሶኬት ውስጥ አስገባለሁ ሲል ኮረንቲ ይዞ እንዳስደነገጠው አስታውሳለሁ። እርሱም በተራው ልጅ ወለደና፥ ይህን ልጁን አንድ ቀን ከሶኬት ጋር ሲጫወት ያየዋል፥ እናም ገና ዓመት ባልሞላው በዚያ ሕፃን ላይ በመጮህ ያስደነግጠዋል። ወዲያውኑም ወደ እኔ ስልክ በመደወል፥ «ሕፃን ሳለሁ አንተና እማማ ስለ እኔ እንዴት ትጨነቁ እንደ ነበረ የተረዳሁት አሁን ነው» በማለት አጫወተኝ። «ወላጅ መሆን የራሱ የሆነ ደስታና ፍርሃት አለው አለ።»

ጳውሎስ ያለፈባቸውን የተለያዩ የመከራ ዓይነቶች ከመዘርዘሩ በፊት፥ በዚህ ዓይነት ለምን «እንደሚመካ» ለመግለጽ ጥንቃቄ አድርጓል። ጳውሎስ ስለ ክርስቶስ ለመመካትና ስለ መከራዎቹ ለመናገር ምንም ችግር አልነበረውም፤ ዳሩ ግን ሁልጊዜም የእግዚአብሔር ባሪያ እንደ መሆኑ ስለሚጋፈጣቸው ከባባድ መከራዎች ለመናገር ያመነታ ነበር። ጳውሎስና መጥምቁ ዮሐንስ፥ «እርሱ [ክርስቶስ] ሊልቅ፥ እኔ ግን

ላንስ ያስፈልጋል» በሚለው አሳብ ይስማማሉ (ዮሐ. 3፡30)። «የሚመካ ግን በጌታ ይመካ» (2ኛ ቆሮ. 10፡17)።

ጳውሎስ ስለ ራሱ እንዲጽፍ በእነዚህ ባለፈባቸው የመከራ ልምምዶች እንዲመካ (እንዲኮራ) ያስገደደ፥ ጥሬና መንፈሳዊነት የጎደለውና የቆሮንቶስ ሰዎች አመለካከት ነበር። በመሆኑም ይህንን ክፍል (11፡1) የጀመረው ስለ መመካቱ በቅድሚያ ይቅርታ በመጠየቅ ሆኖ በቁጥር 16 ላይም ይህንኑ ዓረፍተ-ነገር ይደግማል። በቁጥር 17 ላይ፥ ጳውሎስ የቃላቱን የመንፈስ ቅዱስ ምሪት አይክድም፤ ዳሩ ግን በመመካቱ፥ ከጌታ ባሕርይ ጋር የማይዛመድ ነገር ላለማድረጉ ይገልጻል (10፡1 ተመልከት)። ይሁንና ለቆሮንቶስ ሰዎች የነበረውን ፍቅር ለመግለጽና በዚህም ዓይነት ወደ ጥፋት ከሚመሩዋቸው ሐሰተኞች ለመጠበቅ ይህንኑ ተግባር መፈጸም ነበረበት።

ቀድሞ ነገር፥ የሐሰት አስተማሪዎቹ ለመመካት አላፈሩም ነበር፤ የቆሮንቶስ ሰዎችም መመካታቸውን ለመቀበል ፍርሃት አላደረባቸውም ነበር። ጳውሎስ፥ «በኅብረታችሁ ውስጥ ዋና ነገር መመካት ስለ ሆነ፥ እኔም እመካለሁ» የሚል ይመስላል። ጳውሎስ የምሳሌ 26፡5ን መመሪያ በአእምሮው የያዘ ይመስላል፡- «ለራሱ ጠቢብ የሆነ እንዳይመስለው፥ ለሰነፍ እንደ ስንፍናው መልስለት።»

በተጨማሪም፥ ጳውሎስ የተመካው ቤተ ክርስቲያንን ለመርዳት ሲሆን፥ የሐሰት መምህራን ግን ከቤተ ክርስቲያን ሊያገኙ የሚችሉትን ጥቅም አስተማማኝ ለማድረግና «ራሳቸውን ለመርዳት» ይመኩ ነበር። የጳውሎስ ዓላማ ንጹሕ ሲሆን፥ የእነርሱ ግን በራስ-ወዳድነት የተበከለና የረከሰ ነበር። ቁጥር 20 የአይሁድ ሃይማኖት አስፋፊዎች ቤተ ክርስቲያንን የበዘበዙባቸውን የተለያዩ መንገዶች ይዘረዝራል።

ባሪያዎች አደረጉአቸው፡- ከጸጋው ወንጌል ጋር የሚቃረን የሕግ ትምህርት ያስተምሩ ነበር።

በሉአቸው፡- በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊያገኙ የሚችሉትን ነገር ሁሉ «በማጋበስ በልተዋል»። መዋዕለ ንዋይ የማግኘት መብታቸውን በመጠቀም በዘበዙአቸው።

ቀሙአቸው፡- «ቀሙዋቸው፥» አጠፉአቸው። ምስሉ የሚያመለክተው በወጥመድ የተያዘችውን ወፍ ወይም በማጥመጃ የተጠመደውን የዓሣ ሁኔታ ነው። «በወጥመዳቸው ላይ የሚጥም ነገር አኑረው አጠመዱአችሁ!»

ኮሩባቸው፡- ራሳቸውን እንጂ፥ ኢየሱስ ክርስቶስን ከፍ ከፍ አላደረጉም ነበር፤ ሰዎች እንዲያከብሯቸውና እንደ ታላላቅ መሪዎች እንዲቆጥሩአቸው ወደዱ።

መቱአቸው፡- ይህ ከሥጋዊ ጥቃት ይልቅ፥ የቃላት ተቃውሞን የሚያመለክት ሳይሆን አይቀርም፤ የአይሁድ ሃይማኖት አስፋፊዎች የቆሮንቶስን ሰዎች «ፊት በጥፊ ለመምታት» እና በሕዝብ ፊት ለማሳፈር አልቦዘኑም ነበር።

ጳውሎስ እነዚህን መንፈሳዊነት የጎደላቸውን የአይሁድ ሃይማኖት አስፋፊዎች አመለካከቶችና ተግባራት ገለጻ የደመደመው፥ አንዳንድ «የመንፈስ ምሪት ያለባቸውን ቅኔዎች» በማከል ነበር። «ደካሞች መስለን እንደ ነበርን በውርደት እላለሁ» (ቁ. 21)። የቆሮንቶስ ሰዎች የጳውሎስ የዋህነት ብርታት ሆኖ ሳለ፥ ድክመት ነው ብለው አሰቡ። የአይሁድ ሃይማኖት አስፋፊዎች ትዕቢት ደግሞ ኃይል መሰላቸው። ቅዱሳን አንዳንድ ጊዜ አላዋቂ ሆነው ሲገኙ የቱን ያህል ያስደንቅ!

የአይሁዳዊነት ዝርያን በተመለከተ፥ ሐሰተኛ አስተማሪዎቹ ከጳውሎስ ጋር እኩል ነበሩ፤ ዳሩ ግን የክርስቶስን አገልግሎት በተመለከተ፥ «ቁንጮው ወይም ምጡቁ-ሐዋርያ» ጳውሎስ እንጂ፥ የአይሁድ ሃይማኖት አስፋፊዎች አልነበሩም። እስቲ ጳውሎስ ለክርስቶስና ለአብያተ ክርስቲያናት ብሎ የታገሣቸውን መከራዎች እናስታውስ።

ለክርስቶስ የተቀበላቸው መከራዎች (2ኛ ቆሮ. 11፡23-25)። ጳውሎስ ሐዋርያ ባይሆን ኖሮ፥ እነዚህን መከራዎች ባልተቀበለ ነበር። ከአሕዛብም ሆነ ከአይሁድ «ከልክ ያለፈ ግርፋት» ተቀብሏል። አሕዛብ ሦስት ጊዜ በበትር መቱት፤ አይሁድ ሦስት ጊዜ 39 ጅራፍ ገረፉት። በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የተጠቀሰው አንድ ጊዜ እንደ ደበደቡት (16፡22) እና አንድ ጊዜ በድንጋይ እንደ ወገሩት (14፡19) ብቻ ነው።

ጳውሎስ ገና ከአገልግሎቱ ጅማሬ ላይ ስለ ክርስቶስ መከራ እንደሚቀበል ያወቀው ከመሆኑም (የሐዋ. 9፡15-16)፥ አገልግሎቱን ቀጥሎ ሳለም እግዚአብሔር ይህንኑ በድጋሚ አረጋግጦለታል (የሐዋ. 20፡23)። ሌሎች ስለ እምነታቸው መከራ እንዲቀበሉ ምክንያት የሆነው ሰው፥ ራሱ ስለ እምነቱ መከራ መቀበል ነበረበት።

ተፈጥሮአዊ ችግሮች (ቁ. 25-27)። በዚያን ጊዜ ማንኛውም ተጓዥ ለማለት ይቻላል፤ ከእነዚህ ችግሮች አንዳንዶቹ ሊያጋጥሙት ይችሉ ነበር፤ ጳውሎስ የተጋፈጣቸውን ዓይነት ችግሮች ግን የጌታን ሥራ ለማደናቀፍ ጠላት የተጠቀመባቸው ናቸው ከማለት በስተቀር ሌላ የምንሰጠው አጥጋቢ ምክንያት አናገኝም። የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 27 ከሦስት የመርከብ ስብራት አደጋዎች አንዱን ይዘግባል። ስለ ተቀሩት ሁለቱ ግን የምናውቀው ነገር የለም። ጳውሎስ በዚህ ጉዞ ምን ያህል የግል ንብረቶቹን እንዳጣ ማሰባችን የማይቀር ነው።

ጳውሎስ ባለማቋረጥ ይጓዝ ስለ ነበር፥ ለጉዞ አደጋዎች የተጋለጠ ሰው ነበር። የአይሁድ ሃይማኖት አስፋፊዎች ሰላም ወደሰፈረባቸው ስፍራዎች ይሄድ ነበር። ዳሩ ግን ጳውሎስ ተራ ተጓዥ ሳይሆን፥ ተለይቶ የታወቀ ሰው ነበር። ከአይሁድም ሆነ ከአሕዛብ ጠላቶች ነበሩት፤ አንዳንዶችም ሞቱን ይመኙ ነበር።

ሁለተኛ ቆሮንቶስ 11፡27 የዚህን አስቸጋሪ ጉዞ ውጤቶች ይገልጻል። እኔ እንኳን ከቦታ ወደ ቦታ እየተዘዋወርሁ በማከናውነው ውስን አገልግሎቴ፥ አመቺ በሆኑ መኪኖችና አውሮፕላኖች እጓዛለሁ፤ ይሁን እንጂ ከቦታ ቦታ መጓዝ ምን ያህል እንደሚያዝለኝና እንደሚያሰለችኝ መናዘዝ ይኖርብኛል። ታዲያ ለጳውሎስ የቱን ያህል ከዚህ የበለጠ አሰልቺና አስቸጋሪ ሆኖበት ይሆን! በድካምና በሕመም የተጎሳቆለና የተሰቃየ መሆኑ የሚያስደንቅ አይሆንም። ብዙውን ጊዜ ምግብ፥ መጠጥና እንቅልፍ ያጣ ነበር፤ እንዲሁም አንዳንድ ጊዜ ለሰውነቱ በቂ ሙቀት የሚለግስ ልብስ እንኳ አያገኝም ነበር።

ምንም እንኳ እነዚህን የመሳሰሉ ችግሮች ማንኛውም ሌላ ተጓዥ ሊገጥሙት ቢችሉም፥ ጳውሎስ ግን ለክርስቶስና ለቤተ ክርስቲያን ከነበረው ፍቅር የተነሣ ይህን ሁሉ ችግር ያለ አንዳች ማማረር በጽናት ተቋቋመ። ከሁሉም የሚልቀው ሸክሙ፥ በዙርያው ከሚመለከተው ነገር የተፈጠረ ሳይሆን፥ ከውስጡ የሚመነጨው ስሜት ነበር - የእነዚያ ሁሉ አብያተ ክርስቲያናት ደኅንነት ነበር ጭንቀቱ! ግን ለምን ይህን ያህል ተጨነቀ? ምክንያቱም ራሱን ከአማኞች ጋር በይፋ አንድ በማድረጉ ነው (ቁ. 29)። በመንፈሳዊ «ልጆቹ» ላይ የሚደርሰው ነገር ሁሉ ልቡን ይነካው ስለ ነበር፥ ጥሎአቸው ሊሔድ አልቻለም ነበር።

ጳውሎስ ይህን በችግር የመፈተን ትረካውን ወደ ላቀ ደረጃ የሚያደርሰው፥ እርሱን የመሰለ ታላቅ ሐዋርያ፥ በቅርጫት ውስጥ ተጨምሮ በቅጥር ላይ በማለፍ፥ ከደማስቆ ከተማ የወጣበትን የውርደት

ልምምድ በመግለጽ ነው (ቁ. 32-33)። ከአይሁድ ሃይማኖት አስፋፊዎች መካከል እንዲህ ዓይነቱን ታሪክ ለመናገር የሚደፍር ይኖር ይሆን? በፍጹም አይኖርም! ጳውሎስ ስለ መከራዎቹ በሚተርክበት ጊዜ እንኳ፥ ክብሩን የሚቀበለው ክርስቶስ እንጂ ራሱ እንዳይሆን ይጠነቀቅ ነበር።

እነዚህን ቁጥሮች በምናነብበት ጊዜ፥ የሐዋርያውን ብርታትና መሰጠት ሳናደንቅ አናልፍም። እያንዳንዱ መከራ በሕይወቱ ውስጥ ምልክት እየጣለ ቢያልፍም፥ እርሱ ግን ጌታን እያገለገለ ወደ ፊት ይራመድ ነበር። «ነፍሴን በእኔ ዘንድ እንደማትከብር እንደ ከንቱ ነገር እቆጥራለሁ» (የሐዋ. 20፡24)።

ጳውሎስ ለቤተ ክርስቲያን የነበረውን ፍቅር በርግጥ አረጋግጧል፤ አሁን ቤተ ክርስቲያን ለጳውሎስ የነበራትን ፍቅር ማረጋገጥ ነበረባት።

ዛሬ በወንጌሉ በረከቶች እንደሰት ዘንድ፥ ሌሎች አስቀድመው የከፈሉዋቸውን መሥዋዕቶች እንደ ዋዛ-ፈዛዛ እንዳንመለከት እግዚአብሔር ይርዳን።

# ሰባኪው በገነት

## 2ኛ ቆሮንቶስ 12፡ 1-10

ይህ ክፍል ጳውሎስ ስለ ሐዋርያነቱ ለመከላከልና ለቆሮንቶስ አማኞች የነበረውን ፍቅር ለማረጋገጥ የሚያቀርበውን አሳብ በከፍተኛ ደረጃ የሚገልጽበት ነው። ጳውሎስ ስለ እነዚህ የግል ልምምዶቹ ለመጻፍ ባይፈልግም፥ ዳሩ ግን ችግሩን ለመቅረፍ ሌላ መንገድ አልነበረውም። እንዲያውም ራሱን ከፍ ከፍ ላለማድረግ፥ ጳውሎስ ልምምዱን የገለጸው በአንደኛ መደብ ሳይሆን በሦስተኛ መደብ ነበር። ለአንባብያኑ ከእግዚአብሔር ዘንድ ያገኛቸውን ሦስት ልምምዶች አካፍሏል።

## ክብር - እግዚአብሔር አከበረው (2ኛ ቆሮ. 12፡ 1-6)

የአይሁድ ሃይማኖት አስፋፊዎች ክብር ለማግኘት ይጣደፉ ነበርና «በድጋፍ ደብዳቤያቸው» ይመኩ ነበር (3 ከቁጥር 1 ጀምሮ)። ጳውሎስ ግን ክብርን ከሰው አልፈለገም ነበር፤ እርባና ያለው ክብር ከእግዚአብሔር ብቻ በመሆኑ፥ እርሱም በዚህ መንገድ ብቻ ለመከበር ፈለገ።

በመጀመሪያ፥ እግዚአብሔር ራእዮችንና መገለጦችን በመስጠት አከበረው። ጳውሎስ ደኅንነትን አግኝቶ በተለወጠበት ዕለት፥ የከበረውን ክርስቶስን ተመልክቷል (የሐዋ. 9፡ 3፤ 22፡ 6)፤ ሐናንያ ሊያገለግለው ሲመጣም በራእይ አይቷል (9፡ 12)፤ እንደዚሁም ለአሕዛብ እንዲያገለግል በተጠራ ጊዜም ከእግዚአብሔር ዘንድ ራእይ አይቷል (22፡ 17)።

በአገልግሎቱ ጊዜ፥ ለምሪትና ለብርታት እንዲሆነው፥ ከእግዚአብሔር ዘንድ ራእዮችን ይቀበል ነበር። ወደ መቄዶንያ የተጠራው በራእይ ነበር (16፡ 9)። የቆሮንቶስ አገልግሎቱ እንደ አቀበት አስቸጋሪ በሆነበት ጊዜ፥ እግዚአብሔር ጳውሎስን በራእይ አበረታታው (18፡ 9-10)። በኢየሩሳሌም ከታሰረ በኋላም፥ እግዚአብሔር ጳውሎስን በራእይ አጽናንቶታል (23፡ 11)። በማዕበሉ መሀል አንድ መልአክ ብቅ ብሎ እርሱና ሌሎችም መንገደኞች እንደሚድኑ አረጋገጠለት (27፡ 23)።

ከጥሪውና ከአገልግሎቱ ጋር ከተያያዙ ከእነዚህ ልዩ ራእዮች ጋር፥ መለኮታዊ እውነትን የሚገልጹ መንፈሳዊ መገለጦችም ተሰጥተውት ነበር (ኤፌ. 3፡1-6 ተመልከት)። እግዚአብሔር ለአሁኑ ዘመን ትውልድ ያለውን ዕቅድ የሚያስተውልበትን ጥልቅ መረዳት ሰጠው። በመሆኑም ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ምሥጢራት ተረድቶ ነበር።

እንዲሁም እግዚአብሔር ጳውሎስን ወደ መንግሥተ ሰማይ በመውሰድና መልሶም ወደ ምድር በመላክ አከበረው። ይህም አስደናቂ ልምምድ የተፈጸመው የቆሮንቶስ ደብዳቤውን ከመጻፉ ከ14 ዓመታት በፊት ማለትም በ43 ዓ.ም. አካባቢ ነበር። ይህም ጳውሎስ ወደ ጠርሴስ በሄደበት (የሐዋ. 9፡30) እና በርናባስን ባገኘበት (11፡25-26) ጊዜ መካከል የተፈጸመ ይሆናል። ስለዚህ ክስተት የተሰጠ ዝርዝር ነገር የለም፤ በዚህ ጉዳይ ላይ ጊዜን ሰውቶ መመራመሩም የሚፈይድ አይደለም።

የአይሁድ የሃይማኖት ምሁራን (ራቢዎች) ስለ ራሳቸው ሲናገሩ፥ በሦስተኛ መደብ የመናገር ልማድ ነበራቸውና ጳውሎስም በቆሮንቶስ ውስጥ ለሚገኙ ወዳጆቹ (እና ጠላቶቹ) ስለ ራሱ ልምምድ ለመግለጽ ያንኑ ልማድ ይጠቀማል። ልምምዱ እጅግ አስደናቂ ስለ ነበር፥ እግዚአብሔር በአካላዊው ሁኔታው እንዳለ ወደ ሰማይ ይውሰደው ወይም መንፈሱ ከሥጋው ተለይቶ ይሂድ ጳውሎስ እርግጠኛ አልነበረም። (እስኪ በቅርጫት «በመውረድ» እና ወደ ሦስተኛው ዓለም «በመውሰድ» መካከል ያለውን ልዩነት ያነጻጽሩ።) እዚህ ላይ ጳውሎስ የመንግሥተ-ሰማይን ኅልውናና እግዚአብሔርም ሰዎችን ወደዚያ ለመውሰድ እንደሚችል አረጋግጧል። ሦስተኛው ሰማይ ከ«ገነት» ጋር አንድ ሲሆን፥ እግዚአብሔር በክብሩ የሚኖርበት ሰማየ-ሰማይ ነው። ለዘመናዊው ሳይንስ ምስጋና ይግባውና ዛሬ ሰዎች ደመናት የሚንሳፈፉበትን ሰማያቸውን ጎብኝተዋል (ከደመናት በላይ በአውሮፕላን እንበራለን)፤ ወደ ፕላኔቶች ሰማያትም ይሄዳሉ (ሰዎች በጨረቃ ላይ ለመንሸራሸር በቅተዋል)፤ ይሁንና ሰው ያለ እግዚአብሔር እርዳታ ወደ እግዚአብሔር ሰማይ ሊደርስ አይችልም።

የሚያስገርመው ነገር ጳውሎስ ለ14 ዓመታት ስለዚህ ልምምድ ትንፍሽም አለማለቱ ነው! በእነዚያ ዓመታት፥ ጳውሎስ «በሥጋው መውጊያ» ይሰቃይ ነበርና ሰዎች ለምን እንዲህ ያለ ሸክም እንደ ተጫነበት በማሰብ ሳይገረሙ ላይቀሩ ይችላሉ። ምናልባትም የአይሁድ ሃይማኖት አስፋፊዎች እንደ ኢዮብ አጽናኞች፥ «ይህ ሥቃይ የደረሰበት

በእግዚአብሔር ቅጣት ምክንያት ነው!» ሳይሉ አይቀሩም ይሆናል። (በመሠረቱ መውጊያው ከእግዚአብሔር የተሰጠው ስጦታ ነበር።) ከጳውሎስ ደህና ወዳጆች አንዳንዶቹም፥ «አይዞህ፥ ጳውሎስ፥ አንድ ቀን በመንግሥተ ሰማይ ታርፋለህ» በማለት ሊያጽናኑት ሞክረው ይሆናል። ይህን ቢሉትም ደግሞ ጳውሎስ፥ «ይህ መውጊያ የተሰጠኝ ለዚሁ ነው - ወደ ሰማይ ሄጄ ነበር» ሲል ሊመልስላቸው በቻለ ነበር።

እግዚአብሔር ለጳውሎስ ራእዮችንና መገለጦችን በመስጠትና በተለይም ወደ ሰማይ በመውሰድ አከበረው፤ ዳሩ ግን በሰማይ ሳለ «የማይነገሩ ቃላት» በማሰማትም በተጨማሪ አክብሮታል። በሰማይ ብቻ የሚደመጡትን መለኮታዊ ምስጢራት ሰማ። እነዚህ ነገሮች በእግዚአብሔር እና በሰማይ በሚገኙ ፍጥረታት ብቻ እንጂ፥ በሰዎች አይነገሩም ነበር።

ለመሆኑ የአይሁድ ሃይማኖት አስፋፊዎችስ እንዲህ ስላለ አንድ ልምምድ እንኳን ሊናገሩ ይችሉ ይሆን? የእግዚአብሔር ወዳጅ የነበረው ሙሴ እንኳ፥ ከእግዚአብሔር ጋር የተገናኘው በተራራ ጫፍ ላይ ነበር፤ ይሁንና ጳውሎስ ጌታን በገነት ተገናኘው። ጳውሎስ ይህንን ልምምድ ለማንም ስላልተናገረ፥ በእነዚያ 14 ዓመታት ውስጥ ትልቅ መንፈሳዊ ራስን መግዛት ተለማምዷል። ይህም የእግዚአብሔርን ክብር የሚያመለክት ራእይ ጳውሎስን በሕይወቱና በአገልግሎት ዘመኑ ውስጥ በጽናት እንዲቆም ካስቻሉት ኃይሎች አንዱ እንደ ነበር የሚያጠራጥር አይደለም። የትም ስፍራ ቢኖር - በእስር ቤት፥ በባሕር ላይ፥ በአስቸጋሪ ጉዞዎች - እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እንደ ነበረና በመልካም ሁኔታም ላይ እንዳለ ያውቅ ነበር።

እኔና አንተ ግን እስክንሞት ወይም ጌታችን እስኪመለስ ድረስ ወደ ሰማይ አንሄድም። ዳሩ ግን ዛሬውኑ ከክርስቶስ ጋር በሰማያዊ ስፍራዎች መቀመጣችንን ስናስበው በእጅጉ ያጽናናናል (ኤፌ. 2:6)። «ከሁሉም በላይ» (ኤፌ. 2:21-22) የከበረ የሥልጣንና የድል ሥፍራ አለን። እንደ ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ክብር ባንመለከትም፥ አሁንም የእግዚአብሔር ክብር ተካፋዮች ነን (ዮሐ. 17:22)፤ አንድ ቀንም ወደ ሰማይ ደርሰን የክርስቶስን ክብር እናያለን (ቁ. 24)።

እንዲህ ዓይነቱ ክብር ብዙዎችን ያኩራራል። ሌላ ሰው ቢሆን ኖሮ ለ14 ዓመታት ዝም ብሎ በመቆየት ፈንታ፥ ከመቅጽበት ለዓለም ባሳወቀም ነበር። ዳሩ ግን ጳውሎስ እንዲህ አላደረገም። ከቆይታ በኋላም እውነቱን ገለጸ እንጂ፥ ከንቱ ትምክህት አላሳየም - እውነቶች ለራሳቸው

ይናገሩ። ጳውሎስን በጣም ያሳሰበውም ማንም ሰው የእግዚአብሔርን ክብር ቀምቶ ለእርሱ እንዳይሰጠው ነበር። ሌሎች ስለ ራሱና ስለ ሥራው ትክክለኛ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ፈለገ (ሮሜ 12፡3 ተመልከት)።

ጳውሎስ እንደዚህ ትልቅ ልምምድ እያለው፥ እንዴት ትሁት ሊሆን ይችላል? ይህ የሆነው እግዚአብሔር በሕይወቱ ውስጥ ካስገኘለት ከሁለተኛው ልምምድ የተነሣ ነው።

## በጎነት - እግዚአብሔር ትሁት አደረገው (2ኛ ቆሮ. 12፡7-8)

ጌታ ሕይወታችንን እንዴት ሚዛናዊ ማድረግ እንደሚቻል ያውቃል። በረከቶች ብቻ ቢትረፈረፉልን፥ ልንታበይ እንደምንችል ያውቃል፤ በመሆኑም፥ ሸክሞችም እንዲኖሩን ይፈቅዳል። ጳውሎስ በሰማይ የተመለከተው ልምምድ፥ በምድር ላይ የነበረውን አገልግሎት ሊያከስመው በቻለ ነበር፤ ዳሩ ግን፥ እግዚአብሔር በበጎነቱ ጳውሎስን ከመታበይ ለመታደግ፥ ሰይጣን መውጊያውን እንዲያሳርፍበት አደረገ።

በዚህ ምድር ላይ የሰብዓዊ ሰቆቃ ምሥጢር ሙሉ ለሙሉ እልባት ሊያገኝ አይችልም። አንዳንድ ጊዜ ሰዎች በመሆናችን ብቻ እንሰቃያለን። በዕድሜ እየገፋን ስንሄድ፥ ሰውነታችን ለተለመዱ የሕይወት ችግሮች ይጋለጣል። ምቾቶችን ሊያመጣልን የሚችለው ይኸው አካል ሕመሞችንም ያመጣብናል። የሚያስደስቱን የቤተሰብ አባላትና ወዳጆቻችን መልሰው ልባችንን በኀዘን ሊሰብሩት ይችላሉ። ይህ «ከሰብዓዊ ተፈጥሮ አስቂኝ» ባሕርያት አንዱ ሲሆን፥ ማምለጫ መንገዱም ከሰብዓዊነት ዝቅ ማለት ነው። ይሁንና እንደዚህ ለማድረግ የሚፈልግ ሰው ደግሞ የለም።

አንዳንድ ጊዜ ሞኞችና ለጌታ የማንታዘዝ በመሆናችን እንሰቃያለን። አንድም የራሳችን ዓመፅ ይጎዳናል፤ አሊያም ጌታ በፍቅሩ ሊቀጣን ይችላል (ዕብ. 12 ከቁ. 3 ጀምሮ ተመልከት)። ንጉሥ ዳዊት በኃጢአቱ ምክንያት ብዙ ተሠቃይቷል፤ የኃጢአት ውጤቶች በሥቃይ የተሞሉ ሲሆኑ፥ የእግዚአብሔርም ቅጣት እንዲሁ ነበር [2 ሳሙ. 12፡1-22፤ መዝ. (51) ተመልከት]። እግዚአብሔር በጸጋው፥ ከኃጢአታችን ይቅር ይለናል፤ ዳሩ ግን በአገዛዙ፥ የምንዘራውን እንድናጭድ ያደርጋል።

እንዲሁም መከራ እግዚአብሔር ፈሪሃ-እግዚአብሔር ያለበትን ባሕርይ የሚያንጽበት መሣሪያ ነው (ሮሜ 5፡1-5)። በመሠረቱ፥ ጳውሎስ በሕይወቱ ውስጥ በተፈጸሙ አሰቃቂ ልምምዶች፥

እግዚአብሔር እንዲቀርጸውና እንዲያንጸው ስለ ፈቀደ፥ የበለጸገ የክርስቲያን ባሕርይ ነበረው። በውቂያኖስ ዳርቻ አካባቢ ስትንሸራሸር፥ ጸጥታ ባለበት ቦታዎች የሰሉትን ድንጋዮች ትመለከታለህ፤ ነገር ግን እየተላጋ ማዕበል ያለ ማቋረጥ በሚለትማቸው አካባቢዎች ያሉት ድንጋዮች ውጫዊ ክፍላቸው ለስላሳ ሆኖ ይታያል። እግዚአብሔር እኛ የምንፈቅድለት ከሆነ፥ የሕይወትን «ማዕበሎችና» ነፍሳት በመጠቀም ሊሞርደን ይችላል።

ለጳውሎስ የሥጋ መውጊያ የተሰጠው እርሱን ከኃጢአት ለመጠበቅ ነበር። ወደ ሰማይ ደርሶ የመመለስ ዓይነት አስደናቂ መንፈሳዊ ልምምዶች፥ ሰብዓዊ ራስ-ወዳድነትን የማጎልበት ጠባይ አላቸው፤ ትዕቢት ኩራት ደግሞ ኃጢአትን ወደሚያለማምዱ በርካታ ፈተናዎች ይመራል። የጳውሎስ ልብ በትዕቢት ተሞልቶ ቢሆን ኖሮ፥ እነዚያ ቀጣይ 14 ዓመታት በስኬታማነት ፈንታ በውድቀት ይታጀቡ ነበር።

የጳውሎስ የሥጋ መውጊያ ምን እንደ ነበር አናውቅም። መውጊያ ተብሎ የተተረጎመው ቃል፥ «ሰውን ለማሰቃየት ወይም ለመውጋት የተበጀ ጦር» ማለት ነው። ይህም የሆነ አካላዊ ጉዳት በማስከተል፥ በጳውሎስ ላይ ሕመምና ጭንቀት ያደረሰ ነበር። አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች የዓይን ሕመም ነበረበት (ገላ. 6፡11 ተመልከት) ቢሉም፥ በርግጠኛነት ልናውቀው አንችልም። መከራችን ምንም ቢሆን፥ ጳውሎስ የተማራቸውን ትምህርቶች ልንማርና መጽናናትን ልናገኝ ስለምንችል፥ አለማወቃችንም መልካም ነው።

እግዚአብሔር ልክ ሰይጣን ኢዮብን እንዲፈትን እንደ ፈቀደለት ሁሉ፥ ጳውሎስንም እንዲያሰቃይ ፈቀደለት (ኢዮብ 1-2 ተመልከት)። በዚህ አጥናፈ-ዓለም ውስጥ የክፋት ምንጭ ምን እንደ ሆነ ወይም እግዚአብሔር ክፋት እንዲመጣ ሲፈቅድ በልቡ ውስጥ ያለውን ዓላማ ሙሉ ለሙሉ ባንረዳም፥ እግዚአብሔር ክፋትን እንደሚቆጣጠርና ለክብሩ መግለጫ ሊጠቀምበት እንኳን እንደሚችል አሳምረን እናውቃለን። ሰይጣን ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ በአማኝ ሕይወት ላይ ምንም ሥልጣን የለውም። ጠላት በኢዮብና በጳውሎስ ላይ የፈጸመው ነገር ሁሉ በእግዚአብሔር ፈቃድ የመጣ ነው።

ሰይጣን ጳውሎስን እንዲጎስም ተፈቀደለት። የቃሉም ትርጉም «መምታት፥ በቡጢ መኮርኮም» ማለት ነው። የአንቀጹ የጊዜ አመልካች እንደሚጠቁመው፥ ይህ ሕመም አንድም የማይቋረጥ አሊያም ብዙ ጊዜ የሚከሰት ነው። ጳውሎስ የሚጽፋቸው ደብዳቤዎች፥ የሚሄድባቸው

መንገዶች፥ የሚሰብካቸው ስብከቶች፥ የሚጎበኛቸው አብያተ ክርስቲያናትና በሚያገለግልበት ጊዜም የሚጋፈጣቸው አደጋዎች እንደ ነበሩ ስናስብ፥ የችግሩን ጥልቀት መረዳታችን አይቀርም። ሕመሙ ከእርሱ እንዲወገድ (ጌታው በአትክልት ስፍራው እንዳደረገው [ማር. 14፡32-41]) ሦስት ጊዜ መጸለዩ የሚያስደንቅ አይሆንም (2ኛ ቆሮ. 12፡8)።

እግዚአብሔር መከራዎች ወደ ሕይወታችን እንዲመጡ በሚፈቅድበት ጊዜ፥ መከራዎቹን ልናስተናግድ የምንችልባቸው በርካታ መንገዶች አሉ። አንዳንድ ሰዎች ነጻነትንና ምቾትን እንደ ነፈጋቸው በመግለጽ፥ ተማርረው እግዚአብሔርን ይወቅሱታል። ሌሎች ደግሞ በአስቸጋሪው ልምምድ ውስጥ ምንም ዓይነት ብርታት ስለማያክሉ፥ መከራውን ለመቋቋም በበኩላቸው ጥረት ስለማያደርጉና ተስፋ ስለሚቆርጡ ምንም ዓይነት በረከት ሳያተርፉ ይቀራሉ። የተቀሩት ደግሞ ጥርሳቸውን ነክሰው፥ «እስከ መጨረሻው ድረስ ለመጽናት» ይወስናሉ። ይህ ብርታት ያለበት ምላሽ ቢሆንም፥ ለዕለታዊ ሕይወት የሚያስፈልጋቸውን ጥንካሬ ስለሚያሟጥጥባቸው፥ ከጊዜ በኋላ ዝለው ሊወድቁ ይችላሉ።

ጳውሎስ ከሰይጣን ጉሰማ ነጻ ለመውጣት በመጸለዩ ኃጢአት አድርጎ ይሆን? አይመስለኝም። ከበሽታና ከሕመም ነጻ ለመውጣት ወደ እግዚአብሔር መጸለይ ለክርስቲያን የተለመደ ነገር ነው። እግዚአብሔር እያንዳንዱ አማኝ በሚጸልይበት ጊዜ የግድ ላይፈውሰው ይችላል። ይሁንና ሸክሞቻችንንና ጉድለቶቻችንን ለእርሱ እንድናቀርብ ያበረታታናል። ጳውሎስ ይህ «የሥጋ መውጊያ» ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣበት ጊዜያዊ ፈተና ይሁን፥ ወይም አብሮት ለመኖር የተቆረጠው መሆኑን የማወቅ ችሎታ አልነበረውም።

መከራ የደረሰበት ክርስቲያን በእግዚአብሔር ዘንድ አሳፋሪ ተግባር የፈጸመ እንደ ሆነ እንድናምንላቸው የሚሹ ሰዎች አሉ። «ጌታን ከታዘዝህና በክርስቶስ ያለህን ሁሉ የራስህ አድርገህ ከቆጠርህ፥ በፍጹም አትታመምም» ይላሉ። ይህንን ትምህርት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በፍጹም አላገኘሁም። በብሉይ ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔር ለአይሁዶች የተለየ በረከትና ጥበቃ እንደሚያደርግላቸው የተስፋ ቃል መግባቱ እውነት ነው (ዘዳ. 7 ከቁጥር 12 ጀምሮ)፤ ይሁንና ለአዲስ ኪዳን አማኞች ከበሽታ ወይም ከመከራ ነጻ እንደሚያደርጋቸው የተስፋ ቃል አልገባም። ጳውሎስ ከክርስቶስ ጋር ከነበረው ግንኙነት የተነሣ፥

«ቅጽበታዊ ፈውስ» የማምጣት ብቃት ቢኖረው ኖሮ፥ ለምን ፈውስን ለራሱና እንደ አፍሮዲጡ ለመሳሰሉት ለሌሎች ሰዎች አላስገኘም ነበር? (ፊልጵ. 2 ከቁጥር 25 ጀምሮ)።

በሁለቱ የጳውሎስ ልምምዶች ውስጥ የነበረው ልዩነት ምንኛ የሚቃረን ነው! ጳውሎስ ከገነት ወደ ሕመም - ከክብር ወደ ሥቃይ ተሻገረ። በሰማይ የእግዚአብሔርን በረከት ከቀመሰ በኋላ፥ በምድር ላይ ደግሞ የሰይጣንን ጉሰማ ይቀበላል። እጅግ ከመጠቀው ደስታ፥ ወደ ሥቃይ ይሻገራል፤ ይሁንና ሁለቱም ልምምዶች ጎን ለጎን የሚሄዱ ናቸው። እግዚአብሔር የሚያስፈልገውን ሊያሟላለት እንደሚችል ስለሚያውቅ፥ አንደኛው የክብር ልምምዱ ለማያቋርጥ የመከራ ልምምድ አዘጋጅቶታል። ጳውሎስ ወደ ሰማይ ሄዶ ነበር - ከዚህም ሰማይ ወደ እርሱ ሊመጣ እንደሚችል ተማረ።

## ጸጋ - እግዚአብሔር ረዳው (2ኛ ቆሮ. 12፥9-10)

በዚህ ሕመምን ባዘለ ልምምድ ውስጥ ሁለት መልእክቶች ነበሩ። የሥጋ መውጊያው ሰይጣን ለጳውሎስ የሚያስተላልፈው መልእክት ሲሆን፥ እግዚአብሔርም ለእርሱ ሌላ መልእክት ነበረው - የጸጋ መልእክት። በቁ. 9 ላይ የሚገኘው የግሡ የጊዜ አመልካች አስፈላጊ ነው፡- «እርሱም [እግዚአብሔር] [ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ] አለኝ።» እግዚአብሔር ለጳውሎስ ከእርሱ ጋር የሚሰነብት መልእክት ሰጠው። ጳውሎስ በሰማይ ሳለ የሰማቸውን ቃላት ለእኛ እንዲያጋራ አልተፈቀደለትም፤ ይሁንና እግዚአብሔር በምድር ላይ የሰጠውን ቃላት ያካፍለናል - እነዚህም በጣም የሚያጽናኑ ናቸው።

መልእክቱም የጸጋ መልእክት ነበር። ጸጋ ምንድነው? ጸጋ እግዚአብሔር ለሚያስፈልገን ነገር ሁሉ የምንፈልገው ጊዜ የሚሰጠን ስጦታ ነው። እግዚአብሔር በጸጋው የማይገባንን ነገር ይሰጠናል፤ በምሕረቱ ደግሞ የሚገባንን ነገር አይሰጠንም የሚለው አባባል ማለፍያ ነው። አንድ ሰው ጸጋ የሚለውን ቃል በክርስቶስ ከፋይነት የተገኘ የእግዚአብሔር ባለጸግነት ብሎታል። «እኛ ሁላችን ከሙላቱ [ከክርስቶስ] ተቀብለን በጸጋ ላይ ጸጋ ተሰጥቶናልና» (ዮሐ. 1፥16)።

ይህም የበቂ ጸጋ መልእክት ነበር። ከቶውንም የጸጋ እጦት አይስተዋልም። እግዚአብሔር ለመንፈሳዊ አገልግሎታችን (2ኛ ቆሮ. 3፥4-6)፥ ለቁሳዊ ፍላጎታችንና (9፥8) ለሥጋዊ ጉድለታችን (12፥9) ሁሉ በቂ ነው። የእግዚአብሔር ጸጋ ሊያድነን ከበቃ፥ በመከራችን ወቅት ሊጠብቀንና ሊያበረታንም እንደሚበቃ የሚያጠራጥር አይሆንም።

መልእክቱ የሚያበረታ የጸጋ መልእክት ነበር። እግዚአብሔር የራሱን ብርታት እንላበስ ዘንድ እንድንደክም ይፈቅዳል። ይህም የማያቋርጥ ሂደት ነው - «ኃይሌ በድካም[ህ] ይፈጸማል» (ቁ. 9)። በጠንካራነቱ የሚተማመን ጥንካሬ፥ በመሠረቱ ደካማነት ነው፤ ዳሩ ግን ደካማነቱን የሚያውቅ ድካም ብርታት ነው።

በክርስትና ሕይወታችን፥ ብዙዎቹን በረከቶች የምንቀበለው በለውጥ እንጂ፥ በምትክ አይደለም። ጳውሎስ ሕመሙ ከእርሱ እንዲለይ ሦስት ጊዜ በጸለየበት ጊዜ፥ እግዚአብሔርን ሌላ ምትክ እንዲሰጠው እየጠየቀው ነበር፡- «በበሽታ ምትክ ጤንነትን፥ በሕመምና በድካም ፈንታ ነጻነትን ስጠኝ» ማለቱ ነበር። እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ ጉድለትን የሚሞላው በምትክ ሲሆን፥ ዳሩ ግን ሌላ ጊዜ በለውጥ ነው። መከራውን አያስወግደውም፤ ዳሩ ግን ጸጋውን ስለሚሰጠን፥ የመከራው ጎጂ ገጽታ ወደ ጠቃሚ መልክ ይለወጣል።

ጳውሎስ ስለ ችግሩ ሲጸልይ፥ እግዚአብሔር በሚያደርገው ነገር ላይ የጠለቀ መረዳት ሰጠው። ከዚያም ጳውሎስ ይህ የሥጋ መውጊያ ከእግዚአብሔር እንደ ተሰጠው ተረዳ። ይህ ምንኛ ያልተለመደ ስጦታ ነው! ጳውሎስ የሚያደርገው አንድ ነገር ብቻ ነበር - ስጦታውን ከእግዚአብሔር ዘንድ መቀበልና እግዚአብሔር ዓላማዎቹን ከዳር እንዲያደርስ ፈቃደኛ መሆን። እግዚአብሔር ጳውሎስ «ያለ ልክ ከፍ ከፍ» እንዳይል ስለ ፈለገ፥ ይህንኑ ፍላጎት ከዳር የሚያደርሰውም በዚሁ መንገድ ነበር።

ጳውሎስ መውጊያውን ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደ መጣ ስጦታ አድርጎ በተቀበለ ጊዜ፥ ይህ የእግዚአብሔር ጸጋ ወደ ሕይወቱ ውስጥ ዘልቆ በመግባት የሚሠራበትን ሁኔታ አመቻቸ። እግዚአብሔር ለጳውሎስ የተናገረውና የጸጋውን ዋስትና የሰጠው ከዚያ በኋላ ነበር። አንተም በመከራ ውስጥ በምታልፍበት ጊዜ፥ የእግዚአብሔርን ቃል በማጥናትና በማሰላሰል ተጨማሪ ጊዜ አሳልፍ፤ በዚህም ጊዜ እግዚአብሔር እንደሚናገርህ እርግጠኛ ልትሆን ትችላለህ። እግዚአብሔር ሁልጊዜም ልጆቹ በችግር ውስጥ በሚሆኑበት ጊዜ፥ ለእነርሱ የሚሆን የተለየ መልእክት አለው።

እግዚአብሔር ለጳውሎስ ምንም ማብራርያ አልሰጠውም፤ ይልቁንም፥ የተስፋ ቃል ሰጠው፡- «ጸጋዬ ይበቃሀል።» የምንኖረው በማብራርያዎች ላይ ሳይሆን፥ በተስፋ ቃሎች ላይ ተደግፈን ነው። ስሜቶቻችን ይለዋወጣሉ፤ ዳሩ ግን የእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች

ከተውንም አይለዋወጡም። የተስፋ ቃሎች እምነትን ያነቃቃሉ፤ እምነት ደግሞ ተስፋን ያጠናክራል።

ጳውሎስ የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል ተማመነና እግዚአብሔር ከሚያቀርብለት ጸጋ ተቀበለ፤ ይህም አሳዛኝ መስሎ የታየውን ነገር ወደ ድል ለወጠው። እግዚአብሔር መውጊያውን በማስወገድ አልነበረም ሁኔታውን የለወጠው - አንድ አዲስ ነገር - ጸጋ በማከል ነበር እንጂ! አምላካችን «የጸጋ ሁሉ አምላክ» ነው (1ኛ ጴጥ. 5፡10)፤ ዙፋኑም «የጸጋ ዙፋን» ነው (ዕብ. 4፡16)። የእግዚአብሔር ቃል «የጸጋው ቃል» (የሐዋ. 20፡32) ነው፥ የተስፋ ቃሉም «ጸጋን አብልጦ ይሰጣል» (ያዕ. 4፡6) የሚል ነው። ችግሮቻችንን የምንመለከትበት ሁኔታ ምንም ዓይነት ቢሆን፥ እግዚአብሔር ለጉድለታችን ሁሉ ብቁ ነው።

ዳሩ ግን እግዚአብሔር ጸጋውን የሚሰጠን ዝም ብለን መከራችንን «እንድንታገሥ» ብቻ አይደለም። ደኅንነትን ያላገኙ ሰዎች እንኳ በመከራ መታገስን ሊያሳዩ ይችላሉ። የእግዚአብሔር ጸጋ ካለንባቸው ሁኔታዎችና ስሜቶች በመላቀቅ፥ መጥቀን እንድንወጣና ችግሮቻችን መልካሙን ነገር ለማከናወን ምክንያት እንዲሆኑን ሊያስችለን ይገባል። እግዚአብሔር በይበልጥ አዳኛችንን እንመስል ዘንድ፥ ባሕርያችንን ሊያንጽ ይሻል። የእግዚአብሔር ጸጋ ጳውሎስ መከራውን እንዲቀበል ብቻ ሳይሆን፥ በመከራዎቹም እንዲመካ አስችሎታል። መከራው ረግጦ የገዛው ጌታ ሳይሆን፥ መልካም ይሆንለት ዘንድ የሠራ አገልጋዩ ነበር።

ጳውሎስ በመከራው ምክንያት ያገኘው ትርፍ ምንድን ነው? አንድኛው ነገር፥ በሕይወቱ ውስጥ የክርስቶስን ኃይል መለማመዱ ነው። እግዚአብሔር የጳውሎስን ድካም ወደ ብርታት ለወጠው። «ያድርብኝ ዘንድ» ተብሎ የተተረጎመው ቃል «ድንኳንን ከላይ መዘርጋት» የሚል ትርጉም አለው። ጳውሎስ ሰውነቱን እንደ ደካማ ድንኳን ይመለከተዋል (2ኛ ቆሮ. 5 ከቁጥር 1 ጀምሮ)፤ ይሁንና የእግዚአብሔር ክብር ወደዚያ ድንኳን መጥቶ የተቀደሰ ማደርያ ያደርገዋል።

ለጳውሎስ ሌላም ነገር ተደርጎለታል - በመከራው ለመመካት ችሎ ነበር። ይህም ማለት ከጤንነት ይልቅ ሕመምን መርጧል ማለት ሳይሆን፥ ዳሩ ግን መከራዎቹን እንዴት ወደ ጠቃሚ ነገሮች መለወጥ እንደሚቻል ያውቅ ነበር። እንግዲህ ለውጡን ያመጣው ምንድነው? የእግዚአብሔር ጸጋና የእግዚአብሔር ክብር። በእነዚህ መከራዎችና ችግሮች «ይደሰታል»፤ ይህም ሥነ-ልቦናዊ ሚዛናዊነቱ ስለ ተዛባና በሕመም ደስ

ይለው ስለ ነበረ ሳይሆን፥ ዳሩ ግን መከራውን የሚቀበለው ለኢየሱስ ክርስቶስ በመሆኑ ነው። አስቸጋሪ የሕይወት ገጽታዎችን በተቀበለበትና ባስተናገደበት መንገድ፥ እግዚአብሔርን እያስከበረ ነበር።

ፒ. ቲ. ፎርሳይት፥ «መከራ እንዲወገድ ሳይሆን እንዲለወጥ መጸለዩ ትልቅ ነገር ነው» በማለት ጽፈዋል። እውነታቸውን ነው። ጳውሎስ ድልን የተቀዳጀው በምትክ ሳይሆን፥ በለውጥ ነበር። በዚህም የእግዚአብሔርን የጸጋ ብቃት ተረድቷል።

ከጳውሎስ ልምምድ ውስጥ፥ በርካታ ተግባራዊ ትምህርቶችን ልንማር እንችላለን።

1. ራሱን ለሰጠ አማኝ ከሥጋዊ ይልቅ መንፈሳዊው ነገር እጅግ በጣም ጠቃሚ ነው። ይህም ሥጋዊውን ነገር ገለል እናድርገው ለማለት አይደለም - ሰውነታችን የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ማደርያ ነውና። በምትኩ ሥጋችን በራሱ የነገሮች ሁሉ የመጨረሻ ግብ እንደ ሆነ አድርገን መውሰድ የለብንም ለማለት ነው። በዚህ ዓለም ውስጥ የእግዚአብሔርን ሥራ ለማከናወን የሚረዳን መሣሪያ ነው። እግዚአብሔር ክርስቲያናዊ ባሕርያችንን በማሳደግ የሚያከናውነው ተግባር፥ የባሕርይ ለውጥ ከማይታይበት የሥጋ ፈውስ እጅግ የላቀ ነው።

2. እግዚአብሔር ሸክሞችንና በረከቶችን፥ መከራንና ክብርን እንዴት ሚዛናዊ ማድረግ እንደሚቻል ያውቃል። ሕይወት ከተለያዩ ንጥረ-ነገሮች እንደሚቀመም መድኃኒት ሁሉ፥ በውስጡ ከሚገኙት ባሕሪያት አንዳንዶቹ ሊጎዱን ይችላሉ፤ ዳሩ ግን በተገቢው ሁኔታ ሲዋሃዱ ይጠቅሙናል።

3. ሕመም ሁሉ የኃጢአት ውጤት አይደለም። የኢዮብ አጽናኞች ሙግት፥ ኢዮብ የሚሰቃየው ኃጢአት በመሥራቱ ነው የሚል ነበር። ይሁንና ሙግታቸው በኢዮብም ሆነ በጳውሎስ ላይ የሚሠራ አልነበረም። እግዚአብሔር በሕይወታችን ውስጥ ታላቅ ተግባር ለማከናወን፥ ሰይጣን መከራ እንዲያመጣብን የሚፈቅድባቸው ጊዜያት አሉ።

4. ከሕመም የከፋም ነገር አለ - ይኸውም ኃጢአት ሲሆን፥ ከሁሉም የሚከፋው ኃጢአት ደግሞ ትዕቢት ነው። በእግዚአብሔር ላይ ከሚያምፅ ጤነኛ ሰው ይልቅ፥ ለእግዚአብሔር እየተገዛና በጸጋው ደስ እየተሰኘ የሚኖር በሽተኛ ሰው እጅጉን ይመረጣል። ልዑሉ

እግዚአብሔር፥ ከሁሉም በላይ ኩሩ (ዕቡይ) በሆነው በሰይጣን በመጠቀም፥ ጳውሎስን ትሁት ማድረጉ የሚያስገርም ነው።

5. ሥጋዊ ጉዳት ውጤታማ ክርስቲያናዊ አገልግሎት ከመስጠት ሊያግደን አይገባም። የዛሬዎቹ ቅዱሳን የራሳቸውን ምቾት ወደ መጠበቅ ስለሚያጋድሉ፥ ትንሽ ሕመም በሚሰማቸው ጊዜ ሁሉ፥ ከቤተ ክርስቲያን ለመቅረት ወይም የአገልግሎትን ግብዣ ላለመቀበል፥ እንደ ማመካኛ አድርገው ይጠቀማሉ። ጳውሎስ የሥጋ መውጊያው የማስናከያ ዓለት እንዲሆንበት አልፈቀደም። እንዲያውም እግዚአብሔር ያንኑ መውጊያ ወደ መወጣጫ ደረጃ እንዲለወጥለት ፈቀደ።

6. ሁልጊዜም በእግዚአብሔር ቃል ልናርፍ እንችላለን። ሁልጊዜም በመከራና በሥቃይ ጊዜያት ለእኛ የሚሆን የመጽናኛ መልእክት አለው።

ታላቋ ፈረንሣዊ የረቂቅ ምሥጢር ተከታይ የነበረችው ማዳም ጉዮን በመከራ ውስጥ ለነበረ ጓደኛዋ፥ «አሜን ብለው በተቀበሉት ኃዘን ውስጥ ያለውን ኃይል ብታውቀው ኖሮ ምንኛ በተጽናናህ!» ስትል ጽፋለት ነበር።

ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ስለ ታመነና በእግዚአብሔር ጸጋ ላይ ስለ ተደገፈ፥ ይህንን ኃይል አውቆት ነበር።
ዛሬ ያ ኃይል የአንተ ሊሆን ይችላል።

## ለዝግጅት የሚረዱ ሦስት ነጥቦች

### 2ኛ ቆሮንቶስ 12፡ 11-13፡ 14

ጳውሎስ ደብዳቤውን ለመዝጋት በሚቃረብበት ወቅት፥ ለቆሮንቶስ ሰዎች የነበረው ታላቅ ፍቅር አንድ የመጨረሻ ልመና እንዲያቀርብ ገፋፋው። በቤተ ክርስቲያናቸው የሚያደርገው ሦስተኛው ጉብኝቱ ለእርሱም ሆነ ለእነርሱ የሚያሳዝን ነገር እንዲሆን አልፈለገም ነበር። ለእነርሱ ልቡን ከፍቶላቸዋል፤ ስለ አገልግሎቱ ማብራርያ ሰጥቶአቸዋል፤ ለነቀፋዎቻቸው ምላሽ ሰጥቷል፤ እንዲሁም ለእግዚአብሔር ቃል እንዲገዙና ጌታን እንዲታዘዙም ገፋፍቶአቸዋል። እንግዲህ ከዚህ በላይ ምን ሊያደርግ ወይስ ምን ሊል ይችል ነበር?

በዚህ በደብዳቤው መዝጊያ ክፍል ውስጥ ጳውሎስ የቆሮንቶስ ሰዎችን ወደ መታዘዝና መገዛት ለማምጣት በሚያደርገው ጥረት፥ በሦስት የአቀራረብ ዘዴዎች ተጠቅሟል።

አሳፈራቸው (2ኛ ቆሮ. 12፡ 11-21) ልጆች በነበርን ጊዜ፥ ከወላጅም ይሁን ከጎረቤት፥ «ኀፍረት አይሰማህም!» የሚል ቃል ሲሰነዘርብን፥ ስንት ጊዜ ሰምተን ይሆን? ሰዎች ስለ ክፉ ነገራቸው ወይም አመለካከታቸው ማፈራቸው መልካም ነው። አንድ ጥፋተኛ ሰው የኀፍረት ስሜት የማይሰማው ከሆነ፥ ደንዳና ልብና የደነዘዘ ሕሊና እንዳለው ይታወቃል። «ርኩስን ነገር ስለ ሠሩ አፍረዋልን? ምንም አላፈሩም፤ እፍረትንም አላወቁም» (ኤር. 6፡ 15)።

በመጀመሪያ፥ ጳውሎስ የቆሮንቶስን ሰዎች ሊያመሰግኑት ባለመፈለጋቸው በመውቀስ ያሳፍራቸዋል (2ኛ ቆሮ. 12፡ 11-13)። እርሱን ለትምክህት ከመገፋፋት ይልቅ፥ ስለ እርሱ በትምክህት ሊናገሩ ይገባቸው ነበር። ከዚህ ይልቅ ግን፥ የቆሮንቶስ ሰዎች ተወዳጅነትን አትርፈው ቤተ ክርስቲያናቸውን በመቆጣጠር ላይ ስለነበሩት «ምጡቅ-ሐዋርያት»፥ የአይሁድ ሃይማኖት አስፋፊዎች በትምክህት ይናገሩ ነበር።

ጳውሎስ ከእነዚህ ሰዎች ያንስ ነበር? በምንም ዓይነት! የቆሮንቶስ ሰዎች ጳውሎስን በተግባር አይተውታል፤ እንዲያውም፥ ነፍሳቸውን ጭምር ወደ ትክክለኛ አቅጣጫ የመራላቸው ባለውለታቸው ነበር።

በመካከላቸውም ሐዋርያነቱን የሚያረጋግጡ ተአምራዊ ነገሮችን አድርጎ ነበር (ዕብ. 2፡ 1-4)። ውጫዊ ስደትንና ውስጣዊ ችግሮችን ተጋፍጦ፥ በቆሮንቶስ ውስጥ በአገልግሎቱ ጸንቶ ነበር። ከቤተ ክርስቲያኗ ምንም ነገር አልወሰደም ነበር። ጳውሎስ አሁንም «በእናንተ ላይ ሸክም ሳልሆን ከመቅረቴ በቀር፥ ከሌሎች አብያተ-ክርስቲያናት እናንተን ያሳነስሁአችሁ በምንድነው? ይህም ጥፋት ሆኖ ከተቆጠረ ይቅር በሉኝ» (2ኛ ቆሮ. 12፡ 13 - አዲስ ትርጉም) በማለት በረቀቀ ቅኔአዊ አነጋገር ተጠቅሟል።

ከክርስትና ሕይወት አደጋዎች አንዱ፥ በረከቶቻችንን እንደ ልማዳዊ ነገሮች አድርገን መውሰዳችን ነው። ፈሪሃ-እግዚአብሔር ያደረበት መጋቢ ወይም የሰንበት ትምህርት ቤት አስተማሪ ብዙ ነገር ሊያደርግልን ይችላል፤ እኛ ግን እንደ ተራ ነገር እንቆጥረዋለን። (ላለማዳላት፥ አንዳንድ ጊዜ መጋቢዎች የቤተ ክርስቲያን ምዕመናን በረከቶችን እንደ ተራ ነገር ቆጥረው እንዲቀበሉ በማድረጉ በኩል ጥፋት እንዳለባቸው ለመግለጽ እወዳለሁ።) በዚህ ዝንባሌ በመመራት ካለማመስገናቸው የተነሣ ጳውሎስ ሲያሳፍራቸው እናያለን (ቁ. 14-18)።

ይህን የመሳሰሉ ችግሮች ቢኖሩም ቅሉ፥ ጳውሎስ ግን የቆሮንቶስን ሰዎች በመጎብኘት ታማኝ ነበር፤ እናም አሁን ሦስተኛውን ጉብኝት ሊያደርግ ነበር (13፡1 ተመልከት)። በማመስገን ፈንታ፥ የቆሮንቶስ ሰዎች ጳውሎስስ ዕቅዱን በመቀየሩ ወቀሱት። ጳውሎስ ከቤተ ክርስቲያን ምንም ድጋፍ አላገኘም ነበር፤ ይልቁንም፥ ለቤተ ክርስቲያን በመሥዋዕትነት ሰጥቷል። ይሁን እንጂ እነርሱ ደግሞ ከሌሎች ጋር በመካፈል አመስጋኝነታቸውን ለማሳየት ፈቃደኞች አልነበሩም። ጳውሎስ ይበልጥ ሲወዳቸው፥ እነርሱ ደግሞ ባነሰ ሁኔታ የሚወዱት ይመስል ነበር። ለምን? ምክንያቱም ለክርስቶስ እውነተኛ ፍቅር አልነበራቸውምና ነው (ቁ. 13)። ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያንን ለመርዳት ያለውን ነገር ለማካፈል ይፈልግ ነበር።

የአይሁድ ሃይማኖት አስፋፊዎች ቤተ ክርስቲያንን ለመበዝበዝ የማታለያ ዘዴዎችን ይጠቀሙ ነበር (4፡2 ተመልከት)፤ ዳሩ ግን ጳውሎስ ግልጽና ከአታላይነት የራቀ ነበር። ጳውሎስ የፈጸመው ብቸኛው «በደል» ከእነርሱ የገንዘብ ድጋፍ አለመቀበሉ ነበር። በዚህ ትጥቃቸውን ስላስፈታቸው፥ ገንዘብ ብቻ እንደሚፈልግ አድርገው ለሚያቀርቡት ክስ ምንም ምላሽ ሊሰጡ አይችሉም ነበር። ከእርሱ ጋር አብረው

ከሚያገለግሉት ጳውሎስ የላካቸው ሰዎችም ቢሆኑ፥ አንዳቸውም በምንም መንገድ አልበዘበዙዋቸውም ወይም መጠቀሚያ አላደረጉዋቸውም ነበር።

ልጆች ወላጆቻቸው ለሚያደርጉላቸው በጎ ነገር ሳያመሰግኑ ሲቀሩ እጅጉን ያሳዝናል። እንዲሁም ደግሞ የእግዚአብሔር ልጆች «መንፈሳዊ ወላጆቻቸው» ለሚያደርጉላቸው ነገሮች ባለውለታነታቸውን ሲዘነጉ አሳዛኝ ይሆናል። ለዚህ ለምስጋና እጦት መነሻው ምንድነው? ጳውሎስ በቀጣዩ አንቀጽ ውስጥ ገልጾታል - የቅድስና መታጣት (ቁ. 19-21)። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የከፉ ኃጢአቶች ነበሩና ጳውሎስ ለጉብኝት ከመምጣቱ በፊት ፍርድ ተሰጥቶባቸው እንዲወገዱ ይፈልጋል። ይህ ካልሆነ ግን የአሁኑም ጉብኝቱ በሌላ አሳዛኝ ልምምድ ይቋጫል።

ምናልባትም አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን አባላት፥ «ጳውሎስ ዳግም ሊጎበኘን ከመጣ፥ ተጨማሪ ችግሮችን ይፈጥርብናል» ብለው እየተናገሩ ይሆናል። ጳውሎስ መሻቱ ችግሮችን መቅረፍና አብያተ ክርስቲያናትን ማጠናከር እንደ ሆነ በግልጽ ይናገራል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙትን ኃጢአቶች ለማስወገድ በታማኝነት መጋፈጥንና ድፍረትን ይሻሉ። «አለባብሶ ማረሱ» ግን፥ የበለጠ ለከፋት ይዳርጋል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኝ ኃጢአት በሰው ሰውነት ውስጥ እንዳለ ካንሰር ነው - ተቆርጦ መውጣት አለበት።

እስኪ ቤተ ክርስቲያኒቱ የወደቀችባቸውን ኃጢአቶች እናስብ - በመናዘዝና ንስሐ በመግባት ሊወገዱ የሚገባቸው ኃጢአቶች። እርስ በርሳቸው ስለሚመቀኙ ይጣሉ (ይከራከሩ) ነበር። ገንፍሎ የሚወጣ ቁጣም ነበረባቸው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሥጋዊ ሤራዎችን፥ አድመኛነትንና ሐሜትን ያስፋፉ ነበር። ይህም ሁሉ ከትዕቢትና የራስን አስፈላጊነት ከፍ አድርጎ ከመመልከት የመነጨ ሲሆን፥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሁከትን አስከትሏል (2ኛ ቆሮ. 12፡20)። ይህንን የኃጢአቶች ዝርዝር ከ1ኛ ቆሮንቶስ 13 ጋር ብናወዳድር፥ በማኅበረ-ምዕመናኑ መካከል የፍቅር መተሳሰብ እንዳልነበረ እንመለከታለን።

ከእነዚህ «የመንፈስ ኃጢአቶች» ጎን (7፡1)፥ ታላላቅ የሥጋ ኃጢአቶችም ነበሩ - ዝሙትና ፍትወት። ጳውሎስ ስለ እነዚህ ኃጢአቶች በ1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 5-6 ውስጥ ገልጾአል፤ ዳሩ ግን አንዳንድ ጥፋተኞች ባለመታዘዛቸው ጸንተው ነበር። ለአዲሱ ሕይወት ራሳቸውን

ከመስጠት ይልቅ፥ አሮጌው ሕይወታቸው ዳግመኛ በላያቸው ላይ ግዛቱን እንዲያስፋፋ ይፈቅዱለት ነበር (1ኛ ቆሮ. 6፡9-11)።

ጳውሎስ ለዚህ ለሦስተኛው ጉብኝት ብዙም አልጓጓም ነበር። ቤተ ክርስቲያን እንደሚፈልጋት ሳትሆን ቀርታ ላለማየት ከመሥጋቱም፥ እርሱም እንደሚፈልጉት ሆኖ ሳይገኝ እንዳይቀር ፈርቶ ነበር። ይሁን እንጂ፥ ምንም እንኳ በሁኔታው ማፈሩና ማዘኑ ባይቀርም (የቃሉ ትርጉም «ለሞተ ሰው ማዘን»ን ያመለክታል)፥ ዳሩ ግን ነገሮችን የተቃና ለማድረግ አሁንም በሥልጣኑ እንደሚጠቀም ቃል ይገባላቸዋል። ለእነርሱ የነበረው ፍቅር እጅግ ታላቅ በመሆኑ፥ እነዚህን ችግሮች ችላ በማለት ቤተ ክርስቲያኒቱን ማዳከማቸውን እንዲቀጥሉ ሊፈቅድላቸው አይሻም ነበር።

የቆሮንቶስ ሰዎች ማፈር ሲገባቸው ሳለ፥ እነርሱ ግን አላፈሩም ነበር። ጳውሎስ መልእክቱን በትክክል ማስተላለፉን ለማረጋገጥ ሲል፥ ቀጥሎ በምንመለከተው ሁለተኛው የአቀራረብ ዘዴ ይጠቀማል።

## አስጠንቀቃቸው (2ኛ ቆሮ. 13፡1-8)

በዚህ ስፍራ ሁለት ማስጠንቀቂያዎች ቀርበዋል።

«ራሳችሁን አዘጋጁ» (2ኛ ቆሮ. 13፡1-4)። በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ኃጢአትን ለማስወገድ በምንጣጣርበት ጊዜ፥ የምንመራው በሐሜቶች ሳይሆን በሐቆች መሆን አለበት። ጳውሎስ ዘዳግም 19፡15ን የጠቀሰ ሲሆን፥ ተመሳሳይ አሳብ ያላቸውን ምንባቦች ከዘኍልቁ 35፡30 እና ከማቴዎስ 18፡16፥ እንዲሁም ከ1ኛ ጢሞቴዎስ 5፡19 ላይ እናገኛለን። በተለይ የቤተ ክርስቲያን ምዕመናን እርስ በርሳቸው በማይስማሙበት ጊዜ የምስክሮች መኖር የነገሩን እውነትነት ለማረጋገጥ ይረዳል።

የቤተ ክርስቲያን ምዕመናን ኢየሱስ በማቴዎስ 18፡15-20 የሰጣቸውን ትዕዛዛት ቢከተሉ ኖሮ፥ ራሳቸው ብዙዎቹን ችግሮቻቸውን ለመፍታት ይችሉ ነበር። አማኞች የጌታችንን ትዕዛዛት ባለማክበራቸው ምክንያት ብቻ፥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አናሳ አለመግባባቶች ወደገዘፉና የተወሳሰቡ ችግሮች ሲሸጋገሩ ተመልክቻለሁ። ጉዳዩ የሚመለከታቸው ግለሰቦች በእውነተኛነት መፍትሔ እስካልፈለጉ ድረስ፥ መጋቢውና ማህበረ-ምዕመናኑ ጣልቃ መግባት የለባቸውም።

የአይሁድ መምሕራን ጳውሎስን ደካማ ነው በማለት ከሰውታል (2ኛ ቆሮ. 10፡7-11 ተመልከት)። የጳውሎስ አገልግሎት የውሃትና ገርነት የሚታይበት ሲሆን (1፡24 ተመልከት)፥ የእነርሱ ግን ጠንካራና አምባገነናዊ ነበር። አሁን ግን ጳውሎስ እንዴት ጠንካራ ሊሆን እንደሚችል እንደሚያሳያቸው ያረጋግጥላቸዋል - ችግሮቹን ለመቅረፍ የሚያስፈልገው ይኸው ከሆነ። ማስጠንቀቂያውም፥ «አልራራላችሁም!» የሚል ነበር። የተጠቀመውም «በጦርነት ውስጥ መራራት»ን የሚያመለክት ቃል ነው። ባጭሩ፥ ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ቃል ሥልጣን በሚቃወም በማንኛውም ሰው ላይ ጦርነት እያወጀ ነበር።

ባላንጣዎቹ፥ «እስኪ ጳውሎስ እውነተኛ ሐዋርያ መሆኑን ያረጋግጥ» ብለው ነበር። የጳውሎስም ምላሽ፥ «የደከምሁ በምመስልበት ወቅት፥ እኔም እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ብርቱ ነኝ» የሚል ነበር። በመስቀል ላይ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ደካማነትን አሳይቷል፤ ይሁንና መስቀሉ አሁንም «የእግዚአብሔር ኃይል» ነው (1ኛ ቆሮ. 1፡18)። ጳውሎስ ቀደም ብሎ የመንፈሳዊ ውጊያውን ዘዴ የገለጸ ሲሆን (2ኛ ቆሮ. 10፡1-6)፥ አንባቢዎቹም ነገሮችን ላይ ላዩን በመመልከት ምትክ በጥልቀት እንዲያጤኑ አስጠንቅቋቸዋል።

በዓለም መመዘኛ መሠረት፥ ጳውሎስና ኢየሱስ ሁለቱም ደካሞች ነበሩ፤ ዳሩ ግን በጌታ መመዘኛ መሠረት፥ ሁለቱም ብርቱዎች ነበሩ። ለምሳሌ በአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሥነ-ሥርዓት ጉዳዮችን ፊር በሚያስይዝበት ጊዜ፥ መቼ «መድከም» እና መቼ «መበርታት» እንዳለበት የሚያውቅ ሰው አዋቂና በሳል አገልጋይ ነው።

አሁን በሞት ተለይቶ ወደ ጌታ የሄደ አንድ መጋቢ ወዳጄ፥ በምድረክ ላይ በሚቆምበት ጊዜ ዝግ ያለ ባሕርይ ነበረው፤ በግል አገልግሎቱም ቢሆን አቀራረቡ ይኸው ነበር። እናም አንዲት እንግዳ ሴት፥ ስብከቱን ሰምታ ስታበቃ፥ «ስብከቱን የሚጀምርበትን ጊዜ እየተጠባበቅሁ ነበር» እስከ ማለት ደርሳለች። ግን ለምን? ምክንያቱም እርሷ የተላመደችው ብርሃን ከሚያንጸባርቅ ይልቅ፥ ሙቀት ከሚፈጥር የጋለ የስብከት ድምፅ ጋር በመሆኑ ነው። ይሁንና ወዳጄ ለአገልግሎት እውነተኛዎቹ መመዘኛዎች የትኞቹ እንደ ነበሩ ስለሚያውቅ፥ ጠንካራ ቤተ ክርስቲያን ለማነጽ ችሏል። «በክርስቶስ» እንዴት «መድከም» እና «መበርታታ» እንደሚገባ ያውቅ ነበር።

ዛሬ ሰዎች አገልግሎትን እንዴት ይለካሉ? በኃይለኛ የንግግር ችሎት ወይስ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ይዘት? በክርስቲያናዊ ባሕርይ ወይስ ሰዎችና ጋዜጦች በሚያናፍሱት ወሬ? እጅግ በርካታ ክርስቲያኖች አገልግሎቶችን በሚለኩበት ጊዜ የዓለምን መመዘኛዎች ይከተላሉ። ሆኖም ግን ለእግዚአብሔር መመዘኛዎች ብቻ ትኩረት ሊሰጡ በተገባ ነበር።

«ራሳችሁን መርምሩ!» (2ኛ ቆሮ. 13፡5-8)። ይህ አንቀጽ ጳውሎስ በቁጥር 3 ላይ ማስረጃ ላለው ቃል በማብራሪያነት የሚያገለግል ነው። ጳውሎስ፥ «እኔን ስትመረምሩኝ ነበር፤ ዳሩ ግን ለምን ራሳችሁን ለመመርመር ጊዜ አትወስዱም?» በማለት ይጽፋል። እኔም ብሆን ከግል የአገልግሎት ልምዴ የተረዳሁት፥ ሌሎችን ለመመርመርና ለመኮነን የሚፈጥኑ ሰዎች፥ ራሳቸው በከፋ ኃጢአት ውስጥ የሚኖሩ መሆናቸውን ነው። በርግጥ፥ ራስን የተሻለ አድርጎ ለማቅረብ አንድኛው አማራጭ ሌላውን ሰው መኮነን ነው።

በመጀመሪያ፥ ጳውሎስ የቆሮንቶስ ሰዎች ልባቸውን እንዲመረምሩና በርግጥ ዳግም ተወልደው፥ የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባላት ሆነው እንደ ሆነ ይመለከቱ ዘንድ ይነግራቸዋል፤ በልባችሁ ውስጥ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ምስክርነት አለ? (ሮሜ 8፡9፥ 16)። ወንድሞችን ትወዳላችሁ? (1ኛ ዮሐ. 3፡14)። ጽድቅን ታደርጋላችሁ? (1ኛ ዮሐ. 2፡29፤ 3፡9)። ዓለምን አሸንፋችሁ፥ ፈሪሃ-እግዚአብሔር ያለበትን የመለየት ሕይወት ትኖራላችሁ? (1ኛ ዮሐ. 5፡14)። እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ለማረጋገጥ፥ ከሕይወታችን ጋር ከምናዛምዳቸው በርካታ መመዘኛዎች ጥቂቶቹ ብቻ ናቸው።

በመጋቢነት ካገለገልኋቸው አብያተ ክርስቲያን በአንድኛው ውስጥ፥ በወጣቶች ቡድን የታቀፈና ችግር ጠንሳሽ የሆነ አንድ ልጅ ነበር። ስጦታ ያለው የሙዚቃ መሣሪያ ተጫዋችና የቤተ ክርስቲያን አባል ቢሆንም፥ ዳሩ ግን ችግር እየፈጠረ አስቸግሮን ነበር። በአንድ የክረምት ዕረፍት ወቅት፥ ይህ ልጅ ከቤተ ክርስቲያናችን የወጣቶች ቡድን አባላት ጋር ሔዶ ስለ ነበረ በዚያኑ አጋጣሚ፥ የወጣቶች መሪዎች፥ የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪዎችና እኔም ጭምር ለዚህ ልጅ በየቀኑ ለመጸለይ ተስማማን። ከዚያም በአንድ ስብሰባ ላይ ቆሞ፥ በዚያ ጸሎት ባደረግንለት ሳምንት ውስጥ ደኅንነትን እንዳገኘ መሰከረልን። እስከዚያን ጊዜ ድረስ የነበረው ክርስቲያናዊ ምስክርነት የማስመሰል

ነበር። በሕይወቱ ግሩም ለውጥ ተፈጸመና ዛሬ ጌታን በታማኝነት እያገለገለ ይገኛል።

በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙዎቹ ችግሮች ድነናል በሚሉና ዳሩ ግን ከቶውንም ንስሐ ገብተው በኢየሱስ ክርስቶስ ባላመኑ ሰዎች መፈጠራቸው አይጠረጠርም። ዛሬ የእኛም አብያተ ክርስቲያናት በእንደዚህ ዓይነት ሰዎች የተሞሉ ናቸው። ጳውሎስ እነዚህን ሰዎች የማይበቁ ይላቸዋል - ይህም «አስመሳዮች፥ ተፈትነው የማያልፉ» ማለት ነው። ጳውሎስ ለአንድ ሰው እንደ ዳነና ወደ መንግሥተ ሰማይ እንደሚሄድ ልናረጋግጥለት እንደሚገባ በማጉላት፥ ይህንኑ ቃል በ2ኛ ቆሮንቶስ 13፡6-7 ውስጥ በድጋሚ ጠቅሷል (1ኛ ዮሐ. 5፡11-13 ተመልከት)።

በቁጥር 7 ውስጥ፥ ጳውሎስ የራሱን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ብቻ ሲባል፥ የቆሮንቶስ ሰዎች በፈተናው እንዲወድቁ አለመፈለጉን ግልጽ አድርጓል። ስለ እነርሱ በትምክህት ለመናገር ይችል ዘንድ ብቻ ፈሪሃ-እግዚአብሔር ያለበትን ሕይወት እንዲኖሩ አልፈለገም ነበር። ጌታን እስከታዘዙ ጊዜ ድረስ፥ ለእነረሱ ብሎ ስለ መናቁና ስለ መሰደቡ ግድ አልነበረውም። ጌታ ልቡን ስለሚያውቅ፥ እርሱ የተጨነቀው ስለ ራሱ የስም መጉደፍ ሳይሆን፥ ስለ እነርሱ ክርስቲያናዊ ባሕርይ ነበር።

ከሁሉም የሚበልጠው አስፈላጊ ነገር የወንጌሉ እውነታና የእግዚአብሔር ቃል ነው (ቁ. 8)። ጳውሎስ በዚህ ስፍራ እውነትን መቃወም ወይም ማገድ እንደማይቻል አይገልጽም - ስለ ምን እነዚህ ነገሮች በጊዜው በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እየተፈጸሙ ነበርና! እርሱና ተባባሪዎቹ ግን፥ የመጣው ቢመጣ እውነት እንዲያሸንፍ፥ እውነት እንዲስፋፋ ወስነው ነበር እንጂ፥ እውነትን ለማገድ አልፈለጉም ነበር። በመጨረሻው ጸንቶ የሚኖረው የእግዚአብሔር እውነት ሆኖ ሳለ፥ ሰዎች ግን ይህንን ለምን ለመቃወም ይሞክራሉ? «ጥበብ ወይም ማስተዋል ወይም ምክር በእግዚአብሔር ላይ የለም» (ምሳሌ 21፡30)።

## አጽናናቸው (2ኛ ቆሮ. 13፡9-14)

በመጀመሪያ፥ ጳውሎስ ለእነርሱ ባቀረበው ጸሎት የቆሮንቶስን ሰዎች ያጽናናል (ቁ. 9)። «ኪንግ ጀምስ ቬዥን» በሚባለው የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ «እንመኛለን» ተብሎ የተተረጎመው ቃል፥ በአማርኛ መጽሐፋችን ውስጥ «እንጸልያለን» ተብሎ ተጽፎአል። ጳውሎስ ፍጹማን ይሆኑ ዘንድ ጸልዮአል፤ ይህም ኃጢአት የሌለበት ፍጹምነት ሳይሆን፥ «መንፈሳዊ ብስለት» ነበር። ይህ ቃል

በግሪኩ፥ «ብቁ መሆን፥ መታጠቅ» የሚሉት ቃላት ወገን ነው። የሕክምና ቃል እንደ መሆኑ፥ «የተሰበረ አጥንት መጠገን፥ ተጠምዝዞ የዞረውን እግር ወይም እጅ ማስተካከል» ማለት ነው። እንዲሁም ደግሞ፥ «አንድን መርከብ ለጉዞ ብቁ ማድረግ» እና «ሠራዊትን ለጦርነት ማስታጠቅ» የሚሉ ትርጉሞች ይኖሩታል። በማቴዎስ 4፡21 ላይ «መረብ ማበጀት» ተብሎ ተተርጉሞአል።

ከሙታን ከተነሣው ከጌታችን አገልግሎቶች አንዱ ሕዝቡን ፍጹም በማድረግ ማዘጋጀት ነው (ዕብ. 13፡10-21)። በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ኅብረት ውስጥ (ኤፌ. 4፡11-16) ሕዝቡን ለሕይወትና ለአገልግሎት ለማስታጠቅ፥ በእግዚአብሔር ቃል ይጠቀማል (2ኛ ጢሞ. 3፡16-17)። እንዲሁም መከራን ለመቋቋም መዘጋጃ መሣርያ አድርጎ ይጠቀምበታል (1ኛ ጴጥ. 5፡10)። ክርስቲያኖች እርስ በርሳቸው በጸሎት ሲደጋገፉ (1ኛ ተሰ. 3፡10) እና በግልም ሲረዳዱ (ገላ.6፡1 «አቅኑት» የሚለው ከዚሁ ፍጹም ተብሎ ከተተረጎመው ቃል ጋር አንድ ዓይነት ነው)፥ እግዚአብሔር ያለ ልክ ከፍ ከፍ ያደረገው ጌታ ቤተ ክርስቲያኑን ያገለግላታል - ለአገልግሎትም ብቁ ያደርጋታል።

በመነጣጠል ሕይወት ውስጥ፥ ሚዛናዊነትን የጠበቀ ክርስቲያናዊ ዕድገትና አገልግሎት ተግባራዊ ይሆናል ብሎ ከቶውንም አይታሰብም። አንድ ሰው ሲናገር፥ «አንድን ክርስቲያን ከኅብረቱ ነጥሎ ማሳደግ ማለት፥ አንድን ንብ ከመንጋው ነጥሎ እንደማሳደግ ያህል የማይሞከር ነው» ብሏል። ክርስቲያኖች እርስ በርስ የሚኖሩና እርስ በርስ የሚፈላለጉ ናቸው። አንድ ሕፃን ልጅ ሚዛናዊነቱ ተጠብቆ በመልካም ሁኔታ እንዲያድግ ከተፈለገ፥ በሚያፈቅር ቤተሰብ ውስጥ ማደግ አለበት። ዛሬ አንድን ክርስቲያን በአጥቢያ ማኅበረ-ምዕመናን ውስጥ ካለው ስፍራ ነጥሎ «በግል የክርስትና» ልምምድ እንዲመላለስ የማድረጉ አትኩሮት፥ የተሳሳተና በጣም አደገኛ ነው። እኛ በጎች ስለ ሆንን፥ በአንድ ላይ ልንሰማራ ይገባል። የአንድ አካል ክፍሎችም ስለ ሆንን፥ አንዳችን ሌላችንን ልናገለግል ይገባል።

በ2ኛ ቆሮንቶስ 13፡10፥ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች ሁለተኛውን መጽናኛ ሰጥቷል - የእግዚአብሔር ቃል። ጳውሎስ ይህንን ደብዳቤ የጻፈው የአንድን ማኅበረ-ምዕመናን ጉድለት ለመሸፈን ሲሆን፥ ዳሩ ግን በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል አካል በመሆኑ፥ ዛሬ እኛም እንጠቀምበታለን። ይህ ደብዳቤ የሐዋርያውን በመካከላቸው በአፀደ-ነፍስ የመገኘት ያህል ሥልጣን ተሸክሞአል። የጳውሎስ ትልቁ

ፍላጎት ማኅበረ-ምዕመናኑ ለደብዳቤው የሚኖራቸው መታዘዝ ችግሩን እንዲፈታውና እርሱ በሚጎበኛቸው ጊዜ በሥልጣኑ ላለመጠቀም ነበር።

አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔር ቃል አገልጋይ ከማነጹ በፊት ለመናድና ለማፍረስ የሚገደድበት ጊዜ አለ። (ኤር. 1፡7-10 ተመልከት)። ገበሬው ዘር ከመዝራቱና መልካም ምርት ከመሰብሰቡ በፊት፥ አካባቢውን መመንጠር አለበት። ጳውሎስ እውነትን በልባቸውና በአእምሮአቸው ውስጥ ከማነጹ በፊት፥ ከክርስቲያኖች አእምሮ ውስጥ የተሳሳተውን አስተሳሰብ ማስወገድ ነበረበት (2ኛ ቆሮ. 10፡4-6)። ምንም እንኳ ትልቅ ፍላጎቱ ማነጽ ቢሆንም፥ የቆሮንቶስ ሰዎች አሉታዊ አመለካከት ግን ጳውሎስን ወደ ማፈራረሱ እንዲያመራ አስገደደው።

በራሴ የአገልግሎት ዘመን ውስጥ፥ ሁለት የማነጽ ፕሮግራሞችንና ሁለት እንደ ገና መልሶ የማዋቀር ፕሮግራሞች አከናውኛለሁ። ምንም እንኳን የሚጠይቁዋቸው ልፋቶች ከፍተኛ ቢሆኑም፥ ለእኔ የማነጽ (የግንባታ) ፕሮግራሞች ይቀሉኛል። አንድን አሮጌ ሕንፃ አፍርሶ ከመሥራት ይልቅ፥ አንድን አዲስ መዋቅር በአዲስ መሬት ላይ ማነጹ ቀላልም፥ ጊዜ የማያባክንም ነው። እንደዚሁም፥ የቆየውን አማኝ የተሳሳተ አሳብ ለማስለወጥ ከመሞከር ይልቅ፥ አንድን አዲስ አማኝ ወስዶ የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማሩ ቀላል ተግባር ነው። የእግዚአብሔር መንፈስ በአእምሮአችን ውስጥ የተከማቸውን የተሳሳተ የአስተሳሰብ ግድግዳ እስኪንደው ድረስ፥ የተሳሳቱ አሳቦች ለረዥም ጊዜ እውነትን «ለመቋቋም፥ ለመከላከል» ይችላሉ።

ጳውሎስ ቅዱሳኑ ጸጋን፥ ፍቅርንና ሰላምን እንዲከታተሉ ያበረታታቸዋል (ቁ. 11-12)። «ደኅና ሁኑ» ተብሎ የተተረጎመው ቃል «ጸጋ» የሚል ትርጉም ሲኖረው፥ በዚያን ዘመን የተለመደ የሰላምታ ዓይነት ነበር። «ተደሰቱ» ተብሎም ሊተረጎም ይችላል። ፍጹማን ሁኑ የሚለው ትዕዛዝ፥ በቁጥር 9 ላይ ጳውሎስ ካቀረበው ጸሎት ጋር የተያያዘ ሲሆን፥ «የበሰላችሁ፥ የጸናችሁና ለሕይወት የምትመቹ የሆኑ» የሚል አሳብ አለው። «በአንድ ልብ ሁኑ» የሚለው «ተጽናኑ» የሚል ትርጉም ይኖረዋል። ከእነዚያ ሁሉ ኃጢአቶቻቸውና ችግሮቻቸው ባሻገር፥ ለመጽናናት የሚያስችሉ በቂ ምክንያቶች ነበሯቸው።

በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ መከፋፈል ስለ ነበር፥ በሰላም ኑሩ የሚለው አስፈላጊ ምክር ነበር (12፡20 ተመልከት)። በፍቅር ቢመላለሱና በአንድ ልብ ለመኖር ቢፈልጉ የእርስ በርስ ጦርነቶቹ አብቅተው፥ በኅብረታቸው ውስጥ ሰላም ይኖር ነበር። በአንድ ልብ

መሆን ማለት ሁላችንም በሁሉም ነገር ላይ እንስማማለን ማለት ሳይሆን፣ ዳሩ ግን አላስፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ አለመግባባትን ለማስወገድ እንችላለን ማለት ነው።

አምላካችን «የፍቅርና የሰላም አምላክ» ነው (13:11)። ታዲያ ከውጭ ያለው ዓለም ከአኗኗራችንና የቤተ ክርስቲያንን ሥራ ከምናከናውንበት ሁኔታ በመነሣት የእኛን የፍቅርና የሰላም ሕይወት ሊረዳው ይችል ይሆን? ከደኅንነት ርቆ የጠፋው ዓለም ስለ ቀደመችው ቤተ ክርስቲያን፥ «አቤት እንዴት ይዋደዳሉ!» ይል ነበር፤ እነሆ በዛሬው ጊዜ ግን ቤተ ክርስቲያን የዚህ ዓይነቱን ምስጋና ከተቀበለች ረዥም ጊዜ ሆኖአታል።

ከጥንት ጀምሮ፥ መሳሳም የሰላምታ ዓይነትና እንደዚሁም የፍቅርና የኅብረት መግለጫ ነበር። ይሁንና ብዙውን ጊዜ የሚከናወነው በተመሳሳይ ጾታዎች መካከል ነበር። የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን አማኞች እርስ በርስ የነበራቸውን ፍቅርና መተሳሰብ ለማመልከት፥ የሰላምንና የፍቅርን መሳሳም ያከናውኑ ነበር። ለኢየሱስ ክርስቶስ ከነበራቸው መሰጠት የተነሣ፥ ክንውኑ «የተቀደሰ አሳሳም» ነበር። ለቀድሞዋ ቤተ ክርስቲያን አባላት፥ አዳዲስ አማኞችን የጥምቀት ሥርዓታቸውን ከፈጸሙ በኋላ፥ መሳምና ወደ ኅብረቱ መቀላቀል (አቀባበል ማድረግ) እንግዳ ነገር አልነበረም።

የእግዚአብሔር ሕዝብ ዕለታዊ ኅብረት ለቤተ ክርስቲያን አስፈላጊ ነው። በጉባዔው ኅብረት ውስጥም ሆነ በሌሎች ስፍራዎች እርስ በርሳችን ሰላምታ ልንለዋወጥና አንዳችን ለሌላችን ያለንን አሳቢነት ልንገልጽ ይገባል። በቁጥር 12 ላይ ይህንን ምክር በመስጠት ጳውሎስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሚገኙ ከባድ ችግሮች በአንዱ ላይ እያነጣጠረ ነበር - ይኸውም በመከፋፈላቸውና እርስ በርስ ሊተሳሰቡ ባለመቻላቸው ላይ ነበር።

በቁጥር 14 ላይ የሚገኘው የማጠቃለያ ቡራኬ፥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እጅግ ተወዳጁና አዘውትሮም በአገልግሎት ላይ የሚውል ነው። ይህም በሥላሴ አንድነት ምሥጢር ላይ (ማቴ. 28:19 ተመልከት) እና የእግዚአብሔር ንብረት በመሆናችን በምናገኛቸው በረከቶች ላይ ያተኩራል። የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፥ እኛን ሀብታም ለማድረግ እርሱ ድሀ በሆነበት ጊዜ የተፈጸመውን የልደት ታሪክ ያስታውሰናል (2ኛ ቆሮ. 8:9 ተመልከት)። የእግዚአብሔር ፍቅር እግዚአብሔር ልጁን ለኃጢአታችን መሥዋዕት አድርጎ ወደሰጠበት ወደ ጎልጎታ ይወስደናል

(ዮሐ. 3፡16)። የመንፈስ ቅዱስ ኅብረት፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ስለ ወረደበትና ቤተ ክርስቲያንን ስለ መሠረተበት ሁኔታ ያስታውሰናል (የሐዋ. 2)።

በዚያን ጊዜ የቆሮንቶስ ለአማኞች፥ በዛሬው ጊዜ ደግሞ ለሁሉም አማኞች፥ የጸጋ፥ የፍቅርና የኅብረት በረከቶች በጥብቅ ያስፈልጉአቸዋል። ይሁንና፥ በዚያን ዘመን የአይሁድ ሃይማኖት አስፋፊዎች፥ ዛሬ ደግሞ መናፍቃን፥ ከጸጋ ይልቅ በሕግ፥ ከፍቅር ይልቅ በመለየት፥ እንዲሁም ከኅብረት ይልቅ በመነጣጠል ላይ ያተኩራሉ። መከፋፈልን ያስከተለው የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውድድር ሊቀረፍ የሚችለው ሕዝቡ በእግዚአብሔር ጸጋና ፍቅር ሲመላለስ ብቻ ነበር።

ቤተ ክርስቲያን ተአምር ስለ ሆነች፥ ልትቆም የምትችለውም በእግዚአብሔር የተአምር አገልግሎት ብቻ ነው። ምንም ያህል ሰብዓዊ ጥበብ፥ ብቃት፥ ወይም ዕቅድ ቤተ ክርስቲያን መሆን የሚገባትን እንድትሆን አያደርግም። ይህንን ሊያደርግ የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው። እያንዳንዱ አማኝ በእግዚአብሔር ጸጋ ላይ የሚደገፍ፥ በእግዚአብሔር ፍቅር የሚመላለስ፥ በሥጋ ከመመላለስ ይልቅ በመንፈስ ቅዱስ ኅብረት ውስጥ የሚሳተፍ ከሆነ፥ መፍትሔ ሰጪ እንጂ ችግር ፈጣሪ አይሆንም። ይህም ሲሆን ሕይወቱ የተባረከ ይሆናል። በረከቱም ለሌሎች ይተርፋል!

እግዚአብሔር ይህን ዓይነት ክርስቲያን እንዲያደርግህ በጸሎት ጠይቀው።

ተጽናና - ሌሎችንም አጽናና።

## «... ሁን» በሚል ርእስ ታትመው በስርጭት ላይ የሚገኙ መጻሕፍት

1. ለጌታ የተገዛህ ሁን (የማቴዎስ ወንጌል)
2. ርኅሩኅ ሁን (የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 1–13)
3. የበረታህ ሁን (የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 14–24)
4. በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተመላለስ (የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 1–12)
5. ደፍረህ መስክር (የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 13–28)
6. ጠቢብ ሁን (1ኛ ቆሮንቶስ)
7. ተጽናና (2ኛ ቆሮንቶስ)
8. አርነት መውጣት (ገላትያ)
9. ፍለጋ የሌለው ባለጠግነት (ኤፌሶን)
10. ደስተኛ ሁን (ፊልጵስዩስ)
11. ፍጹም ሁን (ቆላስይስ)
12. ለምጽአቱ ተዘጋጅ (1ኛና 2ኛ ተሰሎንቄ)
13. ታማኝ ሁን (1ኛና 2ኛ ጢሞቴዎስ፥ ቲቶና ፊልሞና)
14. እውነተኛ ሁን (1ኛ ዮሐንስ መልእክት)
15. ንቃ (2ኛ ጴጥሮስ፥ 2ኛና 3ኛ ዮሐንስ፥ ይሁዳ)
16. በብስለት ማደግ (የያዕቆብ መልእክት)
17. ድል አድራጊ ሁን (የዮሐንስ ራእይ)

## በዝግጅት ላይ ያሉ

1. በማየት ሳይሆን በእምነት ተመላለስ (ዕብራውያን)
2. ተስፋ ይኑርህ (1ኛ ጴጥሮስ)

# «በሁሉ እንገፋለን...

**እንጂ አንጨነቅም፤ እናመነታለን እንጂ ተስፋ አንቆርጥም፤ እንሰደዳለን እንጂ አንጣልም፤ እንወድቃለን እንጂ አንጠፋም» (2ኛ ቆር. 4፡8–9)።**

ጦርነት የሚዋጉና ጭንቀት የሚሸከሙ ሰዎች በረከትን ለመቀበል ከማንም የተሻሉ ዕጩዎች ናቸው። ጳውሎስም በቁዘማ ሊሚናጡ የቆሮንቶስ ሰዎች ያበሰረው ይህንኑ መልእክት ነበር። ልክ እንደ ዛሬዎቹ ክርስቲያኖች ብዙውን ጊዜ ይጨነቁና ግራ ይጋቡ ነበር።

እግዚአብሔር ግን አልተዋቸውም–እኛንም አይተወንም። «የመጽናናት አምላክ» ብቻ ሊያደርግ በሚችለው መንገድ በጉዳት የሚታመሱ ልጆቹን ያጽናናል።

ይህ የሁለተኛ ቆሮንቶስ ጥናት እግዚአብሔር እንዴት ፈተናዎችህን ወደ ድል፥ መከራዎችህን ወደ አገልግሎት እንደሚለውጥ ያሳይሃል። ፈለጉን በማወቅ

## ተጽናና

ዶ/ር ዎረን ደብልዩ. ዌርዝቢ በደራሲነታቸው፥ በመጋቢነታቸውና በሬድዮ መጽሐፍ ቅዱስ መምህርነታቸው በስፋት የሚታወቁ አገልጋይ ናቸው። ለብዙ ዓመታት የሺካጎ ሙዲ መታሰቢያ ቤተክርስቲያን መጋቢ ሆነው ያገለገሉ ሲሆን፥ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ «ወደ መጽሐፍ ቅዱስ እንመለስ» ለተባለው ፕሮግራም ዳይሬክተርና የመጽሐፍ ቅዱስ መምህር ሆነው አገልግለዋል። በቪክተር ቡክስ' አሳታሚነት ከሚቀርቡት የአዲስ ኪዳን ተከታታይ ማብራሪያዎች ጋር ከመቶ በላይ መጻሕፍት ጽፈው ለምእመናን አቅርበዋል።

BE ENCOURAGED
Printed by SIM Press

Bible Based Books
SIM Publishing